# ገድለ ሰማዕታት

አዘጋጆች
ገብረ ዮሐንስ ገብረማርያም
ድሜጥሮስ ወልዱ

የካቲት 1994 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

 አድራሻችን
ድሜጥሮስ ወልዱ
ፖ.ሣ.ቁ 2430
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ስ.ቁ. 11 34 24
ፋክስ 55 06 19

Our Address
Dimetros Woldu
P.O.Box 2430
Addis Ababa
Ethiopia
Tel. 11 34 24
Fax 55 06 19

Beide-Mariam Eji
Feb 2014

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

1. መግቢያ
2. ምዕራፍ 2 ፊሊሞን መአንዝር 1
3. ምዕራፍ ፫ የቅዱስ ቴዎዶስ ተጋድሎ ትምህርተወንጌልና ዕረፍት 8
4. ምዕራፍ ፬ የ፵ ሐራሰማይ ሰማዕትነት 13
5. ምዕራፍ ፭ ቴዎቅሪጦስ አናጉንስጢስ 18
6. ምዕራፍ ፮ ገድለዮሐንስ ወልደፀራቢ 30
7. ምዕራፍ ፯ የሰማዕት ፊቂጦር ገድልና ታሪክ 38
8. ምዕራፍ ፰ የቅዱስ ዮሐንስ ዘሥንሑት ታሪክና ሰማዕትነት 58
9. ምዕራፍ ፱ የቅድስት አፎምያ ሰማዕትነትና ታሪክ 69
10. ምዕራፍ ፲ የአርኖሶፊስ ዘቤጥሮስና አስኪሪዮን ገድል 80

www.ethiopianorthodox.org

11. ምዕራፍ ፲፩ የቅዱስ አትናቴዎስ ዘቁዝም ሰማዕትነት 94

12. ምዕራፍ ፲፪ የአባኖብ ሰማዕት ታሪክ 101

13. ምዕራፍ ፲፫ የሦስት ደናግል ጲስጢስ፣ አላጺስ፣ አጋጲስና እናታቸው ቅድስት ሶፍያ ሰማዕትነት 129

14. ምዕራፍ ፲፬ የቅድስት መክብዩና የሰባት ልጆቿ ሰማዕትነት 144

15. ምዕራፍ ፲፭ የቅዱስ ሐሩስጡፋሩስና የሁለት ቅዱሳት አንስት ሰማዕትነትና ገድል 160

16. ምዕራፍ ፲፮ የቅዱስ ባስሊቆስ ሰማዕትነት 167

17. ምዕራፍ ፲፯ የቅድስት ክርስጢና ገድል 176

18. ምዕራፍ ፲፰ የቅዱስ እንጦዎስ ገድል 187

19. ምዕራፍ ፲፱ የቅዱስ አድርያኖስና የሃያ አራቱ ሰማዕታት እንዲሁም የቅድስት እንጦልያ ገድልና ሰማዕትነት 197

20. ምዕራፍ ፳ የኔፊኔዎስ ጳጳስ ሰማዕትነት 210

# መግቢያ

ገድለሰማዕታት በሁለት ታላላቅ ክፍሎች በመከፈል በብራና ተዘጋጅቶ ይገኛል ይህን መጽሐፍ አግኝተው የማግበብ ዕድል የገጠማቸው ኢትዮጵያውያን እጅግ ጥቂቶች ናቸው። ምክንያቱም ይህ መጽሐፍ የሚገኝባቸው አድባራትና ገዳማት ብዙዎች አይደሉምና /በብዙ ገዳማትና አድባራት እንደልብ አይገኝም/። በመጀመሪያው ክፍል የሃያ ሁለት ሰማዕታትን ስም፣ "ገድላቸውንና ሰማዕትነታቸውን" ያጠቃልላል።

እግዚአብሔር በዘመነ ሰማዕታት እጅግ ዕፁብ ድንቅ ሥራን ሠርቷል ቅዱሳን ሰማዕታት በእግዚአብሔር አጋዥነት አረማውያን የሮም ነገሥታትን በትዕግሥታቸው አሸንፈዋል እናቶች ልጆቻቸውን በማስቀደም የዚህን አለም እጅግ አሰቃቂ መከራ ቅንጣት ያህል ለሕይወታቸው ሳይሣሱ ተጋፍጠውታል ልጆቻቸው የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከመጥራት ወደኋላ እንዳይሉ በማበረታታት ቁመው እየተመለከቱ በፈላ ውሃ ሲቀቀሉ፣ አንበሶች ሲቦጫጨቁዋቸው እጅ እግራቸውና ሌላው አካላቸው ባሰቃቂ ሁኔታ እንደዛፍ ቅርንጫፍ ሲቆራረጥ ከእምነታቸው ፈቀቅ ሳይሉ ይህን ዓለም እንዲለዩት ያበራታቱዋቸው ነበር።

"እንክርዳድ ያልተቀላቀለበት ንፁሕ ሥንዴ ሁናችሁ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትነት ቅረቡ፣ የመንግሥተሰማያት ሙሽሮች ሁናችሁ የሰማዕትነት አክሊልን ተቀዳጁ በዚህ ዓለም አምራችሁ ደምቃችሁ ማየትን አንፈልግም ለጥቂት ጊዜ ኑሮ ብላችሁ እጃችሁን ለጠላት ዲያብሎስ አትሥጡ እናንተን አስቀድመን እኛ እናቶቻችሁ በሄዳችሁበት መንገድ እንከተላችኋላን" እያሉ የልጆቻቸውን ባሰቃቂ ሁኔታ ሰማዕትነትን መቀበል ቁመው በመመልከት ለፍፃሜ ያበቁ እናቶች ብዙዎች መሆናቸውን ከገድለሰማዕታት እንረዳለን።

ቅድስት ሶፍያና ቅድስት መክብዩ ከብዙዎቹ የዘመነሰማዕታት ቅዱሳትና ጥቡአት እናቶች መካከል በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ቅድስት

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 2 ፊሊሞን መአንዝር

እስቅለን የተባለው ሰማዕትነትን ከተቀበለ በኃላ አርያኖስ የተባለው መኮንን አንጢኖ ከተባለው አገር ተቀምጦ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሚከተሉት ውስጥ ዋናዋናዎቹን እንዲይዙዋቸው አዘዘ። የተሰበሰቡት ምእመናን ለጣኦታት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ በንጉሡ ተጠየቁ። እንሰዋም ቢሉ ግን ክፉ ሞት እንደሚሞቱ ማስጠንቀቂያ ተሠጣቸው አናግኖሰጢስ የምትባል አገር ተወላጅ የሆነ አጵሎስን የሚባል ሰው ንጉሡ ክርስቶሳውያንን ለማሰቃየት የተዘጋጀውን የብረት ጋንና ሠይፍ አይቶ እጅግ ደነገጠ ፈራ። ንጉሡ አርያኖስ ይባላል ንጉሡን አርያኖስን በሙዚቃና በጥዑም ድምፁ የሚያዝናና ፊሊሞን የሚባል ነበር። ይህ ሙዚቀኛ ፊሊሞን አጵሎሰን እኔ አንተን በመምሰል ለጣኦት እንድሰዋልህ ልብስህን አውልቀህ ሥጠኝ አለው። አጵሎስ የለበሰውን ልብስ አውልቆ ለፊሊሞን ሠጠው።

ፊሊሞን ፊቱን ሸፍኖና ራሱ ተከናንቦ ወደመኮንኑ አርያኖስ ቀረበ አርያኖስ መኮንን ማንነቱን ለማወቅ ሲጠይቅ ከክርስቲያኖቹ አንዱ ነው ነገር ግን ሌሎች ክርስቲያኖች ከሐዲ እንዳይሉት ማንነቱን ደብቆ ለአማልክት መሥዋዕት እንዲያቀርብ ተዘጋጅቷል አሉት አርያኖስምተውት ለአማልክት ከሰዋ ከሌሎች ክርስቲያን ተለይቶ ከመኮነን ይድናል አለ ወድያው ሙዚቀኛው /ዘማሪው/ ፊሊሞን ክንንቡን ገለፀና እኔ ክርስቶስ የማምን አምልኮባእድን የማወግዝ ክርስቲያናዊ ነኝ አለው።

ንጉሡ የራሱ ወዳጅና ከመዣርያ ጋር እየዘፈነ የሚያስደስተው ተከታዩ በእምነት ከሱ መለየቱን አይቶ እጅግ ተናደደ የሱን



ትእዛዝ ያልተቀበሉት ሁሉ በሠይፍ አንገታቸውን እየቆረጠ በእሳት እያቃጠለ እንደፈጃቸው እያየ እንዴት ደፍሮ የክርስቶስ ተከታይና አማኝ ሊሆን እንደቻለ በመገረም የተናገረውን ቃል እንዲሠርዝና ለጣኦታት መሠዋቱን እንዲቀጥል አባበለው /አግባባው/።

ፊሊሞን ዘፋኝ ቅዱሳን ሰማዕታት በትዕግሥታቸው የጠበቁትን የመንግሥተሰማያት ተስፋ አግኝተዋል። ይህም ደግሞ እንዲሁ በባዶ ሜዳ አላገኙትም የሚደርስባቸውን መከራሁሉ ታግሥው ነው የሰማዕትነትን አክሊል ሊቀዳጁ የቻሉት የነሱ መከራንና ሥቃይን አልፎ ወደ ዘላአለማዊ ሕይወት መሻገር እጅግ ያስቀናል በነሱ ትዕግሥትና ሰማዕትነት የማይቀናመንፈስ ቅዱስ የራቀው ሠይጣን የተቆራኘው ብቻ ነው አለው። አርያኖስ በሕይወት ለመኖር ትችል ዘንድ ለአማልክት መሥዋእት ብታቀርብ ይሻለሃል አለው ፊሊሞን በበኩሉ ሕይወት ለሌላቸው ግዑዛን ጣኦታት መሥዋእት አቅርቦ በሕይወት ከመኖር ዘላዓለማዊውን ሕይወት ለማግኘት የወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስክርስቶስ ሕማማተመስቀልን ተካፋይ መሆን ይበልጠኛል ሲል መለሰለት። አርያኖስ ለጊዜው በዝምታ ሸኘው። ነገር ግን ካደባባይ ፈልገው እንዲይዙት ወታደሮች ላከበት ፊሊሞን ከአርያኖስ ከተለየ ጀምሮ በየሠዋራ ቦታው ወንጌለክርስቶስን ማስተማሩ ተያያዘው ሰዎችን ወደአሚነክርስቶስ ለመሳብም ይሽቀዳዳም ነበር። ሊይዙት የተላኩት ወታደሮች ከሕዝብ መካከል ፈልገው አጡት ለጊዜው ሊያገኙት አልቻሉም።

አርያኖስ ንጉሥ/መኮንን/ የፊሊሞን መሠወርን ሰምቶ ቴዎን የተባለውን የፊሊሞን ወንድም አስጠራና ወንድሙን ካለበት እንዲጠቁመው አዘዘው ፊሊሞን ግን የወንድሙን በምትኩ ለጥያቄ መቅረብ ሲሰማ ራሱ ወደንጉሡ ቀረበ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በሮም ሕዝብ ስም እማፀናለሁ ክርስቲያናዊ ነኝ በክርስቶስ አምናለሁ



www.ethiopianorthodox.org

ያልከው ከልብህ ነው ወይስ እየቀለድክነው አለው። ፊሊሞን የሠጠው መልስ ደግሞ "አንተስ ለጥፋት በተዘጋጁ የሮሜ ሰዎች ተማፀንክ እኔ ደግሞ የምምልልሕና የምማፀንህ የሰማዕታት አክሊልና የክርስቲያን ክብራቸው ኃይላቸውም በሆነው እውነተኛው የሰማይና የምድር ታላቅ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እምልልሃለሁ። የተናገርኩትና የገለፅኩት ሃይማኖት ለዘበትና ለቀልድ አይደለም በእውነት በመላ ሕይወቴና በልቡናዬ ሁሉ ተቀብየዋለሁ" የሚል ነበር።

የፊሊሞንን መልስ ሲሰማ አርያኖስ በውስጡ እርር ድብን አለ ነገር ግን እንደፈለገው በሥልጣኑ ተጠቅሞ እንዳያስቃየውና እንዳይገርፈው ሁለት ነገሮች በተቃራኒ መንገድ ተደቀኑበት። 1ኛ/ ብዙ ከአገሩ ሕዝቦች ትምህርተ ክርስትናን አግኝተው ስለነበር በዚሁ 2ኛ/ የፊሊሞን ድምፅ በዘፈን ጊዜ በመላ ሕዝብ ተወዳጅነት ስለነበረው በግላዊ ሥልጣን በሕይወቱ ላይ አንዳች ቢፈፅምበት በሕዝቡ ላይ አደገኛ ተቃውሞ ሊያስከትልበት እንደሚችል ስለተገነዘበ ሕዝቡን ሰብስቦ ፊሊሞንን ባስቸኳይ ልግደለው ወይስ ጥቂት ልታገሠው በማለት ጠየቃቸው። እነሱም ያገርን ደስታ አት ግደል/ኢትቅትል ፍ/ሠሐህገር/ ፊሊሞን ደስታችንና ሕይወታችን ነው በሱ ላይ አንዳችም ነገር ለማየት አንሻም ሲሉ ባንድ ቃል መለሱለት።

በዚህ ጊዜ አርያኖስ ሕዝቡ እንዴት እንደሚወድህ ታያለህን ካለው በኃላ የጣኦት በዓል በሚከበርበት ጊዜ ሕዝቡን በዘፈንህና በሙዚቃ መሣርያህ ልታስደስታቸው ይገባል አለው። እሱን ለማጥፋት ንጉሡ ታጥቆ ተነስቷልና ከህዝቡ ጋር ለመጋጨት ሆን ብሎ የሸረበው ተንኮል ነበር። ፊሊሞንም ይህ በዓል



የእውነተኛው ሰማያዊ በዓል ተቃራኒ ነው ስለዚህየኔ ደስታ በዚሁ የጣኦት በዓል ተካፋይ በመሆን ሳይሆን የሚገለፀው በዓሉ እንዳይደረግ በመቃወም ነው ደስታዬ የሚገለፀው አለው።

አርያኖስ "ክርስቲያኖች እኔንና አንተን አሕዛብ ይሉናል ስለዚህ አንተ ክርስቲያኖች በውሃ ሳያጠምቁህ ክርስቲያን ልትሆን አትችልም። ሳትጠመቅ ክርስቲያን ነኝ ብትል ያንተን ክርስቲያንነት ማንም አይቀበለውም ፫ አለው። ፊሊሞን ይህን ሲሰማ ከተሰበሰቡት መካከል ክርስቲያኖች የሆናችሁ ሁሉ ባካችሁ ኑና አጥምቁኝ አላቸው። ነገር ግን ምንም እንኳ ባደባባዩ ብዙ ክርስቲያኖች ቢኖሩም ክርስቲያንነታቸው ከተገለፀ የመሰደደድ የመገደል ካልሆነ ደግሞ ከማሕበራዊ ኑሮ የመገለል ዕጣ ስለሚገጥማቸው ደፍሮ እኔ አለሁ ክርስቲያን በማለት ሊያጠምቀው የሚሞክር ጠፋ።

ይህን ተመልክቶ ንጉሥ አርያኖስ ካንተ በቀር ማንም ክርስቲያን እንደሌለ አሁን በሚገባ ልትረዳ ችለሃል። ብቻህ ተለይተህም ክርስቲያን ነኝ ማለቱ እንዳበድክ ያስቆጥረኻል ስለዚህ ከወገንህ ከህዝብህ ልትለይ ስለማይገባ ለአማልክት መሥዋዕትህን አቅርብ አለው። በዚህ ጊዜ ፊሊሞን ድምፁን ከፍ አድርጎ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ባክህ በክርስቲያንነቴና አንተን በመከተሌ እንዳላፍር የጥምቀትን ምሥጢር ግለፅልኝ ፍርሐትንና ሐፍረትንም ከኔ ለማስወገድ ቅዱስ መንፈስህን ወደኔላክ እያለ ፀለየ።

ፊሊሞን ፀሎቱን እንዳቆመ ፍፁም ታይቶ በማያውቅ ሁኔታ ድንገት አካባቢው በጉም ተከበበ ላዩ በደመና ተሸፈነና ዝናም ዘነበ በዚህ ጊዜም ፊሊሞን ተጠመቀ። ያሉትም ሁሉ በዝናሙ ተጠመቁ ዝናቡ ባጭር ጊዜ ውስጥ ፀጥ አለ መዝነቡም



www.ethiopianorthodox.org

አቆመ። በዚህ ጊዜ ፊሊሞን እንዲህ አለ "አርያኖስ ሆይ ስማ፣ በሙሉ ልብ ካለማመናችሁ የተነሳ እኔን ማጥመቅ ያስፈራችሁ ሕዝቦች ሆይ የማይፈራው ጌታዩና አምላኬ መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ላመኑት ቅርብና ፈጥኖ ደራሽ መሆኑን አየኸው የዝናቡ አዘናነብ ተረድተክህ ወደሱ ልትመጣ ይገባሃል" አለው።

ንጉሥ አርያኖስ ባየውና በሰማው የእግዚአብሔር ድንቅተአምር ሊመለስ አልቻለም ስለዚህ "በተያጥሮን በሚደረገው የጣኦታት በዓል የጣኦት ምሥጋናህን እንደተለመደው በመልካሙ ድምፅህ ለማቅረብ ከወዲሁ እንድትዘጋጅ ይሁን ሕዝቡ ወደጣዖቱ የሚመጣው በይበልጥ ያንተን መልካም ድምፅ ለመስማትነው አንተ በቦታው ተገኝተህ የተለመደው መዝሙርህን ካላቀረብክ ባንተው ቦታ ሌላ ሰው ተመድቦ ሊዘምር ይችላል። በዚህ ጊዜ ያንተ ልጆች ሌላ ሰው ሲዘምር ቢያየ እጅግ ያዝናሉ ስለዚህ ሌላው ቢቀር ለልጆችህ ስትል መዘመር ይገባሃል፫ በማለት ፊሊሞንን ያግባባው ጀመር። ከአርያኖስ የሰማውን የማግባቢያ ንግግር ተገንዝቦ በአጵሎን ቤት የተቀመጡትና በሱ እጅ የሚመቱ የዘፈን መሣርያዎች እግዚአብሐ እንዲያጠፋለት ፀለየ። መሣርያዎቹም በእግዚአብሔር ኃይል በእሳት ተቃጠሉ። አርያኖስ በሁሉም ነገር ብስጭት ስለደረሰበት ፊሊሞንን ሰዎች ልኮ አስደበደበው። የደረሰበትን ድብደባ በትዕግሥትና በአኮቴት ተቀብሎ ሳለ አርያኖስ እንደገና መጣና እኔና አገር ባንተ ምክንያት ታውከናል ስለደረሰብህ ድብደባ ካሣ ይሠጥሃል ባክህ ተመለስ እያለ ድጋሚ ያግባባው ጀመር።

በድምፃምነቱ የሚወዱት ያገሩ ሰዎች በበኩላቸው ጉልበት የሌለው አለቀሰ ጉልበት ያለው ደግሞ ለመበቀል ተነሳሳ በዚህ ጊዜ ንጉሡ አርያኖስ ከባድ የፖለቲካ ውጥረት አደረበት በፊሊሞን



ላይ እጃቸውን ያሳረፉ ሁሉ ሊቦጫጭቃቸው ሕዝቡ ፈንቅሎ ወጣ። በዚህ ጊዜ ፊሊሞን ሕዝቡ እንዲታገሥ ያግባባ ጀመር። አርያኖስ ግን የፖለቲካ ጭንቀት ቢደርስበትም ፊሊሞንን ለማጥፋት ሆን ብሎ ሌት ተቀን ይጥር ነበር። ብዙ ግፍና መከራም አድርሶበታል። በመጨረሻም ከሁለት የክርስቶስ ተከታዮች ምዕመናን ጋር በሰይፍ አንገቱን አስቆረጠው።

የፊሊሞንና የጓደኞቹን አንገት አስቆርጦ ወደቤቱ ሲመለስ ካልታወቀ አቅጣጫ የተወረወረች የእንጨት ሥንጣሪ አንድ ዓይኑን አጠፋችው በዚህ ጊዜ እጅግ ደነገጠና ጣኦታቱ ዓይኑን እንዲያድኑት ለመናቸው መልስ ሲያጣ ከህዝቡ መካከል ክርስቲያን ሁነው እያለ መከራን ከመፍራት የተነሳ ማንነታቸውን ደብቀው የሚኖሩ ሰዎች እጅግ ብዙዎች ነበሩና ከመካከላቸው አንዱ ፊሊሞንና ጓደኞቹ ከተቀበሩበት መቃብር የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ጠርተህ የጠፋውን ዓይንህ አፈር ብትቀባው ይድናል አለው እሱም እየሮጠ ሄዶ ከሦስቱ ሰማዕታት መቃብር አፈር ዘግኖ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ቢቀባው ዳነ።ወዲያው ጣኦታቱን ከያሉበት አድኖ በማውጣት አጠፋቸው እኔ ክርስቲያን ነኝ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ በሰማይም በምድርም የለም አለ። እሱ ያስገደላቸውን ፊሊሞንና ጓደኞቹም በመንግሥቱ የክብር ልብስ ገነዛቸው በመልካም ሹቶም አስክሬናቸውን ቀባው። ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የነፊሊሞንን ክብርና ፀጋ ለኔ አድለኝ በስምህ የኔ ሕይወት እንድታልፍ እፈቅዳለሁ ላንተ እየመሰከርኩ እንድሞት ፀጋህን አድለኝ ባለፈው የፈፀምኩትንም ሐጢአቴ ይቅር በለኝ እያለ አብዝቶ ፀለየ።

ከቤተመንግሥቱ ጥቂቶቹን አስከትሎ ቤተመንግሥቱን ትቶ ወጣ የክርስቶስ ሐዋርያ በመሆን ካገር አገር ያስተምር



www.ethiopianorthodox.org

ጀመር ብዙ አገርን በስብከት አዳርሶ በመጨረሻ እስክንድርያ ገባ፣ እስክንድርያ በዘመኑ ከዲዮቅልጥያኖስ ግዛቶች አንዷ ነበረች። ዲዮቅልጥያኖስም የአርያኖስ የበላይ ነበር ስለዚህ አርያኖስን አገኘው ለጣኦት እንዲሰግድም አዘዘው አርያኖስ ደግሞ ብዙ ጣኦታትን አጥፍቶ እንደመጣ ነገረው ወዲያው እጅግ ተናደደና ቶሎ እንዳይሞት በሚያስችል ሁኔታ ሌት ተቀን እንዲያሰቃዩት በጭካኔያቸው የታወቁትን አራት አረማውያን ወታደሮች መደደበት እነሱም የቻሉትን ሁሉ እየፈፀሙ ሲያሰቃዩት መከራውን እየታገሰ ኢየሱስ ክርስቶስን ለዚህ ያበቃኸኝ እያለ ያመሰግን ነበር። የትዕግሥቱን ፅናት የተመለከቱ እነዚያ አራቱ አረማውያንም በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑና ለኢየሱስ ክርስቶስ እየመሰከሩ መሞትን መረጡ። የኢየሱስ ክርስቶስ ባሮች እንጂ ያንተ ባሮች አይደለንም ብለው ዲዮቅልጥያኖስንና ጣኦታቱን ሰደቡ። የኢየሱስ ክርስቶስን ተከታዮች የምታሳድድና የምትፈጅ አንተ ያበድክ ነህ በማለት እጅግ ዘለፋ አበዙበት ከአርያኖስ መኮንን ጋርም ተሰልፈው የኢየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ለመስበክ መወሰናቸውንም በግልፅ ነገሩት።

ዲዮቅልጥያኖስ ያሉትን ሰምቶ እንዲህ አላቸው እስካሁን ድረስ በቤተመንግሥቴ ሁናችሁ የምትለምኑኝን ሁሉ እሰጣችሁ ነበር አሁን ደግሞ ሞትን ሥጠን ብላችሁ ስትለምኑኝ ከአርያኖስ ጋር ሞትን እንድትቀምሱ እንዴት አላደርግም አላቸው ካራቱ አንዱና ትልቁ ቴዎጢቆስ የተባለው ደግሞ በኛ ላይ የምትፈፅመውን ክፉ ነገር ሁሉ ከእግዚአበሔር ታገኘዋለህ ካለው በኋላ በውጭም ሆነ በውስጥ ያለውን ንብረታችን ከሁለት ከፍለህ ግማሹ ለሙት ልጆች እንድትሠጥልን አደራ በማለት ጠየቀው ሌላው ጓደኛው ደግሞ እኛ ሰላሞታችን እናስብ ስለሙት ልጆችና አሮጊቶች ደግሞ እግዚአብሔር



ያስባል አለው በዚህ ጊዜ ዲዮቅልጥያኖስ እየተደነቀ ላንድ ሰዓት ፀጥ አለ አርያኖስ ግን እኛን ሰማያዊ ክብር ስለሚጠብቀን ጊዜ አትውሰድብን ቶሎ ግደለን አለው። ዲዮቅልጥያኖስ ወዲያው አሸዋ የሞላ ጆንያ በያንዳንዳቸው ሰውነት ላይ እያሳሰረ አምስታቸውን ወደባሕር ጣላቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በዚሁ ሕይወታቸው እንዲያበቃ አልፈቀደም ስለሆነም አምስቱን አንድ ላይ ዶፋኒ የተባለው ዓሣ ተሸክሞ እስክንድርያ አደረሳቸው ከዚያውም ወጥተው የፊሊሞን መአንዝር አፅም ካረፈበት ሄዱ። በዚያውም አምስቱ እንቅልፍ ያዛቸውና በዚያውም ይህን ዓለም ተሰናበቱት የእስክንድርያ ክርስቲያንም የቅዱሳን ሰማዕታት አፅም ካረፈበት የአምስቱን አስክሬን አሳረፉ።

## ምዕራፍ ፫ የቅዱስ ቴዎዶስ ተጋድሎ፣ ትምህርተወንጌልና ዕረፍት ከዚህ ይነገራል።

አረማውያን በመላ ምድረኤውሮፓ አይለውና ክርስትናን ከገፀምድር አጥፍተናል ካሁን በኋላ ክርስቲያን ብሎ ነገር በአካባቢያችን ድምፁን ከማንሰማበት ደረጃ ላይ ደርሰናል በሚሉበት ወቅት ገላትያ ከምትባለው አገር ቅዱስ ቴዎዶስ ብቅ አለ። ከክርስቲያኖች መካከል ብዙዎቹ አልቀዋል /ተገድለዋል/ ያልቻሉት ደግሞ ተሰደዋል ባሉበት ለመኖር የፈለጉ ግን ክርስቲያንነታቸውን ደብቀውና ሰማቸውን ለውጠው ተቀምጠዋል። በዚህ ጊዜ ከነሱ መካከል በግልፅ ስለክርስቶስ ለመመስከር ታጥቆ የተነሳ አንድ ሰው ተገኘ። እሱም ቅዱስ ቴዎዶስ ነው። ይህ ሰማዕት የተነሳበት አገር ገላትያ ይባላል። የገላትያ ሰዎች



www.ethiopianorthodox.org

የጳውሎስን ትምህርት ከተቀበሉ በኋላ ነው እንደገና ለአረማውያን አሕዛብ የተጋለጡት ያለፍርሐት በግልፅ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ማንሳት ሲጀምር የገላትያ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ሳያነሳ በሰላም መኖር እንዳለበት ካልሆነ ደግሞ ሳይውል ሳያድር እንዲሰደድ ወትውተውት ነበር።

እሱ ግን "እኔ ከዚህ ሸሽቼ ብሔድ የሚገጥመኝ አላውቅም ሕይወታችንን እናተርፋለን በማለት ሲሸሹ በተፈጥሮ በሽታ የሞቱ አሉ በየመንገዱ ብዙ የተፈጥሮ አደጋ አለ። እኔ ይህን የዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚያስጠው ዕድል ገፍቼ የትም አልሸሽም ለንጉሡ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቴን ሠጥቼ ስለሱም እየመሰከርኩ በጎቹን በመሰብሰብ ላይ እያለሁ ይህን ዓለም ብለየው ታላቅ ተስፋ ይኖረኛል" የሚል መልስሠጣቸው በማያያዝም ስብከተወንጌልን ባስደናቂ ድፍረት ያካሄድ ጀመር።

ቴዎዶስ በፍፁም ቃለ እግዚአብሔር እንዳይነገርበት በተከለከለው ጊዜና ቦታ የክርስቶስ ሐዋርያ ሁኖ መገኘት በአረማውያን መንግሥታት ላይ ድንጋጤ ፈጠረ ያካባቢው መኮንን የበታች ሹማሙንቶቹን በተፅዕኖ ስለሆነ የካዱት ቴዎዶስን ምክንያት እየፈጠሩ ላያመጡት ይችላሉ የማለት ጥርጣሬ አደረበትና ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ወታደሮቹን ሰብስቦ ቴዋዶስን ይዛችሁ ካላመጣችሁ ሁላችሁንም እፈጃለሁ በማለት አስጠነቀቃቸው። ነገርግን እነሱ ከመንቀሳቀሳቸው አስቀድሞ ቴዎዶስ በገዛ ራሱ ወደመኮንኑ መጣ ክርስቲያንን በመፍጀቱ፣ ጣኦታትን በማምለኩና የአጋንንት ተገዢ በመሆኑ ትልቅ ውርደት ሊገጥመው እንደሚችል እየገለፀ ገሠፀው መኮንንኑም እጅግ ተናደደና ልብሱን አስወልቀው ዕራቆቱ እንዲያስተኙትና በደረቀ የከብት ቁርበት ጠፍር እንዲገርፉት



አዘዘ።

ግርፋቱን በፀጋና በአኮቴት ተቀብለው ሰውነቱ እየተቦጫጨቀ ቢነሳም ለዚህ ታላቅ ክብር በመብቃቱ እጅግ ደስታ ተሰማው በስምህ ለሥጋዊ ሥቃይ በመብቃቴና የሕመምህም ተካፋይ በመሆኔ አመሰግናሃለሁ እያለ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ይጠራ ነበር። ከግርፋቱ በኃላ መኮንኑ የኔ ሥልጣን ከዚህ በላይም እንደሆነ ልትረዳ ይገባል በሕይወትም እንድትኖር ክርስቶስን መከተልህን ተው አለው። መኮንኑ <u>ቴዎጤቆኖስ</u> ይባላል። ቴዎዶስ ግን አንተ ዓይንህ የታወርክነህ የምታሠቃየውና የምትገድለው በድኑን ነው። ነፍስን የማሰቃየት ችሎታ ግን የለህም። አንተና ጣኦታትህ ተያይዛችሁ ትጠፋላችሁ የክርስቲያኖች ተስፋ ግን እየደመቀና እየበራ ይሄዳል አለው።

መኮንን ቴዎጤቆኖስ "አማልክት የሚያመልኩትን ወገኖቼን አታስከዳብኝ አማልክቶቻችንም አትስደብ እኔንም ከአማልክት ትእዛዝ ለማራቅ አትሞክር ያንተ ሥራ ከአማልክት ትእዛዝ የወጣ ከንቱ ነው እኔ በሥጋህ ላይ መከራ በማፅናት የአማልክትን አመላለክ እንዲገባህ አደርጋለሁ አለው ቴዎዶስ አንተ በሥጋዬ ላይ መከራን ባከበድክ ቁጥር እምነቴ እየፀና ይሄዳል እንጂ አይቀንስም መከራውን ሁሉ እንድታገሠው ጌታዬ ኢየሱስክርስቶስ ሐይል ይሠጠኛል ሕይወቴን እስከማሳለፍ አንተ በኔ ላይ ብዙ ብትደክምም ውጤትህ ከንቱ ነው። ነፍሰገዳይ ትባላለህ እንጂ በጥሩ ስም አትጠቀስም ጨካኝነትህ ተመልሶ አንተን ይበላሃል አለው። መኮንኑ እንደገና አስገረፈው ዕራቆቱንም አውጥቶ በብርድና በፀሐይ አሠቃየው በዚሁ ሁሉ ሊመለስለት ስላልቻለ ወደእሥር ቤት አስገባው እሥር ቤት ሲገባ እሠረኞቹን ሌት ተቀን



www.ethiopianorthodox.org

ያስተምራቸው ጀመር በዚህ መኮንኑ ተጨማሪ ብስጭት ደረሰበት ቴዎዶስ አምስት ቀን ሙሉ በወህኒ ቤቱ ስለሰነበተ በዚያ ያሉትን ሁሉ ክርስቶስን በማመን አፀናቸው አሳመናቸውም።

ከአምስት ቀን በኋላ ከእሥር አስወጥቶ በማቅረብ መኮንኑ ባክህ ሌላ ሥራዬ ልሥራበት የአማልክቶቼ መሰደብ ጊዜ አልሠጠኝም አንተን የተለያዩ ሥቃይ ላደርስብህ ሳስብ ከምናር ባክህ ሰላም ሥጠኝ ለአማልክትም ሥግድ በማለት ያግባባው ጀመር። ቴዎዶሰም "አንተ ብዙ መከራ ካደረሰክብኝ ጀምሮ ከፈጠሪዬ ለመሸሽ አልሞከርኩም ሥጋዬ በተጎሳቆለ ቁጥር በኢየሱስ ክርስቶስ እየታደሰ ይሄዳል። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ አለምን በእጁ ይዞ እያለ የሰዎችን ግርፋትና የጭካኔ ድርጊት በትዕግሥት ተቀበለ መከራ በደረሰብኝ ቁጥር ሕሊናዬ በጌታዬ መሥቀል ሥር ነው የሚሆነው በአምላኬ የምቀበለው መከራና ሞት የክብር አክሊልን ያቀዳጅኛል" አለው።

መኮንኑ ከባድ ንዴት ተሰማውና "አንተ ከኔ ፊት የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስ ስም አትጥራ በማለት ፊቱን በድንጋይ መታው ቴዎዶስ ደግሞ አንተና አማልክቶችህ ርኩሳን ናችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም የረከሰውን ይቀድሳል አንተ ፈጣሪህንና የፈጣሪህን ስም ለመፀየፍ ትሞክራለህ ማንነትህን የዘነጋህ ለርኩሳን አጋንንት የተገዛህ ነህ የሕያው አምላክን ስም መስማት ያስጠላህ ጆሮህ ሰለደነቆረ ነው። አጋንንት ጓደኞችህ ጌታችን በአካለ ሥጋ በየደረሰበት ሁሉ ልታጠፋን መጣህን እያሉ ይንጫጩ ነበር አንተም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ስትሰማ ሰውነትህተቃጠለ ህሊናህ ተኮማተረ አንተ ከነሱ አንዱ ነህና። እኔ የዘለዓለማዊውን ተስፋ በመጠበቅ



የሥጋን መከራ በአኮቴትና በፀጋ እቀበላለሁ አንተደግሞ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ኢሰብአዊ ተግባርን እየፈፀምክ የሕሊና እረፍትን በማጣት ሕሊናህ እየወቀሰህ በቁምህ በእሳት ነደህ ትሞታለህ አሁን ለሚቀረው ክብር አንተ ሌት ተቀን ስትደክምና በሰው ሕይወት ስትፈርድ እኔ እንዴት ለዘለዓለማዊው ክብር አልጭነቅም ይህ የለበስኩት ሥጋ ጭቃ ነው በሌላ በሽታም ሊጠቃ ይችላል የማትሞትዋ ነፍሴ ከሥጋዬ ስትለይ ሰማያዊውን በረከት ልቀበል ይገባኛል" የዚህ ዓለም መኳንንትሆይ ይህን የአጋንንት ሥራ ትታችሁ ወደዘለዓለም ሕይወት ምንጭ ኢየሱስ ክርስቶስ ትመለሱ ዘንድ ማን መጥቶ ይንገራችሁ እግዚአብሔር የሠጣችሁን አእምሮ ሳትጠቀሙበት ከእንስሳት በታች እንደሆናችሁ ዕድሜያችሁ ያልቃል ወደእግዚአብሔር ትመለሱ ዘንድ ማን በነገራችሁ? ከክርስቶስ ጋር መንግሥትን የመካፈል ክብር ትታችሁ በእብደት ጎዳና ትጓዛላችሁ በማለት ከገሰፃቸው በኃላ ክርስቲያኖችን እኔ የክርስቶስን መንግሥት ለማግኘት የዚህን ዓለም ሕይወት ችላ ብየዋለሁ በሕመም ፈንታ ጤንነትን፣ በሐዘን ፈንታ ደስታን፣በጭንቅ ፈንታ ዕረፍትን በረሐብ ፈንታ ጥጋብን በጥም ፈንታ የሰማያት ጠልን ወደሚሰጥ አምላክ እሄዳለሁ በማለት ተናገራቸው።

ክርስቲያኖቹ ይህን ምክር ተናግሮ ሲሰናበታቸው አለቀሱ ቴዎዶስ ግን ንጉሡ ምድራዊ ሹመት ሊሠጠኝ ቢጠራኝ በተደሰታችሁ ነበር ዘለአለማዊ የአምላክ መንግሥት ለመውረስ ስሄድ ግን አለቀሳችሁ። እናንተም የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ተሸከሙት ዘለዓለማዊውን ክብር በዚህ ዓለም ሐላፊ ተድላና ደስታ አትለውጡት እግዚአብሔርም ሐይሉና ብርታቱ ይስጣችሁ ሲላቸው አሜን አሉ።

ሊገድለው የተዘጋጀው የንጉሡ ወታደር በዚህ ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

ለመግደል ዓይኑን ሊሸፍነው ቀረበ ቅዱስ ቴዎዶስ ግን ከፊታዳቸው ውጭ የሚሞቱት ናቸው ሲገደሉ ዓይናቸውን የሚሸፍኑት ስለዚህ እያየሁ መገደልን እፈልጋለሁ አለው ወታደሩም ዓይኑን ሳይሸፍን በሠይፍ አንገቱን ቆረጠው ሰማዕትነቱንም በዚሁ ፈፀመ የቅዱስ ቴዎዶስ አሥክሬን ወስደው ወደየቦታቸው ለመቅበር ብዙዎች ይጓጉ ነበር ነገር ግን ቅዱስ ቴዎዶስ በሞትኩ ጊዜ ወደ ትውልድ አገሬ ወስዳችሁ ቅበሩኝ ብሎ ስለነበር አንድ ሽማግሌ ሰው ያገሩ ተወላጅ ከዚያ ነበርና ራሱ በተናገረው መሠረት ሌሎች ሰዎችን አሰባስቦ አስከሬኑን በአህያ ጭኖ ወዳገሩ በመውሰድ ቀበረው። በሱ የገድል ፅናትም ብዙዎች ክርስቲያን እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

## <u>ምዕራፍ ፬ የ፵ ሐራሰማይ ሰማዕትነት</u>

ሉውክያኖስ የተባለው ንጉሥ በሮም በነገሠ ጊዜ እግዚአብሔርን በሚያመልኩ የሰው ልጆች ከፍተኛ ስደት ደረሰ ከሐዲዎች እግዚአብሔርን በሚያመልኩ ሕዝቦች ላይ እያደነ የመፍጀት ዘመቻ አካሄዱ። ከመከራ ብዛት የተነሳ ጣኦት ለማምለክ ተገደዱ ከሉውክያኖስ የበታች ሹማምንትአንዱ ግሪኮልዮስ መኮንን በጭካኔው የታወቀ ነበር። በዚህ ጊዜ በውትድርና አገልግሎት እያለ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች ተገኙ ቁጥራቸው ፵ ነበር የያንዳንዳቸው ስምም በመጽሐፍ ተዘርዝሯል። ግሪኮልዮስ መኮንን እምነታቸውን ሰምቶ እነሱ በውትድርና አገልግሎት ተመድበው ወደሚኖርበት አገር /ከበዶክያ/ ሄደና የ፵ው ወታደሮች በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እጅግ የጠበቀ ሁኖ አገኘው። መኮንኑ ግሪኮልዮስ ከያሉበት የውትድርና ምደባ ቦታቸው አስጠርቶ እናንተ በጦር አርበኝነታችሁ የታወቃችሁ ናችሁ ጠላትን ስታሸንፉ ኑራቹኋል አሁንም የንጉሥ ልውክያኖስ ትእዛዝን በማክበር



ተወዳጅነታችሁን እንድታሳውቁ ይሁን ካልሆነ ግን ቅጣት ይጠብቃቹኋል አላቸው።

፵ ሐራሰማይ ግሪኮልዮስ መኮንን የሚላቸውን በፅሞና ካዳመጡ በኃላ አዎ አንተ እንደምትለው ምድራዊ ንጉሥን ለማስደሰት በውትድርና ተሠልፈን የንጉሡን ጠላቶች ከገቡበት ገብተን እንገድላቸው ነበር ይወደናል ሥልጣን ይሠጠናል ብለን ለሚሞተው የምድር ንጉሥ ይህን ያህል አገልግሉት ካበረከትን የሰማያዊው ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች ብንሆንማ ምን ያህል ክብርና ሞገስ፣ ተድላና ደስታ እናገኝ ይሆን ሲሉ ባንድ ድምፅ መልስ ሠጡት ግሪኮልዮስ የሚሻላችሁን አሁኑኑ ምረጡ ለአማልክት ብትሠው ክብርና ሐብትን ታገኛላችሁ እምቢ ብትሉ ግን ከክብራችሁ ወርዳችሁ ሐፍረትንና ውርደትን እንዲሁም መዘባበቻ መሆንን ትላበሳላችሁ፣ በሕዝብ ፊት ይህ ሁሉ ሲፈፀምባችሁ ለናንተ ታላቅ ውርደት መሆኑን እወቁ አላቸው።

<u>፵ ሐራሰማይ</u> እኛስ የሚሆነንን መርጠናል እግዚአብሔር አምላካችንን እናመልካለን። የሰው እጅ ሥራ ለሆኑ ጣኦታት መሥዋዕትን አናቀርብም ሕይወታችንን ለንጉሠሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ እናቀርባለን ሥጋችንም ለሱ መሥዋዕት እናቀርባለን ይህ መሥዋዕት የእውነት መሥዋዕትነው አሉት መኮንኑ በአነጋገራቸው ተቆጥቶ አርባውን ሁሉ ስብሰቦ ወህኒ ቤት አሰገባቸው ወህኒ ቤት ከገቡ ጀምሮ ይፀልዩና ይዘምሩ ነበር። ከ፵ው ውስጥ በዕድሜ የሚበልጠው <u>ወፈንዲኪዎስ</u> ይባላል ይህ ሰው ያበረታታቸው ነበር። <u>እግዚአብሔርም</u> የእምነታቸውን ፅናት ተመልክቶ ተገለጠላቸውና እስከመጨረሻው እንዲፀኑ አረጋጋቸው የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ ፈሩ ሌሊቱንም ሁሉ በፀሉት አሳለፉት።



www.ethiopianorthodox.org

ሲነጋ ግሪኮልዮስ መኮንን ከበታች ሹማምንቱ ጋር ባደባባዩ ተሰይሞ ከታሠሩበት አስወጥቶ ከፊቱ በማቆም የምላችሁን ስሙኝ የምላችሁን ከፈፀማችሁ ከንጉሡ ዘንድ አቅርባችሁና በያዛችሁት የውትድርና ሥራ ላይ ከፍተኛ የሥልጣን መአርግ እንዲሠጣችሁ አደርጋለሁ ይህም ስላችሁ እናንተን በመፍራት ሳይሆን እናንተን በማክበር ነው ከምንጠላችሁ ብንወዳችሁ ይሻላል በማለት ያግባባቸው ጀመር።

ኩርዩን /በመካከላቸው የዕድሜ ትልቁ/ እኛ ለራሳችን የሚያዋጣንን ይዘናል የሚሆነን መርጠናል አንተን ጠልተናል አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደናል እኛ ባንተ ዘንድ የተጠላን ነን አንተ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላህ ነህ አለው በዚህ ጊዜ መኮንኑ እንደአንበሳ ጮኸ እንደገና ያሥሩዋቸው ዘንድ አዘዘ እነሱም ተመልሰው ታሠሩ ይፀልዩና ይዘምሩም ነበር። መኮንኑ እንደገና አስጠርቶ ሊያግባባቸው ብዙ ጣረ ቃልህን አንሰማም ትእዛዝህን አናከብርም ለአማልክቶችህ አንሠግድም የምትፈልገውን ሁሉ በኛ ላይ ፈፅም እኛም ለእግዚአብሔር ብለንና እሱንም አምነን በሥጋችን ላይ የሚደርሰውን ሁሉ እንቀበላለን አሉት።

መኮንኑ በዚህ ጊዜ ተናደደና በድንጋይ ራስ ራሳቸውን አስቀጠቀጣቸው። እነሱም ብዙ ታገሱ ቆይቶ ግን ወታደሮቹ እነሱን ለመደብደብ የሚወረውሩት ድንጋይ እየተመለሰ ወርዋሪዎቹን ይቀጠቅጣቸው ጀመር። ይህን ተአምር ሲያዩ ፵ ሐራሰማይ እምነታቸው እየጠነከረ ሄደ ግሪኮልዮስም ከመናደዱ የተነሳ ድንጋይ አንስቶ ሲወረውርባቸው የወረወረው ድንጋይ ተመልሶ ራሱን ፈነከተው። ብዙ ጊዜ መልሶ መላልሶ መኮንኑ በወህኒ ሲያሰቃያቸው ከጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኔ ያመነ ቢሞትም ይድናል



እናንተም ፅኑ ከካሐድያን የሚደርስባችሁንም መከራ በትዕግሥት ተቀበሉት እንጂ አትፍሩ ከዚያ የማያረጅ የሰማዕታትነት አክሊልን ትቀበላላችሁ መንግሥተሰማያትን ትወርሳለችሁ አላቸው በዚህም ደስታቸው እጅግ በዛ።

ግሪኮልዮስ በመጨረሻ የእያንዳንዳቸውን አንገት በገመድ አሳስሮ በገመድ እያስጎተተ በረዶ ወዳለበት ባሕር አስወረወራቸው። በረጋው በረዶ ላይ ተጥለውም ከጧት እስከማታ ዋሉ። በረዶውና ቅዝቃዜውም እጅግ ፀንቶባቸው ዋለ። ሥጋቸው ከቅዝቃዜው ብዛት ተሠነጣጠቀ ከባሕሩዳር ተቀምጠው ይጠብቁዋቸው ከነበሩት ወታደሮች አንዱ ፅናታቸውንተመልክቶ በሃይማኖት ወደነሱ ተጨመረ ሰመእግዚአብሔርን በመጥራትም ለሰማዕትነት ተዘጋጀ።

ከ፵ ሐራሰማይ ውስጥ በጣም በዕድሜ ትንሽ አንድ ወጣት ነበር ስሙም ሚሊጦስ ይባላል ከወንድሞቹ ጋር መከራ እየተቀበለና የሰማዕትነትን ዓላማ እየተከተለ እያለ እናቱ አልባሌ መስላ መጣች። እናቱ እግዚአብሔርን የምታምን ክርስቲያን ነበረች አመጣጥዋ የልጅዋን ሚሊጦስን አኳኋን ለመመልከት ነበር። ከበረዶማው ባህር ሠጥሞ እንደሆን ወይም ደግሞ ከመከራው ፅናት የተነሳ መታገሡን አቋርጦ እንደሆን ለመመልከት ነበር። ነገር ግን ልጅዋ ሚሊጦስ ይህ ሁሉ መከራ እየደረሰበት እያለ ምንም ወደ ኋላ ሳይል መከራውን ታግሦ እግዚአብሔርን እያመሰገነ አገኘችው የዘመነሰማዕታት ክርስቲያኖች እናቶች ልጆቻቸው በሰማዕትነት ለኢየሱስ ክርስቶስ እየመሠከሩ እጅ እግራቸው እየተቆረጠ ለሰብአዊ ፍጡር እጅግ በሚዘገንን አኳኋን ሲገድሉ እልል ይሉ ነበር በመንፈሳዊ ፅናታቸውም ለደስታቸው ወሰን አልነበረውም።



www.ethiopianorthodox.org

ጣኦትን በማምለክ ብቻ የተወሰነ አልነበረም ክርስቲያኖችን ለመንጠቅና ወደአምልኮባእድ ለማስገባት የተሰለፉ ነበሩ።

ንጉሡ ጠጥያኖስን ሲያግባቡትም እንዲህ አሉት አንተ የአማልክት ጓደኛ ነህ እንደነሱም ልትመለክ ይገባል። አንተ አብረህ እንድትመለክ ካስፈለገ ደግሞ ትልቅ በዓል ተደርጎ አንተ የምትገዛው የሮም ሕዝብ ለመሥዋዕቱና ለበዓሉ ክብር ትልቅ ዝግጅት ማድረግ አለበት ስለዚህ ያንተ ጥብቅ ትእዛዝ ለሁሉም ይተላለፍ አሉት።

ንጉሡ በተደረገለት ውዳሴ ከንቱ ተጠልፎ ደስተኛ ሆነ የሮም ግዛት ወደሆነው ሁሉም በነሱ የተነገረውን ትእዛዝ አስተላለፈ። ክርስቲያኖች ጓጉተውና ተማርከው የጣኦቱ በዓል አከባበርና መሥዋዕቱ አቀራረብ እንዲተባበሩ በዚያው እምነታቸውን እንዲለውጡ ለማድረግ ለዚሁ ቅስቀሳ ወደየአቅጣጫው የተላኩ መልእክተኞች ሁሉ በወርቅ የተንቆጠቆጠና ያሸበረቀ መለዮ ለብሰው ነበር በየደረሱበትም በክርስቶስ ማመንን እጅግ ይነቅፉ ነበር።

የመሠርዮቹን ምክር ሰምቶ ንጉሥ ጠጥያኖስ ቅስቀሳውን ማካሄድ ከጀመረ በአምስተኛው ቀኑ እነሱን /መሠሪዮቹን/ ጠርቶ በዓሉ መቼ መደረግ እንዳለበት በሚወያዩበት ወቅት ለያንዳንዳቸው የወርቅና የብር ሽልማት ሠጣቸው አማልክት እንዳይቀየሙም ማንም ሰው ራሱን ከነሱ ውጭ ሌላ ከማመን እንዲያፀዳ አዘዘ ክርስቲያኖች ብቻ የረከሱ ሁነው እንደሚገኙ የውይይቱ የመነጋገሪያ ርእስ ሆነ እንደገና በአሥራኛው ቀንም ክርስትናን የሚያወግዝ ጣኦትን የሚያሞግስ ውሳኔ ተላለፈ።



በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖች ከመቼውም በበለጠ ታላቅ ፈተና እንደሚጠብቃቸው አወቁ በወቅቱ እምሪዮስ የሚባለው ኤጴስቆጶስ በሕዝበክርስቲያን ዘንድ እጅግ የተወደደ ነበር የፀጋ እግዚአብሔር ሐብቱና ሥጦታውም እጅግ የላቀ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በዚሁ ኤጴስቆጶስ መሣሪያነት ብዙ ድንቆችን ሠርቷል ሌት ተቀን ባጭር ታጥቆ ስብከተወንጌልን ያስፋፋና የእግዚአብሔርን ህልዎት ለሰው ልጆች በማሳወቅ ግዴታውን የተወጣ ዳግም ጳውሎስ ነበር።

ኤጴስቆጶስ አምርዮስ፣ ንጉሥ ጠጥያኖስ በማካሄድ የነበረውን እኩይ ተግባር ለመቃወምና ለማውገዝ ክርስቲያኖች እንዳይታለሉና ተሳስተው ወደሱ እንዳይገቡ ለማድረግ ወደየአቅጣጫው መምህራኑ ወንጌልን አሠማራ በግሉም አንዳንዱ በመሆን ሩጫውን ተያያዘው በትምህርቱ ላይም የእግዚአብሔር ባርያዎች ክርስቲያንና ክርስትናንም ያልተቀበላችሁ አረማውያን ሁሉ የእግዚአብሔር ቤት ወደሆነችው ቅድስት ቤተክስቲያን ኑ ምሕላና ፀሎትም ወደእግዚአበሔር እናቅርብ፣ የእኩያን ሥራ በእግዚአብሔር ሐይል እንዲበተን እግዚአብሔርን እንማፀነው ይል ነበር።

በሱና በተከታዮቹ በተደረገው ሐዋርያዊ ተልእኮ ብእለተ ቀዳሚ የክርስቶስ መንጋዎች የሆኑ ሁሉ አንድም ሳይቀር ከሩቅም ከቅርቡም ተሰበሰቡ ምሕላቸውንና ፀሎታቸውንም በኤጴስቆጶስ አምርዮስ መሪነት አካሄዱ ለሚመጣው መከራም ያላንዳች ፍርሐት ዝግጁዎች ሆኑ ምሥጢራተ እግዚአብሔርን በልቡናቸው በማሥረፅ ሕዝቦችን ወደቤተክርስቲያን ለማምጣት ኤጴስቆጶስ አምሪዮስ ለመማረክ ሲሯሯጥ ንጉሥ ጠጥያኖስ በፊናው በወርቅ፣ በብርና በዘፈን ሕዝበሮምን ወደአምልኮ ጣኦት ለመማረክ ሩጫውን አጧጧፈ። በዚሁ ከፍተኛ ትንቅንቅ ተፈጠረ። ንጉሡ ነጋሪት እያስጎሰመ ሰልፍን እያሳመረ ጊዜያዊ ጥቅምንም ለቀራቢዎቹና ለሰላዩቹ



www.ethiopianorthodox.org

አትፈልጉ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ብቻ ፅኑ ሴት ተቀን ወደእግዚአብሔር ከመፀለይ አትቦዝኑ"

በሄሬኔዎስ ኤጴስቆጳስ ፅናትና በክርስቲያኖች የሱን ትምህርት ሰምተው እስከመጨረሻዋ ደም ጠብታ ድረስ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ እግዚአብሔርን መከተል በቤተመንግሥቱ ዙርያ ፍርሐትንና ጭንቀትን ፈጠረ ክርስቲያኖች ግንባር ፈጥረው ሊቋቋሙን ይችሉ ይሆናል የማለትሥጋትም ከንጉሡ ጀምሮ እስከተራዎቹ አረማውያን ድረስ ሰፈነ። በዚህ ፍርሐት የተነሳም ከሰላይነትና ጆሮ ጠቢነት አልፎ በክርስቲያኖች ላይ ሌላ ቅጣት ለማድረስ የሞከረ አልነበረም ቀስ በቀስ ግን ክርስቲያኖች ስለሃይማኖታቸው ደማቸውን እንጂ የማንንም ደም እንዳማያፈሱ ንጉሡም ሆነ ተከታዮቹ ሊረዱ ቻሉና ሠይጣናዊ ዓለማቸውን በሥራ ላይ ለማዋል ተነሱ ንጉሡ በቤተክርስቲያን ውስጥም ሆነ ውጭ ያገኙትን ትንሽም ይሁን ትልቅ ሴትም ትሁን ወንድ ወደጣኦት መጥቶ እንዲሠግድ ንገሩት እምቢ ካለ ግን ባለበት ግደሉት ብሉ ሠይፍንና ጎራዴን ጦርንም የያዙ ወታደሮቹ በያቅጣጫው ላከ። ከነሱ የተወሰኑ ወታደሮች ወዳንድ ቤተክርስቲያን ሲገቡ ቴዎቅሪጦስን አገኙት ጥርሳቸውን በማፋጨት ንዴት በተቀላቀለበት ቁጭት ያዙትና ወደቤተጣኦት ወሰዱት ቴዎቅሪጦስ ገና ለግላጋ ወጣት ነበር። ወታደሮቹ እያንገላቱ ሲወስዱት አንድ ቆምስ ቢያጦሪኖስ የሚባል አገኘውና ልጄ ሆይ ወደጣኦት እንዳትሰግድ ከእግዚአብሔርም እንዳትለይ በርታ አለው እሱም አባቴ ሆይ እኔ መከራውን ሁሉ ለመቀበልና እግዚአብሔርንም ለማገልገል ተዘጋጅቼአለሁ አለው ቆሞሱ ቢያጦሪኖስና አብሮት የነበረው ሌላ ሰው ከወጣቱ ቴዎቅሪጦስ በሠሙት የጥብእትና ለሰማዕትነት መዘጋጀት እየተደሰቱ ሩጫቸውን ቀጠሉ። ተይዞ ወደቤተመንግሥት ሲገባ ለጥያቄ ተይዞ በዚያ



የነበረው ሄሬኔዎስ ኤጴስቆጶስን አገኘውና አንገት ላንገት ተቃቅፈው ተሳሳሙ ንጉሡ ወደአደባባዩ አቅርቦ ቢያጦሪኖስን አንተ የደስደስ ያለህ ለግላጋ ወጣት ለአማላክት ከሰገድክ ጌትነት ይጠብቃሃል ጌታ መሆን ወይስ ባርነትን ትመርጣለህ ሲል ጠየቀው ቢያጦሪኖስ ግን እኔ የኢየሱስክርስቶስ ባርያ ነኝ ሲል መለሰለት ለምን ብሉ ቢጠይቀው ከናቴ ማህፀን ጀምሮ ለባረከኝ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነውባርነቴ ሲል መለሰለት እናትህ ማናት ሲለው እናቴ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትናት አባቴም ሰማይና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው አለው ንጉሡም አንተ መልከመልካም ወጣት ነህ መልካሙ ቁመናህ የበለጠ እንዲዋብ ለአማልክት መሥዋዕት አቅርብ በማለት አግባባው ቢያጦሪኖስግን ንጉሥ ሆይ ትሳሳታለህ በዚህ ዓለም እግዚአብሔርን መመኪያ አድርጎ በፅናት የተጋደለ ተስፋ መንግሥተሰማያት ይጠብቀዋል፣ እኔም ዘለዓለማዊውን መንግሥተሰማያት እንዳገኝ በዚህ ዓለም ለትዕግሥትና ለገድል መዘጋጀት አለብኝ ብዙ ሹመት ፈላጊዎች አሉልህ እንዴት እኔ ገና የ15 ዓመት ልጅ ስሆን ለሹመት ትመኘኝ አለህ አለው ለአማልክት ከመሠዋትና በአሰቃቂ አገዳደል ከመገደል አንዱን ምረጥ አለው። ቢያጦሪኖስ ደግሞ እኔ ለጣኦት አልሠዋም ራሴን ለአምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት አቅርቤ ዘለዓለማዊውን ሕይወት እወርሳለሁ አለው።

ንጉሡ የመጨረሻውን የወጣቱ ውጤት ለማየት ርግብ አስይዞ ጣኦት ወደሚገኝበት ቦታ እንዲወስድ አዘዘና ራሱም ከዚያ እንደሚገኝ አስታወቀ ወጣቱ ቢያጦሪኖስ ወደጣኦቱ በወታደሮች ታጅቦ ኤጴስቆጶሱ አየውና ልጄ ሆይ በኢየሱስ ክርስቶስ አክሊሎችን ልትቀዳጅ እየሄድክ ነው እከፉን አሸንፈው ከዲያብሎስ ችንካሮችም ራቅ በቤተክርስቲያን ቁመህ የሚወጡትንና የሚገቡትን ምእመናን ያስተማርከውን ቃለ እግዚአብሔር አትዘንጋ የምትጓዝበት መንገድ



www.ethiopianorthodox.org

መልካም ነው። አንተን የመሰለ ለግለ ጋ ወጣት በሰማዕትነት ጎዳና ወደመግሥተሰማያት አስቀድሜ በመላኬ እደሰት አለሁ አለው ቴዎቅሪጦስም እኔ ለኢየሱስ ክርስቶስ ራሴን መሥዋዕትነት አቅርቤአለሁ የመሥዋዕትነቴን መንገድ ባርክልኝ ዲያብሉስን አሸንፌ ወደመንግሥተሰማያት እየተጓዝኩ ነኝ አለው ኤጴስቆጶሱም የቅዱሳን ክብር ላንተ ይሁን እድገትህ በዚህ ዓለም ተቋርጧል ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ታሳድግህ በክርስቶስ እምነትህ በቅዱሳን ማሕበር ታቁምህ አለው ከዚያ የነበሩ ክርስቲያን ባንድነት አሜን አሉ።

ቢያጦሪኖስ እንዴት ገድሉን እንደሚፈፅም የመጨረሻውንው ጤት ለማየት ኤጴስቆጶሱና ሌሎች ምዕመናን ተከታትለው ሄዱ ንጉሡ በጣኦቱ ቦታ ቁሞ ጠበቀውና ለጣኦት መሥዋዕት አቅራቢዎቹ እናንተ ስሂን የተባለውን ሹቶ በአማልክቱ ላይ አፍስሱ ርግቧን ይዛችሁ ለቴዎቅሪጦስ ስጡትና ይሰዋ አላቸው በዚህ ጊዜ ቴዎቅሪጦስ "ዘላዓለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የሸመገሉትን ወጣቶችን የምታደርግ፣ ላመኑህ ሐይልህን የምታሳይ በመለኮታዊ ሥልጣንህ ለወፎች እስትንፋስን የሠጠህ፣ እነሱም የሚያመሰግኑህ አንተነህ ለሙታንም ሐይልህን ትገልፃለህ ጣኦቱንም ትነቅለዋለህ የኔን አነስተኛ መሥዋዕትን ተቀበለኝ" በማለት ፀለየ።

ውድያው የመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰተና ጣኦታት በሙሉ ተሠባብረው አመድ ሆኑ ቴዎቅሪጦስም አንተ ብዙዎችን ወደጨለማ የሰደድክ ምንም ሐይል የሌለህ የአጋንንት ማደሪያ ጣኦት እስኪ ከወደቅህበት ተነሳ እያለ ዘበተበት በዚህ ጊዜ ንጉሡ እጅግ ተናደደና ቴዎቅሪጦስን አፍንጫው እንዲቆርጡትአዘዘ አስቆረጠውም በዚህ ጊዜ ቴዎቅሪጦስ የአለም ገዢና የምሥጋና ጌታ እግዚአብሔር



ሆይ በአምላካዊ ሥልጣንህ ከሰማይ ወረደህ የኛን ደዌና በሽታንም ተሸከምክ የሞት ማሠሪያንም ፈታህ ... እያለ ፀለየ።

ንጉሡ ግን የቴዎቅሪጦስ በሃይማኖት መፅናትና አፍንጫውም ተቆርጦ በፀሎትና በእግዚአብሔር ምሥጋና መጠመድ ተመልክቶ እየተበሳጨና እየተናደደ ወደቤተመንግሥቱ ተመለሰ ከግንድ ጋር አጣብቀው እንዲያስሩትም አዘዘ። አፍንጫው ተቆርጦ ከግንድ ጋርም ተጣብቆ ታሥሮ እያለ ሌሊቱን ሙሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ አደረ ኤጴስቆጶሱ ደግሞ በቤተክርስቲያን ምእመናንን ሰብስቦ እግዚአብሔር ሐይልና ፅናት ይሠጠው ዘንድ እየፀለየ አደረ።

በማግሥቱ ንጉሡ ሰፋፊ ብረትን በእሳት አግለው ከዚያ ላይ እንዲጥሉት አዘዘ ቅዱስ ቴዎቅሪጦስ በብረቱ እሳት በተጣለ ጊዜ እጅግ የሚመስጥ ሽታ ከሥጋው እየወጣ አካባቢውን አወደው ንጉሡ ቢቸውግረው እንደገና ልብሱን ገፈው መልሰው እንዲያቃጥሉት አደረገ ቴዎቅሪጦስ የክርስቶስን ስም እየጠራ በትእምርተመስቀል ፊቱን እያመተበ በእሳቱ ውስጥ ሁኖ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር። በዚህ ጊዜ በላዩ ላይ ቴዎቅሪጦስ ሆይ በርታ ከሠይጣን ወጥመድም ራቅ የሚል ድምፅ ተሰማ። ይህንንም አምላካዊ ቃል ቴዎቅሪጦስን በማሠቃየት የነበሩ አረማውያን ሁሉ ሰምተውታል ወድያውም ከፍተኛ ዝናብ ዘነበና እሳቱን አጠፋው።

ቴዎቅሪጦስን መግደል በዚሁ አልሆንለት ሲል ንጉሡ አሥር ክንድ ጥልቀት ያለውን ጉድጓድ አስቆፍሮ ከላይ እስከታች ፍልጥ እንጨት ሹል እየሆነ እንዲሰካ ካደረገ በኃላ ወደዝያ እንዲጣልና አካላቱ ተቦጫጭቆ ይቀር ዘንድ አዘዘ እነሱም ከዚያ አስገቡት ነገር ግን እግዚአበሔር ስለጠበቀው በዚሁም አካላቱ



www.ethiopianorthodox.org

በመጨረሻም አንበሳና ነብር ከሚጠብቁበት ላይ እንዲጣል አዘዙ ሕዝቡም አውሬዎቹ ሲቦጫጭቁት እንዲያዩ አሥጠራቸው ቅዱስ ቴዎቅሪጦስንም ደሙ በየመንገዱ እያንጠባጠበ ወደ ፖርኩ ተወሰደ ክርስቲያኖች የሱን ዕረፍት ለመረዳት በየቤተክርስቲያኑ ተሰበሰቡ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ከቅዱስ ቴዎቅሪጦስ ሰውነት እጅግ የሚመስጥና አካባቢውን በመልካም መዓዛ የሚያውድ ሽታ ይወጣ ነበር። አሕዛብ የሆኑ ሁሉ አማልክቶቻችንን ያወረደና የቀጠቀጠ ስለሆነ ይህን ክፉ ሰው አስወግድልን እያሉ በንጉሡ ላይ ጮኹ ንጉሡ እነሱን ለማስደሰት ከአንበሶቹ በጭካኔዋ የታወቀችና አስከፊ መልክ ያላትን እንስት አንበሳ አስወጣና ወደቅዱስ ቴዎቅሪጦስ ለቀቃት እሷ ግን ደሙን በምላሷ እየጠረገች እንደለማዳ የቤት ውሻ ጅራቷን እየቆላች ትታከከው ጀመር ታሸውም ነበር። በዚህ ጊዜ ቴዎቅሪጦስ ንጉሡንና ተከታዮቹን እናንተ እኔ ሕፃን ስለሆንኩ እግዚአብሔር ቸል የሚለኝ አይምሰላችሁ ሙሴ በሕፃንነት ዘመኑ በእግዚአብሔር ኃይል ፈርኦንን አሳፈረ፣ ዳንኤል በሕፃንነቱ በእግዚአብሔር ሐይል የአንበሶችን አፍ ዘጋ ኤርምያስ ገና በናቱ ከርስ እያለ ለነቢይነት ተመረጠ ሌሎችም ገና በሕፃንነት ዘመናቸው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተመድበዋል ስለዚህ እኔም በአካል ትንሽ ሁኜ ለሕያው አምላክ አገልጋይ እሆን ዘንድ ተመርጫአለሁ ወደናቴ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ለመድረስም እጓጓለሁ። ትዕግስት ግን መመርያዬ ነው። በተፈጥሮ ለሰው ልጅ አገልግሎት ብቻ የተፈጠሩ አእምሮ የሌላቸው እንሳስት ከናንተ ተሽለዋል። እያለ ይገሥፃቸው ጀመር።

ንጉሡ እንስትዋን አንበሳ አስገብተው ተባቱን አንበሳ እንዲያመጡበት አዘዘ። ነገር ግን እንስትዋ አንበሳ ከአይንዋ እንባ እያቀረረ ከእግሩ ንቅንቅ አልልም አለች ከልጅዋ



እንደምትለይም ሆነች። በግድ ጎትተው አስገቧትና ተባት አንበሳን አመጡ ይህም እየሮጠ መጥቶ ለቅዱስ ቴዎቅሪጦስ ሠገደ በእግሩ ላይም ተንከባለለ ፊቱ ወደሰዎቹ አዙሮም በኃይል ጮኸቱን አሰማ በዚህ ጊዜ ሊበላን ነው ወይ እያሉ በጣም ደነገጡ። በሰው አንደበትም አንተ የክፋትና የጥፋት መሣርያ ንጉሥ የአሥራ አምስት አመት ሕፃን ካንተ የሚደርስበትን መከራ ታግሦ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት ሲሆን እያየህ አትመለሰም…" እያለ ገሠፀው ወድያው ቅዱስ ቴዎቅሪጦስን አቀፈው ንጉሡ ተባቱ አንበሳን ወደቦታው አስመለሰውና ቅዱስ ቴዎቅሪጦስን በቀጫጭን ገመድ አጥብቀው እንዲያሥሩት አደረገ ይህም ያደረገበት ምክንያት ገመዱ ወደውስጥ ዘልቆ ገብቶ አካላቱን እንዲቆራርጠው ብሎ ነው። መከራውን ሁሉ በሚቀበልበት ሁሉ ክርስቲያኖች ከኤጴሰቆጶሳቸው ጋር የቅዱስ ቴዎቅሪጦስን በአሸናፊነት ከዚህ ዓለም መለየት በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ነበሩ ንጉሥ እንዴት ባንድ ሕፃን የኔ መንግሥት ይዋረድ አንተ ወራዳ ሕፃን አዋረድከኝ አሸነፍከኝም የኔ መንግሥት የት አለ የገንዘቤስ ብዛት የት አለ ባንተ ተሸነፍኩ ይህንንም ውርደት ልታገሠው አልችልም ከንፈሬ ተንቀጠቀጠ ጥርሶቼም እርስ በርሳቸው ተፋጩ ብሉ ብዙ የመናደድና የቁጭት ቃል አሰምቶ ከራሱ በመጀመር መሀል ለመሀል ለሁለት ሠነጠቀው ሰማዕትነቱንም በዚሁ ፈፀመ አምርዮስ ኤጴሰቆጶስ ከብዙ ምእመናን ጋር እግዚአብሔርን እያመሰገነ አሥከሬኑን ከቅዱሳን መቃብር ጋር አኖረው።

## ምዕራፍ ፩ ገድለዮሐንስ ወልደፀራቢ

ሐዋርያት በዓለም ወንጌልን እንዲሰብኩ ሲላኩ ለቀናተኛው ሐዋርያ ታዴዎስ በጤግሮስና ኤፍራጥስ ወንዞች ዙርያ የስብከት



www.ethiopianorthodox.org

ዕጣ ደረሰው በመጀመሪያ ሮሐ ወደ ተባለችው አገር ደረሰ ፯ ተማሪዎችንም እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ አስተምሮ አራቱ ወደ ደቡብ ምሥራቅ ላካቸው ወደባቢሉንም ተላኩ በዚያውም ወንጌልን አስተማሩ ከባቢሉን እስከሀገረንፅቢን የታዴዎስ ተማሪዎች ወንጌልን ሰብከዋል በነነዌና በዙርያዋም የታዴዎስ ተማሪዎች ወንጌልን ሰብከዋል።

ራሱ ቅዱስ ታዴዎስ ደግሞ በገላትያ በግሪክና በሚዲትራንያን ባህር አካባቢ አገሮች ወንጌልን አስተምሮ ብዙ አብያተክርስቲያናትን ተክሏል ካህናትንም በዚያው ልክ አብዝቷል ኤጴስቆጶሳት ቀሳውስት ዲያቆናትና ምዕመናን እጅግ በዝተው ታይቷል። ሕዝበ ክርስቲያኑ ሌት ተቀን እግዚአብሔርን በማገልገል ተጠምደው ነበር።

ክርስቲያኖች እየበዙ ከሐዋርያት በሰብአአርድእት ከዚያ ሐዋርያውን አበው እየተተኩ በዘመነሰማዕታ ይኖሩ ነበር ዲዮቅልጥያኖስ እስከነገሠ ድረስ ክርስቲኖች ከጊዜ ወደጊዜ እየበዙ በመሄድ ላይ ነበሩ። ዲዮቅልጥያኖስ በአንፆኪያ ስናክሬም በነነዌ፣ ክስዩን በባቢሉን ነገሡና እርስ በርሳቸው ይተላለቁ ጀመር የሁሉንም የመጀመርያ የዕልቂት ዓለማዎች ግን ክርስቲያን ሆኑ። ሦስቱ ነገሥታት እርስ በርሳቸው ቢዋጉም ክርስቲያንን አሳድዶ በመፍጀት ግን ሁሉም አንድ ነበሩ ክርስቲያኖች የሞቱት ሙተው ከሞት የተረፉት በየተራራው፣ በየሸንተረሩና በየዋሻው ተደበቁ አረማውያን በዙ፣ ክርስቲያን አነሱ።

በታዴዎስ ሐዋርያና በተከታዮቹ በነነዌ ክርስትና እንደተሰበከ ከላይ ገልፀናል በዚሁ በነነዌ አንድ ጣኦት እየጠረበ "በርጣሌ" ወደምትባል አገር እየወሰደ የሚሸጥ ሰው ነበረ ያገሩሰው ከዚሁ ሰው ጣኦት እየገዛ በየቤቱ ያስቀምጥ ነበር። ይህ ሰው በዚሁ



ተግባር ለአሥር ዓመት ተጠምዶ ኖረ ሚስቱ ግን በሐዋርያው ታደዎስ በነነዌ ሀገር ወንጌል ከተሰበከላቸው ወገን ስለነበረች ክርስቲያን ነበረች ይሁን እንጂ ክርስቲያንነቷን ደብቃ ትኖር ነበር ለአምስት አመት በሚስትነት የጣኦት ጠራቢው ሚስት ሁና ስትኖር ልጅ አልወለደችም ልጅ እንዲሠጣትም ወደእግዚአብሔር ትፀልይ ነበር። ልጅ እንደምትወልድና ልጁም የእግዚአብሔር ምሥክር እንደሚሆን ራእይ ተገለፀላት ባየችው ራእይ መሠረትም ወንድ ልጅ ወለደች፣ ስሙንም የተደበቀው ዮሐንስ አለችው አባቱ ደግሞ የአማልክት ልጅ የሚል ሥያሜ ሠጠው የስምንት አመት ልጅ እስኪሆን ድረስ በእንክብካቤ ካሳደገችው በኋላ እንዲላላከው ለባቱ ሠጠችው አባቱ የጠረበውን ጣኦት እንዲሸጥ ሁልጊዜ ወደገበያ ይልከው ነበር አራት አመት ጣኦቱን በመሸጥ አባቱን አገለገለከ ፭ አመት በኃላ እንደተለመደው ያባቱን ጣኦት ለመሸጥ ሲጓዝ የእግዚአብሔር መልአክ በመንገድ አገኘው ዮሐንስ ሆይ የት ትሄዳለህ ሲልም ጠየቀው እሱም አባቴ የጠረበውን ጣኦት ለመሸጥ እሄዳለሁ ሲል መለሰለት መልአኩም ለምን ጣኦት ትሸጣለህ አለው ዮሐንሰም ሰዎች እንዲሠግዱበት ሲል መለሰለት መልአኩም ያላንድ አምላክ ሌላ አምላክ የለም የያዝከው የአጋንንት ማደርያ ስለሆነ ጣለው አለው ዮሐንስም የትም ወረወረውና ወደባቱ ተመለሰ።

አባቱ አማልክትን ሸጠህ ያገኘኸው ገንዘብ የት አለ ሲል ጠየቀው ተራራንና ኮረብታን፣ ሰማይንና ምድርን ባህርንና ወንዝን ከፈጠረ እግዚአበሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም አለው አባቱም ክርስቲያኖች በሥራያቸው እንዳያታልሉህ ተጠንቀቅ እነሱ በሥራያቸው ሰውን ያሳስታሉ አለው ዮሐንስ ደግሞ አንተ የምትጠርበው ጣኦት የአጋንንት ማደርያ ነው ስለዚህ እኔ ለጣኦት አልሠግድም አለው። በዚህ ጊዜ አባቱ ተናደደና አሠረው።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ምክንያት መታሠሩ ስትሰማ እናቱ እጅግ ተደሰተች ወደታሠረበት ሄዳም ልጄ ሆይ ባለህበት ፅና በርታ የምንከተለዉ ኢየሱስ ክርስቶስ በአደባባይ ተገርፏል የተለያየ ፀዋት ወመከራን ተቀብሏል በመጨረሻም በመልእልተመስቀል በችንካር ተቸንክሮ ሞትን ቀምሷል። ስለዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ መከራና ሥቃይ የሚቀበሉት ብፁአን ናቸው የክርስቶስ ደም በምድር ላይ ፈሷል አዳምን ያዳነውም በደሙ ነው እናቱ ቅድስ ድንግል ማርያም ከሩቅ ቆማ ሲሰቅሉት ሲገርፉትና ሲቸነክሩት ትመለከት ነበር ስለሱም ታለቅስ ነበር። ዮሐንስ ልጄ ሆይ እኔም እንደሷ ከሩቅ ሁኜ የሚደርስብህን መከራ ደምህም ወደምድር ሲፈስ እመለከታለሁ ጥብአት ይደርብሕ አትፍራ አትተክዝ በልብህ ትካዜ አይኑር አለችው።

ዮሐንስ "እናቴ ሆይ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለማረድ እጁንና እግሩን እንዳሠረው ለማረድም በሆዱ እንዳስተኛው አስታውሳለሁ በዚህ ጊዜ ይስሐቅ ደስተኛ ነበር ከአቤል ፃድቅ ጋር መንግሥተሰማያትን እንድወርስ ስለተዘጋጀሁ ደስ ብሎኛል የዮፍታሄ ልጅ አባቷ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ወደኃላ እንዳይል ሴት ልጁ አባቴ ሆይ የገባኸውን ቃል ኪዳን ፈፅም ስላለችው በገዛ ልጁ መሬት ላይ አጋድሞ እንዳረዳት አስታውሳለሁ ስለዚህ እኔም ሕይወቴን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ ተዘጋጅቼ አለሁ መንግሥተሰማያትን እውርስ ዘንድ ስሜም በምድር ተደምስሶ መቅረት የለበትም አላት በዚህ ጊዜ እናቱ ከፍተኛ ክርስቲያናዊ ደስታ ተሰማትና አንገቱን ይዛ ሳመችው እንዲህም አለችው ልጄ ሆይ ደምህ በምድር ላይ ሲፈስ እያየሁ እደሰታለሁ እንጂ አላዝንም አንተን ዘጠኝ ወር የተሸከምኩባትንም ሆዴ አፀናታለሁ ከደምህም እቀባታለሁ አለችውና ተለይታው ሄደች።



ሲነጋ አባቱ መጥቶ ከታሠረበት አውጥቶ ሕዝብንም ሰብስቦ እናንተ ያገር ሕዝቦች ሆይ ይህ ልጅ ለአማልክት አልሠግድም ብሎ በኢየሩሳሌም አይሁድ ለሠቀሉትና ታሞ ለሞተ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሠግዷል ሲል አጋለጠው ለምን ለአማልክት መሥገድ ትተህ ለኢየሱስ ክርስቶስ ትሠግዳለህ አሉት እሱም እኔ የአጋንንት ማደርያ ለሆኑት ሠውሠራሽ ጣኦታት አልሠግድም አላቸው በዚህ ጊዜ አባቱ ተናድዶ መጥረቢያ አነሳና አገቱን መታው። ለብዙ ደቂቃ እንደቆመ ቆየ ደሙ ወደታች ወረደ በራሱ ደምም ተጠመቀ። እናቱም መጥታ በልጄ ደም እንድጠመቅ ስላደረግኸኝ ከክርስቲያን ማሕበርም እንድቆጠር ስለፈቀድክልኝ ልጄንም ስላንተ እየመሠከረ ለሥጋው ሳይሳሳ ከክብር ወደ ክብር እንዲሻገር ሳላደረግኸው ጌታዩ ኢየሱስክርስቶስ ሆይ አመሰግናሃለሁ የአሥራ አምስት ዓመቱ ሕፃን ልጄ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ እኔም የልጄን መንገድ እከተላለሁ የልጄ ደም ብቅድስና ፈሰሰ ደማቸውን በቅድስና የሚያፈሱ ክርስቲያን ብፁአን ናቸው አለች።

እየተደሰተችም ሄዳ ካህናትንና ምእመናንን ሰበሰበች እነሱም በምስጋናና በዝማሬ ደሙ ከፈሠሠበት ቦታ ላይ ቀበሩት። አባቱ ልጁን ከገደለ አንስቶ ሰላም አላገኘም ጣኦት አምላኪዎችን አስደስታለሁ ብሎ የፈፀመው ስሕተት ያንገበግበው ጀመር በእጁ የተገደለው ልጁ በፀፀት ሊያገኘው አልቻለም ከዚህ የተነሳ መጀመሪያ የሚጥል በሽታ ያዘው በየገደሉና በየጉራንጉሩ እየጣለ ያንፈራግጠው ጀመረ ቀጥሎ ጨርሶ አበደ ልብሱን ጥሎ ዕራቆቱ ይሄድ ጀመር በሰዎች ላይም ድንጋይም ይሁን ሌላ እየወረወረ አደጋ ማድረሱን ተያያዘው በዚህ ጊዜ እጅ እግሩ ታሥሮ ይቀመጥ ጀመር።

የሰማዕቱ ዮሐንስ እናት /ያበደው ሰው ሚስት/ እንዲያያይዟት ሰዎችን አሰባስባ የልጅዋ ዮሐንስ ደም ወደፈሰሰበትና ወደተቀበረበት



www.ethiopianorthodox.org

ቦታ ወሰደችው በዚያውም ቁማ ልጄ ሆይ አባትህን እንደባእድ አትመልከተው ከመንፈስ ቅዱስ የራቀ እንዲሆንም አታድርገው በስሙ ሰማዕትነትን የተቀበልክለት ኢየሱስ ክርስቶስን ወደሱ ይስበው ዘንድ ለምንለት ካለች በኃላ ፀሎቷን በመቀጠል ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ ፍጡርህ እንዲድን እንጂ እንዳይጠፋ መልእክተመስቀል በመሠቀልሕ ታምሃል ሙተሃልም ስለዚህ በፈሰሰው የልጄ ደም እማፀናሃለሁ መልእልተመስቀል የፈሰሰው ደምህ ለሐዋአን ሥሬየት ነው ስለዚህ ባሌ ወዳንተ ሳይመለስ አይሙትብኝ አለች። በዚህ ጊዜ በሰውየው ላይ ያደረው ሠይጣን እኔ በጣኦት ላይ አድሬ ሰዎች ሁሉ እንዲሠግዱልኝ አደርግ ነበር በባልሽ ላይ አድሬም ዮሐንስን አስገደልኩት አሁን ግን በዮሐንስ ልጅሽና ባንቺ ፀሎት ከሱ ወጣሁ መድረሻም አጣሁ እያለ ጮኾ ለቀቀው።

ይህ ሰው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አመነ ሚስቱንም በፅናቷ፣ ልጅዋ ሲሞት ከማዘን ይልቅ በመደሰትዋ እጅግ አደነቃት ቅዱሱን ልጄ ከኔ ወልደሽ ለኔም የዘለዓለምን ድሕነት ያስገኘሽልኝ ክብርት ባለቤቴ ሆይ አንቺን ለሰጠኝ እግዚአብሔር አመሠግነዋለሁ። የኔ ወንድነት ከንቱ ነበር ያንቺ ሴትነት ደግሞ በቅድስና የተሞላ ነበር ከኢየሱስ ክርስቶስ ሳትርቂ ከኔ ጋር መኖርሽን እጅግ አደንቃለሁ በማለት ባለቤቱን. አከበራት።

የነነዌና የአሜር ንጉሥ ስናክሬም ሲሞት ኔሮን የሚባል ንጉሥ በምትኩ ተተካ ይህ ንጉሥ ዓለዊ /ክህዷ/ ነበር። መነገሻ ከተማውም "ሐመዳን" በምትባለው አገር አደረገ። ንፅቢን ለተባለችው አገር ነው ይህ ስም የተሠጠው ንፅቢን ለምሥራቅና ለምዕራብ አገሮች አማካይ ሥፍራ ናት።

ይህ ኔሮን ሦስት ሰዎች የቅርብ ባለሟሎች ነበሩት ሦስቱ ማንኛውንም ምሥጢሩ ያውቃሉ ያረጋጉታል ይመክሩታል አብረውት



ይበላሉ ይጠጣሉ በሄደበት ሁሉ አብረው ይንቀሳቀሳሉ። የሦስቱ ሃይማኖት ግን የተለያየ ነበር አንዱ ክርስቲያን ሁለተኛው አይሁዳዊ ሦስተኛው አረማዊ ነበሩ። ንጉሡ ሁልጊዜ ጧትጧት መላ ሠራዊቱን አስከትሉ በፈረስ ተቀምጦ እስከሦስት ሰዓት ድረስ ከተማውን ከዞረ በኋላ ከመላ ሠራዊቱና መኳንንቱ ጋር ምሳ ከበላ በኃላ ሦስቱን አማካሪዎቸ ብቻ አስከሉ ወደልዩ መኖሪያው ይሄድ ነበር በዚህ አኳኃንም እስከ ፲ ዓመት ድረስ ተቀመጠ።

ከዚያ በኃላ አይሁዳዊው በክርስቲያናዊው ላይ ቅንዓት አደረበት ሁልጊዜ ምግብ ሲበላ ክርስቲያናዊው በትዕምርተመስቀል ያማትብ ነበርና ለንጉሡ በምንበላውና በምንጠጣው ላይ እያማተበ ክርስቲያናዊው ሥራይ እያደረገብን ነው ስለዚህ ድርጊቱን እንዲያቆም እዘዘው በማለት ነገረው። ንጉሡ የአይሁዳዊውን የስብቀት ቃል ሰምቶ ክርስቲያናዊውን በምንበላውና በምንጠጣው ላይ አታማትብ አለው እሱም እሺ አለና ማማተቡን ትቶ አንድ ዓመት ቆየ። ካንድ አመት በኋላ "ማራራ" የምትባል አገር ይገዛ የነበረው ንጉሥ የንፅቢን ንጉሥ የኔሮን ተቀናቃኝ ከመሆኑ የተነሳ ንፅቢንን ጨምሮ ለመግዛት ፍላጎት ስለነበረው ኔሮንን ከምግቡ ላይ መርዝ ጨምሮ በማብላት እንዲገድልለት አሥር ሺ ዲናር አስይዞ ለምግብ ሐላፊው ላከለት የንጉሡ /የኔሮን/ የምግብ ቤት ሐላፊም ገንዘቡን ተቀብሎ መርዝ የተጨመረበት ምግብ ለንጉሡና ለሦስት ተከታዮቹ ሊያቀርብላቸው ሲዘጋጅ መልአክ ለክርስቲያናዊው ተገልፆ ካንድ ዓመት በፊት ታደርግ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም በምግቡ ላይ እንድታማትብ ከኢየሱስ ክርስቶስ ታዝሃል ስለዚህ ሳትፈራ አማትብ አለው። እሱም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በምግቡ ላይ አማተበ በልቡም በስመአብ ወወልድወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ይል ነበር። ሲያማትብ ግን ማንም አላየውም ነበር



www.ethiopianorthodox.org

መብሉና መጠጡ ግን ባልተለመደ ሁኔታ ረጋ።

ንጉሡ ሊጎርስ እጁን ወደምግቡ ሲልክ ክርስቲያናዊው አትቅመሰው ይቅር ብህ ብሎ እጁን ያዘው ንጉሡ እያየም ክርስቲያናዊው አንድ ውሻ ጠራና ከቀረበው ምግብ አንሥቶ ለውሻው ሠጠው ውሻውም ወዲያው ሞተ ንጉሡም ክርስቲያናዊውን ምክንያቱ ምንድር ነው ብሎ ቢጠይቀው አንተንና እኛን ለመግደል በምግቡ ላይ መርዝ ተጨምሯል አለው ንጉሡም እንዴት አውቅኸው አለው።

ክርስቲያናዊው በኢየሩሳሌም ለሰው ድህነት ብሎ በተሰቀለው ንጉሠሰማያት ወምድር ኢየሱስክርስቶስ መስቀል ይህ ነገር ሊታወቅ ችሏል አለው ንጉሡ ወደ አይሁዳዊው ፊቱን በማዞር አንተ ክርስቲያናዊው የክርስቲያን በትእምርተመስቀል ማማተብ ሥራይ ሁኖ ምግቡን ይመርዘዋል ይገድላልም ብለህ ነግረኸኝ የለም እንዴ አለው የክርስቲያን ማዕተብ ገዳይ አይደለም አዳኝ እንጂ አለና በነገረ ሠሪነቱ ገሠፀው ከሐላፊነቱንም አስወገደው ከተቃጣበት የመርዛማ ምግብ አሟሟት ስለዳነም ጌታዮ ኢየሱስ ክርስቶስ በማሕየዊ መስቀሉ ስላዳነኝ ክርስቲያን ለመሆን እፈልጋለሁ አለና ካህናትን ሰብስቦ በመጥራት እንዲያጠምቁት ጠየቃቸው በስመአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስም አጠመቁት።

መርዙን ከምግቡ ላይ ማን እንደጨመረ ለማወቅ ፈልጎ ንጉሡ የምግብ ሐላፊውን አስጠርቶ ጠየቀው ይህ ሰው ምክንያቱን ልገለፅልህ እንደማትገድለኝ አስቀድመህ ቃል ግባልኝ አለው እሱም እንደማይገድለው ቃል ገባላት በምግቡ ላይ መርዝ የጨመረው ራሱ መሆኑንና ይህንንም ለማድረግ ያነሳሳው በአሥር ሺ ዲናር ተገዝቶ መሆኑን ገለፀለት ንጉሡም ይህን ሰው ትምህርተክርስትና አስተምሮ ንጉሡ በካህናት አስጠመቀው ስሙም አብርሃም ተባለ።



ይህንን ኔሮን የተባለውን ንጉሥ ለማስገደል መልእክተኞችን የላከ ንጉሥ ነነዌንም ይገዛ ነበር። በምሥጢር ኔሮንን ለማስገደል ያደረገው ምሥጢር ስለተገለፀበት እጅግ ፈራ። እንዳይበቀለውም አምስት መቶ የወርቅ መክሊትን መቶ ፈረሶችን፣ በሠላሳ በቅሎች የተጫነ ውድ ልብስን ላከለት ኔሮንም ለበቀል መነሳት የክርስቲያኖች ተግባር አለመሆኑን ገልፆ ለበቀል እንደማይነሳሳ ቃል ገባለት ለሰማዕቱና ባባቱ እጅ ለተገደለው የፀራቢ ልጅ ዮሐንስ መታሠቢያ የሚሆን ቤተክርስቲያንን ሠራ።

ዮሐንስ ወልደ ፀራቢ በተቀበረበት አካባቢ አንድ አይሁዳዊ ነጋዴ ከልጁ ጋር በእንግድነት አደረ ሌሊት ከተኙበት ልጁን እባብ ነከሰውና ሞተ። አባትየው ኡኡ አለ ሰዎች አታልቅስ ዮሐንስ ወልደፀራቢ ከተቀበረበት ቦታ ሄደህ ዮሐንስን ከእግዚአብሔር እንዲለምንልህ ለምነው አሉት ወደመቃብሩ ተጠግቶም እጅግ አለቀሰ። የልጁን አስከሬን እንዲያመጣ መልአከእግዚአ.ብሔር በቃል ነገረው መልኩን ግን አላሳየውም ሰውየውም የልጁን አስከሬን አመጣ። ወደእግዚአብሔርም ተማፀነ የእግዚአብሔርም መልአክ የዮሐንስን ወለደፀራቢ ፀሎትን ተቀብሎ እግዚአብሔር ልጅህን አድኖልሃል አለው ልጁም ዳነ።

ሲነጋ የክርስቲያን አምላክ ልጄን አዳነ እያለ አይሁዳዊው ጮኸ አባትና ልጅ በእግዚአብሔር አምነው ተጠመቁ። ይህ አይሁዳዊ ወደትውልድ አገሩ ገባና ሚስቱን ልጆቹንና ዘመዶቹን አምጥቶ እንዲጠመቁ አደረገ።

## ምዕራፍ ፮ የሰማዕት ፊቁጦር ገድልና ታሪክ

ፊቁጦር ሰማዕት በዲዮቅልጢያኖስ ዘመን የነበረ ነው ትውልዱ ከቤተመንግሥት ዘርያ ነው። ብሉያትንና ሐዲስትን



www.ethiopianorthodox.org

አጠናቅቆ ከማወቁም በላይ እግዚአብሔርን የሚፈራ ትዕግሥተኛ ትሕትናን የተላበሰ ዕውቀቱ በመንፈሳዊ ዕውቀትና ጥበብ የታነፀ ነበር። እናቱ ማርታ ትባል ነበር የማርታ አባት ፋሲለደስ የሚባል የምሥራቅ ንጉሥ ልጅ ነበር።

ፋሲለደስ የትውልድ አገሩን ትቶ ወደአንፆኪያ መጥቶ ይኖር ነበር የሞተውም ከዚሁ እንዳለ ነው አባቷ ፋሲለደስ ከሞተ በኋላ አያቷ ንጉሥ ሕርማኖስ ለተባለው መኮንን አጋባት ሕርማኖስ በንጉሡ ግራናቀኝ ከሚቀመጡ ታላላቅ መኳንንት አንዱ ነበር። ሕርማኖስ በተፈጥሮው ጨካኝ ሲሆን ማርታ ደግሞ ርህርህትና እግዚአብሔርን የምትፈራ ነበረች ማርታ ባልዋ ሳያውቅ ምፅዋትን ትሠጥ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ልጅ አልወለደችም ነበር ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል ወደቤተክርስቲያን ሄደችና የእመቤታችንን ተማሕፅኖ እየጠየቀች ጌታችን ኢየሱስክርስቶስ እሱን የሚያገለግል ልጅ እንዲሠጣት ለመነችው እንደአባቱ ጨካኝ የሚሆን ከሆነና እግዚአብሔርንም የማያውቅ ከሆነ ግን እንዳይሠጣት በፀሎቷ እግዚአብሔርን ለመነች።

እግዚአብሔርም ሥእለቷን ሰምቶ አረገዘች የካቲት አሥራ ሦስት ቀንም ወንድ ልጅን ወለደች ስሙንም ፊቂጦር አለችው። ትርጓሜውም ሐዘኔን አስወግድ ማለት ነው። የማርታ መውለድን ባሮቹ ሄደው ለሕርማኖስ ነገሩት ንጉሡ ድግልያኖስ ይባላል። ይህ ንጉሥ ባሮቹ በለሆሣሥ ለሕርማኖስ ሲነግሩት ስማና ሕርማኖስ ሆይ የምትናሩት በለሆሳስ ምንድን ነው አለው እሱም የማርታ ወንድ ልጅ መውለድን እንደነገሩት ገለፀለት በዚህ ጊዜ ንጉሡ ድግልያኖስ የማርታ አያት ስለሆነና አባት ሁኖ ያገባትም ራሱ ስለነበር እጅግ ተደሰተ ብዙ ወርቅ ብርና የክብር ልብስንም



ወስዶ አበረከተላት በየዓመቱም የፊቂጦር የልደት በዓል ንጉሡ ባለበት እንዲሁብታላቅ ደስታ ይከበር ነበር።

የማርታ በዓል ደግሞ ድብቅ ሁኖ ለድሆችና ለምስኪኖች ምፅዋትን ብመስጠት የተመሠረተ ነበር። ሕርማኖስ በበኩሉ ለሀብታሞችና ለመኳንንት ሥጦታን እያበረከት ያከብረው ነበር የእግዚአብሔር መልአክ ግን ለፊቂጦር ከወርቅ የተሠራ ልብስ ከሰማይ አወረደበት ንጉሡ ድግልያኖስ የፊቂጦርን የልደት በዓል የሚያከብረው በቤተመንግሥቱ ከመኳንንቱና ከመሳፍንቱ ጋር በመሆን ነበር ለተወሰኑ ዓመታት አያቱ ንጉሥ ድግልያኖስ ሕፃን ፊቂጦርን ከተለወደ ጀምሮ መልኩ ሳያየው ቆይቶ ነበር። በኋላ ግን አምጣልኝና ሕፃኑን ልየው ብሎ መኮንኑን ሕርማኖስ አዘዘው መኮንን ሕርማኖስም ያመጡት ዘንድ መልእክተኞችን ላከ በዚህ ጊዜ እናቱ ማርታ መልአክ ያለበሰውን የወርቅ ልብስ አልብሳ ላከችው መልእክተኞቹም ሕፃን ከመሆኑ የተነሳ መሄድ ስለማይችል ተሸከመው ወሰዱት የክርስቶስ ፀጋን ተሞልቶ ፊቱ እጅግ የተዋበና ደምግባቱ የሚማርክ ሁኖ ሲያየው እጅግ ተደነቀ እያገለባበጠ ሳመውና ወደንግሥቷ ሚስቱ እንድታየው ላከው።

ንግሥቲቱም ውበቱን እጅግ የተለየ ልብሱን አይታ እጅግ ተደነቀች ንግሥቲቱ እሱን ስታይ ልጅ ስላልወለደች አዘነች ፊቂጦርም ከንግሥቲቷ ጋር ጥቂት ቆይቶ ወደናቱ ማርታ ተወሰደ ንጉሥ ድግልያኖስ ንግሥቲቱን ሕፃኑን ካየሽ ወዲህ ከባድ ሐዘን ደርሶብሽ እመለከትሻለሁ ምክንያቱ ምንድር ነው ብሎ ቢጠይቃት እኔ ንግሥት ተብዬ ስጠራ የሕፃኑን ያህል የወርቅ ልብስ ልታለብሰኝ ባለመቻልህ አሳዝኖኛል አለችው። ንጉሡ ድግልያኖስ ወድያው



www.ethiopianorthodox.org

የፌቄጦር ሕፃን አባት የሆነውን ሕርማኖስ አስጠርቶ ሕፃን ፌቄጦር የለበሰውን የወርቅ ልብስ ከየት አገኘሽው ወይስ ራስህ አሠርተኸው ነው ሲል ጠየቀው ሕርማኖስም እኔ ስለዚህ ልብስ የማውቀው ነገር የለኝም ማርታ ብቻ ናት የምታውቀው አለው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ማርታ ልጅዋ ፌቄጦር እንዲጠመቅና የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅ እንዲሆን ለማድረግ ተዘጋጅታ ነበርና ወደ ባልዋ ሕርማኖስ ልጄ ፌቄጦርን ለማጥመቅ ወደቤተክርስቲያን መሄዴ ነው ስትል ላከችለት ሕርማኖስም ለንጉሡ ይህን ነገረው። ንጉሡ ይህን ሲሰማ ንግሥቲቷሚስቱን ከማርታ ጋር አብረሻት ወደ ቤተክርስቲያን ሂጂ አጃቢ ያስፈልጋታል ክብርም ይሆንለታል አላት። ማርታና ንግሥቲቱ ሕፃኑን ፌቄጦር ይዘው ወደቤተክርስቲያን ሄዱ።

ሕፃኑን ፌቄጦር ለማጥመቅ ቴዎድሮስ ሊቀጳጳሳት ተዘጋጅቶ ቆየ በክብር ተቀብሎም አጠመቀው እጁ በሕፃን ፌቄጦር ላይ በማሳረፍም ልጄ ፌቄጦር ሆይ በሕፃናት ራስ ላይ እጁን ያሳረፈ ኢየሱስ ክርስቶስ የባረካቸውም አንተንም ይባርክህ ሲለው ሕዝቡ አሜን ይሉ ነበር ዳግመኛም እግዚአብሔርም የተባረከህ ዘር ያርግህ አለው ሕዝቡም አሜን አሉ ሦስተኛም እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጆች ይስሐቅንና ያዕቆብን እንደባረካቸው ይባርክህ አለው ሕዝቡም አሜን አሉ።

ንግሥቲቱ በሊቀጳጳሱ ለሕፃኑ የተደረገውን ፀሎተ ቡራኬ ስትሰማ ከባድ ቅንአት አደረባት ንዴትና ብስጭትም ተነሳባት ልጅ የላትምና ማርታ መልአክ ከሰማይ አውርዶ ያለበሰውን ልብሰ ወርቅ ሊቀጳጳሱ እንዲያለብሰው ስትሠጠው ንግሥቲቱ ልብሱን ለመንጠቅ እጅዋን ዘርግታ እየተንደረደረች ቀረበች። በቤተክርስቲያኑ የተሰበሰቡ ምዕመናን ቅሌቷን አይተው ሳቁባት ንዴቷ በዚህም



ተባባሰና ሕፃኑን ፌቄጦር ከሊቀጳጳሱ እጅ ቀምታ ልትገድለው በደረጃው ላይ ወረወረችው። ሕፃኑ ሞተ ብለው ምዕመናኑም ተደናገጡ። ማርታ ከቤተክርስቲያን ወጣችና ከተወረወረበት የቤተክርስቲያኑ ደረጃ አነሳችው ሕፃኑ ፌቄጦር ሕይወቱን ዘንግቶ ነበር ማርታ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ፀሎት እየተማፀነች ጌታዮ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ልጁን ያገኘሁት በፈቃድህ ስለሆነ ከደረሰበት አደጋ ጠብቀህ ሕይወቱን ሥጥልኝ እኔ ያንተ አገልጋይ ሁኖ ልጄን እንዳየው እጓጓለሁ አሁንም ያንተን ልጅነት እንዲያገኝ ነው ወደቤትህ ያመጣሁት እያለች ፀለየች ሕፃኑም ከሞት ተርፎ ወድያው ነፍሱን አወቀና አይኖቹ ተከፈቱ እናቱ ማርታም በጣም ተደሰተች በቤተክርስቲያኑ የነበሩ ምዕመናንም በሕፃን ፌቄጦር ከሞት መትረፍ እጅግ ተደሰቱ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ።

ማርታ ቅዱስ ቁርባንን ከልጅዋ ጋር ተቀብላ ወደቤቷ ሄደች ንጉሥም ወደቤቱ ሲገባ ሐዘኑና ብስጭቱ ብሶባት አያት። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ድግልድያኖስ "ለምንድር ነው ብስጭቱ እየባሰብሽ የሄደው ታመምሽ ወይስ ያጣሽው ነገር አለ" ሲል ጠየቃት። እሷም "ለምን አላዝን ለምንስ አልበሳጭ እኔ ንግሥት ባለቤቴ አንተም ንጉሥ ስትሆን የማርታ ልጅ የለበሰውን ልብስ ያህል እንድለብስ አላስቻልከኝም ስለዚህ ሕፃኑ ከኔ ከንግሥቲቷ የበለጠ ልብስ መልበሱ አሳዝኖኛል አናድዶኛል" አለችው። ባልዋ ንጉሥ ድግልያኖስም በይ የፌቄጦር ሕፃንን ልብስ ከፈለግሺው ሕርማኖስን እነግረውና እንዲያመጣልሽ አደርጋለሁ አላት።

ማርታ የንግሥቲቱንና የንጉሡን አኳኋን ስለተረዳች ከመላእክት ለሕፃን ፌቄጦር የተበረከተውን ልብስ ከሠዋራ ቦታ ደበቀችው



www.ethiopianorthodox.org

ልብሱም በሕፃኑ ፊቂጦር መጠን የተዘጋጀ ነው ነገር ግን ሕፃኑ በዕድሜ ባደገ ቁጥር ልብሱም የሕፃኑን የእድገት ደረጃ ተከትሉ ያድግ ነበር ሕፃኑ ፊቂጦር ለትምህርት ሲደርስ ማርታ እናቱ ት/ቤት አስገባችው ትምህርቱንም ደረጃ በደረጃ ተምሮ የነቢያትን የሐዋርያትን መፃሕፍት ትርጉም ተምሮ አጠናቀቀ ሌሎችንም የቤተክርስቲያን ጥበቦች አጠናቀቆ ተማረ። ያምንና ፀሎትን የሚያዘወትር ለነዳያንና ለምስኪናንም ምፅዋትን የሚያዘወትር ሆነ።

ንጉሡና ንግሥቲቱም እጅግ ወደዱት አባቱ ሕርማኖስ ግን ጋብቻን ባለመውደዱ በጣምያዝን ነበር ከጥቂት ጊዜ በኃላ ግን ዲግልድያኖስ ኢየሱስ ክርስቶስን ካደ። ወደያገሩም አብያተ ክርስቲያንን ዝጉ አብያተጣኦታትን ክፈቱ የሚል የአዋጅ መልእክትና ትእዛዝ በግዛቱ ወዳሉ አገሮች በጽሑፍ አስተላለፈ ሰው ሁሉም ለጣኦታት እንዲሠግድ አልሠግድም ያለ ግን ባለበት እንዲገደል ንብረቱም እንዲወረስ ጥብቅ ትእዛዝ አስተላለፈ። አጵሎን የተባለውን ጣኦት በአንፆኪያ ዙሪያ እንዲያዘሩትና ሕዝቡም እንዲሰግድለት አዘዘ። ፊቂጦር ጠጠር በዕንቅብ ሞልቶወደ ረጅም ግንብ ወጣና በሠረገላ ተጭኖ በሚያልፈው አጵሎን ላይ ደፋው። በዚህ ጊዜ ልጅዋያደረገው ለንጉሡ እንዳይነግሩበት እናቱ ፈራች። ሰዎቹ ግን ማርታ ሆይ አትፍሪ ፊቂጦር ያደረገውን ለንጉሡ አንነግርብሽም አሏት። ማርታም መቶ ሐምሳ ግራም ወርቅ ለጣኦታ ካህናትና ለአጵሎን ተከታዮች ሠጠቻቸው።

ማርታ ወርቁን አጵሎንን ለሚያዞሩና ለጣኦቱ ካህናት የሠጠቻቸው ስለወደዳቻቸው አይደለም ልጄን ያስገድሉብኛል በማለት ፈርታ እንጂ የማርታ ባልና የፊቂጦር አባት ሕርማኖስ እግዚአብሔርን ክዶ ለጣኦት መስገዱን ስለተረዱ እናትና ልጅ /ፊቅጦርና ማርታ/ በጣም አዘኑ ከሕርማኖስ ጋር ማዕድ መካፈላቸውንም አቆሙ። የዲግልያኖስ የልጅ ልጅ መሆኑ ፊቅጦር የታወቀ ሲሆን ንጉሡ ከካደ ጀምሮ ፊቂጦር ወደቤተመንግሥቱ ዞር አላለም። ዲግልያኖስ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን ሁሉ እንዲገደሉና ሬሳቸው በየተገደሉበት እንዲወድቅ እንጂ እንዳይቀበሩ አዘዘ። ፊቂጦር ግን የናቱን ሠራተኞች እያስከተለ በክብር ልብስ እየገነዘ ይቀብራቸው ነበር። የተገደሉትን ሲቀብር የተመለከቱ ሁሉ በመልካም ውበቱና ጠባዩ ስለሚወዱትና የንጉሡ የልጅ ልጅና የታላቅ መኮንን ልጅ በመሆኑ ስለሚፈሩ የተገደሉትን ሰማዕታት በመቅበሩ ለንጉሡ አልነገሩበትም።

ይህ በዚህ እንዳለ ዲዮቅልጥያስ /ዲግልዮስ/ ሕርማኖስ መኮንን ልጅህ ፊቂጦር ለምንድርነው የማላየው ወደቤተመንግሥቴ መምጣቱን አቆመ ይሆን ሲል ጠየቀው እሱም ልኬ እንዲመጣ አደርጋለሁ አለውና ወደማርታ መልእክተኛን ልኮ ልጅዋ ፊቂጦርን እንድትልከው ነገራት ማርታም ፊቂጦር ታሞ ተኝቷል ስለዚህ ለመምጣት አይችልም የሚል መልስ ሠጥታ እንዲመለሱ አደረገች ሊጠሩት መምጣታቸውን ግን ለፊቂጦር አልነገረችውም። ፊቂጦር በንጉሡ መጠራቱ ቢያውቅ ኑሮ ግን በክርቶስ ስም ሰማዕትነትን ለመቀበል ፈጥኖ በሄደ ነበር። ከጥቂት ቀናት በኃላ ፊቂጦር ወደ ቤተመንግሥት እንዲመጣ ድጋሜ መልእክተኞች ወደ ማርታ መጡ በዚህ ጊዜም ፊቂጦር ከናቱ ጋር አልነበረም ስለዚህ ማርታ ለመልእክተኞቹ አምስት ግራም ወርቅ ሠጥታ ታሞ እንዳገኙትና ወደንጉሡ መሄድ እንደማይችል ለንጉሡ እንዲነግሩት ለመነቻቸው እነሱም ይህንን ለንጉሡ ተናገሩ ይህ ሁሉ ሲሆን ፊቂጦር የሰማው አልነበረውም በመጨረሻ ግን ዲዮቅልጥያኖስ ሕርማኖስን ልጅህን ፊቂጦር ናፈቅኩት ላየው ስለምፈልግ አምጣልኝ ስላለው ሕርማኖስ ራሱ ሄዶ ፊቂጦርን አመጣው።


www.ethiopianorthodox.org

ንጉሡ "ዲዮቅልጥያኖስ ልጄ ፊቂጦር ሆይ ምን ሁነህ ነው ከኔ ዘንድ ሳትመጣ የሰነበትከው ብዙ ጊዜ ሳላይህ በመቆየቴ ቅር ተሰኝቼ አለሁ" በማለት ጠየቀው ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን ከወደድከው እኔ አንተን እወድሃለሁ ካንተም አልርቅም፣ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን ከጠላኸው ግን እኔም እጠላሃለሁ ካንተም እርቃለሁ ሲል ፊቂጦር መለሰለት በዚህ ጊዜ ሕርማኖስ የፊቂጦር አባት እጅግ ተቆጣ ዲያቅልጥያኖስ ግን ተወው ልብ ያለገዛ ገና ሕፃን ስለሆነ ነው ይህን የተናገረው በማለት ሕርማኖስን አፅናናው።

ማርታ ግን ስለልጅዋ ሕይወት ትፈራ ነበርና በሱ ላይ የሚፈፀመውን ሁሉ እንዲነግሩዋት በጎን መልእክተኞችን ትልክ ነበር በሕይወት እንዳለ ስለነገሩዋትም ልቡናዋ ተረጋጋ ሕርማኖስ ወደቤቱ መጣና ፊቂጦር ልጅሽ አሁን ሕፃን አይደለም አሥራ አምስት ዓመት ሞልቶታል ስለዚህ የክርስቶስን ስም በአፉ እንዳይጠራ እንዳያነሳውም ምከሪው ብሏት ወደ ዲዮቅልጢያኖስ ተመለሰ። ዲያቅልጢኖስ ግን ሕርማኖስን ወደ ቤትህ ሄደህ ፊቂጦርን አምጣውና አንተ ለአጵሎን እንደሠገድህ እሱም መስገድ አለበት ከዚያ በኃላ የሚበቃውን ገንዘብ አሸክመዋለሁ አለው ሕርማኖስም በታዘዘው መሠረት ወደቤቱ ሄዶ ልጁ ፊቂጦርን አመጣውና ወደ ቤተመንግሥት አስገባው። ፊቂጦር ግን አያቱን ዲዮቅልጢያስ እንዴት አደርክ አላለውም ሰላምታም ነሳው ዲዮቅልጢያኖስ ግን በግድ ስቦ ራሱን ሳመውና ንግሥቲቱና እህቷ አግባብተው ለጣኦት እንዲሰግድ እንዲያደርጉት ወደነሱ ላከው።

ንግሥቲቷም "ፊቂጦር ሆይ ክርስቶስን መውደድህ በሆድህ ደብቀው ውስጣዊ አስተሳሰብህ ማንም ሊያውቅብህ አይችልም ነገር ግን ንጉሥ እንዲወድህና ደስ ብሎትም ከፍተኛ ሹመት እንዲሠጥህ ለማስመሰል ስትል ለጣኦት ሥግድለት፣ ከዚያ በኃላ ከማንም በበለጠ ከፍ ያደርገሃል" አለችው። ፊቂጦር ግን አንቺን ጨምሮ ሁላችሁ ለጣኦታት የምትሠግዱ ወዮላችሁ በዚህ ዓለም የምትኖሩት ላጭር ጊዜ መሆኑን እያወቃችሁ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ከሚሠጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ወጥታችሁ ገሐነመ እሳትን መርጣቹኋል ስለዚህ ወዮላችሁ" በማለት መልስ ሠጣት።

ዲዮቅልጥያኖስ ንጉሥ ድጋሚ አሥጠርቶ ወሰደውና በአርባ በቅሎች ጭነት ወርቅን የከበሩ ልብሶችን ሸልሜ የእስክንድርያ ንጉሥ አድርጌ እሾምሃለሁ ስለዚህ ከኛ ጋር ለጣኦት ሥግድ አለው ፊቂጦር ደግሞ "ወርቅህን፣ ሹመትህንና ብርህን አልፈልግም ለጣኦትህም አልሠግድም የምሠግደው ለኢየሱስክርስቶስ ብቻ ነው የማመልከውም እሱን ነው" አለው አባቱ ሕርማኖስ መኮንን "ልጄ ፊቂጦር ሆይ የሁሉ የበላይ የሆነው ንጉሥ ስለወደደህ አይደለም በግድ አቅርቦራስህ የሳመህ ስለወደደህ አይደለም ንግሥቲቱና እህቷ እንዲያግባቡህ የላከህ ስለወደደህ አይደለም ወርቅን ብርንና የከበረ ልብስን ሠጥቶ ከፍ እንዲያደርግህ የፈለገው" አለው። "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ያዋርዳቸዋል የተዋረዱትን ደግሞ ከፍ ያደርጋቸዋል ከዚህ ከሐዲ ንጉሥ ክብርም ልዕልናም አልፈልግም ራሴን በሳመኝ ጊዜ እባብ እንደነካኝ ቆጠርኩት ወደንግሥቲቷ በላከኝ ጊዜ ከአራዊት ጋር እንደቆየሁ ቆጠርኩት" በማለት ፊቂጦር መለሰለት በዚህ ጊዜ ሕርማኖስ በራሱ ጠጉር ጎትቶ ወደቤተመንግሥቱ ደረጃ ቁልቁል ወረወረው ራሱ ተገመሰ ደሙም በደረጃው ላይ ፈሰሰ። ሕርማኖስ ከዚህ አያይዞ ይህ ርጉም ልጅ ልጄ አይደለም እንደፈለግህ አድርገው አለው /ለንጉሡ/።

ንጉሡ ግን አንተ የፈፀምከበት ቅጣት ይበቃዋል ካለው በኋላ ለባሮቹ የፊቂጦር ደም የፈሰሰበትን ድንጋይ ነቅላችሁ ጣሉት



www.ethiopianorthodox.org

በምትኩ ሌላ ድንጋይ ተኩበት አላቸው ፊቂጦር እነዚህ የተነቀሉ ድንጋዮች በከሐዲዎች ከመረገጥ ወጥተው የቤተእግዚአብሔር መዓዝኖች ይሆናሉ በማለትትንቢት ተናገረ። ሕርማኖስ በፊቂጦር ፅናት እጅግ ተናደደና በልጓም አፉን ለጎመው ለንጉሡም ንጉሥ ሆይ ሄርሜኔዎስ ወደተባለው የእስክንድርያ መኮንን ላከውና እሺ ብሎ ለአማልክት ከሰገደ ከፍ ያድርገው እምቢ ካለ ግን በፈለገው መንገድ አሠቃይቶ ይግደለው አለው።

ዲዮቅልጢያኖስ ንጉሥም "እሺ ብሎ ከሠገደ ከፍተኛ ሥልጣንና ማዕረግ ሥጠው እኔም እንድደሰት ውጤቱን ላክልኝ እምቢ ካለ ግን የቻልከውን ሁሉ ሥቃይ ፈፅመህ ባሰቃቂ አሟሟት ግደለው የሚል ደብዳቤ አሥይዞ በወታደሮች ላከው ወታደሮቹ በመርከብ እሱን ይዘው ለመጓዝ ሲዘጋጁ እናቱ ማርታ "...ልጄ ፊቂጦር የበደለው በደል የለውም አባቱ ሕርማኖስ ስለተጣላው ብቻ ነው ለመከራ የተዳረገው አንተ ከንጉሡ ምንም ዝምድና ሳይኖርህ ለከፍተኛ ሹመት በቅተሃል ልጄ ፊቂጦር ደግሞ ከንጉሣውያን ቤተሰብ መሆኑን አትዘንጋ አንተን የሚረዳበት ጊዜ ሊኖር ይችላል ገና ለገና ንጉሡን አስደስታለሁ ብለህ በልጄ ላይ ግፍ አትፈፅምበት..." የሚል ደብዳቤ በጎን ላከችበት፤ ይህንን ወደ እስክንድርያ ከማርታ የፊቂጦር እናት የተላከው ደብዳቤ ይዞ የተጓዘው ከፊቂጦር ባሮች አንዱ ሆርዮን ይባላል።

ሆርዮን ፊቂጦርን ይዘው ወደ እስክንድርያ ከሚጓዙ ወታደሮች ጋር ተቀላቀለ የፊቂጦር ባርያም ስለሆነ ከወታደሮቹ ጋር ተመሳስሎ በሰላም ወደእስክንድርያ ጉዞ ቀጠለ። ነገር ግን መርከቧ ካለችበት በእግዚአብሔር ሐይል ፀጥ አለች እንዳትንቀሳቀስም ሆነች ፊቂጦር ግን አዘነእኔ የክብር አክሊል እንድቀዳጅ ፈቃድህ ይሁንልኝ በስምህ እየመሠከርኩ የቅዱሳን ሰማዕታትን ማሕበርተኝነት

ተካፋይ መሆንን እናፍቃለሁ በጉጉትም እጠብቀዋለሁ እያለ ፀለየ። ያ የሱ ባርያ ሁኖ ከናቱ ማርታ ወደእስክንድርያው ገዥ ሄርሜኔዎስ መኮንን የተላከውን ደብዳቤ የያዘው ሆርዮን ስለተሠጠው ደብዳቤ በምሥጢር ነገረው በዚህ አዝኖ ይዘውት እንዲጓዙ የተመደቡትን አራት ወታደሮች ከናቱ ማርታ ጋር እንዲያገናኙት ለመናቸው እነሱም ወደናቱ ማርታ ወሰዱት። ነገር ግን ከመርከብ ሲያወርዱት ንጉሡን ሰድቦ ችግር እንዳያመጣባቸው አፉን ለጎሙት ወደናቱ ቤት እስኪደርስ ድረስም አፉ እንደተለጎመ ነበር።

ከናቱ ማርታ ቤት ሲደርስ ልጓሙን ላንድ አፍታ ፍቱልኝና ከናቴ ጋር ልናገር ልሰነባበታትም አላቸው ማርታ እናቱም በልጓም አፉ ተዘግቶ ስታይ ልጄ ፈረስ መሆኑ ነው በልጓም የተለጎመው እያለች አለቀሰች ወታደሮቹም ላንድ አፍታ ልጓሙን አወለቁለት። የፃፈችውም ደብዳቤ አነበበላትና እናቴ ሆይ ለምን የክብርን አክሊል እንዳልቀዳጅ ዕንቅፋት ትፈጥሪብኝአለሽ የጌታን መቃብር ሲጠብቁ እንዳደሩ ወታደሮች ለምን ትሆኛለሽ እነሱስ ብዙ ገንዘብ ተቀብለው ነው በእንቅልፍ ላይ እያለን ተማሪዎቹ የጌታን አስከሬን ሠረቁት ያሉ እናቴ ሆይ አሁን እኮ እነሱን መስለሻል የመንግሥተ ሰማያትን አክሊል መቀዳጀት እንዳልችል አታድርግቢኝ እናቴ ሆይ እንግድነቴን ተቀብይ በሰላምም ተሰናበችኝ አላት ይህን ተናግሮ እንደጨረሰ ከቤት ወጣ ወድያውም ለጎሙት እናቱ እንደገና መለጎሙን ስታይ አለቀሰች ከሐዘን ብዛትም አንጀቷ ተቃጠለ።

በመርከብ ሲሳፈሩ መርከቧ የተለመደውን ጉዞዋ ቀጠለች እስክንድርያም ደረሰች ሄርሜኔዎስ ካለበት ቦታ ሲደርሱ ከንጉሡ የተላከበትን ደብዳቤ ሠጡት ሄርሜኔዎስ ፊቂጦርን እንዲህ አለው" ...ፊቂጦር አንተ ትልቅ ሰው ነህ የንጉሥ ቃልም ትልቅ ነው" ይዘውት የመጡትን ወታደሮች ደግሞ "አባቱ ሕርማኖስ ከንጉሥ


www.ethiopianorthodox.org

ጋር የለም እንዴ? አባቱ በሕይወት እያለ ፊቂጦርን ወደኔ መላክ ለምን አስፈለገ ሲል ጠየቃቸው እነሱም አባቱ ፈቅዶ ነው ወዳንተ እንዲላክ ያደረገ አሉትና አስረከበውት ተመለሱ።

ሄርሜኔዎስ ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ እንደገና ለፊቂጦር አነበበለት የክርስቶስ ፍቅርህን በልብህ ይዘህ ለማስመሰል ስትል ለአማልክት ስገድ ሕዝብም ንጉሥም በዚህ ጊዜ እጅግ ደስ ብሎአቸው ከፍ ሊያደርጉህ ይችላሉ አለው ፊቂጦር በሠጠው መልስ እንዲህ አለው "ጌታዩና መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ፊት የካደኝን እኔም ከአባቴ ፊት በመንግሥተሰማያት እክደዋለሁ ብሏል"

ሄርሜኔዎስ እንደገላውዴዎስ ሰማዕት ራስህን ከፍ ከፍ አታድርግ አለው ገላውዴዎስ የእግዚአብሔርን መንገድ በተከተለ ጊዜ ለምን አታከብረውም ነበር ሲል ፊቂጦር መለሰለት ሄርሜኔዎስ ለምን ለብቻዩ አትነግረኝም ነበር በሕዝብ ፊት ለምን ታዋርደኛለህ አለው በመናደድም ወስዳችሁ ለአማልክት አሠግዱት ሲል ወታደሮቹን አዘዘ አልሠግድም ካለ ግን እንዲቀጠቅጡት መመርያ ሠጣቸው የእስክንድርያ ያገር ሽማግሌዎች ግን እኛ የንጉሥ የልጅ ልጅ ባገራችን እንድትገድልብን ቅንጣት ያህል መብት አንሠጥህም ፊቂጦር ባገራችን ከተገደለ ንጉሡ እኛን ሊያጠፋን ይችላል አገራችንም ምድረበዳ ያደርጉታል ሲሉ ተቃወሙት።

የሕዝቡ ተቃውሞ ሲፀናበት ሄርሜንዮስ ፊቂጦርን ወደአንደኛው መኮንን አርያኖስ አሰቃይቶ እንዲገድለው ላከው ፊቂጦር ወደአንደኛው ንጉሥ ሲደርስ ያገሩ ሰዎች የንጉሥ የልጅ ልጅ በመሆኑ ብርቅ ሆኖባቸው ሊያዩት ተሰበሰቡ ገና ከመርከብ ሳይወርድም እጅግ የበዛ ሕዝብ እሱን ለማየት ከወደቡ ተከማቸ እሱን አጅበው ከሚጓዙት ወታደሮች መካከል ፒፋምን የሚባለው ሰው የክርስቶስ ፍቅር እንዳለው መንፈቅ ቅዱስ ለፊቂጦር ገለፀለት ፊቂጦርም ፒፋምንን ጠርቶወደኔ ቅረብ አለው እሱም ወደሱ ቀረበና አንገት ለአንገት ተያይዘው ተሳሳሙ።

ፊቂጦር ለፒፋምን "አሁን አንተ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ሰማእት እንድትሆን ፀንተህ ተጋደል የሥጋንም መከራ አትፍራ ሐላፊ ነውና በመከራህና በሥቃይህ ደግሞ መንግሥተሰማያትን ትወርሳለህ አለው። ፒፋምን የፊቂጦርን ምክር እንደሰማ ፈረሱን ተወ የታጠቀውን ሠይፍና ጉራዴንም አውልቆ ጣለው ከዛሬ ጀምሮ የምድራዊ ንጉሥ ወታደር አይደለሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ነፍስዩንም ስለክርስቶስ እሠጣለሁ አለ። ወታደሮቹ ፒፋምንን ከፊቂጦር ጋር ይዘው ወሰዷቸው ከአርያኖስ መኮንን ዘንድም አደረሱዋቸው።

አርያኖስ ፊቂጦርን ተመለከተው ከመኮንነ እስክንድሪያ ሄርሜኔዎስ የተላከለትንም ደብዳቤ አነበበና ፊቂጦርን ናና ለአማልክት እንስገድ አለው ፊቂጦርም ለርኩሳን ጣኦታት አልሠግድም ለመድሐኔዓለም ክርስቶስ ነው የምሠግደው አለው። ብዙ ሥቃይና መከራ ተቀብለህ ተዋርደህ በመጨረሻ በመጥፎ አሟሟት ከምትገደል ለአማልክት ብትሠግድ ይሻለሃል አለው። ፊቂጦር ጌታዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሩዋቸው ነፍስን የሚገድሉና ሥጋን የሚያጠፉትን ፍሩዋቸው ብሏል ሲል መለሰለት።

አርያኖስ ባሮቹን በጅራፍ ይገርፉት ዘንድ አዘዛቸው እነሱም ተረባርበው ገረፉት በዚህ ጊዜ አካላቱ እየተሰነጠቀ ደሙ እንደውሃ ፈሰሰ። የፊቂጦርን መገረፍ ሲሰሙ ያገሩ ሽማግሌዎች ተጠራርተው ተሰበሰቡና ልጆቻችንን ሚስቶቻችንና አገራችንን እኛንም ጨምሮ



www.ethiopianorthodox.org

ንጉሡ እንዲያጠፋንነው ፌቂጦርን ወዳገራችን አምጥተህ ለማስገደል የገረፍከው አሁንም አንዳች ነገር እንዲደርሰበት አንፈልግም እስካሁን በማስገረፍህ ለፈሰሰው ደሙ ተጠያቂም አንተ ብቻ ትሆናለህ አሉት።

አርያኖስ ከሕዝቡ ተቃውሞ ብዛት ደንግጦ ክስትሮን ወደ ተባለችው ቦታ ላከው በዚሁ በረጅም ግንብ የተከበበ እሥር ቤት ነበር። ፌቂጦር ወደ ክስትሮን ሲወሰድ በመንገድ አንድ እግሩ የተሠበረ ሽማግሌ አየው። ይህ ሽማግሌ ፌቂጦርን ይዘው የሚጓዙትን ወታደሮች ይህ ማን ነው ሲል ጠየቃቸው እነሱም የሕርማኖስ ልጅ ፌቂጦር ነው ሲሉ መለሱለት ይህ ሽማግሌ ወደ ፌቂጦር ቀርቦ ከሚፈሰው ደሙ በእጁ ነካና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምናለሁ ብሎ የተሠበረውን እግሩ ቀባው። ደገመና ፌቂጦር ሰማዕትነትን የተቀበለልህ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ባንተ አምናለሁ አለ ወድያውም የተሠበረው እግሩ ዳነ።

ከሮም ወደ እስክንድርያ ፌቂጦርን ያመጡ፣ ከእስክንድርያ ወደአንደኛው መኮንን ፌቂጦርን ያመጡ፣ የሄርሜንዮስ ወታደሮች ከአንደኛው መኮንን ወደ ክስትሮን ፌቂጦርን ለማድረስ የተላኩ ወታደሮች በሙሉ ይህን ተአምር አይተው በቅዱስ ፌቂጦር አምላክ እናምናለን ዲዮቅልጢያኖስ ንጉሥ ሄርሜንዮስ የእስክንድርያ መኮንንና የአንደኛው መኮንን አርያኖስ ከአማልክቶቻቸው ጋር የረከሱ ናቸው አሉ። ፌቂጦርን ደግሞ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ስለሐጢአታችንና ባንተ ላይ ስለፈፀምነው ግፍ በእግዚአብሔር ይቅርታ እንድታሠጠን እንለምንሃለን አንተን ገርፈናል አስገርፈናል አሉት ከዛን ጊዜ ጀምሮም ወደፈለገው ይሄድ ዘንድ አሰናበቱት።



ያን በፌቂጦር ደም ከእግሩ ስብራት የተፈወሰው አረጋዊን ፌቂጦር መጥረቢያ ምሣርና መሮ /መንደል/ እንዲሠጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመነው አረጋዊው ሰውም የተጠየቀውን መሣርያ ሠጠው። ፌቂጦር እነዚህን የእጅ ሥራ መሣሪያዎች ይዞ ወደክስትሮን ሄደ ከዚያም ተቀምጦ እንጨት እየቆረጠና የቤት ቁሳቁስ እየሠራ የዕለት ጉርሱን ያገኝ ጀመር። ግማሹ ደግሞ ለነዳያን ይጠጥ ነበር። በዚህ ተግባር ጥቂት እንደሰነበተ "አስቲፓኑ" በመባል የምትታወቅ ሴት ማንነቱን ተረዳች፣ ይህቺ ሴት ማንነቷን ደብቃ የምትኖር ክርስቲያናዊት ነበረች። ይህቺ ሴት ፌቅጦር ወደ ቤቷ እንዲገባ ለመነችው እሱም ገባ በቁስሉ ላይም ዘይት ቀባችው የሚበላውንም አቀረበችለት። የእግዚአብሔር ሰው መሆንዋንም ተረዳ እሷም በክርስቶስ ስም እማፀናሃለሁ ወደ ቤቴ እየገባህ ምግብ እንድትመገብ ስትልም ተማፀነችው በማያያዝም የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት ፌቂጦር ሆይ እኔ ሐጢአተኛ ነኝ ያንተን የሰማዕቱን በረከት ከተካፈልኩ እግዚአብሔር ይቅርይለኛል ባክህ አትራቀኝ በማለትም ማንነቷዋን ገለፀችለት ቅዱስ ፌቂጦርም የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን በማለት አጠቃላይ መልስ ሠጣት።

ፌቂጦር ከእንጨት እየቀረፀ ማንኪያ ይሠራና መስቀል ይቀርፅበት ነበር ማደሪያውም ካንድ ተራራ ላይ እየወጣ ብቻውን ያድር ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ተራራ ላይ አድሮ ሲወርድ ሠይጣን ከአንፆኪያ ሰዎች አንዳንዱ በመምሰል በመንገድ ተገናኘውና ፌቂጦር ማለት አንተነህን ብሎ ጠየቀው እሱም አዎን እኔ ነኝ አለ ፌቂጦር በበኩሉ መልሶ አንተ የየት አገር ሰው ነህ የትስ ታውቀኛለህ ሲል ጠየቀው እኔ በአንፆኪያ አውቃሃለሁ አባትህ ሕርማኖስና እናትህ ማርታም አውቃቸዋለሁ እናትህ ማርታ አንተ በዚህ ጎስቋላና ወረዳ ኑሮ በመኖርህ አዝናለች አሁንም ቢሆን



www.ethiopianorthodox.org

ወደሷ ልመልስህና ተሹመህ ከብረህ ሚስት አግብተህ በሹመትና በሽልማት ለመኖር ትችላለህ አለው።

ፊቂጦር መለሰና "እኔ አሁንም ከናቴና አባቴ ጋር ነው ያለሁት አባቴ ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እናቴም ቤተ ክርስቲያን ናት እኔ እግዚአብሔርን አገለግላለሁ እሱም በእጅ ሥራዬ እንድመገብ ፈቅዶልኛል" አለው። ሠይጣኑም የእጅ ሥራዬ ይምትለው ምንድን ነው አለው ፊቂጦርም ትዕምርተመስቀል የቀረፀበትን ማንኪያ አሳየው ሠይጣኑም ትእምርተ መስቀሉን ተመልክቶ እንደጢስ ተነነ እንደጉምም በንኖ ጠፋ ፊቂጦር በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነ እግዚአብሔር መጠጊያዩና ጉልበቴ ነው የሚለውንም መዝሙረዳዊት እየጠቀሰ ፀለየ ፀሎቱ ጨርሶም ቀን ቀን ወደሚውልበት ቦታ ሄደ። ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንግዳ መስሉ ወደሱ መጣ ከመፃሕፍተነቢያትና ሐዋርያት ስለክርስቶስ ስላላቸውም ትርጓሜ እያነሳ ከሱ ጋር ተነጋገረ።

ከኢየሱስ ክርስቶስ የመፃሕፍትን ቃል በመስማቱ ፊቂጦር እጅግ ተደሰተ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ግን አላወቀም ለፊቂጦር ከወርቅ የተሠራች ቀለበት ነበረችውና ኢየሱስ ክርስቶስ የታጠቅሃት ቀበቶ ወርቅ እንዳለባት አያለሁ ወርቅ ትወዳለህ እንዴ አለው ፊቂጦር እኔ ከቤቴይዤት የወጣሁት እሷ ብቻ ናት በቀበቶዋ ላይ ያለውን ወርቅ እንግዳ ሲመጣብኝ ምግብ እገዛበታለሁ አለውና ከወርቁ ቀርፎ ወስዶ ምግብ ገዝቶ ሲመለስ የተሠራ ማዕድ ቆጭ ብሎ ጠበቀው እንዲመገብም አዘዘው በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ተረድቶ ሠገደ አምላኬ ሆይ ባደረግሁት ድፍረት ይቅር በለኝ ብሎ ሠገደ ኢየሱስ ክርስቶስም ፊቂጦር ሆይ በዚህ ዓለም ያለውን ክብር፣ አባትህንና እናትህን ትተህ እኔን አባት ቤተ ክርስቲያንን እናት በማድረግህ ፍፁም ነህ ወጣት እያለህ ንፅሐ ድንግልናን መረጥክ ባለፀጋ እያለህ ድህነትን ስለኔ መረጥህ እኔም ካንተ አልለይም ብሎት ተለየው ፊቂጦርም እጅግ ተደሰተ።

ሠይጣን አንድ ያገር ሽማግሌ መስሉ ወደ ዲዮቅልጥያኖስ ዘንድ ቀረበና እኔ ከግብፅ የመጣሁ ሰው ነኝ አመጣጤም ለአማልክቶችህ ለመስገድ ነው አለው የግብፅ ሕዝብ ሁኔታስ እንዴት ነው ብሎ ሲጠይቀው ሕዝቡ አንተን ያከብራል ለአማልክቶችህም ይሠግዳል ለአማልክት አልሠግድም ብሉ አንተን እየሰደበና አማልክቶችህን እያንቋሸሸ የሚገኘው የሕርማኖስ ልጅ ፊቂጦር ብቻ ነው አለው።

ዲዮቅልጥያኖስ ወደ እስክንድርያው መኮንን ሄርሜኔዎስ "ፊቂጦር አማልክትን ካከበራቸውና ከሰገደላቸው ወደኛ አምጣውና ትልቅ ደስታ ላድርግለት ካላከበራቸውና ካልሠገደላቸው ግን ባሰቃቂ አገዳደል ግደለው በሱ ተመርተው በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትንም ሁሉ ፍጻቸው ገድለህ ጨርሳቸው ከመካከላቸው አንድም አታሥቀር" የሚል የትእዛዝ ደብዳቤ አስይዞ አራት ወታደሮቹን ላከ። ወታደሮቹም እስክንድርያ ደርሰው ለሄርሜኔዎስ ሠጡት። ሄርሜኔዎስ ደግሞ ደብዳቤውን አንብቦ ደብዳቤውን ይዘው የመጡት ወታደሮች ባሉበት ወስደው ለአርያኖስ የአንጺናው መኮንን እንዲሠጡት ላካቸው። አርያኖስ ደግሞ ደብዳቤውን ከዲዮቅልጥያኖስ የተላኩትን አራት ወታደሮች ጨምሮ ብዙ የራሱን ወታደሮች አስከትሉ ሄደና ፊቂጦር ወዳለበት ቅስጥሮን ሄደ። ራሱ አርያኖስ ፊቂጦር ካለበት ገባና ደስ ይበልህ ሰላም ላንተ ይሁን አለው ፊቂጦርም አመጣጡን ስለተረዳ ሰላምና ደስታ የሌለህ አንተነህ እኔስ ከክርስቶሳውያን ወገኖቼና ወንድሞቼ ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ሰላምና ፀጋ የተሞላን ነን ክርስቶስን የካደው ያንተ ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስም ሰላም የለውም አለው አርያኖስ እኔ የሰላምታ ቃልን በትህትና አነጋገርኩህ፣


www.ethiopianorthodox.org

አንተ ግን ዘለፋና ስድብ ይህን ያህል አወረድክብኝ እኔ ዛሬ ወዳንተ የመጣሁት በራሴ ፈቃድ አይደለም ንጉሡ ስላንተ በላከው ደብዳቤ ምክንያት ታዝዤና ተገድጄ ነው ልመጣ የቻልኩት ካለ በኃላ ከዲዮቅልጥያኖስ የተላከውን ደብዳቤ አነበበለት።

ፊቂጦርም የደብዳቤውን ፍሬ ነገር ሰምቶ ለኔ ይህ አባባል አዲስ አይደለም ከንጉሡ ከሄርሜኔዎስና ካንተ ጋር የተጣለሁት ለርኩሳን የሰው እጅ ሥራዎች አማልክት አልሠግድም ለመድሐኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እሰግዳለሁ እሱንም ብቻ አመልካለሁ ስላልኩ አይደለም ወይ አለ። ከዲዮቅልጢያኖስ ከተላኩት አራቱ ወታደሮች አንዱ ሠይፉን መዘዘና በሰይፉ መያዣ መታው። አከታትለውም ይህ ነገር አይጠቅምህም ከአማልክት በቀር ሌላ አምላክ የለም በልና አንገደልህ እንተውህ ካልሆነ ግን እንደክብት እናርድሃለን አሉት። ፊቂጦር መለሰና ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እሰግዳለሁ አለ።

በዚህ ጊዜ ወርውረው ወደ ምድር ጣሉትና እንደበሬ አረዱት ሰማዕትነቱን ቅዱስ ፊቅጦር ፈፀመ እሱ ሰማዕትነትን በተቀበለበትና ደሙ በፈሰሰበት ቦታ እናቱ ማርታ ቤተክርስቲያንን ሠራች ማርታ ሰማዕትነትን በመቀበሉ ደስ አላት።

## ምዕራፍ 7 የቅዱስ ዮሐንስ ዘሥንሑት ታሪክና ሰማዕትነቱ

ዲዮቅልጥያኖስ ሿ፳ በወንድ ስም የሚጠሩ ሿ፳ በሴቶች ስም የሚጠሩ ጣኦታትን ከሁለቱ እያቀናጀ ወደ ሠላሳ አምስት አገሮች ላከ በዚሁ መሠረት ወደግብፅ ሁለቱ በወንድና ሴት የተሰየሙ ጣኦታት ተላኩ። ጣኦታቱ እንዲመለኩም ያገር መሪዎቹ ትእዛዝ አስተላለፉ ከዚያውም ላይ ከነሱ ውጭ ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰግድና የሱንም ስም የሚጠራ ቢገኝ ባለበት እንዲገደል ታወጀ።



የአሥራ ስምንት ዓመት ወጣት ዮሐንስ ዘሰንሑት ይህን አዋጅ ሰምቶ አለቀሰ ባልተወለድኩ በተሻለኝ ነበር እያለም አምርሮ አለቀሰ ዮሐንስ ርሕራሄ በተሞላበት ፍቅር ከሕዝብ ዘንድ እጅግ የተወደደ ወጣት ነበር። ከህፃንነቱም ጀምሮ ተወከፎ ተነገድን ያዘወትር ነበር ሌት ተቀን ከፀሎት አይለይም ነበር ይህም ሁኖ ሥራው በጎችን መጠበቅ ነበር በሱ ጠባቂነት በጎቹ እጅግ በዙ። የሱን ማንነት ያወቀ ማንም አልነበረም እሱ ግን ዕድሉ ከሰማዕታት ዕጣ ፋንታ እንዲያደርግለት እግዚአብሔርን ይለምን ነበር። እግዚአብሔር ፀሎቱን ሰምቶ መልአኩን ላከለት መልአኩም "ዮሐንስ" ብሎ ከጠራው በኃላ እግዚአብሔር ፀሎትህን ሰምቶ እኔን ወዳንተ ላከኝ ስምህ በመንግሥተሰማያት ስለተፃፈ ደስ ይበልህ። አትፍራ በመከራህ ሁሉ እንዳልለይህ እግዚአብሔር ወዳንተ ልኮኛል አለው ዮሐንስ ወደምድር ወድቆ ለመልአኩ ሠገደ መልአኩም አስነሳው መንፈስቅዱስ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከዮሐንስ ፍርሐትን አሰወገደ።

ዮሐንስ ወደአባት እናቱ ገባና ወላጆቼ ሆይ ከናንተ የኔ ድርሻ የሆነውን ሁሉ ለናንተ በአደራነት ሠጥቻለሁ ያረባኋቸውንም በጎች በአደራነት ተቀበሉኝ ከዛሬ ጀምሮ የእግዚአብሔር ባርያ ነኝ በማለት ተሰናበታቸውና ጉዞውን ለመቀጠል ተዘጋጀ ቤቱንም ተወ። ጌታዮና አምላኬ ሆይ ቤቴን እንደተከፈተ ትቼዋለሁ አልዘጋሁትም ስላንተ ስምም የሚፈፀምብኝን መከራ ሁሉ ለመቀበል ተዘጋጅቼ አለሁ መንግሥተሰማይ እንዳይዘጋብኝ እለምነሃለሁ በምቀበለው መከራ ሁሉአንተ አትለየኝ እያለ ፀለየ።

አባት እናቱ ከነሱ በመለየቱ እጅግ አለቀሱ ልጃችን ዮሐንስ ሆይ ሰው እየሰማህ የእግዚአብሔርን ስም አታንሳ አለዝያ ብዙ መከራና ሥቃይ ይደርስብሃል ወዮልን በዚያ በሚደርስብህ



www.ethiopianorthodox.org

መከራ እኛ ወላጆችህ ቤዛ በሆንህ ምንኛ መልካም ነበር በማለትም ሐዘናቸውን ገለፁለት ዮሐንስ ለወላጆቹ ወላጆቼ ሆይ በገሐነመ እሳት ውስጥ ሁኜ ብታዩኝ እጅግ ታዝናላችሁ በሰው ፊት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምን እክዳለሁ እሱም ባባቱ ፊት ክብር ይሠጠኛል። ይህን እንደሚያደርግ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯልና አላቸው። እንደገናም ስለኔ አባቱን እናቱንና ወንድሞቹን ትቶ የሞትን መስቀል ያልተሸከመና ያልተከተለኝ የኔ አይደለም ብሏል። በዚህ ዓለም ስለስመእግዚአብሔር መሞት ሞት አይደለም ሕይወት እንጂ የመንግሥተሰማያትንም ርስት ያሠጣል አላቸው።

ከዚያ አባትና እናቱ በየተራ አንገቱን እያቀፉ ሳሙትና እያለቀሱ ተለዩት እሱ ግን ጉዞውን ቀጥሎ ጌታዬ መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ መንገዴን አቃናልኝ አባቴንና እናቴንተውኩ አባቴና እናቴ አንተነህ ተቀበለኝ ርዳኝም ይል ነበር ብዙ መንገድ በመጓዝም አትሪብ ወደምትባል አውራጃ ደረሰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድሐ ሰው መስሎ ታየውና ወንድሜ ሆይ እኔ ተራቁቼ አለሁ አለው ዮሐንስም ከለበሰው ልብስ አንስቶ ሊሠጠው ጀመረ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የዋህነቱን ተመልክቶ ብርሃነ ፀጋን አለበሰው ፈገግ ብሎም ተመለከተው እኔ ማንነኝ ታውቀኛለህን ሲል ጠየቀው ወድያውም ያንተ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ ስለዚህ ዮሐንስ ሆይ አትፍራ ፈተና ይጠብቀሃል። ግን በፅናት ትወጣዋለህ እኔ ካንተ አልለይምና የእናቴ ቅድስት ድንግል ማርያም በረከትም አሳድርብሃለሁ አለውና አረገ። ዮሐንስም ከፍርሐት የተነሳ ከኢየሱስ ክርስቶስ በተደረገለት ክብ በአትሪብ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ከሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም እያለ ይመሠክር ጀመር።



መኮንኑ የዮሐንሰን ቃል ከሩቅ ሰምቶ እየተናደደ ወጣ ጭንቀትና ፍርሐት ስላደረበትም መንጋጋውን አስለጎመው። ከአፉም ደም ይፈስ ነበር ደናስዮስ ለተባለው አሽከሩንም ሠጠውና በሠንሠለትና በእግርብረት አሥረህ ከመጥፎ ቦታ ላይ አሳድረውና ነገ ወደኔ አምጣው አለው ዲዮናስዮስም የታዘዘውን ሁሉ ፈፀመበት ሌሊት ታሥሮ በመሠቃየት እያለ ግን እግዚአብሔሐርን እየለመነና ሐጢአቴን ይቅር በለኝ እያለ ይፀልይ ነበር መልአከእግዚአብሔር ግን ከሰማይ ወረደና የታሠረበትን ሁሉ ፈታለት። በአካላቱ ላይ ደርሶ የነበረውን ሥቃይ አቃለለት። የታሠረበት የጨለማውንም ቦታ አበራለት። ዮሐንስ በዚህ ወደሰማይ በማንጋጠጥ ፀለየ በመዝሙረዳዊት መቶ አርባ ስምንት የተፃፈውንም ፀሎት አነበበ።

ሲዘምርና ሲያመሰግን የሰሙ ዲዮናስዮስና ሚስቱ እንዲሁም ሴት ልጁ ሁኔታውን ለመመልከት ካለበት ሄደው ቢመለከቱ ሠንሠለቱ ለብቻ እግር ብረቱ ለብቻ ተጥለው ተመለከቱ መልአከ እግዚአብሐርም ከሱ ጋር ተቀምጦ አዩ። በቤታቸው ተቀምጦ የሚጦር አንድ አይነሥውር ነበረና ወደቅዱስ ዮሐንስ አቀረቡት እሱም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በመጥራት አይኑን አበራለት በዚህ ጊዜ ዲዮናስዮስ፣ ከሚስቱና ሴት ልጁ ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። ወደመኮንኑ ቤትም ሦስቱ ሄደው በሩን አንኳኩ መኮንኑም ለግላዊ ፍላጎታቸው የመጡ መሰለው ወደቤቱ ገብተው ግን የቅዱስ ዮሐንስ አምላክ በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን የእግዚአብሔር መልአክ ከሱጋር ቁሞ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን አይተናል የታሠረበትን ዕግር ብረት ከእግሩ፣ ሰንሰለቱን ከእጁ ፈትቶለት ጨለማንም ገፎ ብርሃንን ተክቶለት አይተነዋል በቤታችን የሚኖረውንም አይነሥውር አይኑን አብርቶለታል አንተ ግን የረከስክ ነህ እንዲህ ያለውን የእግዚአብሔር ቅዱስ ለመከራና ለፈተና የምትዳርግ አሉት መኮንኑም እጅግ ተቆጣና ሁለቱን ባልና ሚስት ሴት ልጃቸውንም



www.ethiopianorthodox.org

ጭምር አትሪብ ከምትባል ከተማ ወደውጭ አውጥተው በድንጋይ እንዲደበድቡዋቸው አዘዘ። ሊደበድቡዋቸው የተዘጋጁትን ወታደሮች ወደፈጣሪያችን ጥቂት ፀሎት እንድናደርስ ጥቂት ደቂቃ ታገሱን ብለው ሦስቱ በሕብረት ጌታችን ሆይ ተቀበለን..." እያሉ ፀለዩ። ወድያውም በመንፈቀሌሊት ሦስቱ ተደብድበው ተገደሉ የመንግሥተ ሰማያትንም አክሊል ተቀዳጁ። ነፍሳቸውንም መልአከእግዚአብሔር አሳረገ ወደብርሃን ማደርያም አስገባቸው የቅዱሳን ሰማዕታት ማሕበርተኞችም ሆኑ።

ሲነጋ የስንሑት ተወላጅ የሆነውን ዮሐንስ ያመጡት ዘንድ መኮንኑ አዘዘ። ዮሐንስ መጥቶ ሲቀርብ ባለንጀሮቼን በሥራ ይህ አሳበድክ አለው /መኮንኑ/ ዮሐንስ በሠጠው መልስ እኔስ መሠርይ አይደለሁም እነሱ ግን መንግሥተእግዚአብሔር ስለጠራቻቸው ሄደዋል አንተና ጣኦቶችህ ግን ርኩሳን ናችሁ አለው።

መኮንኑ እጅግ ተቆጣና የገላ መታጠቢያ ለማሞቅ ወደሚነደው የእሳት ነበልባል እንዲወረውሩት አዘዘ እነሱም ወረወሩት እስከ ሦስት ቀንም ከላዩ ላይ ክፍሉን ዘግተውበት ሰነበቱ በሦስተኛው ቀን መኮንኑ እስቲ የሚያመልከው አምላክ አድኖት ከሆነ እንየው በማለት እየዘበተ መጥቶ የማንደጃውን ክፍል ቢያስከፍት ምንም ከሰውነቱ ክፍል በእሳት ሳይነካ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተ አገኘው። በዚህ ጊዜ መኮንኑ አፈረ፣ ተዋረደ፣ መኮንኑን በመከተል ግልብጥ ብለው የመጡት የአትሪብ ሕዝቦች ባንድ ድምፅ ጮኹ እኛ ካሁን ጀምሮ ክርስቲያኖች ነን የቅዱስ ዮሐንስ አምላክ በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን አሉ እነሱም ሠላሳ ወንዶች አምስት ሴቶችና አምስት ሕፃናት ናቸው። መኮንኑም ወድያው አንገት አንገታቸውን አስቆረጠ የመንግሥተሰማያትንም አክሊል ከሰማዕት ጋር ተቀዳጁ።

በነሱና በነዲዮናስዮስ መገደል የአትሪብ ከተማ ታወከች በመኮንኑ ላይም ከፍተኛ ተቃውሞ ተነሳበት፣ ዮሐንስን ግን ወደወህኒ ቤት አስገቡት በወህኒ ቤቱ ክርስቲያኖች ታሥረው አገኘ የታሠሩበት ምክንያትም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ስለጠሩና ስላመኑ ነው። ወንድሞቼ ቅዱሳን ሆይ ሰላም ለናንተ ይሁን አላቸው እነሱም ቅዱስ ዮሐንስ ወንድማችን ሆይ የእግዚአብሔር ሰላምታ ላንተ ይሁን አሉት ሁሉም ሰላም ተባባሉ። ቅዱስ ዮሐንስ ወንድሞቼ ተነሱ ሰማዕትነታችንን እንዲያስፈፅመን ወደእግዚአብሔር እንፀልይ አላቸው ተነስተውም ረጅም ፀሎት አደረሱ። በማግሥቱ መኮንኑ ቅዱስዮሐንስን ከእሥረኞቹ ለይቶ አስወጣውና በሥራይህ አገሬን አመዘበርክ አለው ዮሐንስ ደግሞ እኔስ መሠርይ አይደለሁም የእግዚአብሔር ሐይል ግን ሥራውን ሲሠራ አንተም ሆንክ እኔ እያየን ነው አለው መኮንኑ አንተ ባለንጀሮቼ ሳይቀሩ በሥራ ይህ አሳበድክ ለመሆኑ የየት አገር ተወላጅ ነህ አለው "እኔ ስንሑት" ከምትባል አገር ከዚያም "ብና" በመባል ከምትታወቅ ክፍል ነው ትውልዴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ያንተን ፈተና እንድታገሰው ፅናት የሚሠጠኝ አንተ ግን የእግዚአብሔን ሐይል ሥራይ ትላለህ በዚህም የረከስክ ነህ አለው መኮንኑም በቁጣ እየተቃጠለ በእውነት የአማልክቶቻችን ሐይል እስካሁን ጠብቆሃል አሁንም ከተዘጋጀብህ ግርፋት እንድትድን ለአማልክት መሥዋዕትን አቅርብ አለው።

ዮሐንስ የንጉሡ አማልክት ያሉብትን አሳየኝና ልስገድላቸው አለው መኮንኑ በዚህ ጊዜ ካገሩ ሰዎች አንድም ሳይቀር እንዲሰበሰቡና ዮሐንስ ለንጉሡ አማልክት ሲሰግድ እንዲመለከቱ በአዋጅ ጠራቸው የአትሪብ ሕዝብ እንጻለ ግልብጥ ብሎ ወደመኮንኑ መጣና ብርባ ወደተባለው የአማልክት ቦታ መኮንኑን ተከትሎ ሄደ። ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ጊዜ ድምፁን እጅግ ከፍ አድርጎ በእውነት አንተ ጣኦት ሊሠገድልህ የሚገባ አምላክ ነህ ሰማይንና ምድርን የፈጠርከስ አንተነህን አለው ጣኦቱም እንደሰው እየተናገረ እኔ አምላክ አይደለሁም አለ። ዮሐንስ በዚህ ጊዜ ዓይኑን ወደሰማይ በማንጋጠጥ ሕያውና ቀዳማዊ የሆንከው ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከዚህ የተሰበሰቡ ፍጡሮችህ አንተ የሁሉ ፈጣሪና ጌታ መሆንህን ያውቁ ዘንድ ሐይልህን እንድታሳይ እለምንሃለሁ ይህን መኮንንና አማልክቶቹም እንድታጠፋቸው ፈቃድህ ይሁን ካለ በኋላ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣እሱን ለማወቅ ዓይነ ልቡናዮን ያበራልኝ በማለት ፀለየ።

በዚህ ጊዜ አንተ ጣኦት ካለህበት ወደታች እንድትሠምጥ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላህለሁ ብሎ ምድሩን ቢረግጠው ጣኦቱን ምድር ተከፍታ ዋጠችው ይህን አምላካዊ ሐይል ሲያይያ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ እኛ ዮሐንስ ምስክሩ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን እግዚአብሔር ብቻ ነው አምላክ ሥግደትና መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ብቻ እናቀርባለን እያለ፣ ጮኸ። በዚህ ጊዜ መኮንኑ ሰይፍንና ጎራደን በታጠቁ ወታደሮቹ አሥራ አምስት ወንዶችን አሥር ሴቶችንና ሰባት ሕፃናትን አስገደለ እነሱም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰማእታትን ሆኑ መንግሥተሰማያትንም ወረሱ ዮሐንስም አንተ ያበድክ ሰው እኔ ከአምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሁኜ ከዚህ አለሁ አንተና የረከሱ አማልክቶችህም ከንቱነታችሁም በእግዚአብሔር ሐይል ታወቀ ለመሆኑ አማልክቶችህ የትናቸው እኔም ልሥግድላቸው ንጉሥህስ የታለ በማለት ዘበተበት መኮንኑ ግን ሐፍረት ተሰምቶት ዝም አለ ወደቤቱም ሄደ።

በማግሥቱ ይህ መኮንን ወደአርያኖስ የላዕላይ ግብፅ



መኮንን "ካንተ ወደኔ ከተላከው ዮሐንስ ክርስቲያናዊ የደረሰብኝን መከራ ልግለፅልህ ዮሐንስ ለንጉሥ አማልክት አልሠገድም ከማለቱም በላይ በኔ ላይም የልብ በሽታ አሳድሮብኛል እሱ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው የሚያመልከው እሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ጠርቶ ከንጉሡ ዲዮቅልጢያኖስ የተላኩትን አማልክት አስጥሞአቸዋል። በሱ ብዙ ጥፋትና ውርደት ስለደረሰብኝ በሁለት ወታደሮች አስይዤ ወዳንተ እንድልከው ተገድጄአለሁ። እጆቹ በሠንሠለት ዕግሮቹ በዕግር ብረት ታሥሮ ወዳንተ ይመጣል /ልኬዋለሁ/" የሚል ደብዳቤ አስይዞ በሁለት ወታደሮች አሳጅቦ ላከው ወታደሮቹና ዮሐንስ በመርከብ ተሳፍረው ጉዞ ጀመሩ በመርከብ ጉዞው ብዙ ቀናት የሚወስድ ነው ነገር ግን በጉዞው ወቅት ለዮሐንስ መብልና ውሃ እንዳይሠጠው ከለከሉ ዮሐንስ ግን ጌታዬ ሆይ በግርፋቱ ጊዜ ወደእሳት በተጣልኩ ጊዜና በሌሎችም ፈተናዎቹ ከኔ አልተለየህም አሁንም በጉዞዮ አንተ አትለኝ አትራቀኝም እያለ ፀለየ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሱ ብቻ ተገልፆ አነጋገረው የታሠረባቸውን ሠንሠለቶችና እግር ብረቶችንም ፈታለት፣ እጁና እግሩ አጥብቀው ስላሠሩት ተሸክመው ነው ከመርከቡ ያሳፈሩት ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያይ ዮሐንስ ወድቆ ሰገደለት ጌታችንም ከዮሐንስ ፍርሐትን አስወገደ ይህን ዓለም አሸንፈህ መንግሥተሰማያት እስከትገባ ድረስ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ቦታ ካንተ አልለይም በማለትም የምሥራች ቃል ነገረው ከዚያም ተሠወረበት ዮሐንስ ግን በራብና በጥም ሳይበሳጭ ሌሊቱን ሁሉ እየፀለየና እግዚአብሔርን እያመሠገነ አደረ።

በመርከቡ ከተሣፈሩት ሰዎች መካከል ከእንቅልፍ ነቅቶ የዮሐንስ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ቃል በቃል መነጋገርን



www.ethiopianorthodox.org

የሰማ አንድ ሰው ነበር ዮሐንስ ፀሎቱን ሲጨርስ ይህ ሰው ሰላም ላንተ ይሁን ወንድሜ ሆይ በማለት ዮሐንስን ተናገረው ዮሐንስም የሰማይና የምድር አምላክ በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደእግዚአብሔር በሚያምን ሁሉ ሰላም ይሁን በማለት መለሰለት። ሰውየው "እስካሁን እኔ ክርስቲያን አልነበርኩም አሁን ግን አንተ በምታምነውና ስለ ስሙ መከራ በምትቀበልለት እግዚአብሔር አምኛለሁ" አለው። ዮሐንስም እግዚአብሔር አንተን ከማሕበረሰማዕታት እንዲጨምርህ እለምነዋለሁ አለው። ሰውየው "ወንድሜ ሆይ እህል ውሃ እንደ ከለከሉህና በረሀብ ሊገድሉህ እንደፈለጉ ተረድቻለሁ የምትቀምሰውን ነገር ልስጥህን" አለው። ዮሐንስ እኔ ጌታዩና መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ በፀጋውና በረድኤቱ ስለጎበኘኝ አልራበኝም ውሃም አልጠማኝም የእግዚአብሔር በረከት ይደርብሕ አለው።

ከተሳፈሩበት አገር ተነስተው "አስዩጥ" ከሚባል አገር ደረሱ። ጊዜው ምሽት ነበርና እንዲያደርሱት የተወከሉት ሁለቱ ወታደሮች ከመርከቡ አውርደው ወደ ከተማ ወሰዱትና እሱን ይዘው ለማደር ሄዱ ያንዲት ድሃ ሴት ቤት አገኙ። ወታደሮቹ ስንቃቸውን ጨርሰው ስለነበር ድሐዋን ሴት የምንበላውን ስጭን አሏት እሳ ግን ከድሕነቷም በላይ ደካማ ነበረች እሷም እኔ ደካማና ድሃ ስለሆንኩ ከኔ ቤት ምንም የሚላስ የሚቀመስ የለም አለቻቸው ቅዱስ ዮሐንስ በበኩሉ የምታመልኪው ምንድር ነው ሲል ጠየቃትና ትልቁን አጵሉንን አመልካለሁ አለችው። ዮሐንስ የሷን መልስ ሰምቶ "አንቺ እውነትም ድሀ ነሽ ካንቺ በባሰ ደግሞ አማልክቶችሽ ድሆች ናቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ብታምኚ ኑሮ የመንፈስ ድሐ አትሆኚም ነበር የመንግሥተ ሰማያት ተሥፋ በሕይወትሽ ተቀርፆ የዚህን ዓለም ድህነት እንደምንም እንዳትቆጥሪው ባደረገሽ ነበር አላት።

ይህቺ ሴት ወድያው በእግዚአብሔር አመነች ሌሊቱንም ሁሉ ከቅዱስ ዮሐንስ ትምህርተሃይማኖትን ስትማር አደረች እውነተኛ ክርስቲያንም ለመሆን በቃች ዮሐንስም ከማሕበረ ምዕመናን እንድትቆጠር እግዚአብሔርን ለመነላት በስመ እግዚአብሔርም ባረካት ሌሊቱ በሷ ቤት እንዳሉ አለፈ። ሲነጋ ወታደሮቹ ቅዱስ ዮሐንስን ወደአርያኖስ መኮንን ወሰዱት እሱንም አግኝተው ያ መኮንን በአድራሻ ለሱ ስለቅዱስ ዮሐንስ የፃፈውን መልእክት ለአርያኖስ መኮንን ሠጡት። የደብዳቤውን ፍሬ ነገር እንዳነበበ ወዲያው ለመታጠቢያ ቤት ማሞቂያ ተብሉ ሌት ተቀን ግንድና ፍልጥ ተማግዶበት ከሚነዳው ክፍል ቅዱስ ዮሐንስን እንዲወረውሩት አዘዘ እነሱም ወረወሩት ግን እሳተ እንዳይነካው መልአከእግዚአብሔር ወርዶ ጠበቀው መኮንኑ አርያኖስ ግን በሦስተኛው ቀኑ እስቲ ከእሳቱ እግዚአብሔር አድኖት ከሆነ እንመልከት በማለት እየተዘባበተ መጣ። እሳቱ በእግዚአብሔር ሐይል ጠፋና ዮሐንስ ከማንደጃው ክፍል ወጥቶ በመኮንኑ አርያኖስፊት ቆመ ፊቱም የበራና በመልካም እንክብካቤ የሚኖር ሰው ይመስል ነበር። "አንተ ጣኦታትን በማምለክና የንፁሐን ሰማዕታትን ደምን በማፍሰስ ሕይወትህ የረከሰ እኔ ከአምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አለሁልህ፣ አንተም የአጋንንት ማደርያ ከሆነው ጣኦትህ ጋር አለህ። በማለትም መኮንኑን ገሠፀው።

የባኞው /መታጠቢያው/ ፅዳት ማገጾ ሠራተኞች አምሳ አምስት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ነበሩ። እነሱ በሙሉ ግልብጥ ብለውና ሥራቸውንም አቁመው በሰልፍ መጡና ከመኮንኑ አርያኖስ ፊት ቆመው "ያላንድ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስና የሌሎችም ክርስቲያን አምላክ ሌላ አምላክ የለም። እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ወልደእግዚአብሔር እናምናለን" ሲሉ የእምነት ቃላቸውን አሰሙ።

መኮንን አርያዮስ በሠይጣናዊ ንዴትና ብስጭት ልቡ ተቃጠለና አምሳ ስምንቱን ሰዎች /55 ወንዶችና ሦስት ሴቶች/ ወደ አደባባይ አስወጥቶ በሠይፍ አንገት አንገታቸውን ቆርጦ ጣላቸው የሰማዕትነትን አክሊል ሁሉም ተቀዳጁ የመንግሥተሰማያት ባለቤትም ለመሆን የማሕበረ ሰማዕታት አባሎች ሆኑ። /የነሱ በረከት በሁላችን ላይ ይደር/።

አርያኖስ ወደ ቅዱስ ዮሐንስ ፊቱን አዞረና በሥራይህ ሰዎችን እያሳሳትክ አገሬን ለጥፋት ዳረግሃት አለውና ወደሥቃይ ቦታ ውሰዱትና እንዳለፈው የፈፀምንበትን ደግመን እንፈፅምበት አለ። እጅግ ጨለማ ወደሆነና ከመሬት በታች ወደተሠራ የመከራ ቦታም አስከተተው ዮሐንስ ከዚሁ ለመከራ የተዳረጉ ክርስቲያኖችን አገኘ እሥረኞቹ በሙሉ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የታሠሩ ነበሩ አንድም የሌላ እሥረኛ በመካከላቸው አልነበረም። ዮሐንስ ወንድሞቼ ሆይ ሰላም ለናንተይሁን አላቸው እነሱም አንተ ቅዱስ መሥተጋድል ሆይ የእግዚአብሔር ሰላም ባንተ ላይ ይደር ምሕረትና ሰላም በኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምኑ ሁሉ ትሁን አሉት። ዮሐንስ ደግሞ ሁለት ጊዜ ከተጣልኩበት የእሳት ቃጠሎ ያዳነኝን እግዚአብሔር አመሰግነዋለሁ አለና ከመንፈሳዊ ደስታ ብዛት የተነሳ "እንነሳና በሕብረት እንፀልይ ተባብለው ፀሎት ጀመሩ መዝሙረ ዳዊትን ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ" የሚለውን መቶ አምሳኛውን አነበቡ።

ሲነጋ መኮንኑ ቅዱስ ዮሐንስን ከጨለማው ወሕኒ ቤት አስወጥቶ ወሰደው አገሬን በሥራይ አበላሸህብኝ በማለትም ዘለፋውን ጀመረ ዮሐንስ በበኩሉ እኔ የሥራይ ሰው አይደለሁም የሥራይ ሥራንም አላውቅም ነገር ግን ሥራይን ሁሉ የሚሽር ኢየሱስ ክርስቶስን አመልካለሁ አለው መኮንኑ ከሁሉ በላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በፊቱ እንዲነሳ አይፈልግም ማንም የማይጠጋው ተራጋጭ ፈረስ ለመኮንኑ ነበረው ፈረሱን በመጀመሪያ በልጓም ለጉመው እንዲይዙትና ዮሐንስን ከፈረሱ ጀርባ ጋር በገመድ ካሠሩት በኃላ ፈረሱን እንዲለቁት በዚህም እያስጎተቱ ባገሩ ሁሉ እንዲያዞሩት አዘዘ ከዚህም አያይዞ ከአማልክት በቀር ሌላ አምላክ አለ የሚል ካለ የዮሐንስ ቅጣት ይጠብቀዋል እያለ አዋጅ የሚነግር ሰው በየቦታው ላከ።

ዮሐንስ በፈረሱ እየተጎተተ አካላቱ በየቦታው ተቆራረጠ ደሙም ፈሰሰ አንድ አይነ ስውር የክርስቲያን አምላክ ብርሃንን ስጠኝ ብሎ ከፈሰሰው የዮሐንስ ደም አይኑን ቢቀባ ተፈወሰ አይኑ በራ። እንዲሁም አንድ በለምጽ የተያዘ ሰው ስመእግዚአብሔርን ጠርቶ ከፈሰሰው የዮሐንስ ደም ቢቀባ ከለምፁ ተፈወሰ ሌሎችም ከአሕዛብ ወገኖች በየመንገዱ የተንጠባጠበውን ደሙ እየተቀቡ ከተለያዩ የሥጋ ሕመሞች ለመፈወስ ችለዋል አንዲት ሴት ደግሞ ተቆርጦ የተጣለውን የአካላቱን ክፍል አግኝታ አይነሥውር የነበረችውን ሴት ልጅዋ ብታስነካት ዳነችላት። ይህንን ተአምር ብቻ በማየት ኢየሱስ ክርስቶስን አምነው ሰማእትነትን የተቀበሉ ክርስቲያን እጅግ ብዙ ናቸው።

ዮሐንስ በዚሁ ሰማዕትነቱን ተቀበለ ነገር ግን አልሞተም በየቦታው በፈሰሰው ደሙና በተቆራረጠው ሥጋው ብዙዎች ሲፈወሱና ኢየሱስ ክርስቶስንም እያመኑ ለሰማዕትነት ሲሰለፉ ሲመለከት





www.ethiopianorthodox.org

መኮንን አርያኖስ ሌላ አደጋ እንደተደቀነበት በመፍራት የአካላቱ ቁርጭራጭ ከያለበትተለቅሞ ወደ ባሕር እንዲጣል አዘዘ። እነሱም እንደታዘዙት ወደባሕር ጣሉት። ነገር ግን ሲመለሱ ከባህር ወጥቶ ተከተላቸው። በዚህ ጊዜ ወደባሕር የጣሉትና ሲጥሉት የተመለከቱ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ ወድያውም በአርያኖስ መኮንን ሰማዕትነትን ተቀበሉ /ተሠይፉ/ አርያኖስ እንደገና ለሞት የሚያደርስ ሌላ ብዙ መከራም በዮሐንስ ላይ አደረሰ ነገር ግን እግዚአብሔር በሱ ላይ አድሮ የሚያሳየውን ተአምራትና የሱን ፅናት በመመልከት ብዙዎች እግዚአብሔርን አመኑ ከዮሐንስ አምላክ በቀር ሌላ አምላክ የለም አሉ አርያኖስን አንተና አማልክቶችህ የረከሳችሁ ናችሁ አሉት እሱም በሰይፍ አስፈጃቸው እነሱም ሰማዕትነትን ተቀበሉ።

አርያኖስ ዮሐንስን በሥራይህ አገሬን ለማጥፋት ተነስተሃል በማለት ከዘለፋው በኃላ ሞት የተፈረደባቸው ክርስቲያኖች ወደታጨቁበት የጨለማ ወህኒ ቤት አስገባው ከክርስቲያኖቹ ጋር ሌሊት ሲፀልዩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታያቸው ወንድሞቼ አትፍሩ በማለትም አረጋጋቸው እነሱም ወድቀው ሰገዱለት እሱም አስነሳቸው ዮሐንስን ደግሞ ባንተ ፅናትና ባንተላይ በማደርገው ተአምር ብዙዎች የመንግሥተሰማያት ባለቤቶች ሁነዋል ካሁን ወድያ ይህን የመከራ ዓለም ልትገላገለው አንድ ሳምንት ቀርቶሃል አለው።

ዮሐንስ በዚሁ የጨለማ ቦታ ሦስት ቀን ሰነበተ በእሥር ቤቱ እያለ ዩልያስ የሚባል ክርስቲያን ፀሐፊ ታሥሮ ገባና ከዮሐንስ ጀምሮ በዚያ የታሠሩትን ክርስቲያን ታሪክ ከያንዳንዳቸው እየጠየቀ ፃፈ። ሰማዕታቱም የሰማዕታት በረከት ይደርብህ እያሉ መረቁት ወድያው አርያኖስ መኮንን ባንተ ምክንያት ብዙ ድካምና ጭንቀት



ተሰማኝ ለንጉሥ አማልክት ባለመስገድህ ታላቅ ሐፍረት እየተሰማኝ ነው አሁንም ካልሰገድህ እገድልሃለሁ አለው። ዮሐንስ ግን ይህን ዓለም ትቶ ወደዘለዓለሙ መንግሥተሰማያት ለመሄድ በመዘጋጀቱ ታላቅ ክብርና ደስታ ተሰማው አርያኖስን አንተ ከሐዲ በኔ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የገለፀውን ተአምር አይተህ የማትመለስ ልበደንዳና ርኩስ ነህ አማልክቶችህም ርኩሳን ናቸው ሲል በድፍረት ገሠፀው።

አርያኖስ ብዙ ደክሞ ሊመለስለት ስለልቻለ በስለታም ሠይፍ አንገቱን እንዲቆርጡት ወታደሮቹን አዘዘ አርያኖስ ብዙዎቹ ወታደሮቹ በዮሐንስ ፅናትና በእግዚአብሔር ገቢረተአምር ክርስቲያኖች እየሆኑና ያለፍርሃት አንገታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየተቆረጡ ሰማዕት በመሆን ሰለተመናመኑበት ከፍተኛ ብስጭት አድሮበት ነበር ዮሐንስ ለመጨረሻ ጊዜ ለመሠየፍ የተመደቡት ወታደሮች ወደሚሠየፍበት ቦታ ወሰዱትና "ለዚህ ታላቅ ፀጋ ስላበቃኸኝ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አመሰግንሃለሁ ..." እያለ ፀለየ።

ፀሎቱን ጨርሶ ለወታደሮቹ እንካችሁ ብሎ አንገቱን ሠጣቸው እነሱም ቆረጡት ግንቦት ስምንት ቀን ሰማዕትነትን ተቀበለ። ያ በወህኒ ቤት ታሥሮ እያለ የሕይወት ታሪኩን ጠይቆ የፃፈለት ዩልያስ ሥጋውን በክብር ገነዘ ከሁለት ተማሪዎቹ ጋርም አስክሬኑን በመርከብ አስጭኖ ወደትውልድ አገሩ ሥንሑት ወሰደው። የሰማዕትነቱንም መጽሐፍ አስቀድሞ ለስንሑት ሕዝብ አስረከበ የስንሑት ሕዝብ ይህን የመሰለና በሰማዕትነቱ ኢየሱስ ክርስቶስን አገልግሎ ይህን አለም በክብር የተሰናበተ ቅዱስ ሰው አስክሬን ስለመጣላቸው እጅግ ተደሰቱ። የየአብያተ ክርስቲያናቱንዋይ ቅድሳትን ለክብሩ በማስወጣት ካህናት ዝማሬና ምሥጋና እያሰሙ አስክሬኑን አጅበው እስከቤተክርስቲያን አደረሱት ሰባት ቀን ሙሉም የሱ መታሰብያ ፀሎት አደረሱ የሱ የተጋድሎ ታሪክ የሰሙ



www.ethiopianorthodox.org

ወደመፍራት አዘነበሉ እንዲህም አሉ እኛስ የልዑል እግዚአብሔር ባሮች ነን ተግተን የምንጠብቀውም እሱን ማመን ብቻ ነው። እምነታችንን ይዘንከአምላካችን ዘንድ እንቀርባለን እግዚአብሔር "ደገኛ ባርያ ሆይ በጥቂቱ የታመንክ ከሆንክ በብዙ እሾማሀለሁ" ያለበትን ተስፋ የምንጠብቅ ነን አንተም ብትሆን አትሳሳት ምድራዊ ሹመትን ፈላጊ ምድራዊ ንጉሥን ደጅ ይጠናል ይህም ምድራዊ ሹመት ሐላፊና ጠፊ ነው። ሐላፊዎች ሐላፊውን ደጅ ይፀኑታል ይገዙለትማል እኛ ደጅ የምንፀናው ግን የማያልፈውንና የማይጠፋውን ዘለዓለማዊ እግዚአብሔርን ነው። ይህንን ተስፋ ጠብቀን የማይሠረቀውን የማያረጀውንና ማለቂያ የሌለውን መንግሥተሰማያትን እንወርሳለን አሉ። ወደመኮንኑ አንቲጳስም ፊታቸውን በማዞር እኛ ካንተ የሚመጣብንን መከራ ለመቀበል ዝግጁዎች ነን ሐብታችን ሹመታችንና ክብራችን በእግዚአብሔር ብቻ መመካት ነው ራሳችን ለሞት እንሠጣለን በዚሁ ከሞትን እግዚአብሔር ዋጋችንን ይከፍለናል። ራሳችንን ለሞት አዘጋጅተናል ይኸውም በእግዚአብሔር እምነት በመፅናት ነው" አሉ።

አንቲጳስ የነሱን መልስ ሲሰማ እጅግ ተበሳጨ ፊቱም ተለዋወጠ እያንጓንጓቸውን በተናጠል ለያይተው ያሰቃዩዋቸው ዘንድ አዘዘ። በትእዛዙ መሠረትም ለየብቻቸው ለያይተው አሰቃዩዋቸው ነገር ግን መሸቶ በነጋ ቁጥር ስለክርስቶስ መታገሣቸው በበለጠ ይበዛ ነበር። በዚህ መሠረት ሶፍያን አይዞሽ ሩጫሽ በእምነት ይሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋን ተሸለሚ ማሸነፍ ላንቺ ነው ዓለም ካንቺ ጋር ትንቅንቅ ይዟል አሸናፊነት ላንቺ ነው ከእግዚአበሔር የተሠጠሽ ብርሃን ሳይጨልም ሩጫሽ ካምስት ጠባባት ድናግል ቁጥርሽ ይሁን እንደነሱ የሙሽራውን ብርሃን



ልበሺ ድካምሽና መጋደልሽ በሰማያት ዋጋን ለሚከፍል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚል ምዕዳን ከክርስቲያኖች ወንድሞቿ ተሠጣት።

ሶፍያና ወገኖቿ 19 ቀን ሙሉ በተናጠል መከራ ሲቀበሉ ሰነበቱ ከ19 ቀን በኃላ አንቲጳስ መኮንን ለመጀመሪያ ጊዜ የኬልቄዶንን ክርስቲያን በስብቀት ካጋለጠው ነገረሠሪ አጵልያኖስ ጋር በነሱ ላይ ምን ማድረግ እንዳለበት ተማከረ በፍርድ አደባባዩም ተቀምጦ ለጥያቄ ለ19 ቀናት ከታሠሩበት አመጣቸው በመካከላቸው ቅድሰት አፎምያ ትገኝ ነበር።

አንቲጳስ " እንደሕፃናት አእምሮ የሌላችሁ ናችሁ ባለፉት ሳምንታት ግን መከራን አውቃችሁታል ልብም ገዝታችኋል ስለዚህ እወቁበት ለአምላክ አሪስም ስገዱ" አላቸው እነሱ ግን ካለፈው በበለጠ ባንድ ድምፅ አፎምያን በግንባር ቀደም አሰልፈው "አንቲጳስ ሆይ አንተ ለምንድር ነው ከስህተትህ የማትመለሰው የፈጠርህን እግዚአብሔርንስ ለምን ረሳኸው" አሉት። በዚህ ጊዜ ወታደሮቹ ፊት ፊታቸውን በጥፊ መቱዋቸው ለአሪስ እንዲሠግዱም አስገድዱዋቸው" አላቸው እነሱም እንደታዙት ብዙ ጊዜ በጥፊ ፊት ፊታቸውን ደግመው ደጋግመው መቱ ነገር ግን በእግዚአብሔር ማመናቸው መከራ በተቀበሉ ቁጥር ይፀና ነበር።

አፎምያና ወንድሞቿ የኬልቄዶን ክርስቲያን ከአንቲጳስ መኮንን የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ በትዕግሥትና በፀጋ ከመቀበል በቀር ሊመለሱለት እንዳልቻሉ ተመልክቶ አጵልያኖስ ብዙ ሥቃይ ካደረስክባቸው በኋላ ወደዲዮቅልጥያኖስ ላካቸው በማለት መከረው አንቲጳስም የሱን ምክር ተቀብሉ ወደ አሥርቤት አስገባቸው ከአፎምያ ጋር ቁጥራቸው 49 ነበር። በዚህ ሰዓት አጵልያኖስ አፎምያን ከ49ኙ ለይቶ ለብቻዋ ወሰዳት አፎምያም ርዳኝ



www.ethiopianorthodox.org

አትተወኝ ሕይወቴን ላንተ ሠዋቻለሁ ..." እያለች ወደ እግዚአብሔር ፀለየች። በመጨረሻ አፎምያን ለብቻዋ ለይተው ወሰዷትና አንቺ ሴት ነሽ ክብርሽ ተጠብቆ እንደሌሎች ሴቶች ወርቅና ብር ኑሮሽ በተዋበ ልብስም ተንቆጥቁጠሽ የመታየት ጊዜሽ በከንቱ ማለፍ የለበትም አሁንም አሪስ ለተባለው የንጉሥአምላክ ስገጂና ያ ሁሉ ይደረግልሻል አሏት አፎምያ ለዚሁ መልስ "ስትሠጥ ሥጋዬን በወርቅ ባሸበርቀው የሥጋነት ጠባዩ አይተውም ነፍስ ስትለየው ይፈርሳል ይበሰብሳል ስለዚህ የሚፈርሰውንና የሚበሰብሰውን ሥጋ በወርቅና በብር በከበረ ልብስም እያሠማመርኩ ነብሴን ለመጉዳት አልሻም መፍረስና መበስበስ የማይቀርለትን ሥጋዬ እገለገልበት አለሁ እንጂ አላገለግለውም እሱን ሳገለግል ዘለዓለማዊው ፀጋ ሊያመልጠኝ አልፈልግም። ስለዚህ የሚመጣበኝን የሥጋ መከራ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እቀበለዋለሁ እንጂ ለርኩስ የአረማውያን ጣኦት አልሠግድም" አለች።

አንቲጳስ መኮንን በዚህ ጊዜ ተናደደና እንዴት በሴት እንሸነፍ በማለት የዛቻ ቃል ካሰማበኃላ ልዩ መንኩራክር አሠርቶ በሚሽከረከረው ብረት ላይ እንድትታሠርና መንኮራኩሩ ሲሽከረከር ወደመሬት አጣብቆ እንዲገድላት አደረገ በዚህ ጊዜ አፎምያ ወደ እግዚአብሔር ስትፀልይ እንዲህ አለች "ጌታና አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ፈቃድህ ከሆነ በዚሁ ነፍሴ ከሥጋዬ ትለይ በኔ መከራ መታገሥ ሌሎች ወዳንተ እንዲመጡ ፈቃድህ ከሆነ ደግሞ መከራውን አስችለኝ በርድኤትም አትለየኝ"

በመንኮራኩሩ ላይ ታሥራ ሰውነትዋ መቆራረጥ ሲጀምር መልአክ እግዚአብሔር ወርዶ መንኩራኩሩን ሠበረው የመንኮራኩሩ ኅታቾችም አሳመጣቸው። አፎምያም ምንም ሳትሆን ተነሳች።



አንቲጳስም እጅግ ተናደደ በጣኦቱ ስምም ምሎ ለአማልክት ካልሠገድሽና ለነሱም መሥዋእትን ካለቀረብሽ በእሳት እለበልብሻለሁ ማንም ረዳትም አይኖርሽም አላት አፎምያም አንተ እኔን ?ምታቃጥልበት እሳት በውሃ የሚጠፋ እሳት ነው ስለዚህ ይህን ፈርቼ ከዘለዓለሙ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ አልወጣም በክርስቶስ ያመኑትን ፃድቃን ምድራዊ እሳት ያስፈራቸውም ይታገሡታል ሐይላቸውና ፅናታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ነውና በዚህ ዓለም መከራና ሥቃይ አይደነግጡም ደስ ይላቸዋል እንጂ አለችው።

አንቲጳስ እስከ 45 ክንድ ርቆ ወላፍኑ ሰውን የሚገርፍ እሳት አስነድዶ ወደዚያ እንዲከቷት አዘዘ እንድትፈራም ካጠገቡ አቆሟት እሷም ይህን ነበልባለእሳት በመታገሥ ክብርህን እንድገልፅ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሐይልና ፅናት ሥጠኝ ለሟቹ ሥጋዬ እንዳልሳሳ ያባቶቼንና እናቶቼን ሰማዕታት መንገድ እንድከተልም አንተ ርዳኝ ሰዎች ለሰው ሠራሽ ጣኦታት እየሰገዱ ይጠፋሉ እንደነሱ እንድጠፋም ይፈልጋሉ እያለች ፀለየች ፀሎቷን ስትጨርስ ወገቧ ላይ በረጅም ገመድ አሥረው ወደእሳቱ እንዲወረውሯት ወታደሮቹን አዘዘ ሴትንስ የተባለው ከወታደሮቹ አንዱ በገመድ ሊያሥራት ታዘዘ እሱ ግን በዚች ቅድስት ሴት ላይ እጄን መዘርጋት አልችልም ቅዱሳን መላእክት ሊቀበሏት ከፊቷ ቁመው እየታዩኝ ነው ስለዚህ እኔን ከዚህ ሥራ ነፃ እንድሆን አድርገኝ አለው ሌሎቹም በዚሁ በሴትንስ አባባል ተስማሙ ቅድስት አፎምያን ወደ እሳት አንወረውርም ብለው በአንቲጳ ላይ አደሙ ስለዚህ ሌሎች ወታደሮች መጥተው እነሱን እንዲጠብቁ አደረገ። ሌሎች ሁለት ወታደሮችንም አስመጥቶ ወደ እሳቱ አስወረወራት። ነገር ግን ገና ወደእሳቱ ከመድረሷ መላእክት ተቀበሏት እሳቱንም



www.ethiopianorthodox.org

ወላፍኑን ወደሌሎች አዙሮ የዲዮቅልጥያኖስን ተከታዮች አቃጠለ አፎምያ በእሳቱ ማሀል ቁማ ኢየሱስ ክርስቶስን በግርማ መንግሥቱ አየችው እጅዋንም ዘርግታ ፀለየች እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶን አመሰገነች።

ከነበልባል እሳቱ ወጥታ ከመኮንኑ ያፈነገጡትን ወታደሮች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተማፀነችላቸው አንቲጳስ በበኩሉ እንዴት እንደምገድላት እስካስብ ድረስ እሥርቤት ክተቷት አለ። ለመታሠር ስትወሰድም እግዚአብሔርን ታመሰግን ነበር እነዚያ ወደእሳት አንወረውራትም ያሉ ሁለት ወታደሮችም የተጋድሎዋን ፅናት አይተው ተደነቁ እግዚአብሔር ከቅዱሳን ሰማዕታት ጋር እንዲቆጥራት ለመኑላት በእሥርቤት ሁሉም ተገናኝተው ነበርና።

በማግሥቱ አንቲጳስ ለጥያቄ ወደ አደባባዩ አስመጣት ሁለቱ ወታደሮችንም ከሷ ጋር አቅርቦ ለአማልክት እንዲሠግዱ አዘዛቸው እነሱ ግን እስካሁን ባለመረዳታችን እግዚአብሔር በሚያሳዝን ተግባር ተሠማርተን ኑረናል አሁን ግን በቅድስት አፎምያ ብቻ እየተመራን እግዚአብሔርን ለማገልገል እንፈልጋለን እግዚአብሔርም ይቅር ባይ አምላክ ነውና ያለፈውን ሐጢአታችንና ስህተታችንን ይቅር ይለናል አንተ ራስህ ተሳስተህ እኛን ስታሳስት ኑረሃል ከዛሬ ጀምሮ መሪያችንና ንጉሣችን እኛንና አንተን የፈጠረ እግዚአብሔር ብቻ ነው እኛ ተስፋ መንግሥተሰማያትን እንከተላለን አንተ ግን የፈለግኸውን ፈፅምብን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንቀበለዋለን አሉት።

አንቲጳስ ተቆጥቶ እንደገና ወደእሥርቤት እንዲመልሱዋቸው አዘዘ "እነሱም ሁሉን የያዝክ እግዚአብሔር ሆይ ደገኛና ንፁህ ነህ በጥበብህ ሁሉን ሠራህ በባሕር ውስጥ ዓሣ ነባሪን የፈጠርክ ምድርን በውሃ ላይ የሠራሃት፣ ብርሃንን ከጨለማ የለየህ ከይሲን የገደልከው የሞትን ፃዕር የፈታህ ከዚህ ከሐዲ ፃዕር ፍታን አንተን ከማገልገልም አታርቀን" እያሉ ፀለዩ። ያለ ፍርሐተና ጭንቀትም ሕይወታቸውን አሳልፈው ሠጡ።

አንቲጳስ የነሱን ጥበአት ተመልክቶ ግራ በመጋባት ወደቤቱ ሄደ የሱም ወታደሮች በሰይፍ አንገታቸውን ቆረጡዋቸው የመንግሥተሰማያትንም የሰማዕትነት አክሊል ተቀዳጁ ክርስቲያኖችም የነዚህን ሰማዕታት አስክሬን ገነዙ በድናቸውንም በክበረ ግምጃ ሸልመው ቀበሩዋቸው ሲነጋ አንቲጳስ የቅድስት አፍምያን ቃል ለመቀበል መጣ እሷንም ከእሥርቤት አውጥተው ለጥያቄ ሲወስዷት እንደንቦሳ እየተደሰተችና እየዘመረች መጣች በመዝሙርዋም አምላኬ ሆይ አዲስ ምስጋናን አቀርባለሁ ስምህንም አመስግኜ እደሰታለሁ ትል ነበር እየዘመረችም በፍርዱ አደባባይ ቆመች።

አንቲጳስ መኮንን በዚህ ጊዜ ዕብደትሽ እስከመቼ ነው ለምንስ ነፍስሺን በገዛ ራስሽ ታጠፍያለሽ ጥፋትሽን ንጉሥ የሚያመልከው ታላቁ አምላክ ይቅር ይላል ስገጂለት መሥዋዕትንም አቅርቢለት እሺም በይው ሕይወት ታገኚያለሽ የሱንም እናት ለመሆን ትበቂያለሽ አላት። አፎምያግን ለአንቲጳስ ጥያቄ ሳቅ የተቀላቀለበት መልስ ስትመልስለት "እውነትም አንተ ዕብድ ነህ እኔ የጥፋት እናት እንድሆንልህ ትፈልጋለህ የዲጳዎች የአጋንንት ማደሪያዎች የርኩሳን የሐሰተኞች የደንቆሮዎች እናት አልሆንም አለችው በመቀጠልም አንተ በኪይሲ ወጥመድ የተያዝክ ነህ ውሸትን ልብስህ አድርገሃል የኔ ሐብት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው" አለችው።

መኮንን አንቲጳስ አራት ድንጋይ አምጥተው ጉጠትን

www.ethiopianorthodox.org

በየመዓዙኑ እንዲያስቀምጡና ቅድስትአፎምያን ወደዚያ እንዲያስገቧት አዘዘ ይህች ቅድስትና የእግዚአብሔር በግ አፎምያ እያለቀሰችና እየሰገደች አምላክኬ እግዚአብሔር ሆይ አንተን እማልዳለሁ ባንተ ፊትም እንበረከካለሁ አንተንም እየለመንኩ እንባዬን አፈሳለሁ ጀርባዬን ለግርፋት አዘጋጅቼ አለሁ ፊቴንም ከአረማውያን ጥፋት ወደኋላ አልመለስኩም ስምህን ብቻ እከተላለሁ አንተን መፍራትን እፈልጋለሁ ለባርያህ ይቅር በለኝ እኔን ለማሰናከል ብዙዎች ይፈታተኑኛል እኔን ከድክመትና ከፍርሐት አንፃኝ አለች።

አንቲጳስ አፎምያን የሚገድልበት ሌላም መንገድ ፈለገ ጥልቅ ጉድጓድ አስቆፈረና ውሃሞላው መርዛማ አውሬዎችንም ወደዚያው ከተቱበት አፎምያ ወደዚሁ ሊከቷት መዘጋጀታቸውን ስለተረዳች ሕሊናዋን በአሚነእግዚአብሔር አሸበረቀችው፣ መከንኑም እንዲህ ስትል ዘለፈችው "አንተ ሥጋህን የምታስደስት እየመሰለህ በሠይጣናዊ መንገድ ልጓም እንደሌለው ፈረስ ትፈነጫለህ በሰማያት መከራ ይጠብቅሃል ባየኸው ሐይለእግዚአብሔር ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆንክም እግዚአብሔርን የምትፈታተነው እስከመቼ ድረስ ነው ካንተ ወታደሮች ዕብደትህን ተረድተው ባንተ ትእዛዝ ሰማዕትነትን ተቀብሏል ክብርና ፀጋንም ከእግዚአብሔር ለመጎናፀፍ ችለዋል ከነሱ በተማርክ ነበር የክርስቶስን ተከታዮች ትሰድባለህ ሕይወት ሠጭውን እግዚአብሔር አስመረርከው" ይህን ብላ ስትጨርስ ፊቷን በትእምርተመስቀል አማተበችና ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲህ ስትል ጠራችው የኔ ብርሃን ክርስቶስ ሆይ ከዳንኤል ጋር ወደአዘቅት እንደገባህ ከኔ ጋርም ወደዚሁ ጉድጓድ ግባ። ከዮናስ ጋርም ወደ አሣ ነባሪ ሆድ እንደገባህ ከኔ ጋር ግባ። ይህን ብላ በገዛ ራስዋ ወደ ጉድጓዱ ውሃ ተወርውራ ገባች።



በጉድጓዱ ውስጥ የተሰበሰቡት መርዛሞች አውሬዎች ተሯርጠው ተቀበሏት፣ ውሃውንም እንዳይነካት እናት ልጅዋን ከአደጋ ለማትረፍ በጀርባዋ እንደምትሸከም በጀርባቸው ተሸክመው እሹሩሩ አሏት ይህን ያደረጉት በእግዚአብሔር ሐይል ተሸንፈው ነው።

አንቲጳስ በአፎምያ ላይ የሚገለፀውን ሐይለእግዚአብሔር አይቶ አማካሪውን አጵልያኖስ ይህ ነገር ምንድር ነው አፎምያን በመከራዋ ሁሉ የሚደርስላትና የሚረዳት ማነው ሲል ጠየቀው አጵልያኖስም "አጋንንት እየረዷት ነው እንዲህ የምትሆነው አለው አንቲጳስ ደግሞ አጋንንት ከረዷት አማልክቶቻችን ለምን አይበቀሏትም አለው አጵልያኖስ ከደግነታቸው ብዛት ታግሠዋታል አለው። አንቲጳስ በአጵልያኖስ ተመርቶ እንዲህ አለ ሥለት ያላቸው ድንጋዮችና ሥለት ያላቸው አስይፍቶች ሥለታቸውን ወደ ላይ በማድረግ በምድር ይረብረቡ በበላያቸውም አመድ ይሸፍኑዋቸው ከዚያ በላያቸው ላይ አፎምያ ትራመድ አለ እንዲሁም አደረገ።

አፎምያ ከሩቅ እየሮጠች ትመጣና ሠይፎቹና ሥለታም ድንጋዮች በአመድ ተሸፍነው ካሉበት ስትደርስ ተሰናክላ በመውደቅ መገለባበጥ እንዳለባት ተወሰነ ያን ሁሉ ፈተና ያለፈች አፎምያ የተዘጋጀውን ፈተና በአኮቴት ተቀበለችና ወደኋላ ሳትል ከዚያ ተሰናክላ እንድትወድቅ ወታደሮቹ እያሯሯጡ ሠይፎቹና ሥለታሞቹ ድንጋዮች ከተደበቁበት ቦታ አደረሷት አፎምያ በኢየሱስ ክርስቶስ ሐይል ምንም ሳትሠናከል በመጣችበት አኳኋን በሩጫ ያን ቦታ ተሻገረችው ያልገባቸው ወታደሮች ግን እሷን ተከትለው በአስይፍቱ ተቆራርጠው አለቁ ሞቱ። እሷ ግን ያ ሁሉ ሲሆን እንደበቷ ከእግዚአብሔር ምሥጋና አልተለየም ነበር።

አንቲጳስ መኮንን እንደገና ወደአደባባይ እንድትቀርብ



www.ethiopianorthodox.org

አደረገና "አፎምያ ሆይ አንቺ ደግ ሴት ነሽ አመጣጥሽም ከደጋግ ቤተሰቦች ነው ስሕተትሽ ትንሽ ነው እኔ ለንጉሥ አማልክት በንጉሥ ትእዛዝ ስሠግድ እኖራለሁ አንቺን በማዋረዴ ይቅር በይኝና በፈቃድሽ አሪስ ለተባለው አምላክ ሰዊ ሥግጅለትም ባለመስገድሽ ቤተሰቦችሽና ዘመዶችሽ ተዋርደዋል ከሕብረተሰብም ተለይተዋል" በማለት ሊያግባባት ጀመረ። አፎምያ ግን ፊትህ መራራ፣ እንደበትህ በአታላይነት የተሞላህ ነህ እኔስ ፈጣሬንና አምላክዮን አልተውም አላበድኩምና አለችው አንቲጳስ ሆይ አትሳሳት እኔን አሳምነህ ከእግዚአብሔር ለማራቅ የምትችልበት መሣርያም ሆነ አንደበት የለህም ይልቁንስ በኔ ላይ የምትወስደውን ርምጃ ቶሎ ውሰድ አለችው አንቲጳስ በዚህ ጊዜ እጅግ ተቆጣና አስደበደባት የሚደበድቡዋትም ለአማልክት ብትሠዊ እንተውሻለን ብትሠዊ ይሻልሻል ይሏት ነበር። እሷ ግን ድብደባውን በአኮቴትና በምስጋና ትቀበለው ነበር ጌታዮ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ነፍሴን ተቀበላት በማለት ከመፀለይ ጋር ጣአታትን ትዘልፍ ነበር።

አንቲጳስ መኮንንና አማካሪው አጵልያኖስ አፎምያ እንዳማትመለሰላቸውና ሥቃዮን ሁሉ እንደምትታገሠው አረጋገጡ በዚህ ጊዜ ወደእሳት ጋን አስወረወሯት ነገር ግን በእግዚአብሔር ሐይል እሳቱ ሳይነካት በሕይወት ተረፈች አሁንም እነአንቲጳስ እጅግ ተበሳጩና እሷን የሚገድሉበትን መንገድ ፈለጉና አንበሶችና ድቦች ካሉበት ወረወሯት እሷም እግዚአብሔር ሆይ ነፍሴን ተቀበላት ብላ ከፀለየች በኋላ ፊቷን አማትባ ከአውሬዎቹ ፊት ቆመች አውሬዎቹም እየመጡ የእግሯን ትቢያ ላሱ እንጂ ምንም አልነኩዋትም ነገር ግን ከአውሬዎቹ መካከል አንዷት መርዛም አውሬ መጥታ ነከሰቻትና ሞተች አስክሬንዋንም ከአውሬዎቹ ገቢ አውጥተው ጣሉት።



ፋሉፎሉስ የተባለው አባቷና እናቷ መጥተው ገንዘው ኬልቄዶን ከተባለው ከተማ መውጭያዎችባንዱ ቀበሯት፣ አብረዋት ክርስቶስን በማመን ሰማዕትነትን በመቀበል ብዙ መከራና ሥቃይ ሲቀበሉ የነበሩት አርባ ስምንት ሰማዕታትን ግን ሳይገድላቸው ዲዮቅልጢያኖስ ወደሚገኝበት ዲዮቅልጥያኖስ እንደፈለገ ይፈርድባቸው ዘንድ ላካቸው የያንዳንዳቸውንም ማንነት በጽሑፍ ገልፆላከለት በጉዞ ጊዜም በየመንገዱ እንዳይሞቱ የሚወስዱዋቸው ወታደሮች ጥንቃቄ እንዲያደርጉላቸው አዘዘ ንጉሡ ራሱ የወረርሽኝ በሽታ ይዞት በከባድ ሥቃይ ነበርና አፎምያ ሰማዕትነትን ተቀብላ ያረፈችት ወር ግንቦት ሲሆን ቀኑ ተለይቶ አልተገለፀም።

## ምዕራፍ ፱ የአርኖሶፈስ ዘቤጥሮስና እስኪርዮን ገድል

እነዚህ ሦስት ሰማዕታት ወታደሮች ሁኖው ዲዮስጳሌዎስ ለተባለው መኮንን በጥበቃ ስለተመደቡ በመኮንኑ ግቢ አብረው ይኖሩ ነበር በዚህ ሥራ እያሉ ግን ክርስቲያኖች ነበሩ። በፀሎትና በምሥጋና ከእግዚአብሔር ያላቸውን ግንኙነት ያጠናክሩ ነበር።

ጵሮጳሲጦስ የተባለው መኮንን መምለኬ ጣኦት ስለነበር እነሱንም ከአምልኮተእግዚአብሔር ለማፈናቀል ይጥር ጀመር ከእውነተኛው የጽድቅ መንገድ ርቀው ጣኦትን እንዲያመልኩ ለሱም እንዲሠግዱና መሠዋዕት እንዲያቀርቡ ብዙ አግባባቸው እነሱ በሱ አግባቢነት እንዳልተመለሱ ተረድቶ ዱክስ ወደተባለው መኮንን ላካቸው ዱክስ በጭካኔው የታወቀ አረመኔ ነበር። ብዙዎች ጓደኞቻቸው ወታደሮች መከራን በመፍራት ከደው እነአሪኖሶፈስ ብቻ ቀርተው ነበር /ሦስቱ/። ዱክስ ንጉሥ በግዛቱ ያለ ሁሉ ለአማልክት እንዲሰግዱ አውጅዋል። ለንጉሥ የማይገዛና የማይታዘዝ ሁሉ ነውረኛና ጥፋተኛ እንደሆነ አታውቁምን አላቸው /ዱክስ/



www.ethiopianorthodox.org

እነሱ እውነት ብለሃል ለንጉሥ የማይታዘዝ ጥፋተኛ ነው ስለዚህ ጥፋተኞች እንዳንሆን ለዘላዓለማዊው የሠማይና የምድር ንጉሥ እንሠግዳለን ለሱም እንሠዋለን በሱም እናምናለን አሉት።

ጵሮጰሲጦስ መኮንን የሦስቱን መልስ ሲሰማ ተናደደና መሪያቸው የሆነውን 3ኛው "ዘቤጥሮስ" የተባለውን ዘሉ አንገቱን አነቀው ግን ሁለተኛው መስተጋድል አርሶኖፊስ ጵሮጰሲጦስን ወንድሜን ለምን ታንቃለህ አለው። ጵሮጰሲጦስ ተደፈርኩ ብሎ እጅግ ተናደደና ባንድ ቤት አስገብተው እንዲያሥሩዋቸው አደረገ ለሁለት ቀንም እህል ውሃ እንዳይሰጣቸው ከለከለ ይህን ያደረገበት ምክንያት ተማርረው የሱን የክህደት መንገድ እንዲከተሉለት ስለ ፈለገ ነው ።

ከሁለት ቀን በኃላ ከቤት አስወጥቶ ወደራሱ አቀረባቸው በሽንገላ ቃልም ያግባባቸው ጀመር። መኮንኑ ዘቤጥሮስን ሲያንቅ አርሶኖፊስ ከሶስቱ አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ወንድሜን ለምን ታንቀዋለህ ብሎ ጵሮጰሲጦስን እንደገሠፀው ከላይ ገልፀናል። መኮንኑ ጵሮጰጢስ አቅርቦ ሲያግባባቸው አርሶኖፊስን አስቀድሞ "አንተ ገና ወጣት ነህ አባትህንም አታሳዝነው እኔንም ከሁለት ቀን በፊት ደብድበኸኛል እኔ ግን ይህን ሁሉ አልያዝኩብህም ምንም እንዳልበቀልህ ቃል እገባልሃለሁ ከፈለግህ አሁንም ደግመህ ደብድበኝ። ነገር ግን ለአማልክት ሥግድ" አለው።

ይህ ወጣት አርሶኖፊስ እምነቱን ጠብቆ ወደእግዚአብሔር ለመሄድ ቆርጦ ተነስቷል ስለዚህ ጵሮጰሲጦስን በከንቱ አትድከም ለሚያልፈው ዓለም አልንበረከክም ለርኩሳን አማልክትም አልሰግድም እኔ ከዚህ ርኩስ ዓለም ቶሎ ለመገላገል እፈልጋለሁ ከዚህ ዓለም ከሄድኩ ደግሞ ወደንጉሠሰማያት ወምድር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው



የምሄደው አለው። ጵሮጰሲጦስ በዚህ ጊዜ አባባሉን ሰምቶ እጅግ ተናደደ በሱ ላይ የሚያደርገውንም አጣ። ለጊዜው ከወጣቱ አርሶኒፊስ ጋር መነታረኩን አቁሞ ከሶስተኛው አስኪርዮን ጋር ይነጋገር ጀመር። እንዲህም አለው "አንተአስኪርዮን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለንጉሡ አምላክ ትሰዋ ነበር ያሳቱህና እንዳትሠግድ መሰዋዕትንም እንዳታቀርብ እነዚህ ሁለት መጥፎ ጓደኞችህ አሳብደውሃል አሁንም ለንጉሥ አምላክ መሥዋዕትን አቅርብ ስገድለትም" አለው። አስኪርዮን ግን ዉሸት አትናገር ለጣኦት የሠገድኩበትና መሥዋዕት ያቀረብኩበት ጊዜ የለኝም አሁንም ለጣኦት አልሠግድም ለእግዚአብሔር ብቻ እሰግዳለሁ ለሱም እገዛለሁ በማለት መለሰለት በዚህ ጊዜ ሦስቱ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ የምታደርገውን አድርግ እንጂ ከኢየሱስ ክርስቶስ መድሐኔዓለም በቀር ሌላ የምናመልከውና የምንሰግድለት አይኖረንም ሲሉ ባንድ ቃል ድምፃቸውን አሰሙት።

ጵሮጰሲጦስ መኮንን በትእዛዝ እጅ እግራቸውን አሳሠረ በያንገታቸውም ማነቆ ከተተና እኔ ይህን ሥልጣን እንዳለኝ ተመለከታችሁን? በጭካኔው ወደታወቀው መኮንን ዱክስ ብልካችሁ ከማለቅ በቀር ሌላ ዕድል አይጠብቃችሁም ይልቅስ ለሱ አሳልፌ ከመሥጠቴ በፊት አሁኑኑ ለአማልክት ሥግዱና ከእሥር ልፍታችሁ አላቸው እኛ ካንተ ርዳታ አንጠብቅም ረዳታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደእግዚአብሔር ብቻ ነው ለጣኦት እንሠግድም የምታደርገውን አድርግ አሉት።

ጵሮጰሲጦስ እንዳልተመለሱለት ስለተረዳ በወታደሮች አሳስሮ ወደዱክስ መኮንን ላካቸው። ዱክስ ካለበት ሊቆን ከሚባል አገር አደረሱዋቸው በዚያውም ከዚሁ መኮንን /ጵሮጰሲጦስ/ እንደነሱ



www.ethiopianorthodox.org

አለው። ጴጥሮስ ግን አሪኖሶፊስ ወንድሜና ከሱ በፊት ሌሎች ቅዱሳን የተቀበሉትን የሰማዕትነት መንገድ ብቻ እከተላለሁ ያንተን መንገድ አልከተልም አለው።

ዱክስ መኮንን ሌላ አማራጭ ሳይሞክር አሪኖሶፊስ በተሠቀለበት አኳኋን ራሱን ወደታች ዘቅዝቀው እንዲሰቅሉት አዘዘ። ነገር ግን ሕይወቱ ሳታልፍ ቶሎ አወረደውና ለመሞት መቅረጡና በትዕግሥት ኢየሱስ ክርስቶስን እያመሠገነና ነፍሱን ወደሱ እያማፀነ ስላየው እንደገና ጉድጓድ ቆፍረው ከዚያ እንዲከቱትና በላዩ ላይ ፈረሶች እንዲሄዱበት አደረገ ነገር ግን እግዚአብሔር ጠብቆት በዚሁ ሊሞት አልቻለም ከጉድጓድም አወጡት በዚህ ጊዜ ከሥቃይ ብዛት የተነሳ አካሉ በጣም ጠውልጎ ነበር መናገርም አቅቶት ነበር ሰውነትህ እስኪጠወልግና እስኪኀሰቁል ከምትሳሳት ለምን ለአማልክት አትሠግድም በማለት መኮንን ዱክስ ጠየቀው ጴጥሮስ ግን መናገር ስላቃተው ራሱን በመነቅነቅ እምቢ አለ።

መኮንን ዱክስ የሚፈፅምበትን ነገር ስላጣ እሥርቤት አስገብተው በረሀብ እንዲቀጡት እህል ውሃ እንዳይሠጡት አደረገ። ያለ እህልና ውሃ ለተወሰነ ጊዜ ካቆዩት በኃላ ለአማልክትሠዋና እህል ውሃ እንስጥህ አሉት ጴጥሮስ ግን በዚህ አልተመለሰላቸውም ከእሥር ቤቱ በማውጣትም ብዙ አንገላቱት /ገረፉት አካላቱን ቆረጡት ኀተቱት/ ለአማልክት እሰግዳለሁ እስኪል ድረስ በየሰዓቱ የምትችሉትን ቅጣት ሁሉ ፈፅሙበት በማለት ለወታደሮቹ አሳልፎ ሠጠው። እነሱም በየሰዓቱ እየተቀባበሉ ይህ ነው የማይባል መከራ በሱ ላይ አደረሱ።



ጴጥሮስ በዚሁ ሁሉ ፈተና እያለ መኮንን ዱክስ ሦስተኛውን ሲኬርዮንን ከታሠረበት አስመጥቶ በጓደኞችህ ላይ እየደረሰ ያለው ወራዳ መከራ እንዳይደርስብህ ከወዲሁ ራስህን እንድትጠብቅ ለማስጠንቀቅ ነው የጠራሁህ ስለዚህ ለአማልክት መሥዋዕት አቅርብና ነፃ ልልቀቅህ በክርብም እንድትኖር ላድርግ በማለት ያግባባው ጀመር አስኪሪዮን ግን ራሴን አውቃለሁ ራስህን የማታውቅና ለርኩሳን ጣኦታት ስትሠግድ የምትኖር አንተ ነህ አለው። ወድያው የመሰቀልንና የመገረፍን ሌሎችንም ፈተናዎች አደረሰበትና ዱክስ ድጋሚ ለጥያቄ አቅርቦ ቀድሞ ለአማልክት ትሠዋ እንደነበር ሰምቻለሁ አሁንም እንደቀድሞው መሥዋዕትን ለአማልክት ሠዋ አለው።

አስኪሪዮን ፍፁም ውሸት ነው ለጣኦት የሠገድኩበትና መሥዋዕት ያቀረብኩበት ጊዜ የለም ለጣኦት የምትሠዋና የምትሠግድ አንተነህ አለው በዚሁ መኮንን ዱክስ እጅግ ተበሳጨና በክፋታቸው ለታወቁ ምርጥ ወታደሮቹ አስረክቦ እንደምንም አሰቃይታችሁ ለጣኦት እንዲሠግድ ካለደረጋችሁእናንተን ነው የምገድለው በማለት አስጠነቀቃቸው።

ጨካኞቹ ወታደሮች ከመኮንኑ ዱክስ በተቀበሉት ከባድ መመሪያ መሠረት ከተማውን አዞሩት ለጣኦት እንዲሠግድም ብዙ አግባቡት ብዙም አጣደፉት እሱ ግን ንቅንቅ የሚል አልሆነው። በዚህ ጊዜ ወታደሮቹ ተቸገሩ የዱክስ ፍላጎት እንደምንም ተመልሶ ለጣኦት እንዲሠግድለት ነው ጨካኞቹ ወታደሮችም ከባድ ሥጋት አደረባቸው ብዙ አሠቃይተው ለጣኦት እንዲሠግድ እንዲያደርጉ እንጂ መኮንኑ ዱክስ ጥብቅ መመሪያ የሠጣቸው አሰቃይተው እንዲገድሉት አይደለም ስለዚህ አስኪርዮን በሚደርስበት ሥቃይ ለጣኦት ሳይሠግድ እንዳይሞትባቸው ሠጉ።



www.ethiopianorthodox.org

ሊጠይቁዋቸው የመጡትን ምዕመናን ጴጥሮስ ዛሬ ያርፋል ሁላችንም ለሞት በሚያበቃ አኳኋን እንገኛለን ስለዚህ ከኛ ብዙ አትራቁ አላቸው ምዕመናኑም እሺ ብለው በመጠባበቅ ላይ እያሉ ጴጥሮስ ዓረፈ። ጴጥሮስ በግንድ ተጣብቆ በረሐብና በጥማትም ሕይወቱ እንዳለፈች ተመልከተው የመኮንኑ ወታደሮች የጴጥሮስን አስከሬን አውጥተው እንደገና ዘጉት ጴጥሮስን ደግሞ ምእመናኑ ወስደው በክብር ቀበሩት።

ሼልጥዮስን ቀድሞ የሚያውቀው ጓደኛው አስቴንው የሚባል ሊጠይቀው መጥቶ በመስኮትአቀርቅሮ ተመለከተውና ሼልጥዮስ ወንድሜ ሆይ ወደኋላ እንዳትል ፅና ያንተው ዕድል ከቅዱሳን ሰማዕታት ዕድል ነው በርታ ይህን ደካማ ዓላም አሸንፈኸዋል ሲል ሼልጥዮስም እኔ ምንም ሐይል የለኝም በእግዚአብሔር ሐይል ግን ሁሉን አሸንፋለሁ ሲል መለሰለትና ድሮ የሚያውቃቸውን ወገኖቹን ስምስማቸውን እየጠቀሰ ሰላምታ እንዲያቀርብለት አደራ አለው።

ቀጥሉ የአስክሪዮን እህቶች መጡ በመዝገያው ፊት ለፊትም ቆሙና ወንድማችን አስክርዮን ሆይ ከተለየኸን አምስት ዓመት ሆነ አንተ እህቶችን እጅግ የምትወድ አልነበርክም ወይ ፊትህን እንድናይ እንወዳለን ወታደሮቹን ካንተ ጋር ለመገናኘት እንዲፈቅዱልን ለምነናቸው ፈቅደውልናል እባክህ ውጣና እንይህ በልቅሶና በሐዘን ተውጠን እያለ ሳናይህ እንዳንቀር ባክህ ናልን ያንተን የወንድማችንን ፊት ለማየት ብንበቃ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሐጢአት አይቆጠርም እያሉ ለመኑት።

ቅዱሳኑ የታሠሩበትን ቤት የሚጠብቀው ዘበኛም ውጣና እህቶችህን አነጋግራቸው ለምን ይህን ያህል እየጮኹ ዝም ትላቸ ዋለህ አለው። አስክርዮን ከተቻለህስ ፍቀድላቸውና ወደኔ ይምጡ



አለው ነገር ግን ወታደሩ አልፈቅድም አለው እኔማ ከግንዱ ጋር ስለታሠርኩ ወጥቼ ላያቸው አልችልም ጉልቤቴም እጅግ ደክሟል አለው እህቶቹም ድምፁን ብቻ በመስማት ፊቱን ሳያዩት እያለቀሱ ሄዱ።

አርሴንስ የተባለው ዲያቆን በመስኮት ሰላም አላቸውና አርሴንስ ከነአርሲኒዮስ ጋር ሰማዕትነትን ተቀብሉ በከባድ ሕመም የሚቸነው አርጌንስ ወንድም ነው እነአስኪርዮን አርሴንስ ሰማዕትነቱን ፈፅሞ ሊሞት ሊየተቃረበ ነውና አስከሬኑን ወደትውልድ አገሩ ለመውሰድ እንድትዘጋጅ አደራ አሉት። አርጌንስ ራሱም ከግንድ ጋር ተጣብቆ ከታሠረበት ሁኖ እንደነአሰኪርዮን እህልውሃ ተከለክሎ ለብዙ ቀናት ስለቆየ እጅግ አካላቱ ተዳክሞ እያለ ወንድሜ አርሴንስ መሆንህን ተረዳሁ ሞቴ ስለተቃራበ አስከሬኔን ወዳገሬ ወስደህ እንድትቀብር አደራ አለው።

ሼልፒስ የአርጌንስን ወንድም አርሴንስን ወንድምህን አርጌንስ ወዳገሩ ወስደህ ከቀበርከው ክርስቲያኖች በሱ ሰማዕትነት ብዙ ትምህርትን ያገኛሉ። በዚህም በጎ ሥራህ እግዚአብሔር ዋጋህን ይከፍልሃል አለው። ወድያው ሰማዕቱ አርጌንስ አብረውት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲሉ በመከራ ላይ የሚገኙትን ጥቂት ውሃ አግንቼ ጉሮሮዮን ባርሰው ኑሮ ከወንድሜ አርሴንስ ዲያቆን ጋር ጥቂትመናገር በቻልኩ ነበር አላቸው እነሱም መኮንኑ የቀጣን ውሃ ንና እህልንም በመከልከል ስለሆነ ውሃ አናገኝልህም አለው በዚህ ጊዜ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠማሁ እያለ መልእልተመስቀል ሙቷል እኔስ ይህንን እንዴት አላስብም በማለት ራሱን ወቀሰ ወንድሙ አርሴንስም ወንድሜ አርጌንስ ሆይ ይህን ዓለም አሸንፈህ የመንግሥተሰማያትን አክሊል ለመቀዳጀት ጥቂት ነው የቀረህውሃ ጥሙንም ታገሠው እያለ ያበረታታው ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

አጣብቀው አሥረውናል ግን ያ ሁሉ መከራ ሲደርስብኝ የኢየሱስ ክርስቶስን መከራ ከማስታወስ ችላ አላልኩም ይህ ሁሉ መከራ ተደራርቦብኝ እያለ አንደበቴ ሳይዘጋ ምላሴ ሳይደርቅ ካንቺ ጋር ቃል በቃል ለመናገር በመቻሌ እግዚአብሔር ሐይልና ፅናት እንደሠጠኝ ምሥክር ነው መንፈስ ቅዱስ ለዚህ ታላቅ ፀጋ አበቃኝ ካሁን በኋላ ዓለም አይረግጠኝም የሕይወትን መንገድ ተከትዩ ጉዞዩን ቀጥያለሁ እናተ ሆይ አንቺም የኔን የልጅሽን መንገድ እንድትከተይ እለምንሻለሁ" አላት።

ቬልፊዮስ ከናቱ ጋር ቀሳውስትና ዲያቆናት ሊጠይቁት መጥተው ነበርና እናቱን የህይወትን መንገድ እንዲያስተምሯት አደራ ብሎ ተሰናበታቸውና ወደታሠረበት ተመለሰ ከዲያቆናቱ አንዱ ወደመስኮቱ ጠጋ ብሎ የታሠሩትን ክርስቲያኖች እንደምን አደራችሁ ካላቸው በኋላ ደስ ይባላችሁ ምንጊዜም ስለክርስቶስ ብላችሁ መከራን በመቀበል የምትገኙ ቅዱሳን መስተጋድላን ሆይ በረከታችሁ ለሁላችን ይድረስ አላቸው እነሱም ሌት ተቀን በጨለማ ታሥረው ለብዙ ቀናት ከመቆየታቸው የተነሳ ዕለቱን ለማስታወስ ስላልቻሉ ዛሬ ዕለቱ ምንድን ነው ቀኑስ ስንት ቀን ነው ብለው ጠየቁት ዲያቆኑም ቀኑና ወራቱን ለይቶ ነገራቸው።

ቬልፍዮስ በዚህ ጊዜ ዲያቆኑን እንዲህ አለው ሕያው እግዚአብሔር አሁንስ መከራው ይብቃችሁ እያለን ነው እየጎበኘንም ነው አስኬርዮን ነፍሱ ከሥጋው ልትለይ ነው ነፍሱን ለፈጣሪው ሊያስረክብ ተዘጋጅቷል በዛሬው ዕለት ይርፋል አለው ወድያውም አስኪርዮን ገድሉን ፈፅሞ አረፈ ሌሎች ምእመናን በየጊዜው እየተመላለሱ ይጎበኙዋቸው ነበር በዚሁ ዕለትም በረከታቸውን ለመቀበል ቅዱሳን ምዕመናን ወደነሱ መጡ ቤልፊዮስም ወድያው አረፈ ቅዱሳን ምዕመናን የሁለቱንም አስከሬን ወስደው ቀበሩ።

## ምዕራፍ ፲፩ የአትናቴዎስ ዘቁዝም ሰማዕትነት

ቅዱስ አትናቴዎስ በመክስምያኖስና በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ነው ሰማዕትነቱን የተቀበለው አትናቴዎስ ከነገሥታት ቤተሰቦች ነው ትውልዱ። ስለዚህ በቤተመንግሥት የክብር ቤት ነበረው በጦርነት ጊዜም በአርበኝነቱ የታወቀ ነበር ከተራ ቤተሰብ የተወለዱ ሁለት የቅርብ ወዳጆች ነበሩት ስማቸው ሠርጌስና በኮስ ይባላል እነዚህ ሰዎች "ፃፋ" በምትባል አገር ስለኢየሱስ ክርስቶስ እየመሠከሩ ሰማዕትነትን ተቀበሉ።

የሁለቱን ሰዎች በሰማዕትነት መሞት ተከትሎ ነገር እንዳይቀ ሰቀስበት በመስጋት ቤተክርስቲያን የተባለ ሁሉ በያለበት እንዲዘጋ መክስሞያኖስ አዘዘ መክስሞያኖስ አትናቴዎስ ዘቁዝምን እጅግ እንደሚወደውና ፈቃዱንም እንደሚፈፅምለት ይገምት ነበር። በዚህ ምክንያት የግብፅ አገረገዢ አድርጎ ብዙ ወታደሮችም እንዲከተሉት በማድረግ ላከው ብዙ የጦር መሣርያንም አሥታጠቀው።

ወደግብፅ ከመሄዱ በፊት ግን ሁለቱን ወዳጆቹ ሠርጌስንና ባኮስን በድብቅ የናንተን ዓላማ እንጂ ክርስቲያኖች እያሳደደ አብያተክርስቲያናትን በመዝጋት ያለው ንጉሥ ዓለማ ከዛሬ ጀምሮ አልከተልም እግዚአብሔር እንዲረዳኝ እናንተም ፀልዩልኝ አላቸው። አትናቴዎስ ይህን ተናግሮ ከመክስምያኖስ በታዘዘው መሠረት ወደእስክንድርያ ሄደ። እንደደረሰም ከቅዱስ ጴጥሮስ ተፍፃሜተ ሰማዕት ጋር ተገናኘ ከሱም ፀሎተ ኩራኬ ተቀበለ። በዚህ ጊዜ አትናቴዎስ እጅግ ተደሰተ።

የእስክንድርያ ክርስቲያን እነሱን እንዲፈጅ **ወይም** ደግሞ እያስገደደ ለመክሰምያኖስና ለዲዮቅልጥያኖስ ጣኦታት እንዲሰግዱ



www.ethiopianorthodox.org

እንዲያደርግ መምጣቱ ተነግሮአቸው ስለነበር ተጨንቀው ነበር ነገር ግን ከተፍፃሜተሰማዕቱ ቅዱስጴጥሮስ የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት ጋር ተገናኝቶ ለኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት መዘጋጀቱን መግለፁ ሲሰሙ እጅግ ተደሰቱ ከመክስምያኖስ የተሠጠውን ክርስቲያኖችን የማሳደድ ሥልጣኑ ትቶ ራሱ ከክርስቲያኖቹ ጋር ስለተሰለፈ የንጉሡ መክስምያኖስ አረሜናዊ ተግባር ለጊዜው በምድረግብፅ ጋብ ብሎ ታየ።

አትናቴዎስ ከመክስምያኖስ የተሠጠው ሥልጣን ለጊዜው ተጠቀመበት፣ አብያተጣኦትን ከመክፈት ይልቅ በያሉበት አዘግቶ በምትካቸው አብያተክርስቲያናትን ሠራ። በእስክንድርያና አካባቢዋ የነበሩ ጣኦታትን በሙሉ አዘግቶ በምትካቸውም አብያተ ክርስቲያኖትን አሠርቶ ሲያበቃ እንደገና ወደ ለእላይ ግብፅና ታሕታይ ግብፅ ዘመቻውን ቀጠለ ተዘግተው የነበሩትን አብያተክርስቲያናት በሙሉ አስከፈተ ክርስቲያኖች የመኖር መብታቸውን እንዲያገኙ አደረገ በአረማውያን እጅ ላይ ወድቀው የቆዩትንም ቅዱሳት መካናት ለክርስቲያኖች መለሰ።

የአትናቴዎስ ክርስቲያንነት ያስቀናቸው አረማውያን "አማልክት እንዲሰገዱና እንዲመለኩ፣አብያተክርስቲያናት እንዲዘጉ ያደርግ ዘንድ ካንተ የተላከው አትናቴዎስ አቅጣጫውን ለውጦ አማልክትን አስወግዶአቸዋል የተዘጉትን አብያተክርስቲያናት ከማስከፈቱም በላይ ድሮ ያልነበሩትን አብያተክርስቲያናት በማሠራት ላይ ነው በሱ ድጋፍ ያለምንም ቁጥጥር ክርስቲያኖች ሕዝቡን ወደነሱ እምነት በማስገባት አገሩን ወረሩት አትናቴዎስ ያንተን ትእዛዝ ከዷል" የሚል ደብዳቤ ለንጉሥ መክስምያኖስ ላኩለት የነሱን ደብዳቤ ተቀብሉ መክስምያኖስ አነበበውና ዱብዕዳ ሆነበት የመንግሥቱን ባለሥልጣኖች በሙሉ ሰብስቦ ይህ ነገር እውነት ነው ብላችሁ ትቀበሉት አላችሁእኔ በበኩሌ አትናቴዎስ ክርስቲያን ይሆናል ብዬ አልጠረጥርም እሱ እኔን ከሁሉ አብል ይወደኛል በቅንነትም ይታዘዘኛል እሱ አማልክትን እንደሚጠላቸው ባውቅ ኑሮ ባልሾምኩትም ነበር ወደግብፅም ባልላኩት ነበር አላቸው።

መኳንንቱና መሳፍንቱ ከንጉሣቸው መክስምያኖስ የተነገራቸውን ሲሠሙ ንጉሥ ሆይ አትቆጣ ብስጭትም አይደርብህ በደብዳቤ ብቻ የሚመጣ መልእክት ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ አይደለም ሰዎችን ላክና ሁኔታውን አረጋግጠው ይመለሱ አሉት። ንጉሡ መክስምያኖስም የመኳንንቱን ምክር በመቀበል መክስምያኖስ ለዘለዓለም አሸናፊ ነው ለአሸናፊዎች አማልክት ሰው ሁሉ እንዲሠግድላቸውና እንዲያመልካቸው ንጉሥ አዟል አትናቴዎስ በክርስቶስ እንደሚያምንና ለሱም እንደሚሰግድ ሰማሁ ስለዚህ ከስህተቱ ከተመለሰ በኔ ዘንድ ከፍተኛ ልዕልናን ያገኛል ሥልጣኑም ከፍ ይልለታል እምቢ ካለ ግን ትልቅ ቅጣት ይጠብቀዋል ሕይወቱም ከዚህ ዓለም ይወገዳል በወራዳ አኳኋን ይገደላል የሚል ፁሑፍ በማስያዝ አንትያቶስ የተባለውን መልእክተኛውን ወደእስክንድርያ ላከ አንትያቶስ ከመስክምያኖስ መኳንንት አንዱ ነው።

አንትያቶስ ብዙ ሠራዊት አስከትሉ ነው ወደ እስክንድርያ የተላከው አንትያቶስ ግብፅ ከደረሰ በኋላ አትናቴዎስን አስጠራው እሱም ወደሱ መጣ። በዚህ ጊዜ ከመክስምያኖስ ወደሱ የተላከውን ደብዳቤ አነበበለት በቃልም "ወንድሜ ሆይ ህጋችንን ለምን ተውክ የአማልክትን ፍቅርስ ከልቡናህ እንዴት አወጣህ እንዴትስ ክርስቲያን ሆንክ ልእልናህንና ግርማህንስ ለምን አጠፋህ" አለው።

ቅዱስ አትናቴዎስ "ላንተም ለኔም የተሠጠን ግርማና

www.ethiopianorthodox.org

ልዕልና በዚህ ዓለም ለጥቂት ጊዜ ታይቶ ይጠፋል" በማለት መልስ ሠጠው አንቲያቶስ የአትናቴዎስን አባባል ሰማና ወንድሜ ሆይ የምትናገረውን ሁሉ ወደጎን ተውና ይልቁንስ ተነሰ እንሂድና "ቁልዝም" በተባለው ባህር ደሴት ያሉትን አብያተክርስቲያት እንዝጋቸው ለአማልክትም እንገዛ ንጉሡም በዚሁ ደስ ይበለውና ከፍተኛ ሥልጣን ይስጥህ እጅግም ይውደድህ አለው።

ቅዱስ አትናቴዎስ ለዚሁ የሠጠው መልስ "ለመሄዱ ያንተን ትእዛዝ አክብሬ ወደደሴተ ቁልዝም ካንተ ጋር እሄዳለሁ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የማምነው የማመልከውም እሱን ብቻ ነው ስለዚህ በቁልዝም ባህር ደሴት የማመልከው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕትነቴን እንዲፈፅምልኝ እለምነዋለሁ" የሚል ነበር። ከዚህ በኋላ ቅዱስ አትናቴዎስና መኮንኑ አንትያቶስ ተያይዘው ወደ ቁልዝም ባሕር ደሴት ሄዱ።

አትናቴዎስ ከደሴቱ ውስጥ ከሚገኘው አንድ ቤተክርስቲያን ቅጽር ቁሞ እያለቀሰ እንዲህ ሲል ፀለየ ጌታዬ አምላኬ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ በብርሃን ውስጥ የምታድር ለጥበብህ ሥፍር ቁጥር የሌለው የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠርከ ሁሉ ባንተ ፊት ኢምንት ነው ሁሉ ካንተ ፊት ይንቀጠቀጣል ያመሰግንህማል ከማርያምና ከመንፈስ ቅዱስ የተመሰገንህ አንተነህ የእሥራኤልን ልጆች ባህርን ያሻገርከ አንተነህ ነፍሴን ትምራት ዘንድ እለምናሃለሁ ሐጢአቴንና በደሌን አስተሥርይልኝ ሰማዕትነቴን በዚሁ ቦታ ፈፅምልኝ የቤተክርስቲያንን ልጆችምበቀናች ሃይማኖት አፅናቸው።

ፀሎቱን ጨርሶ ወደቤተክርስቲያን ገባ በቅጽረቤተክርስቲያኑም ማሕበረምእመናን ተሰብስበው አገኛቸው ዕለቱም በዓለ ልደት ስለነበር ሕዝበክርስቲያኑ የበዓሉን ስብሐተእግዚአብሔር በማድረስ ላይ ነበሩ። ቅዱስ አትናቴዎስ በስብሐተእግዚአብሔር ተጠምደው ሲያያቸው እጅግ ተደሰተ። ክርስቲያኖቹ ገና ምድረግብፅን ከተረገጠ ጀምሮ በሃይማኖተ ክርስቶስ የፀና መሆኑን ሰምተው ሰለነበር ሊያዩት እጅግ ይጓጉ ነበርና።

አንትያቶስ መኮንን ውጭ ቁሞ ይጠብቀው ስለነበር ከክርስቲያኖቹ ጋር ተገናኝቶ በመንፈሳዊ ሰላምታ መታየቱ እጅግ ስላሳሰበው አስጠርቶ ካመጣው በኋላ አትናቴዎስ ሆይ ክብርህን ብትጠብቅ ይሻለሃል የሰው መሳለቂያና መዘባበቻ ልትሆን ትፈልጋለህን ባክህ ተው አለው አትናቴዎስ በበኩሉ "እኔ ከጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር አልመለስም አማልክትን አላመልክም ለአጋንንትም መሥዋዕትን አላቀርብም ስለዚህም የአለምን ክብር ትቻለሁ ሐላፊ ነውና እኔ ዘለዓለማዊውን ሕይወት እንድወርስ እፈልጋለሁ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ካለበት የምገባው በዚህ ዓለም እሱን አገልግዬ ነው እንዲያውም እኔ አንተንም ወደዘለዓለማዊው አምላክ ለማስገባት እወዳለሁ ለመንግሥቱ ማለቂያ ለሌለው አምላክ የተገዛና በሱም ያመነ ሁሉ ዘላዓለማዊ ሕይወትን ያገኛል" አለው።

መኮንን አንትያቶስ ደግሞ ደጋግሞ ክርስቲያንነቱን እንዲያቆም ለመነው ና እምቢ ካልክ ግን ንጉሡ ባንተ ላይ እንድፈፅመው ያዘዘኝን ቅጣት ሁሉ እፈፅምሃለሁ አለው። ቅዱስ አትናቴዎስ እኔ ከፍቅረእግዚአብሔር ወጥቼ ለአማልክት እንደማልሠግድ ለአጋንንት መሥዋዕት እንደማላቀርብ ብዙ ጊዜ መልሼ መላልሼ ነገርኩህ ንጉሣችሁ መክስምያኖስ ራሱ አሳሳችና ከሐዲ ነው ስለዚህ ለሱ አልታዘዝም ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እታዘዛለሁ ሕይወቴንም ለሱ መሥዋዕት አቀርባለሁ ስለሰሙም እሞታለሁ እሱ ስለኛ ሙቷልና አለው።

መኮንኑ አንትያቶስ ቁጣን በተላበሰ አነጋገር አንተ



www.ethiopianorthodox.org

የምትሠቃይበትን ዝግጅት ጨርሻለሁ በዛሬው እለት ለአማልክት መሥዋዕት ማቅረብና ለነሱም መስገድ አለብህ ካልሆነ ግን የተዘጋጀብህን መከራ ለመቀበል ተዘጋጅ አለው አትናቴዎስ የዘለዓለም ኩነኔን እንጂ ያንተን ኩነኔ አልፈራውም የፈለግኸውን አድርግ አለው መኮንኑ ከቁጣው መለስ ብሎ አትናቴዎስ አባቶቻችን ምን ያህል እንደሚያከብሩህ አታስታውስም አሁንም ባክህ ተመለስ የተከተልከው ምክር ትክክል አይደለም በገዛ ራስህ በሕይወትህ አትፍረድ አለው። አትናቴዎስ መለሰና መጽሐፍ እግዚአብሔርን በፍፁም ልብህ በሀሣብህ ሁሉ እና በፍፁም ነፍስህ እግዚአብሔርን ውደደው እንዳለ አልሰማህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም አባትና እናቱ እህቱና ወንድሙን ከኔ አብልጦ የሚወድ የኔ አይደለም እንዳለ አልሰማህም አለው። መኮንኑ አምላክህ ማነው አለው አትናቴዎስ ሲመልስ "የኔ አምላክሰማይንና ምድርን ከሷም ውስጥ ያለውን ሁሉ የፈጠረውን እኛንም የፈጠረ እኔም ስለሱ የምሞትለትን ነው የማመልከው አለው።

መኮንኑን ተከትለው የመጡ ያገር ሽማግሌዎች ከዚያ ነበሩና ይህንን የመሰለ የድፍረት ቃል ለመኮንኑ ልትመልስ አይገባህም ይልቁንስ የሱን መልካም ምክር ተቀበልና የሚጠብቅህን ክብርና ልዕልና ከሱ ዘንድ ለመቀዳጀት ታደል ንጉሥና አማልክትም ሊወዱህ ይችላሉ አሉት አትናቴዎስ ግን ያለምንም ፍርሐት እግዚአብሔርን ስላላሰበውና ልቡናውም ስለታወረ በዚሁም ያባቱን ሠይጣን ፈቃድ ለመፈፀም ስለተነሳ መልስ እሠጣዋለሁ አላፍረውም አላቸው። መኮንኑ በዚህ ጊዜ ይህ ሰው በኔ ላይ ብዙ ጊዜ ተሳለቀ ብዙ ዘበተብኝ እኔ ግን ከትህትና አነጋገርናክብር መስጠት አልፌ በሱ ላይ ያደረግሁት ነገር የለኝም ካለ በኃላ እስካሁን ድረስ ብዙ ታግሼህ አለሁ አሁንም ለአማልክት እንድትሠዋ



አዝሃለሁ በማለት የንዴት ቃል ሠነዘረበት።

ቅዱስ አትናቴዎስ "ለምን ትሳሳታለህ የአምላኬን ፍቅር ትቼ የምመለስና አጋንንትን የምከተል ይመስለሃልን ዘለዓለማዊውን ደስታ ትቼ ከእግዚአብሔር ዘንድ በታላቅ ተስፋ የምጠባበቀውን ዘለዓለማዊ ሕይወት ትቼ ከኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ወጥቼ ካንተ ጋር የምሰለፍ ይመስልሃለን" ሲል መለሰለት።

መኮንን አንቲያቶስ ግን ለዚሁ አባባሉ የሠጠው መልስ እኔ የነበረህን ክብርና ልዕልና ንጉሡም ከሁሉ አብልጦ እንደሚወድህ ስለማውቅ መጥፎ ቃልን አልመልስልህም የሚል ነበር። ቅዱስ አትናቴዎስ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ለዚች አለም ጥበብ እግዚአብሔር አሳበዳት ብሏል ዳግመኛም የጠቢባንን ጥበብ አጠፋዋለሁ ብሏል አለው። መኮንኑ በመጽሐፋችሁ የቄሣርን ለቄሣር ሥጡ የእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ሥጡ የሚል ፅሑፍ ተፅፎ የለም ወይ አለው። አትናቴዎስ መልካምአልክ ነገር ግን ይህ ቃል የተነገረው ስለትዕግሥቱ ስለየዋህነቱ ነው አለ መኮንኑ እስከመቼ ድረስ ነው የምታገሥህ በል ተነሳና መሥዋዕት ለአማልክት ሰዋ አለው አትናቴዎስም እንዲህ ሲል መለሰለት "እኔ እግዚአብሔርን ብቻ እፈራለሁ ስለዚህ ለአማልክት አልሠዋም ዘለዓለማዊው ኩነኔ ያስፈራኛል ያንተ ኩነኔ ግን ያልፋል" አለው። እንደገና መኮንኑእኔ ላደርስብህ የምችለውን ቅጣት አትፈራም ሲለው ጌታዬና መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሯቸው ሥጋንና ነፍስን የሚገድሉትን ፍሩ እንጂ ብሏል ድጋሜም የሞቴን መስቀል ያልተሸከመ ሊያገለግለኝ አይችልም ብሏል ስለዚህ ከዚህ ውጭ የሆነውን ሁሉ አልፈራውም አለው።



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ አትናቴዎስ ሲመለስለት እንዳልቻለ ከልቡ ስለተረዳ ሠይፍ አምጡና አንገቱን ቆረጡት አለ። ቅዱስ አትናቴዎስ ግን ሠይፍ እስኪያመጡ ድረስ ዓይኖቹን ወደሰማይ በማንሳት" በትዕግሥት እግዚአብሔርን ደጅ ፀናሁት እሱም ሰማኝ ፊቱንም መለሰልኝ ጌታዩና አምላኬ ሆይ አመሠግናለሁ ለሰማዕታትነት አዘጋጅ ተኸኛልና ጠላትን በሰውና በመላእክት ፊት አሸነፍኩት እለምንሃለሁ እማልድሀማለሁ ነፍሴን ከቅዱሳን ጋር ታሣርፋት ዘንድ ከትንሽነቴ አንሰቶ እስካሁን ድረስ ከክፉ ነገር ጠብቀህ አቆይተኸኛል ለዓለም ሁሉ ሰላምህን ሥጥ ድህነትንና ፅናትንም ሥጥ ስደትንና ምንዳቤን ከቤተክርስቲያንህ አስወግድ በመንግሥተሮም ውስጥ የሚገኙትንም ክርስቲያን መንግሥታቸውን አፅና አንተ እግዚአብሔር ሆይ ሕዝበክርስቲያንን አፅናቸው ክፋትንም ሁሉ ከላያቸው ላይ አስወግድ ልጆቻቸውንም ባርክ ስምህን ያመሰግኑ ዘንድ እያለ ፀለየ።

ፀሎቱን እንደጨረሰ ወደምድር ተንበረከከ ወዲያውም በሰይፍ አንገቱን ቆረጡት ነፍሱንም በእግዚአብሔር እጅ ሠጥቶ ሐምሌ ፳ ቀን ዓረፈ። የቁልዝ ምእመናንም መኮንኑን ለምነው አስከሬኑን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም በታነፀው ቤተክርስቲያን በክብር አኖሩት ይህች ቤተክርስቲያን በሀገረቁልዝ የምትገኝ ናት ካህናትና ምእመናንንም ተሰብስበው በዚሁ ሰማዕት አማካይነት ታላቅ መንፈሳዊ በዓል አደረጉለት።

## ምዕራፍ ፲፪ የአባ ኖብ ሰማዕት ታሪክ

ዲዮቅልጥያኖስ ከሮም እስከግብፅ ድረስ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ሲያነሳ የተገኘ ሁሉ በተገኘበት እንዲገደል ሠራዊቶቹን አዘመተ። በያገሩ የበተናቸውንም ጣኦታት በቁጥር 70 ሲሆኑ 35 በወንድ



ስምና በሴት ስም የሚጠሩ ነበሩ ከነሱ ውስጥም የሁሉ የበላይነት የነበራቸው ሲውስ፣ አጵሉንና አርጳሜስ የሚባሉ ጣኦታት ነበሩ ብዙዎች ክርስቲያን የነበሩ ሰዎች መከራን በመፍራት እግዚአብሔርን ተው ለነዚህም ጣኦታት ሠገዱ መሥዋእትንም አቀረቡላቸው ብዙዎች ደግሞ እግዚአብሔርን አንተውም ብለው ተሠደዱ፣ ታሠሩ ተገደሉም።

በሕዝቦች መካከል ከባድ መለያየትን ተፈጠረ አባት ልጁን ልጅ አባቱን ወንድም ወንድሙን ሚስት ባልዋን ባል ሚስቱን ወዳጅ ወዳጁን አሳልፎ ለሞት እስከመሥጠት ድረስ በብዙዎች መካከል ብላ ተባላ የመሆን ጊዜ ተፈጥሮ ነበር ከዚህም በተነሳ ምክንያት የእግዚአብሔርን ስም ማንሳት በብዙ ቦታዎች ተከልክሉ ነበር። እኔ ክርስቲያን ነኝ ብሎ መናገርም ጨርሶ የቀረባቸው አካባቢዎች ነበሩ።

ከሐዲው ንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ወደክህደት እንደገባ መጀመሪያ አንፆኪያ ቀጥሎ አርማንያ ከዚያም ወደተለያዩ አገሮች እየዞረ አሰሳ ያካሄድ ነበር በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የተለያዩ ባለሥልጣኖቹን ልኮ ክርስቲያኖችን እያሰሱ እንዲያጠፉ አሠራጭቶ ነበር ይህንን ተልእኮ ለማከናወን አውህያስና ቅብርያል የተባሉ እንደራሴዎቹ አትሪብ ወደተባለው አገር ላካቸው። ከዚህችው አገር የተገኙ ክርስቲያን በሁለቱ የንጉሡ እንደራሴዎች እየታደኑ እስርቤት ገቡ ከክርስቲያኖቹ መካከል ሰርጊዮስ የሚባል አንድ የ20 ዓመት ወጣት ነበር። ሰርጊዮስ እየደጋገመ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ስላነሳ መከራውን በግንባር ቀደም ተቀባይ ሆነ ከሱ ጋርም ሌሎች አስራ አራት ክርስቲያኖች የመከራው ተሳታፊዎች ነበሩ።

የዲዮቅልጢያኖስ እንደራሴዎች ያሠሩዋቸውን ክርስቲያን ከጭንቀትና መከራ ብዛት የተነሳበኢየሱስ ክርስቶስ ማመናቸውን



www.ethiopianorthodox.org

ለማስተው ከየታሠሩበት ያወጡና ገርፈውና ሌላም ፈተና ፈፅመው መልሰው ያሥሩዋቸው ነበር አትሪብ በተባለችው አገር በየቦታው ስምንት መቶ ሃምሳ ክርስቲያኖች ታሥረው ነበር። እነዚህን ሁሉ ገራፊዎች ተመድበውባቸው ከየታሠሩበት በማውጣት የተለያዩ ሥቃያት ያደርሱባቸውና መልሰው ያሥሩዋቸው ነበር፣ ይህ ሁሉ ድርጊት ከሥቃይ ብዛት ኢየሱስ ክርስቶስን ክደው ለጣኦት እንዲሠግዱ ለማድረግ ነው።

በሀገረአትሪብ መቃራ የሚባል ሰውና ማርያም የምትባል ሚስቱ ደጋግ ሰዎች ነበሩ ሁለቱባልና ሚስት በቅድስና የተጠመዱ ነበሩ የነበሩበት ቦታ ልዩ መጠሪያ ነሒሳ ይባላል። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ እንደተከተሉ ይህን ዓለም በሰላም ተገላገሉት።

እነዚህ ደጋግ ሰዎች አንድ ልጅ ብቻ ነበራቸው ስሙም አባኖብ ይባላል። /አባኖብ በመባል ይታወቃል/ አባኖብ አባት እናቱ ሲሞቱ ገና የ12 ዓመት ልጅ ስለነበር በወላጆቹ ሞት እጅግ ሐዘን ተሰማው ሌት ተቀን ያለቅስ ነበር። አባኖብ ማለት ትርጉሙ ወርቅ ማለት ነው። ይህ ሕፃን በቤተክርስቲያን አካባቢ ትምህርተክርስቲያን ተምሮዋል ደጋጎች አባት እናቱም በመልካም ክርስቲያናዊ ስነምግባር አሳድገውታል አባኖብ ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል በቀረበ ጊዜ ቀዳሹ ካህን ለምዕመናኑ የእግዚአብሔር መንግሥት ተቃዋሚዎች ተነስቷል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳናመልክና ሥጋወደሙንም እንዳንቀበል ሠይጣን በሰዎች አድሮ ሊፈታተነን ተነስቷል ምእመናን ወንድሞቼና እህቶቼ ሆይ እንዳትሳሳቱ ተጠንቀቁ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከመናገር ወደኋላ እንዳትሉ የዚህን ዓለም መከራ በአኮቴት እንቀበለው የገሃነመእሳት ራት እንዳንሆን የዚህ ሐላፊ ዓለም ከንቱ ውዳሴ እንዳያታልለን



በዚህ ዓለም እሳት መቃጠልን አንፍራ የዚህ ዓለምን እሳት ከፈራን የዘለዓለም እሳት ይጠብቀናል ይህ ዕለት ቅዱስ ቁርባንን ለመጨረሻ ጊዜ የምንቀበልበት ነው። ከዛሬ ጀምሮ ለመንግሥተ ሰማያት አክሊል የተዘጋጀን እንሁን በማለት ቃለምዕዳን አሰማ።

ይህ አረጋዊ ካህን ንግግሩን ሲፈፅም በእግዚአብሔር ሰላምታ ተሰናበታቸው ሠርሆተሕዝብስለሆነም ሁሉም ወደየቤቱ ሄደ። እያንዳንዱ ክርስቲያን ታላቅ ሐዘን ተሰምቶት ነው ወደየቤት የተመለሰው ምክንያቱም በክርስቲያኖች ላይ ትልቁ ፈተና ተደቅኗልና ሕፃኑ አባኖብ ለመጦሪያውብለው ወላጆቹ የተውለት ጥቂት ገንዘብ ነበረው። ከአረጋዊው ካህን የመጨረሻው የመሰነባበቻ መንፈሳዊ ንግግር ስለሰማ ከቅዱስ ቁርባኑ በቀር ምንም ሌላ ነገር መቅመስ አልፈቀደም።

ከወላጆቹ የቀረለት ወርቅና የከበረ ልብስም በቤቱ ነበረው፣ ነገር ግን ወላጆቹ ከቤታቸውግድግዳ ላይ "ማንኛውም እንደወርቅ ይቀልጣል የከበሩ ልብሶችም በብል ይበላሉ፣ ገንዘብም ይጠፋል ዓለምና በውስጧ ያሉ ሁሉ ያልፋሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል" የሚል የፃፉበት ምክር ነበርና ልብ ብሎ ተመለከተው ወድያው ያለውን ንብረት በሙሉ ለድሆች መፀወተው ከቤቱም ወጥቶ ወደምሥራቅ አቅጣጫ እጁን ዘርግቶ "ጌታዩና አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደእግዚአብሔር ሕያው ሆይ ቤቴን እንደተከፈተ እንደተውኩት አንተንም በፍፁም ልቡና እንደተከተልኩህ አይተህ ከሐዲው መኮንን ካለበት ሄጄ ስለስምህ ልመሰክር ነውና መንፈስ ቅዱሳን ልከህ አፅናኝ አሸንፈው ዘንድ። ጌታዩና አምላኬ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ላክልኝ መኮንኑ ካለበት ደርሼ የመንግሥተ ሰማያት በር የሆነውን ሰማዕትነት ይከፍትልኝ ዘንድ እንዲመራኝ እኔም ያንተን ዘለዓለማዊነትንና ጽድቅን መስክሬ እንጻልፍ"



www.ethiopianorthodox.org

እያለ ፀለየ። ፀሎቱን አከናውኖ ሲያበቃ ጉዞውን ቀጠለና ካንድ ወንዝ ደረሰ ወንዙንም ተሻግሮ ሰሞኑድ ከተባለው የክርስቲያኖች ሠፈር ደረሰ በዚህም አካባቢ አብያተክርስቲያኖች ተዘግተው አብያተጣኦታት ተከፍተው አየ። በከባድ ፍርሐትም ተውጦ ባገሩ ማህል ሲንቀሳቀስ አረማውያን ኢየሱስ ክርስቶስንና ተከታዮቹን ሲሰድቡ ሰማ እስኪመሽ ድረስም ዝም ብሎ ዋለ ሲመሽ ምሕረትህ የበዛ መዓትህ የራቀ ቸር አባት ሆይ እንደኔ ያሉትን ሐጢአተኞች የምትቀበል ሦስቱ ሰብአሰገልን መርቶ ስጦታ እንዲያበረክቱ መልአክን የላክህላቸው አዳምን ሐዘኑን ሰምተህ ወደገነት ያገባኸው እኔን ደሜን ለማፍሰስ ያበረታታኝ ዘንድ መንፈስቅዱስን ላክልኝ በማለት ብዙ ፀለየ።

ሚካኤል መልአክ ወድያው ወርዶ አካባቢውን አበራው ወድያውም ሕፃኑ አባኖብ ደንግጦ ወደምድር ወደቀ እንደሞተም ሆነ መልአኩም ዳሰሰውና አነሳው እኔ ሚካኤል ነኝ ከልዑል እግዚአብሔር አፀናህ ዘንድ ተልኬአለሁ በገድልህ በርታ አለው ሲነጋም መኮንኑ ካለበት ሄደና በፊቱ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን እሱም መከራ ያደርስብሃል እኔም ካንተ ጋር እንዳልለይ ከእግዚአብሔር ተልኬአለሁ ወደደቡባዊውም ክፍል ሀገረአትሪብ ይወስዱሃል እኔም ካንተ አልለይም አለው።

ሲነጋ ቅዱስ አባኖብ መኮንኑ ካለበት ሄደ በጣኦቱ መግቢያ ላይም ክርስቲያኖችን የሚያሰቃይበትን ቦታ እያዘጋጀ አገኘው በዚህ ጊዜ አባኖብ በከፍተኛ ድምፅ እየጮኸ አንተ አረማዊ የፅድቅ ጠላት መኮንን እኔ በጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ የማምን ነኝ የፈለግኸውን ሁሉ በፍጥነት ፈፅምብኝ እኔ ለረከሱ አማልክቶችህ አልሰግድም አለ። መኮንኑም ከዚህ የ12 ዓመት ሕፃን ይህን የመሰለ



የጥበአት ቃል በመስማቱ ተደነቀ "አንተ ወጣት ማን ወደዚህ አመጣህ አንተስ ማነህ ገና ፀሐይ ሳይወጣ በጧቱ እንዴት ልትመጣ ቻልክ" አለው። ቅዱስ አባኖብም አንተ ሰነፍ መኮንን አእምሮ ቢስ እንደሆንክ ትኖራለህ አንተ መድሐኔዓለም ክርስቶስን እንደምትሰድበው የሚያመልኩትንም እንደምትገድላቸው ሰማሁ ከቦታዬም ወጥቼ ወዳንተ መጣሁ አመጣጤም ሰማይንና ምድርን ለፈጠረው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ደሜን ለማፍሰስ ነው እሱ ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ ወፎችንና አራዊትን እሱ ፈጠረ ማንኛውም የሚታየውንና የማይታየውንእሱ ፈጠረ አንተ የምታመልከው ጣኦት ዕውር ነፍስ የሌለው ራሱን ማዳን የማይችል ነው ታድያ የሌሎችን ነፍስ እንዴት ሊያድን ይችላል? የፈቀድከውን በኔ ላይ አድርግ እንጂ ለአማልክቶችህ እኔ አልሰግድም አለው።

መኮንኑ ሲመልስ አንተ ከነማንነህ ከማን ብሔርስ ነህ ስምህስ ማን ይባላል? በጣም ነገር ታበዛለህ አለው እሱም አንተ ከሐዲ ስማኝ ስሜ አባኖብ ይባላል ብሔሬ ኒሂሣ ነው የእግዚአብሔርን ጥሪ ተቀብዮ ወደዚህ መጣሁ ባንተ የሚፈፀምብኝን መከራ ለመቀበል ተዘጋጅቼአለሁ ዝግጁነቴም ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሠጠኝ ሐይል መጠን ነው እኔ ሐይል የለኝም ሐይሉም ብርታቱም የእግዚአብሔር ነው ላንተና ካንተ ጋር ለአማልክቶችህ ለሚሰግዱ ወዮላችሁ አንተና ንጉሥህ እናንተንም ተከትለው ለርኩሳን ጣኦታት የሚሰግዱ ሁሉ ትጠፋላችሁ የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘለዓለም ይኖራል በማለት መለሰለት።

በዚህ ጊዜ መኮንኑ እጅግ ተናደደ ነገር ግን ቁጣውን በውስጥ አድርጎ አንተ ሕፃን ነህ አእምሮህ ግን ብሩህ ነው አንድ ጊዜ ብቻ ብገርፍህ ሁለተኛን ግርፋት ለመቀበል አቅም



www.ethiopianorthodox.org

የለህም የምልህን ከሰማኸን ልጄ አደርግሃለሁ በገዥነትም ከፍ አደርግሃለሁ ለአጽሉን ከሰገድክ ከቤተመንግሥት ወገን አጋባሃለሁ አለው።

ቅዱስ አባኖብ እግዚአብሔር ይፍረድብህ ያንተን አምላክ ከድንጋይ የተሠራውን አጽሉንንም ያጥፋው የሚል መልስ ሠጠው በዚህ ጊዜ መኮንኑ ቅዱስ አባኖብን በደረቱ አስጣለው ወታደሮቹም ሆዱ ላይ ገረፉት በዚሁም ተፈራረቁበት ሁለት ሁለት እየሆኑ በመፈራረቅ ብዙ ስለገረፉት የሆዱ አንጀት ተዘረገፈ የጎድኑ አጥንቶችም ተሰበሩ ቅዱስ አባኖብ በዚህ ጊዜ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ በጆሮው የሚሰማ በዓይኑም የሚያይ ወደዓለም የመጣ ስለኛም ሕማማትን ሁሉ የተሸከመ ስለኛም ሞትን የቀመሰ አንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የማትሞት የማትጠፋ ስለኛ ተቀበርህ ስለሐጢአታችንም ደምህን በመስቀል ላይ አፈሰስክ በሥልጣንህም ሞትን አሸንፈህ ተነሣህ ዛሬ እኔን ስማኝ በዚህ ደካማ ዓለም መካራን በመቀበል ላይ ነኝ መከራውንም የምቀበለው ስለስምህ ብዬ ነው ላንተ ክብርና ምስጋና እስከዘለዓለሙ ይሁን እያለ ፀለየ።

ይህን በማለት ላይ እያለ ቅዱስሚካኤል ብሩህ አክሊል ይዞ ታየው። ቅዱስ አባኖብንም እንዲህ አለው "አንተ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሆይ ፅና በርታም የጌታህ ኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል በፈቃድህ የተሸከምክ ቅዱስ ሆይ እኔ ሁሉን በሚይዝ እግዚአብሔር ቀኝ የምቆም የመላእክት አለቃ ሚካኤል ነኝ ከእግዚአብሔር እየታዘዝኩ ሰማዕታትን ሁሉ የማፀናቸውና አክሊልን እስኪቀዳጁ ድረስም የማበረታታቸው እኔ ነኝ በእሥር እያሉም በእግዚአብሔር ምህረት የምጎበኛቸው እኔ ነኝ ገድላቸውን እስኪፈፅሙ ድረስ እንዳልለያቸው ከእግዚአብሔር የታዘዝኩ እኔ ነኝ አሁን አንተ ገድልህን ስትፈፅም ከእግዚአብሔር የታዘዘልህን አክሊል በእጁ



ታያለህ በራስህ ትቀዳጃዋለህ።"

በዚህ ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል አካላቱን ዳሰሰውና ከሕመሙ ተፈወሰ ሥቃይ እንዳልደረሰበትም ፍፁም ጤነኛ ሆነ የተዘረገፈውን አንጀቱ መልአኩ ጤናማ አደረገለት አባኖብ በሐይለእግዚአሔር ተነሳ ወደመኮንኑም ሄዶ ይገሥፀው ጀመር። እንዲህም አለው "አንተ ከሐዲ መኮንን ሆይ አሁንስ ምን ልትል ነው እነሆ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ አስነሳኝ በኩነኔህ ከደረሰብኝ የአካል መበጣጠስም አዳነኝ አሁንም የምትፈልገውን ሁሉ አድርግብኝ እኔ አማልክቶችህ የረከሱ መሆናቸውን እነግርሃለሁ።"

መኮንኑ የበታች ሹማምንቱን ሰበሰበና ይህ ህፃን በክርስቲያን ሥራይ እንዴት እንደተያዘኑ እዩ ወዮለት ይህ ጎስቋላ ሕፃን ዛሬ ወጣትነቱ ይበላሻል ይጠፋልም አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያድነው በማይችልበት ሁኔታ አስቃየዋለሁ አላቸው ከዚህም አያይዞ ወደ እሥር ቤት እንዲከቱት አዘዘ በብረት አስረውም ወደሚታሠርበት ወሰዱት በየቦታው ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስም የታሠሩ ሰማዕታት ይገኙ ነበር። እሥር ቤቶቹ በእሥረኞች ተሞልተው ምንም ክፍት ቦታ አይገኝም ነበር። ይሁን እንጂ ከባድ ሥቃይ ካለበት እሥር ቤት መርጠው አስገቡት። በታሠረበትም ብዙ ሰዎችን አገኘ።

የዚህ ቅዱስ አባኖብ ሕፃን በሰማዕትነት መሠለፍ ሲያደንቃቸው ከደረሰበት ሥቃይና መከራ ብዛት ልብሶቹ እንዳሉ በደም ተጨማልቀው ሲመለከቱ እጅግ ደስ አላቸው ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሰማዕትነቱን በድል አድራጊነት በመወጣት ላይ ነበርና የታሠረበት ከባድ ብረትንና የሕፃንነቱን ሁናቴ ሲመለከቱ የእግዚአብሔር ፀጋ በሱ ላይ ማደሩን ተረዱ።

በዚሁ እሥር ቤት ዮልዮስ ቀሲስና፣ ብልሐተኛ አባይ



www.ethiopianorthodox.org

ስሐቅና፤ አበባብሩዳን ጨምሮ ብዙአበው ሰማዕታት በዚሁ እሥር ቤት ስለነበሩ በመንፈሳዊ ሰላምታ ሰላም ተባባሉ ቅዱስ አባኖብንም ሰላም አሉት "አንተ ሕፃን ነህ በእግዚአብሔር ፊት ግን ትልቁ አንተ ነህ በመንግሥተሰማያት ዘለዓለማዊ የሆነውን አክሊል እስክትቀዳጅ ድረስ አይዞህ በርታ እግዚአብሔር አንተ አርአያ ትሆነን ዘንድ ወደኛ ላከህ ምስጋና ይድረሰው" በማለትም ተፅናኑበት አባኖብም አባቶቼ ቅዱሳን ሆይ እኔ ሕፃን ከመሆኔ የተነሳ ጥንካሬ የለኝም ብዙ ቀምነገሮች ይጎድሉኛል እግዚአብሔር መከራውንና ሥቃዩን ያስችለኝ ዘንድ በፀሎታችሁ ርዱኝ አላቸው እነሱም ከየት እንደመጣ ለምን ወደሰማዕትነት ደረጃ እንደደረሰ አስቀድመው ጠየቁትና ከወላጆቹ ታሪካዊ አመጣጡ እስከሱ ያለውን ዘርዝሮ ካስረዳቸው በኋላ ባንድ ድምፅ አማልክቶችን ሰደቡ ሀገረአትሪብ

ለመሄድ ወደመርከብ ከመሳፈሩ አስቀድሞ ከታሠሩበት ድረስ በመሄድ ከመከራ ብዛት የተነሳ ከእምነታቸው ወጥተው ይሆናል የማለት ግምት አድሮበት መኮንኑ ጎበኛቸውና እያመማቸው "ክርስቶስ አምላካችን ሕያው ነው እኛም በስሙ ሰማዕትነትን ለመቀበል ተዘጋጅተናል አንተና አማልክትህ ርኩሳን ናችሁ አንተ አማልክቶችህ ንጉሥህ ዲዮቅልጥያኖስ ርኩሳን ናችሁ አሁንም ባንተ እጅ ሰማዕትነትን እስክንቀበል ድረስ አንሰግድልህም" አሉት።

የሰማዕታቱ ባንድ ድምፅ እሱንም ጨምሮ የጣኦታቱንና ንጉሡን መዘለፍ ሲሰማ ሌላ የፖለቲካ ቀውስ ይፈጠርብኛል የማለት ሥጋት አደረበትና ጉዞውን ሠርዞ በነሱ ሕይወት ላይ ለመፍረድ ወዳደባባይ ወጣ። ከእሥር ቤቱ ከነበሩት ቅዱሳን በተጨማሪ በየክፍሉ የቁም እሥር በማድረግ በዓይነቁራኛ ያስጠብቃቸው የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ከያሉበት ሁነው ድፍረት በተሞላበት ሁኔታ እኛ ክርስቶሳውያን ነን ክርስቲያንነታችን በግልፅ እንጂ በድብቅ አይደለም በሰማይም በምድርም በሌሎችም አለማት ካንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተንና ርኩሳን አማልክቶችህ ያጠፋቹኋል በማለት ከፍተኛ ድምፅ ሲያሰሙ አገሩ ታወከ።

መኮንኑም ስመኢየሱስ ክርስቶስን የጠራ ሁሉ በያለበት በሥለታም ሰይፍ እንዲታረድ አዘዘ ወታደሮቹ በየእሥር ቤቱ ያሉትን ሰማዕታት መደዳውን እንደገብስ አጨደው ከጨረሱ በኋላ አሰሳ በማካሄድ ከጧቱ ሦስት ሰዓት እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ህፃን ሽማግሌ፣ ወንድ ሴት ሳይባል ሲፋጁ ዋሉ ከተማዋ በሰማዕታት ደም ተጥለቀለቀች በየሠፈሩ ከታረዱት ሌላ በየአደባባዩ የታረዱት ሰማዕታት ብቻ ከሁለት ሺ በላይ ነበር ቀኑ መጋቢት ዘጠኝ ቀን ነበር።

ይህን ካደረገ በኃላ መኮንኑ ብዙ ጠላቶችን በዛሬው እለት አስወግጃለሁ ከእንግዲህስ የኔ ጌታ ወደሆነው ንጉሥ ልሂድና እሱ ያዘዘኝን ሥራ ላከናውን አለ ይህ ሁሉ ሲሆን ሕፃኑ አባኖብ ከእሥር ቤት በሕይወት ይገኝ ነበር መኮንኑ ይህን ተናግሮ ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ ወዳለበት ለመሄድ ሲነሳ ከወታደሮቹ አንዱ አባኖብ የሚባል ሕፃን በእሥር ላይ ይገኛል አልተገደለም እሱ ብዙዎችን አስቷል በሱ እየሳቱ ክርስቶስን ያመኑ እጅግ ብዙዎች ናቸው ብሎ ነገረው ቅዱስ አባኖብ በመከራው ፅናት የተነሳ እጅግ ተጎድቶ ስለነበር ሊንቀሳቀስ አይችልም ነበር። ስለዚህ ከታሠረበት ተሸክመው አመጡት።

ከመኮንኑ የሚነገረውን ሲያዳምጥ ከቆየ በኃላ ቅዱስ አባኖብ በእጁ ትብያን ከመሬት ዘግኖ አንተ ውሻ ንጉሥህም ያበደ ብሎ

www.ethiopianorthodox.org

ከፊቱ ላይ በተነበት መከራውን በመቀበሌ ዘለዓለማዊ አክሊልን እቀዳጃለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ለሰማዕታት የሚሠጠው አክሊል እንዳያመልጠኝ የዚህን ዓለም መከራ እጋፈጠዋለሁ ጌታዩና መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስም አልተለየኝም መንፈስ ቅዱስን ልኮ አበራትቶኛል አሁንም የፈለግኸውን ሁሉ አድርግብኝ አለው።

መኮንኑ እንደገና እጅ እግሩን አሥሮ ወደሚጓዝበት መርከብ ወሰደውና በመርከቡ ምሶሶላይ ቁልቁል ተንጠልጥሎ እስከሀገረ አትሪብ እንዲጓዝ ወሰነበት በዚሁም ተንጠልጥሎ እያለ መኮንኑና ሠራዊቱ እያዩት የአጽሉንን ሐይል ተመልከት እስቲ የምታመልከው ክርስቶስ ይምጣናያድንህ እያሉ እየዘበቱበት ቀን ሙሉ በመርከቡ ተጓዙ መኮንኑና ተከታዮቹ በመርከቡ ላይ ይበሉ ይጠጡ፣ ይደሰቱም ነበር ወደማታ ገደማ ሀገረአትሪብ ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው መኮንኑ ይጠጣበት የነበረው ፅዋ ለማስቀመጥ እጁ ሲያንቀሳቀስ ፅዋው ከእጁ ጋር ተጣብቆ ቀረ እጁ እስከትከሻው ድረስ ደረቀ የድንጋይ ያህልም እጅግ ከበደው በገዛ እጁ ሊያንቀሳቅሰው አልቻለም ተከታዮቹ ወታደሮችም በሙሉ ታወሩ መኮንኑ ቀና ብሎ ቢመለከት ከቅዱስ አባኖስ አፍ ደም ሲፈስ አየ ምክንያቱም ይህ የማይባል መከራ ተፈፅሞበታልና በዚህ ጊዜ መኮንኑ አንተ ህፃን በምታመልከውና እስካሁንም መከራ በተቀበልክለት ኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ አንተ እውነተኛ አገልጋዩ ነህ ኢየሱስ ናዝራዊ ገና በዚህ የሕፃንነት ዕድሜህ ለሰማዕትነት ያበቃህም እሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የክርስቲያን አምላክ ነው እባክህ ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን ሁሉ የንፁሐን ክርስቲያንን ደም በማፍሰሴ ሊያጠፋኝ ነው ለምንልኝ የሱም ፈቃድ ሁኖ አሁን ከምንጓዝበት አገር ኒሒሳ ከደረሰን ስለ እውነተኛው አምላክክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ ከወታደሮቼ ጋር እንመሰክራለን አለው።



ዓይናቸው የታወረው ወታደሮች በበኩላቸው እኛ የክርስቶስ ተከታዮች እንሆናለን በሱም እናምናለን የቅዱስ አባኖብ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እያሉ በተሣፈሩበት መርከብ አትሪብከ ተባለው አገር ደረሱ ከወደቡ ላይ መርከቡ ሲቆም መኮንኑ ሊነሳ አልቻለም በዚህ በአትሪብ ቅብርያንና አውሕያስ የተባሉ የዲዮቅልጥያኖስ ወኪሎች መኳንንት በክርስቲያኖች ላይ መከራ በማድረስ ላይ ነበሩ። በዕለቱም በአደባባይ ላይ ብዙ ክርስቲያኖችን ሰብስበው ክርስቲያኖችን በመግረፍ፣ በመደብደብና በመጎተት ላይ ነበሩ።

አባኖብን ይዞ የመጣው መኮንን ሊንቀሳቀስ ባለመቻሉ በመርከቡ ላይ ቀርቶ የታወሩት ወታደሮቹ ግን ቅብርያን መኮንን ክርስቲያኖችን ወደሚያሰቃዩበት አደባባይ በሰዎች እየተመሩ ሄዱ መኮንን ቅብርያል ድንገተኛ ነገርን በማየቱ ደንግጦ ምን ሆናችሁ አላቸው አባኖብ በስራዩ አሳወረን አሉት እሱ አባኖብ ማለት ማነው? ብሎ ጠየቀ እነሱም ታሪኩን ነገሩት አገራችሁን ስለምን ትታችሁ መጣችሁ በማለት ጠየቃቸው።

መሪአችን መኮንን ታሞ ከአጽሉን ዘንድ ርዳታ ሊያገኝ አልቻለም አጽሉን ከሕመሙ አልፈወሰውም በሰዎች እየተመራንና የምንረግጠውን ስናውቅ እየተንገላታን ካንተ ዘንድ ደርሰናል አሉት።

ቅብርያል ወታደሮቹን ሂዱና ተሸከማችሁ ወደኔአምጡት ብሎ አዘዘ፣ እነሱም በታዘዙት መሠረት ከመርከቡ በማውረድ ተሸከመው አመጡትና ቅብርያል ካለበት የፍርድ ቦታ አስቀመጡት የቅብርያል ጓደኛ መኮንን አውህያስ ከዚያ ተቀምጦ ስለነበር ማነው እንዲሁ ያሳመመህ በማለት ጠየቀው ይህ መኮንን የታመመው ያልሰልያስ ይባላል መኮንኑ ስምኖዳ እየተባለም ይጠራ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

ብዙዎች ክርስቲያኖችን አሰወግጃለሁ። ለዓይን ፍፁም ሰው መስሉ የማይታይ ህፃን ከመካከላቸው ሾልኮ ቀርቶ በሥራዬ እንዲህ ተጫወተብኝ ብዙዎች ክርስቲያኖች ከእጄ ላይ ወድቀዋል እንደዚህ ሕፃን ያለ ክፉ ሰው ግን አልገጠመኝም በሥራዬ ተጫወተብኝ አለው ወድያውም ካለበት ቅዱስአባኖብ ሕፃንን ያመጡት ዘንድ አዘዘ እስከዚያው ድረስ ቅዱስ አባኖብ እንደታሠረ በመርከቡ ላይ ይገኝ ነበር። የታዘዙት ወታደሮች ከእሥራቱ ፈትተው መኮንን ቅብርያል ካለበት አመጡት።

ከመኮንን ቅብርያል ፊት በቀረበ ጊዜ ቅዱስ አባኖብ ፊቱ እንደፀሐይ ያበራ ነበር ዓይኖቹም ምንም የሕፃንነት መልክ ባልተለያቸው አኳኋን በመንፈስ ቅዱስ ሐይል እንደኮከብ ያፍለቀልቁ ነበር ከመልካም ግብዣ የወጣ ይመስል መንፈሱ በደስታ ተሞልቶ ነበር ቅብርያል መኮንን ስምህ ማን ይባላል ብሉ ጠየቀው አባኖብ የጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ እባላለሁ ከዚህ ቦታ ደሜ ስለጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማፍሰስና እናንተንና ሌላ ነፍስን ሲያድኑ ቀርቶ ራሳቸውን እንኳ ማዳን የማይችሉትን አማልክቶቻችሁ ለማሳፈር ወደዚህ መጥቻለሁ በማለት መለሰለት።

ቅብርያል መኮንን ከሁሉ አስቀድመህ ሰምኑድ ከተባለው ቦታ አሁን እንዳለህና ይህም ቦታ ብዙዎች አማልክትን የካዱ ክርስቲያን የተፋጁበት እንዳንተ ኢየሱስ ክርስቶስን እናምናለን ያሉት ሁሉ የተቀጡበት መሆኑን አትጠራጠር አሁንም ለአማልክት መሥዋእት ሠዋ ካልሆነ በእጄ ትገደላለህ በማለት አስፈራራው ቅዱስ አባኖብ ግን ይህንን በፍፁም አላደርገውም አንተ ከሃዲ መኮንን የዘለዓለሙ ሕይወቴን ኢየሱስ ክርስቶስ ትቼ ለጣኦት እንድሰግድ የምታሥፈራራኝ በምን ብትገምተኝ ነው አንተና ንጉሥህ ዲዮቅልጥያኖስ አምላክ የለሾች የተዋጣላችሁ ከሐዲዎች



ናችሁ በማለት መለሰለት።

መኮንን ቅብርያል እጅግ ተቆጣና ልብሱን አውልቀው ዕራቆቱን እንዲያቆሙት አዘዘ ወታደሮቹም ልብሱን ገፈው መቶ ጊዜ በጂራፍ ገረፉት ከዚያም በማያያዝ በብረት አልጋ ላይ አስተኙት "ተይ" ና "ፒሳ" የተባሉን መርዞች ጨምረው ከበታቹ እሳት አነደዱበት የእሳቱ ነበልባል እስከ 12 ክንድ ድረስ ወደላይ ተነሳ።

ቅዱስ አባኖብ ፀሎተ ፲ ደቂቅን አንስቶ እግዚአብሔርን አመሰገነ "ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በዚህ እሳት ውስጥ እያለሁ ስማኝ ይቅርባይና ቸር አምላክ ማንንም ቸል የማትል በሰዎች የተናቁትን ሁሉ በቸርነትህ የምትጎበኝ ሁሉን ቻይ ቸር አምላክ አንተ ብቻ ነህ የነበርክ ያለህ የምትኖር አንተ ብቻ ነህ መድሐኒቴና ጌታዬ ሆይ ወደኔ ና ርዳኝም ተከላዎችና ነጣቂዎች ከዚህ አሉ እነሱም ሐይልህንና ሥልጣንህን ያዩ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን" እያለ ፀለየ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠረገላ ብርሃን ወርዶ ወዳጄ አባኖብ ፅና አትፍራ እኔ ካንተ ጋር ነኝ ስለኔ ይህን ሁሉ ድካም ተሸክመሃል እያለም አፅናናው ይህ መኮንንም ባንተ ፅናት በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደኔ ይመለሳል ሰማዕትም ይሆናል ብዙዎችም እሱን ተከትለው ሰማዕትነትን በመቀበል የመንግሥተሰማያት ዜጎች ይሆናሉ ይህም የሚሆነው ባንተ እጅ ነው አለው።

የታሠረበት የብረት አልጋ ከበታቹ እሳት እንዲነድበት የተደረገው ጠፋ። ሰው ከቅዝቃዜ ብዛት ካጠገቡ ለመቆም በማይችልበት ሁኔታም ቅዝቃዜው እጅግ በረታ አካባቢው እጅግ ከመቀዝቀዙ የተነሳ ወታደሮቹና መኮንኑም ወደየቤታቸው ገቡ አባኖብ ከታሠረበት



www.ethiopianorthodox.org

ተነስቶ ወደሌላ ቦታ ሄደ። በደረሰበትም ቦታ ክርስቲያኖችን የማጥፋት አዋጅ ሲነገር ሰማ አዋጁም፣ "እወቁ ከናንተ መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው የሚል ካለ አማልክት በጦርነት ጊዜ ድልን እንድንቀዳጅ ይረዱናል ስለዚህ ለአማልክቱ አልሰግድም የሚል ካለ ይገደል" የሚል ነበር። አባኖብ የደብዳቤውን አባባል በመቃወም ገሠፃቸው እናንተ ህግ አፍራሾች ድንጋዩን አጽሉን እያላችሁ የምታመልኩ ድንጋይ ልብ አለውን እኔ ከተማገድኩበት እሳት በሥልጣኔ አልወጣሁም ሁሉን የሚችል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በሥልጣኑ በሕይወት ከናንተ መካከል እንድመላለስ ያደረገኝ ይህን ሁሉ እየተመለከታችሁ ግን ከጥፋት እስካሁን አልተመለሳችሁም አላቸው በዚህ ጊዜ መኮንኑ ቅብርያኖስ ታላቅ ውርደት ተሰማው አማልክቶቻችን አጵሉንና አርሚስ እናታቸውም አርዳሚስ ክርስቲያኖችን ሁሉ ለማጥፋት ረድተውናል ሐይላቸውም አሳይተዋል ይህ ሕፃን ግን ሊጠፋልን አልቻለም እኛንና አማልክቶቻችንን አዋረደ ሥራዩ እጅግ የረቀቀ ነው በማለት የንዴት ንግግሩን አሰማ ወድያውም አባኖብን በጉጠት ዓይኖቹን አስወጣው።

አባኖብ ክፉ ነገርን የማይባቸው አይኖቼ ወጡ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህን መከራ ለዘዓለማዊ ደስታ መግቢያ እንዲሆነኝ አድርግልኝ አይኖቼ በዚህ ዓለም አላየሁባቸውም በዓይነ ህሊናዮ ግን ያንተን መንግሥትንና ክብርን አያለሁ በማለት ፀለየ። ከዚያ አያይዞ መኮንኑ ብዙ ሥቃይ ፈፀመበት ብዙ ጊዜ አሥገረፈው የአካላቱ ሥጋ እስኪቆረጥ ድረስ አስደበደበው ነገር ግን በሐይለ መንፈስ ቅዱስ ዓይኖቹ ዳኑ። በሕይወትም ለመንቀሳቀስ ቻለ።

በአባኖብ ላይ የተፈፀመው ከዚያ ሁሉ የአካላት መቆራረጥና የዓይን መዳን የተመለከቱ የአትሪብ ሕዝቦች በሙሉ እኛ በአባኖብ አምላክ እናምናለን እኛ ክርስቶሳውያን ሁነናል አሉ መኮንኑ

ቅብርያልም በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ ከወታደሮቹም አብዛኞቹ አምነው ከአባኖብ ጋር ተሰለፉ መኮኑንን ቅብርያል ከሌሎች መኳንንት ተለይቶ ከምዕመናን ጋር ወግኖ ስለተሰለፈ በከሐዲነታቸው እንደጠፉ ከቀሩት መኳንንት መካከል የሰምኑድ መኮንን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመኑን በግልፅ የተናገረውን ቅብርያኖስ መኮንን በጫማው መታው። በህገሩም በግፍ እንዴት ሰው ይገደላል የሚል ጥያቄ ተነስቶ ሁከት ተጀመረ የሰምኑዱ መኮንን እሱን መሰለው የጣኦታት ተገዢዎች ከሆኑ ወታደሮቹ ጋር በስተመጨረሻ የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን የበቃውን ቅብርያኖስን ጨምሮ ስምንት መቶ አምሳ ስምንት ሰማዕታትን ከጧቷ እስከ ቀኑ ሰባት ሰዓት ድረስ ሲያስፈጅ ዋለ። ይህ የቅዱሳን ሰማዕታት የሰማዕትነት ቀን ግንቦት አሥር ቀን ነው የተፈፀመው። አባኖብ አይዛችሁ የመንግሥተሰማያት አክሊል ይጠብቃቹኋል ፅኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ከናንተ ጋር ነው ይህን ዓለም ልታሸንፉት ተቃርባቹኋል ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ ብርሃን ልትሄዱ ነው እያለ ያበረታታቸው ነበር።

በክህደቱ ቁሞና ዲዮቅልጥያኖስን አስደስታለሁ ብሉ ከላይ የተጠቀሱትን ሰማዕታት ያስፈጀም መኮንን ስም አውህያስ ይባላል። አውህያስ አባኖብን ዛሬ አንተ ባየኸው የሰዎች ደም መፍሰስ ተደሰትክን የብዙ ሰዎች ደም ዛሬ ፈሷል ለዚህም ምክንያቱ አንተነህ በይበልጥ መኮንኑን ወዳንተ እምነት አስገብተህ ደሙን አፍሰሃል ይህ ሁሉ ሁኖ ግን ባንተ ላይ ቂም የለኝም ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስም አንተን አልተቀየመም ህፃን ነህና እኔና ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ ካንተ የምንጠብቀው አንድ ነገር ብቻ ነው። ይኸውም አንተ ለአማልክት እንድትሠግድና መሥዋእትንም እንድታቀርብ ፈቃደኛ ትሆን ዘንድ።



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ አባኖብ "ዲዮቅልጥያኖስ ያንተ ጌታ ከሆነ የኔ ጌታ አይደለም የኔ ጌታ ሁሉን በእጁ የያዘ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማይና የምድር ጌታ ስለሆነ እንዳንተና እንደ ዲዮቅልጥያኖስ ያሉትን ትዕቢተኞች አዋርዶ ባዶ እጃቸውን ይሰዳቸዋል አንተና ንጉሥህ ዲዮቅልጥያኖስ የዲያብሎስ መሣርያዎች ናችሁ" በማለት ገሠፀው ወድያው መኮንን አውህያስ በደረቱ አስተኝተው በምሣር እንደግንድ እንዲከተክቱት አዘዘ ወታደሮቹም በሆዱ አስተኝተው መጀመሪያ ከእግሩ በታች ቅልጥሙን ከተከቱት፣ ቀጥሉ ከጉልበቱ በላይ ከሁለት ቆረጡት ከዚያም እጆቹን ከክንዱ ላይ እንደግንድ ከትክተው ቆረጡትና ሕይወቱ ሳትወጣ ትተውት ሄዱ።

አውህያስ መኮንን በዚህ ጊዜ እየጮኸ አሁን በሞትና በሕይወት መካከል ሁኖ በሜዳ ላይ እንዲጣል አድርጌአለሁ እስቲ ገሊላዊው ኢየሱስ ይምጣና ያድነው ከደረሰበት የመቆራረጥ አደጋም የፈውሰው በኔ ዘንድ ከአጵሎስና አርሚስ በቀር ሌላ አምላክ የለኝም አለ ውሾችም እንዲበሉት ሰብስቦ ላከበት ግን ይህ ከሀዲ በእግዚአብሔር ላይ እንዳፌዘና ክርስቲያኖችን እንደተዘባበታቸው እንዲቀር የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረም ክርስቲያኖች የቅዱስ አባኖብ አካል የተጣለበትን ቦታ አላወቁም ነበር። አንድ አባሌ የሚባል ሕፃን ብቻ የተጣለበትን ቦታ አይቶ ነበር።

እግዚአብሔር በሱ መሣርያነት ብዙዎች ወደሱ እንዲሙጡ አሁንም በዚሁ ሕይወቱ እንድታልፍ አልፈለገም ከተጣለበት በአምላካዊ ሥልጣኑ አስነሳው። "ይህን ከሐዲ መኮንን /አውህያስ/ ታሳፍረው ዘንድ ፅና በርታ የሚል አምላካዊ ቃልንም ሰማ እግዚአብሔርም እያመሰነነ ከተጣለበት ተነስቶ ወደእስርቤት ሄደ ወደእሥር ቤቱ በሚሄድበት ጊዜ ብዙ ሕፃናት ወጣቶች፣ ሴቶችና ወንዶች ተከተሉት ያላንድ እግዚአብሔር ሌላ አምላክ የለም የአህዛብ አማልክት አጋንንትና የአጋንንት ማደርያዎች ናቸው የአባኖብ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት አምላክ ብቻ እውነተኛው አምላክ ነው" ይሉ ነበር።

የነሱ ምስክርነት በመኳንንትና በነገሥት ዘንድ ተሰማ የሕፃኑ አባኖብ በቤተሞቅህ /እሥርቤት/ መኖርንም ታወቀ መኮንኑ አውህዮስና ተከታዮቹ ክርስቲያን ሁኖ የሚያስቸግረንን "ህርማ" መኮንን ካለበት እስክንድርያ እንድንልከው ታዛናል ስለዚህ ሕፃኑን አብኖብን ወደእስክንድሪያ እንላከው ተባባሉ እሱ ግን በእሥር ቤቱ የታሠሩትን ሁሉ አስተምሮ በሱ ላይ የተፈፀመውንም አምላካዊ ገቢረተአምር ገልፆ የክርስቶስ ወገኖች እንዲሆኑ ክርስቲያኖች በመሆናቸው የታሠሩትንም እንዲፅናኑ አድርጓል።

አውህያስና ተከታዮቹ ግን ከአባኖብ ከፋት ውርደትና ስድብ እንድናርፍ ባስቸኳይ ወደእስክንድርያ እንላከው ካለሆነ ግን በመሠርይነቱ ብዙ ሕዝብ ይዞብን ይጠፋል ተባባሉ። ከመካከላቸው አንዱ መልካም አልክ እሱ ከዚህ ከሆነ እንዋረዳለን ነገሥታትም ይረክሳሉ ይዋረዳሉ በማለት የአውህያስን አባባል ደገፈ አውህያስ ከእስር ቤት እጆቹን በብረት ሠንሠለት አስጥሞ በማስጨነቅ ሲያመጣው ብዙ ሕዝብ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሆይ በፀሎትህ አስበን እኛም አንተ የምትሞተውንሞት ለመሞት ተዘጋጅተናል በማለት ይከተሉት ነበር።

አውህያስና መኳንንቱ ግን ወደእስክንድርያው መኮንን "ንጉሣችን ሰው ሁሉ ለአማልክት አጵሎን፣ ዘውስ፣ አትናስና



www.ethiopianorthodox.org

እናታቸው አርዳሜስ" እንዲሠግድ አዟል። ለነሱ ላልሰገደ ግን እንዲገድሉት ታዟል አርማንዮስ ሆይ ከደቡባዊው የግብፅ ክፍል የሆነ አንድ አስቸጋሪ መሠርይ ሕፃን እጅግ አስቸግሮናል ይህ ሕፃን በምንም ሊሞትልን አልቻለም ከሁሉ በላይ ደግሞ በሱ ምክንያት ሕዝቡ ሁሉ ክርስቲያን እየሆነ ከማስቸገሩም በላይ ሕዝቡ በኛ ላይ ተነስቶብናል ሕዝቡ እኛን በጦር ሊወጋን ተነሥቷል በዚህም ምክንያት ሕፃኑን አባኖብን ወዳንተ ልከነዋል ከኛ አቅም በላይ ስለሆነብን ነው ወዳንተ የላክነው ለመንግሥትህ ሰላም ይሁን የሚል ደብዳቤ ፅፈው ቅዱስ አባኖብንም እጅንና እግሩን አንድ መቶ ኪሉ ግራም የሚመዝን ብረት /ዘይከውን ድልወቱ ምእተ ልጥረ/ አሥረው እየጎተቱ ወደእስክንድርያ ለመላክ ወደመርከብ ሲያስወጡት ሕዝቡ ከዚህም ከዚያም ተሰባሰቡና ይህን ቅዱስ የእግዚአብሔር አገልጋይ የትም እንዲወሰድብን አንፈቅድም እሱ የሚሞተውን ሞት እንሞታለን እንጂ በማለት ወደቡን አስጨነቁት።

በዚህ ጊዜ አረማውያኑ መኳንንት እጅግ ደነገጡ ወድያውም ወንድ ሴት ትልቅ ትንሽ ሳይመርጡ በሠይፍ እንዲያጭዱዋቸው አዘዙ። ወድያው አንገት አንገታቸውን ይቆርጡዋቸው ጀመር ግማሾቹን ወድያው እንዲሞቱ አድርገው ይቆርጡዋቸዋል ግማሾቹን ደግሞ ከብዙ ፃዕርና ጭንቅ በኃላ ሕይወታቸው እንዲያልፍ በማድረግ በሞትና በሕይወት መካከል ይተውዋቸው ነበር። ቅዱስ አባኖብ በከባዱ ብረት ታሥሮ ካለበት ሁኖ ያፅናናቸው ነበር "መንግሥተሰማያትን እስክትወርሱ ድረስ በርቱ ፅኑ" ይላቸውም ነበር መላእክተብርሃን ያንጊዜ የተገደሉትን ሁሉ አክሊላትን ሲያቀዳጁዋቸው ለአባኖብ ይታዩት ነበር።



በዚህ ዕለት የተገደሉት አንድ ሺ ወንዶች ሰማንያ ሁለት ሴቶች ናቸው። ሰማእትነት የተቀበሉበት ቀን ሰኔ አሥር ቀን ነው ኣባኖብን ደግሞ ወደመርከብ አስወጥተው ወደእሰክንድርያ ጉዞ ቀጠሉ። "በመርከቡም እያለ አባኖብ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰማዕታት አክሊልን ሲቀዳጁ አየሁ በነሱም ላይ መንፈሳዊ ቅንአት አደረብኝ እባክህ ጌታዬ ሆይ እኔም የነሱን ክብር እስካገኝ ድረስ አፅናኝ አበርታኝ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ፈቃድህን በኔ ላይ እስክትፈፅም ድረስ አፅናኝ እኔ እንግዳ እንደሆንኩ አንተ ታውቃለህ ካገሬ አውጥተው ወደሌላአገር እየወሰዱኝ ነው። ሥጋዬን የሚዳስስ ዘመድ የለኝም ጌታዬ ኢየሱስ ክርሰቶስ ሆይ አባቴም እናቴም አንተነህ ተስፋዬ መጠጊያዬ ክብርና ረዳቴም መመኪያዬም አንተን ብቻ አድርጌአለሁ ስለዚህ ከኔ አትራቅ" በማለት ፀለየ። ኢየሱስ ክርስቶስም መልአኩን ልኮ አፅናናው የተላከውም መልአክዘለዓለማዊውንና የማይጠፋውን አክሊለ መንግሥተሰማያት እስክትቀዳጅ ድረስ የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና በረከት አይለይህም ብሎት ተሠወረ ከሦስት ቀን ጉዞ በኋላ በመርከቡ ደፍድ ከምትባል አገር ደረሱ ከዚሁ ያገሩ መኮንን ክርስቲያኖችን እያሰቃያቸው አገኙት። ክርስቲያኖቹ ተገርፈው ተደብድበው የረሃብና የጥም ቅጣት ተፈፅሞባቸው በስተመጨረሻ እንዲሠየፉ ከባህሩ ወደብ ላይተጥለው ነበር እነሱ ተጥለውበት የነበረው አሸዋማ ቦታ ሕይወት ያለው ፍጡር ሊቆይበት የሚችል አልነበረም ይህም የተደረገበት ምክንያት ሌሎች ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን ለማትረፍ እንዳይሞክሩ ነው።

ሁለት ሰዓት ሲሆን እንዲት መንፈስ ርኩስ ያደረባት ሴት በመርከቡ ላይ ወጣች እቺ ሴት መናገር የማትችል ዲዳ



www.ethiopianorthodox.org

ነበረች በዚህ ጊዜ ግን እንደበቷ ተከፍቶ የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ አባኖብ ሆይ እግዚአብሔር ለዚህ ታላቅ ክብር ጠራህ የደምህ መፍሰስ ታላቅ ዋጋ አለውደምህ ብዙ ጊዜ ስለክርስቶስ ስም ፈሷል ኤሴና ጤቅላ እህቱ አረጋዊው ቀሲስም በክርስቶስ ሰማዕትነት ወንድሞችህ ሁነዋል በማለት ጮኸች በሷ ላይ ያደረው ጋኔንም 47 ዓመት ከኖርኩበት ማደርያዮ በአባኖብ ተባረርኩ በማለት እየጮኸ ወጣ።

ክርስቲያኖችን ለመፍጀት የተሰበሰቡት ወታደሮች ዲዳዋን ሴት ያውቋት ነበር በአባኖብ አማካይነት የእግዚአብሔር ሐይል እንዳዳናት ተመልክተው ወታደሮቹ እጅግ ደነገጡ ከድንጋጤ የተነሳም እህል አልቀመሱም ሌሎች የሴትየዋን መዳን ከሰሙ ክርስቲያኖች ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ሥጋት አደረባቸውና ዜናው እንዳይሰማ ለመደበቅ ተሯሯጡ ከበሽታዋ የተፈወሰች ሴት ደግሞ እኔ ከአባኖብ ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰማዕትነትን እቀበላለሁ በማለት ጥቡእነቷን አሳየች።

የእስክንድርያው መኮንን ሁኔታውን ተመልክቶ ፈራ በሽተኛዋን ሴት አድኖ ለዚህ ካበቃት ወደከተማ ካስገባሁት ሕዝቡ በሙሉ እሱን እየተከተለ ክርስቲያን ይሆንብኛል ስለዚህ መልሳችሁ ወዳመጣችሁበት አገር ውሰዱት እንጂ አልቀበላችሁም በማለት ከአትሪብ ያመጡትን ወታደሮች ተናገራቸው ወታደሮቹ አባኖብን ለመመለስ መርከቧን ለማንቀሳቀስ ሲጀምሩ ሴትየዋ እኔም ከሱ ጋር ወደሄደበት አገር ሄጄ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰማዕትነትን እቀበላለሁ ብላ ወደመርከቡ ለመውጣት ስትንጠላጠል ከወታደሮቹ አንዱ በሰይፍ አንገቷን ቆረጣት በዚህ የመንግሥተ ሰማያትን አክሊል ተቀዳጀች ሰማዕትነቱን የተቀዳጀችው ሰኔ 24 ቀን ነው።



አባኖብን ወደእስክንድሪያ ያደረሱበት ዕለቱ ሐምሌ ሁለት ቀን ነበር። የእስክንድርያው መኮንን ለመኳንንቱ ምሳ አስገብቶ አገኙት ስሙ ደቅስ ይባላል። ከአትሪብ መኮንን የተላከውንም ደብዳቤ ሠጡት ስለአባኖብ በቃልም አስረዱት ታሥሮ በመርከብ ላይ መሆኑንም ገለፁለት መኮንኑም ወደሱ እንዲያመጡት አዘዘ ምክንያቱም ሕዝቡ ከተመለከተው በሱ አማካይነት ወደክርስቶስ እንዳይመጣ ስለሰጋ ነው። አባኖብ ወደፍርዱ አደባባይ ሲገባ አንተ የፍርድ ቦታ ወዳንተ በእግዚአብሔር ሐይል መጣሁ አለ መኮንኑ ባየውም ጊዜ አንተ እንዳንድ ልጅ አድርጌ ተመለከትኩህ በሌላ በኩል የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ስታነሳ ስሰማህ እጅግ ጠላሁህ አሁንም ልጄ ሆይ ይህን ጥቅም የሌለውን ስም ከመጥቀስ ተጠበቅ በዚሁ ስም ብዙዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል። የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ በማለቱ በመስቀል ላይ አይሁድ ሰቅለው ከገደሉት ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንተ ምናለህ አለው።

ቅዱስ አባኖብ "አንተ የምድር አርዌ አፍህን ዝጋ ዝምበል ሥጋ በል አውሬ ነህ አንተ እግዚአብሔር እንዲያጠፋህ ተዘጋጅተሃል ሥጋህንም አሞራዎችና ውሾች ይበሉሃል ንጉሥህ ዲዮቅልጥያኖስም እንዲሁ ለጥፋት ተዘጋጅቷል እኔስ በመድሐኔዓለም ክርስቶስ አምናለሁ ሰማያትንና ምድርን እሱ ፈጥሯል ስለኛና ስለሐጢአታችን እሱ ታመመ እሱ የማይሞትና የማይጠፋ ዘለአለማዊአምላክ ነው። እሱ እንደሞተ ከመቃብርም እንደተነሳ እንዳረገ፣ በአብ ቀኝም እንደተቀመጠ ዳግመኛም በግርማመንግሥት እንደሚመጣ አምናለሁ አንተ ግን ከልብ ነህ ንጉሥህ ዲዮቅልጥያኖስም እንዳንተ ነው" አለው።

ደቅስ መኮንን በዚህ ጊዜ እጅግ ተናደደ ወርውረው በደረቱ እንዲጥሉት አዘዘ አሥር የብረት በትሮችንም በእሳት አግሎ ሁለቱ በዓይኑ ላይ ሁለቱ በጆሮው ሁለቱ በእጆቹ ሁለቱ በእግሮቹ መላ



www.ethiopianorthodox.org

ሰውነቱ እሰኪግል ድረስ ተከለበት ሰውነቱም ጋለ እንዲህ እንደሆነም ከእግሩ ላይ ገመድ አሥረው እየጎተቱ ወደ እስርቤት ወሰዱት ጊዜው መሸቶ ስለነበር መኮንኑ ደቅስ ወደቤቱ ሄደ ግብዣም አደረገ።

ሌሊት ሲሆን ቅዱስ አባኖብ "ስለስቱ ደቂቅን ፀሎታቸው የሰማህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይበዳንኤልም ላይ ያሳየኸው ተአምር ሶስንናንም ከውሸት ምስክሮች ያዳንካት እኔንም ከነዚህ የህግ ወንጀለኞች አድነኝ እነሱ አምላክ የለሾች ናችውና" እያለ በመፀለይ ላይ እያለ ሱርያል የተባለውመልአክ ተገለፀለት የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት አባኖብ ሆይ ፅና እኔ ሱርያል እባላለሁ ኢየሱስክርስቶስ ወዳንተ ልኮኛል አፀናህ ዘንድ በሚደርስብህ ነገር ሁሉ አበረታታህ ዘንድ ተልኬአለሁ በማለት ዳሰሰው ከደረሰበት ሕመም ሁሉም ፈወሰው። ሐይልንም ሠጥቶት ወደሰማይ አረገ።

ሲነጋ በእስክንድሪያ ከተማ የሚሰቃዩበትን ቦታ አዘጋጁበት አማልክተጣኦታቱንም አውጥተው በዚሁ ብዙ ሹቶ ቀብተው አስቀመጡዋቸው መኮንኑ ደቅስ ከዚያ ሲደርስ አባኖብን ያመጡት ዘንድ አዘዘ ሊያመጡት ሲሄዱ ከእሥር ቤቱ እየፀለየ አገኙት እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ነበር በዚሁ ተደነቁ ወደደቅስ መኮንንም አመጡት ይህ ነው አገራችንና ሕዝባችንን ያጠፋ በማለትም ተናገሩት።

በመኮንኑ ፊት ባቆሙት ጊዜም መኮንኑ አገርህ የት ነው ስምህስ ማን ነው በማለት ጠየቀው። አባኖብም ሲመልስ ስሜንና አገሬን ለምን ትጠይቃለህ አለው መኮንኑ "እኔን አትፈራኝምን" ሲል መለሰለት። ቅዱስ አባኖብ በማቴዎስ ወንጌል ነፍሳችሁን



የሚገድሉትን እንጂ ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሩዋቸው ተብሉ ተፅፏል ስለዚህ የፈለግኸውን ፈፅምብኝ በሥጋዬ ላይ ሥልጣን አለህ በነፍሴ ላይ ግን ሥልጣን የለህም ነፍሴ በኢየሱስ ክርስቶስ እጅናትና እኔ ስለሐጢአቴ የዘለዓለም ሕይወትን አገኝ ዘንድ መከራን በሥጋዬ እቀበላለሁ ዘለዓለማዊው ዕረፍት በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ይገኛል ስለዚህ ያንተን ሥጋዊ ቅጣት አልፈራውም ለአማልክትህም ፈፅሞ አልሠግድም" አለው።

መኮንን ደቅስ ባክህ አገርህና ስምህን ንገረኝ አለው ስሜ አባኖብ ይባላል አገሬም ንሂሣ ነው አለው መኮንኑ በል አጭር ቃል ልንገርህ ሞትና ሕይወት ከፊትህ ናቸው ከሁለቱ አንዱን ምረጥ አጽሉን በመልካም ሽቶ አምሮ አታይምን በዓለም ሁሉ እሱን የመሰለ አታገኝም ስለዚህ ብዙ ሐብት እሰጥሃለሁ ታላቅ ሹመትንም እሾማሃለሁ በማለት ያግባባው ጀመር አባኖብ ግን አንተ ከሐዲ ርጉም እኔ ካገሬ ወደዚህ ቦታ የመጣሁት የተለያየ ሥቃይ እንድታደርስብኝ ተብሉ ነው እስካሁን ብዙ ሥጋዊ ቅጣት ተፈፅሞብኛል ግን ከመድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊለየኝ አልቻለም ስለዚህ አንተን ለማስደሰት ብዮ ጌታዮንና መድሐኔቴን ኢየሱስ ክርስቶስን አልክደውም ለጣኦቶችህም አልሰግድም ብሉ መልስ ሠጠው።

መኮንኑ ተቆጣና ቅጣት አዘዘበት ወታደሮቹ ግን እኛ በሱ ደክመናል ያልፈፀምንበትንም ቅጣት የለም ግን ድካማችን ከንቱ ሁኗል። እባቦችን በወጥመድ የመያዝ ልምድ ያላቸው ሦስት ሰዎች ከዚህ አሉ ትላልቅ መርዛሞች እባቦችና ዘንዶዎች አሉዋቸው ስለዚህ ለነሱ አስረክበው አሉት። መኮንኑም የነሱን ምክር በመቀበል ዘንዶዎችና እባቦች ካሉበት አስወሰደው ሦስቱ ዘንዶዎችና እባቦችን የሚያሳድጉ ሰዎች አባኖብን ተረከቡት ከሁለት መቶ እስከ ሦስት



www.ethiopianorthodox.org

መቶ ሰውን በቅፅበት የሚውጡ ዘንዶዎችና በቅፅበት ብዙ ሰዎችን ነድፈው የሚጨርሱ መርዛሞች እባቦች አዘጋጅተናል ሲሉም እነዚህ ሰዎች ለመኮንኑ ነገሩት መኮንኑም አስቸጋሪውን ሰው የማጠፋበት ዘዴ ተከሠተልኝ ብሎ ተደሰተ።

ከሁሉ በማስቀደም አባኖብን እልም ያለ ጨለማ ካለበት የሥቃይ ቦታ አስገቡትና ዘንዶዎቹንና እባቦቹን ለቀቁበት የዘንዶዎቹ ርዝመት ከአራት ክንድ በላይ ነበር ውፍረታቸውም እጅግ አስፈሪ ነበር የተመለከታቸው ሁሉ እጅግ ይፈራና ይደነግጥ ነበር። ነገር ግን እነዚህ ዘንዶዎችና እባቦች አባኖብን ምንም አልነኩትም እንደ ጓደኛቸው አደረጉት ረድኤተ እግዚአብሔር አልተለየውም ነበርና የጨለማውም ቦታ በራ ጨለማው ተገፈፈ።

ሲነጋ ቤቱን ቢከፍቱት አባኖብ ቆሞ እየፀለየ ዘንዶዎቹና እባቦቹ እየሰገዱለት አገኙት ድርጊቱ በከተማው ተሰማ ሁኔታውን ለማየት የከተማው ሕዝብ ግልብጥ ብሎ መጣ ብዙዎችም በዚሁ ተአምር ብቻ ካንድ እግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም እያሉ መሠከሩ ክርስቲያኖችም ሆኑ። መኮንኑ ግን እውነትም እኔ እንደዚህ ሕፃን መሠርይ የሆነ ሰው አላየሁም እኔን ለማዋረድ ወደኔ መጥቷዋል አለ ከእባቦቹም አንዱ አፈትልኮ ሄደና በመኮንኑ አንገት ላይ ተጠቀለለ ነገርግን አልነደፈውም መኮንኑ እጅግ ደንግጦ አባኖብ ሆይ በኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ ስም እለምናሃለሁ ወደአምላክህ ለምነህ ከጥፋት እንድታድነኝ ብሎ ለመነው ከዚያው የተሰበሰቡት ህዝቦችም እንዲፈውሰውና እንዲፀልይለት ለመኑት።

አባኖብ "አንተ እባብ በጌታዩና መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከአንገቱ ውረድ" አለው እባቡም በፍጥነት ከመኮንኑ አንገት ተፈታትቶ ወረደና ወደነበረበት ተመለሰ። ይህን በመመልከት ሳያምኑ



የነበሩ ብዙ ሕዝቦች አመኑ በመስፍንነት መዓረግ የዲዮቅልጥያኖስ ተከታዮች ከነበሩት መሳፍንት መካከል ሦስት መሳፍንት በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ ከክርስቲያኖች ጋርም ሰማእትነትን ተቀበሉ መኮንኑ ደቅስ ግን ከእባቡ መነደፍ ቢድንም ወደክህደቱ ተመለሰ በእጁም 45 ሰማዕታት ተሰየፉ። አባኖብን እንዲከድ ያግባባው ጀመር አባኖብ በበኩሉ ከሸክላ የተሠራ እቃ ከተሰበረ በኋላ ቢጠግኑት ማፍሰሱን አይተውም አንተም እንደሱ ነህ ባንተ አግባቢነት ከኢየሱስ ክርስቶስ ከዘለዓለም ሕይወት ወጥቼ ወዳንተ የጥፋት ጎዳና እንድገባ ትፈልጋለህን በማለት ገሠፀው መኮንን ደቅስም እንደገና ወደእሳት አስገባው እግዚአብሔርም ከመቃጠል ጠበቀው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልፆ የኔ አገልጋይና ወዳጄ አባኖብ ሆይ እስካሁን ባንተ ገድልና ባንተ አማካይነት በሚገለፀው የኔ ሐይል ብዙዎች የመንግሥተሰማያትን አክሊልን ተቀዳጅተዋል አሁን የብርሃን አክሊልን አሳይሃለሁ ካገርህ ስለመውጣትህ ስለደምህ መፍሰስና ስለትዕግሥትህ የክብር አክሊል ይሠጣሃል አለው፣ ልዮልዮስ የተባለው ከክርስቲያኖች አንዱ ጌታችን ቃል ለቃል ሲያነጋግረው አይቶ ወደሱ መጥቶ ሰገደና አንተ ሕፃን ነገሥታትንና

መኳንንትን ያሳፈርክ አንተን የተሸከመች ሆድ የተባረከች ናት የተወለድክባትም አገር የተባረከችናት፣ ያንተ ሥጋ የሚቀበርባት አገርም የተባረከች ናት ያንተንም ስም የሚያስታውስ ሰው የተባረከ ነው አንተ የክርስቶስ ሰማዕት ሆይ ባክህ ትንሽ ጊዜ ሥጠኝ ባንተ ላይ ያየሁትን በጆሮዩ የሰማሁትን እስክፅፍ ድረስ አለው ልዮልዮስ የእሥር ቤቱ ጠባቂ ነበር።

አባኖብ "ወንድሜ ልዮልዮስ ሆይ ጥቂት ውሃ እጠጣ



www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ ፍቀድልኝ አለው ዮልዮስም ተነሥቶ ውሃ ሠጠው አባኖብም ውሃውን ጠጥቶ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ውሃ ይስጥህ ሐጢአትህንም ያስተሥርይልህ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስም ኩነኔ አትይ ብሎ ከመረቀው በኃላ ልዮልዮስ ወንድሜ ሆይ የምለምንህን ስማኝ ሰማእትነቴን ፈፅሜ ሕይወቴ ስታልፍ ሥጋዬን እንድትከፍን፣ ከዚያም ተሸክመህ ወደአባቶቹ አገር እንድትወስደው ከዚያ እግዚአብሔር በሚፈቅደው ጊዜ ሊገለጽ ይችላል የተወለድኩባት መንደር ትንሿ ነሂሣ ናት" አለው።

በዚህ ጊዜ ልዮልዮስ ተቀምጦ በአባኖብ ላይ የደረሰውን ገድል ፃፈ በስተመጨረሻ ሁለቱተነስተው ቁመው ፀለዩ በመጨረሻ ቅዱስ አባኖብ ዮልዮስን ባረከውና ልዮልዮስ ተለይቶት ሄደ ቅዱስ አባኖብ ብቻው ከእሥር ቤት ቀረ መኮንኑም ወታደሮቹን ልኮ የቅዱስ አባኖብን ሁኔታ እንዲመለከቱ አደረገ አባኖብ ተቀምጦ ከፊቱ የተቀዳ ውሃ ተቀምጣ አገኙ። አባኖብ ከቃጠሉ መሬት መጥቶ ውሃን ለመጠጣት እንደጓጓ ሰው ሊጠጣው ሲቃጣ መስሉ ታያቸው "እግዚአብሔርን እየለመነና እያመሰገነም ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ እስካሁን በመከራ ላይ ሳለሁ አልተለየኸኝም መከራዬን አቅልለህልኛል በምህረትህም አስደስተኸኛል" ብሎ ሳይጨርስ ወታደሮቹ ወደአደባባይ ወሰዱት አባኖብ በታሠረበት ቦታ ሁኖ አምላኩ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያመሰግን ውሃ በመጠጫ ተቀድቶ ከፊቱ ላይ ተቀምጦለት አገኘነው አሉት መኮንኑም እንደክርስቲያኖች ችግር የፈጠረብኝ የለም ከሁሉ በባሰ ደግሞ ይህ ሕፃን ባስቸጋሪ ሁኔታ ብዙ ተፈታተነኝ እሱ ትልቁ የሥራይ ሰው ነው አለ።

ልዮልዮስ አስቀድሞ የአባኖብን ታሪክ ፅፏል የእሥር ቤቱ የጥበቃ ክፍልና የመኮንኑ ደቅስ ፀሐፊ ነው። ይህ ሰው በዚህ ጊዜ ለመኮንኑ ደቅስ እንዲህ ሲል መለሰለት "አንተ ይህን ሕፃን



ባሰቃቂ ቅጣት እገድለዋለሁ ብትል አምላኩ ይታደገዋል አይሞት ልህም አንተም በመኳንንትህ ፊት ትዋረዳለህ ታፍራለህም አሁን ችላ በለውና ጥቂት ዕረፍት ያድርግ አለው ልዮልዮስ ቅዱስ ሰው ነበር ለቅዱሳን ሰማዕታትም ብዙ መልካም ሥራ ሠርቷል በረከታቸውን ለማግኘት ሰማዕታትን ይገንዛቸው ነበር።

መኮንን ደቅስ ወታደሮቹን እንዲህ አላቸው "ይህን ክፉ ሰው ከከተማው ወደውጭ አውጡትና አንገቱን በሥለታም ሰይፍ ቁረጡት እኛም በሱ ምክንያት ከሚፈጠርብን ጭንቀት እንዳን ዕረፍትንም እናግኝ" አላቸው። ወታደሮቹም ቅዱስ አባኖብን አውጥተው ከዛፍ ላይ ግራና ቀኝ እጆቹን ወጥረው ካንድ ዛፍ ጋር ካሠሩ በኃላ አንገቱን ለመቁረጥ ተዘጋጁ፣ ቅዱስ አባኖብ በዚህ ጊዜ ወታደሮቹን ወንድሞቼ ሆይ ጥቂት ደቂቃ እንድትታገሱኝ እለምናቹኃለሁ ስላላቸው እነሱም የጥቂት ደቂቃዎች ጊዜ ሠጡት በዚህ ጊዜ ቅዱስ አባኖብ እጅግ ጮኾ "ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ስለስምህ በዚህ ዓለም መከራ ተቀብያለሁ ነፍሴን ተቀበል የሲኦል መኳንንት ነፍሴን እንዳያስጨኑቋት እኔ ያላያኋቸው ፀዋጋን መናፍስት እንዳይታይዋት የእሳት ነበልባልና ሞገዱ አይከሰቱብኝ ብርሃናውያን መላእክት ይቀበሉኝ ፀጋህን ለሥጋዬ ሥጥ" በማለት ፀለየ። ወድያው ወታደሩ ሠይፋን አንሥቶ አንገቱን ቆረጠው ሐምሌ 24 ቀን ቅዱስ አባኖብ አረፈ። ዕለቱ እሁድ ዘጠኝ ሰዓት ነበር።

ፀሐፊው ልዮልዮስ እስከመንፈቀሌሊት ሲጠበበቅ አድሮ የቅዱስ አባኖብ አስከሬን ወደወደቀበት ሄደና ወድቆ አገኘው በግምጃም ገንዞ መልካም መዓዛ ያለውን ሹቶ አርከፈከፈበት በትንሽ ታንኳም ጭኖ ከሦስቱ አገልጋዮቹ ጋር በመሆን ለሦስት ቀን ተጉዞው ከትውልድ አገሩ አደረሱት ያገሩ ሰዎችም የቅዱስ አስከሬን



www.ethiopianorthodox.org

መጣልን በማለት ተሰባሰቡ በድብቅም ተሸከመው በመንበረታቦት ሥር አስቀመጡት ዘመነሰማዕታት አልፎ ዘመነ ሰላም እስኪሰፍን ድረስም ከዚሁ ውስጥ ደብቀው አኖሩት።

አባኖብን ጨምሮ በዘመነ ሰማዕታት ሰማዕትነትን የተቀበሉ ቅዱሳን 19 እልፍ 84 ናቸው። ልዮልዮስ ስለቅዱስ አባኖብ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ያሻነፈ ታላቅ ቅዱስ ነው ለክርስቲያኖችም መልካም አርአያ ሆኗል አንድ ሕፃን ያን ያህል መከራ ታግሦ ዓለምን ሲያሸንፍ እኛስ ክርስቲያኖች ለምን የፍቅር አንድነት አይኖረንም በበኩሌ ከሱ ብዙ ተምሬ ፍኖተእግዚአብሔርን ተከትያለሁ እያለ ምክሩን ለግሦናል።

## ምዕራፍ ፲፫ የሦስት ደናግለሮሜ ጲስጢስ፣ አላጲስና አጋጲስ ሰማዕትነት

ፍፁም የሆነ የሕይወት ቃል በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ በታች ለሁሉም በተዘራ ጊዜ ብዙዎች በእግዚአብሔር አመኑ ለማይጠቅም አምልኮ ጣኦትም ከመገዛት እየወጡ የሐጢአት ሥርየትን አገኙ። ነቢያት፣ ሐዋርያት ወንጌላውያንና መምህራን ኢየሱስ ክርስቶስን መሠረት አድርገው ሰዎች እንዲድኑ አስተምረዋል።

ሶፍያ የምትባል ደግ ሴት ነበረች ባለፀጋም ነበረች እሷ ወደሮሜ ሄደች ሶስት ሴቶች ልጆቿም አብረው ሄዱ ሶስቱ ሴቶች ልጆቿ ውበታቸው እጅግ የሚያማምሩ ነበሩ። ከሦስቱ ሴቶች ልጆቿ ጋር የኢየሱስ ክርስቶስን እምነት ለመቀበል ፈለገች ሦስቱ ሴቶች ልጆቿ በእግዚአብሔር ፀጋና ጥበብ ታሳድጋቸው ነበር። እነዚህ ሴቶች የቅድስት ሶፍያ ልጆች በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እጅግ



የጠነከሩ ለሥጋቸው ቅንጣት ያህል የማይሳሱ ሆኑ በዚህም ሦፍያ እጅግ ደስተኛ ሆነች። እግዚአብሔርንም እጅግ ታመሰግን ነበር። የእግዚአብሔር ፀጋ በሶስቱ ልጆቿ እንዲበዛና ጥብአታቸው የጎላ እንዲሆን እየመላለሰች ወደእግዚአብሔር ትፀልይ ነበር።

ሦስቱ ጲስጢስ አጋጲስና አላጲስ ገና ሕፃናት ነበሩ እንጂ ለአቅመ አዳም ምንም አልደረሱም ነበር። በፀጋ እግዚአብሔርና በሃይማኖት ፅናት ግን እጅግ ትልቆች ሆኑ። መፃሕፍተሐዲስትንና የሐዋርያትን ሥራ ደግሞ በሚገባ ተማሩ። በየሳምንቱ በእለተሰንበት ወደቤተክርስቲያን እየሄዱ ስብሐተእግዚአብሔርን ይሰሙና ቅዱስ ቁርባንን ይቀበሉ ነበር።

አጢዎኮስ የሚባል መኮንን ሶፍያንና ልጆቿን በሥይማኖዊ መንገድ ተመለከታቸው ሁኔታቸውንም አጠና። ከዚህም ኢያይዞ ሶፍያንና ልጆቿን አድርያኖስ ከተባለው የሮም ንጉሥ ዘንድ ከሰሳቸው የክሱም አቀራረብ እንደዚህ የሚል ነበር "አንዲት ሴት ከሦስት ሴቶች ልጆቿ ጋር በከተማችን ትገኛለች ከየት ስትንቀዠቀዥ እንደመጣች አናውቅም ሚስቶቻችን አለምን ሁሉ በያዘ እግዚአብሔርና በልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንዲያምኑ ከማድረጓም በላይ በምሳ ሰዓት እንኳ ምሳ እንዲበሉ ወደቤት አይመጡም እሷንና ሦስቱን ሴቶች ልጆቿን ብቻ መከተል የየዕለቱ ሥራቸው ሆኗል የአማልክቶቻችን ክብር በነሱ ተሠርዟል።"

ንጉሥ አድርያኖስ ይህን ከሰማ በኋላ በፍጥነት ወታደሮቹን ወደነሱ ላከ ወታደሮቹም ሦስቱን ቅዱሳት ሴቶች ልጆች ከናታቸው ጋር ታሥረው ወደንጉሡ ተወሰዱ ከቤተመንግሥቱ ቅጽር አጠገብ ሲደርሱ አራቱም ፊታቸውን በትእምርተመስቀል አማተቡ። የእግዚአብሔር ፀጋም አልተለያቸውም በየደረሱበት ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

ይከተላቸው ነበር።

ንጉሡ አድርያኖስ በቤተመንግሥት ቆይቶ ሲመለከታቸው ውበታቸውን በመመልከት እጅግ ተደነቀ ሊያነጋግራቸውንም ፈራ እጅግም አከበራቸው ብዙ ከተቸገረም በኋላ ቅድስት ሶፍያን አቅርቦ አንቺ ምንድርነሽ ስላንቺስ የምሰማው ምንድር ነው የሮምንስ አማልክት እንዴት ትክዳለሽ የሮሜ አማልክት አለምን የፈጠሩ ናቸው አንቺ ክርስቲያናዊት ከሆንሽ ግን አስቀድመሽ ስምሽን ንገሪኝ አላት። ቅድስት ሶፍያ እኔ የእግዚአብሔር ባርያ እባላለሁ፣ ክርስቲያኖዊት ነኝ ወላጆቼ ግን ሶፍያ ብለው ሰይመውኛል ዘመዶቼም ደጋግ ናቸው መድሐኔዓለም ክርስቶስ በመሪነቱ ወደዚህ አገር እን ድመጣ ፈቀደ እነዚህን ሦስት ልጆቼ መባ አድርጌ እንዳቀርብለትም ጠራኝ አለችው።

አድርያኖስ በቅድስት ሶፍያ አባባል ቶሎ አልተቆጣም በመልካም መስተንግዶ ከደህና ቤት ከነልጆቿ እንድትስተናገድ አደረገ። ከነልጆቿ ያስተናገደ ሰው ጳላድስ የሚባል ደግ ሰው ነው በዚሁ ሰው ቤት በመስተንግዶ እያሉ ቅድስት ሶፍያ ሦስቱን ልጆቿ በእምነታቸው ስታበረታታቸው ስታፅናናቸውና ስታስተምራቸው አደረች ራሳችሁን ጠብቁ ተስፋችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተመሠረት ነው እሱ ያፅናቹኋል ሕፃንነታችሁን ብቻ አትመልከቱ እናንተ የእግዚአብሔር ገንዘቦች ናችሁ ሽልማታችሁ ፀጋእግዚአብሔርና ሰማዕትነት ነው የናንተ ቅድስና የኔን ሐጢአት ያስተሥርይልኛል የናንተ ጥብአት የዘለዓለማዊው ንጉሥ አሽከሮች ያደርጋቹኋል ካሁን ጀምሮ ከእግዚአብሔር ዘንድ እናንተ አማላጆች ሁናቹኋል እናንተ ሕፃናት ልጆቼ የመንግሥተሰማያት ሙሽሮች ናችሁ እንኳን እናንተ እኔንም በናንተ ገድልና ፅናት በኋላ ዘመን ክርስቲያኖች



ያነሱኛል ከዚህ ሁሉ በበለጠ ግን እኔም ሆንኩ እናንተ የኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘቦች በመሆናችን መንግሥተሰማያትን እጅ የማድረግ ዕድል ማግኘታችን ነው። ልጆቼና አስተማሪዎቼ እኔን አስተምሩኝ እናታችሁን አስተምሩ ሊያሰናክላችሁ የሚቃጣውን ፍቅረዓለም ተጣሉት አታስጠጉት እነሆ ዓለምን ለያዘ እግዚአብሔርና ለልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን ተሠጥቷቹኋል እግዚአብሔር ትዕግሥትንና አሸናፊነትን ያቀዳጃቹኋል ትላቸው ነበር።

ሦስቱ የቅድስት ሶፍያ ሴቶች ልጆች ጲስጢስ፣ አላጲስና አጋጲስ የናታቸውን ምክርና ምዕዳን በልባቸው ያበቅሉትና ያሠርፁት ነበር ፍሬፀጋመንፈስ ቅዱስና ጥበብም በሕይወታቸው ሞላ እግዚአብሔር ሰማዕትነትን ለመቀበል እንዲያድላቸውና እንዲያፀናቸውም ተግተው ይፀልዩ ነበር የገድላቸውንም ዋጋ በመንግሥተሰማያት ያድላቸው ዘንድ እግዚአብሔርን በፀሎት ይለምኑት ነበር ደስ እያላቸውም ለእናታቸው እኛ በእግዚአብሔር እምነታችን የፀና ሁኗል ከፍጡራን ወደሚቃጣው ኩነኔ አቅሪብን በዚሁ በኩል ብቻ ወደመንግሥተሰማያት እንድንሸጋገር ተዘጋጅተናል ፅናታንን ገድላችንና እምነታችንን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተካክልናል ንፁሕ ህጉን ተምረናል እሱ ብቻ ድካማችንን ይመለከታል እኛም በሃይማኖት መሰላልነት ወደሱ እንወጣለን የመንፈሳዊ ጥበብ ተሸላሚዎች እንሆናለን ንጉሡ ለሚጠይቀን የምንሠጠውንም መልስ እሱ ይሠጠናል አሏት።

ቅድስት ሶፍያ የሦስቱ ሕፃናት ቅዱሳት ልጆቿ ጥበአትንና መንፈሳዊ ጥንካሬን ባወቀች ጊዜ ልጆቼ ሆይ እኔ እናንተን የወለድኩዋችሁ በዚህ በሚያልፈው ዓለም በሚቀር ሕይወት ብቻ ነው በትንሿ ትዕግሥታችሁ በዚህ ቀን ያልፋል የማይባለውን



www.ethiopianorthodox.org

መንግሥተሰማያት ትወርሳላችሁ እኔም ፍፁም የሆነ ንፁሕ መሥዋእትን ለእግዚአሐር በማቅረብ እናንተን እከተላለሁ አለቻቸው። ቅድስት ሶፍያ ከሦስቱ ቅዱሳት ሕፃናት ልጆቿ ለመስተንግዶ ባረፉበት ቤት ሦስት ቀን ሰነበቱ ከሦስቱ ቀን በኋላ ግን ንጉሡ ወደሱ ያቀርቡዋቸው ዘንድ አዘዘ ንጉሡ ወደሱ እንዲያቀርቡዋቸው ያዘዘው ሦስቱን ሴቶች ሕፃናትን ነው። እናታቸው ቅድስት ሶፍያግን ለጊዜው እንድትቀርብ አልተጠራችም ስለዚህ ሦስቱን ሕፃናት ወታደሮቹ ለይተው ሲወስዱዋቸው ቅድስት ሶፍያ ከበስተኋላ ራቅ ብላ ትከተላቸው ነበር ደስታዋም እጅግ ከፍተኛ ነበር። ወደቤተ መንግሥት ሲገቡ ንጉሡ አድርያኖስ እናንተ ሴቶች ልጆች ደም ግባታችሁና ውበታችሁ እጅግ ያማረ ነው ከሰው የተፈጠራችሁ አትመስሉም አካላችሁና መጠናችሁ ደግሞ ትንሽ ነው ገና እድገት የሚጠብቃችሁ ለጋ ሕፃናትናችሁ ስለዚህ የእናታችሁን ታላቅነት፣ የናንተን ትንሽነት ከጥፋት እንድትታደጉ የምላችሁን ልብ ብላችሁ ስሙኝ በአባትነት ደረጃም ተመልከቱኝና አድምጡኝ የኀለም ነገሥታት ለሆኑ አማልክት መሥዋእት አቅርቡ እኔም ልጆቼ አደርጋችሁ አለሁ ካሁን ጀምሮ ባላችሁ መልካም ውበት ላይ የንጉሥ ልጆች ተብላችሁ ተሠየሙበት ለዚህም ዝግጁዎች ሁኑ። በናንተ የኔ ልጆች መሆን ምክንያት መኳንንቶቼን መሳፍንቶቼን የጦር አለቆቼንና መላ ሠራዊቴን ሰብስቤ ታላቅ የደስታ በዓል አደርጋለሁ።

ከዚህ ውጭ ግን ይህን ሁሉ የመከርኳችሁንና የሠጠኋችሁን ዕድል ወደጎን ጥላችሁ እንቢ ብትሉኝ የተለያዩ እጅግ የሚያስጨንቁና ሠጋለባሽ ላንዲት አፍታ እንኳ ሊሸከሟቸው የማይችለውን ቅጣቶች እፈፅምባችሁ አለሁ እናንተ ደግሞ ሕፃናት ከመሆናችሁም በላይ የሰውነታችሁ መልካም ደምግባት ፈፅሞ የማይችለው ነው። ብዙ



ቅጣት ከተፈፀመባችሁ በኃላ አካላታችሁ ቆራርጬ ለውሾች እሠጠዋለሁ አሁንም ቢሆን እናንተን ለሥቃይና ለመከራ አሳልፌ ከመሥጠቴ በፊት ያላንዳች ማመንታት እሺ በሉኝ አላቸው።

እነዚያ ቅዱሳት ለጋ ሕፃናት ሴቶች ባንድ ቃል እኛ እንዲህ ያለውን አንፈልግም እኛ የጠራንን ንጉሣችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናውቀዋለን አባታችን እሱ ነው እኛም ልጆቹ ነን እሱእኛን ይቀበለናል የኢየሱስ ክርስቶስ መድሐኒዓለም ጥሪቶች ነን ያንተን ቅጣት ለመቀበል ተዘጋጅተናል እኛ የመድሐኒዓለም ክርስቶስ ልጆች ሁነን ያንተን ልጆች ለመሆን አንችልም ካሁን ጀምሮ በሥጋችን ላይ የምታደርገውን ሁሉ ፈፅምብን ከዚሁም የእግዚአብሔርን ሐይል ለማየት ትችላለህ ሁሉን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው ሲሉ መለሱለት። በዚህ አድርያኖስ ንጉሥ እጅግ ተቆጣና እናታቸውን ቅድስት ሶፍያን ለጥያቄ ጠራት።

ቅድስት ሶፍያ ስትቀርብ የሦስቱ ሴቶች ሕፃናት ልጆችሽ ስም ማን ማን ይባላል ዕድሜያቸውስ ስንት ይሆናል ሲል ጠየቃት። ቅድስት ሶፍያም ትልቋ ልጄና የመጀመርያዬ ስሟ "ጲስጢስ" ይባላል ዕድሜዋ አሥራ ሁለት አመት ነው የሁለተኛዋ ስም "አላጲስ" ነው ዕድሜዋም አሥር አመት ሁኗል ሦስተኛዋ ልጄ "አጋጲስ" ትባላለች ዕድሜዋ ፍፁም ዘጠኝ አመት ነው ስትል አስረዳችው።

ንጉሡ አድርያኖስ ትልቋን አላጲስን አሥጠራትና ስትቀርብ "ለትልቁ አምላክ አርሰጤንስ መሠዋት አቅርቢ ከዚህም ላይ ከለጋ ሕፃንነትሽ በተጨማሪ ውበትሽን ተመልከቺ" በማለት አዘዛት ቅድስት ጲስጢስ ሁሉን በቃሉ የፈጠረውን እግዚአብሔር በዕብደታቸው መታወር ለሚተውት ወዮላቸው መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ አስተምሮናል "ነፍስ የሌለውን የድንጋይ ምስልእውቀት የሌለውን



www.ethiopianorthodox.org

ጣኦት የሚያመልኩ እንዳሉ እናውቃለን" አለችው። ንጉሥ አድርያኖስ በዚህ ጊዜ ልቦናው በንዴትና በቁጣ ተሞላ ወድያውም ልብሷን ገፈው ዕራቆቷን በማውጣት እስከታምን ድረስ እንዲገርፏት አዘዘ። ባዘዘው መሠረትም አሥራ ሁለት ወታደሮች ዕራቆቷን አውጥተው እየተፈራረቁ ገረፏት ግን ሁሉም ሲቀጠቅጧት በትዕግሥት ቻለችው እግዚአብሔር ከሷ በረድኤት አልራቀምና። ነፍሴን መግደል አትችልም ሥጋዬን ግን እንደፈለግኸው ግደለው አንተ ለረከሱ የድንጋይ ጣኦታት ራስህን ያስገዛህ ከሐዲ ንጉሥ ነህ በማለትም ገሠፀችው የሷን ጥብአት ከተመለከቱ ሰዎች መካከል ይህቺን ለግላጋ ሕፃን እየተፈራረቃችሁ ስትቀጠቅጡ ሐፍረት አይሰማችሁም ወራዶች ናችሁ የፈለገችው ብትል እቺ ሕፃን ለመገረፍና ለመገደል ደርሳለች? በማለት የተቃውሞ ቃላቸውን አሰሙ ቅድስት ጺስጢስም ንጉሡን እኔ ከጌታዩና መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሁኜ አሸንፋሀለሁ አንተ የማይናገረውን ከድንጋይ የተሠራ ጣኦት ታመልካለህ ተያይዛችሁም ትጠፋላችሁ እኔን ዕራቆቴን አውጥተህ ብትገርፉኝና ብታሠቃዩኝ አላፍርም በሃይማኖቴ የፀናሁ ነኝና አንተ ግን በድንቁርናህ ታፍራለህ ጌታዩና መድሐኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢምንት በሆንኩት ፍጡር አማካይነት ያሳፍርሃል አለችው።

ንጉሥ አድርያኖስ በቅድስት ጺስጢስ የደረሰበትን ሽንፈት እጅግ አሳበደው "የከሰልን ክምር በብረት ላይ አቀጣጥለው ፍም ሲሆን ወደዚያ ቅድስት ጺስጢስን እንዲወረውሯት አዘዘ እነሱም ወደዚሁ ወረወሯት ነገር ግን እግዚአብሔር ጠበቃት ነበልባሉ ጠፋ አልተቃጠለችም እንደሠረገላ ሁኖ የፍሙ ክምር በሕይወት ተሸከማት። እሷም በከፍተኛ ድምፅ ጌታዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በኔ በባርያህ ላይ ተመልከት በዚህ ከሐዲ ንጉሥም እንዳልሸነፍ



ሐይልን ሥጠኝ"አለች በተጣለችበት የፍም ክምር ላይም ከሦስት ሰዓት በላይ ቆየች።

ንጉሥ አድርያኖስ ከዚሁ አውጥተው የተለያዩ መርዞች ከተሞላ በርሜል ውስጥ እንዲከቷት አዘዘ ወታደሮቹም የተለያየ መርዝ ከተሞላ በርሜል ለማስገባት ሲወስዷት ፊቷን ታማትብ ነበር ስመእግዚአብሔርንም በማንሳትም ትፀልይ ነበር በገዛ ራስዋ ተወርውራ ወደ በርሜሉ እንድትገባ ወታደሮቹ አዘዟት እሷም አምላኬና ፈጣሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለስምህ መከራውን ለመቀበል ተዘጋጅቻለሁ ብላ በመወርወር ከቤርሜሉ ገባች። አካላትን ከሩቅ የሚበጣጥሰው ይህ መርዝ ምንም አልነካትም በዚህ ጊዜ ንጉሡ አድርያኖስ በከባድ ሐፍረትና ውርዴት ተዋጠ። በፈለገውም መንገድ ሊያሳምናት ወይም ሊገድላት ባለመቻሉ ከንዴትና ብስጭት የተነሳ የሚሆነውን አጣ ምን ቅጣት በሷ ላይ መፈፀም እንዳለበትም ሊያገኝ አልቻለም በስተመጨረሻ በሰይፍ አንገቷን ለማስቆረጥ ወሰነ። በሠይፍ ሊያስቆርጣት መወሰኑን ስትሰማ እጅግ ደስ አላትና እናቷን ቅድስት ሶፍያ ፈቃደ እግዚአብሔር ሁኖ ይህን ዓለም በአሸናፊነት እንድትለየው ትፀልይላት ዘንድና የቀሩትም ሁለት እህቶቿ እንድታፅናናቸው አደራ አለቻት ለእህቶቿም እህቶቼ ሆይ በህብረት ነው ክርሰቶስን ያመነው ለዚህ ታላቅ ክብርና ሰማዕትነት እግዚአብሔር በናታችን አማካይነት ጠርቶናል ስለዚህ ታገሱ በሃይማኖታችሁም ፅኑ። እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን ለተወሰነ ጊዜ ይህቺን ዓለም አየናት ካንዲት እናትም ተወልደናል። እቺ እናታችን ምንኛ ቅድስት ናት፣ እኛ ሰማዕትነትን ለመቀበል ስንዘጋጅ ትደሰታለች የኛንም የመጨረሻ ፅናት ለማየት እጅግ ትጓጓለች እቺን የመሰለች ቅድስትና ለዘለዓለም ክብርና የእግዚአብሔር ፀጋ ልጆቿን የምታዘጋጅ እናት እግዚአብሔር ሠጠን ከዚህ በላይ



www.ethiopianorthodox.org

ደግሞ ስለኛ ወደእግዝአብሔር ትፀልያለች። ስለዚህ እህቶቼ ሆይ መድሐኔአለም ክርስቶስን አናሳዝነው እናታችንም ደስ እናሰኛት እያንጻንጻችን በሆድዋ ዘጠኝ ወር ተሸክማናለች። ከተቀደሱ ጡቶቹዋም ወተትን ጠብተናል፣ የእግዚአብሔርን ጥበብም አስተምራናለች ካሁን በኋላ እኔ ትክክለኛውን መንገድ ተከትዩ መሄዴ ነው። ስለዚህ የተወደዳችሁ እህቶቼ ሆይ የኔን ኮቴ ተከተሉ ሳጭር ጊዜ ሕይወት ስትሉም እግዚአብሔርን እንዳትክዱ፣ መልካሙን የእግዚአብሔር አፈጣጠራችን ሳናበላሸው ለእግዚአብሔር ማስረከብ አለብን ወድያውም እግዚአብሔር ለኛ ያዘጋጀውን መንግሥተሰማያት እንወርሳለን በማለት በጥብቅ አደራ አለቻቸው።

ይህን ሁሉ ተናግራ ስትጨርስ ከቅድስት ሶፍያ እናቷ ጋር አንገት ላንገት ተቃቅፈው የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ በተሞላበት መንፈስ ተሳሳሙ እናቷንም እንድትፀልይላት ማለደቻት። እጅግም በመደሰት ላይ ነበረች። እንዲሁም ከቅዱሳት እህቶቿ ጋርም አንገት ላንገት በመተቃቀፍ ተሳሳመችናሁሉንም ተሰናብታ አንገቷን በሠይፍ ለመቆረጥ አዘጋጀች። እናቷና እህቶችዋም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ያወድሷት ነበር። መልካሟ የኛ እመቤት በፈቃድሽ ሰማዕትነተን ተቀበይ ሰይፍን አትፍሪ መልካሙን የእግዚአብሔር መንገድ ተጓዢ እኛም ያንቺን ፈለግ እንከተል ዘንድ በአፀደ ነፍስ ሁነሽ ለምኝልን ፀልይልን ጥቡአን ሁነን ጠላትን እናሸንፈውና ከንቱ ሂደቱንም እንቃወም ዘንድ። አሁን መልካሙን መንገድ ልትጓዢው ነው እኛንም እህቶችሽን አስቢን በመንግሥተሰማያት እኛንም ትቀበይናለሽ አሏት።

ቅድስት ሶፍያ እናቷም "ልጄ ጲስጢስ ሆይ እኔ ወለድኩሽ በጥበብ ወተትም አሳደግሁሽ በጥብአትም አፅናናሁሽ በደስታ



ወደዘለዓለማዊው ብርሃን ተጓዥ የዚህ ዓለምን አታላይነት አታስቢ እሱ ሐላፊ ነውና ጥቂት ታገሽ ፍፅምት ሁነሽ እኔንና እህቶችሽን ወደብርሃን ትመሪን ዘንድ" በማለት ተሰናበተቻት አንገቷን ለመቆረጥ ሰይፍ ይዘው ሲጠጉ ተመልክታ እጆቿን ወደላይ በማንሳት "ጌታዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አመሰግንሃለሁ እኔን ሐጢአተኛዋን ለዚህ ስላበቃኸኝ እኔን ባርያህንም ስላልተውከኝ አመሰግንሃለሁ ባሮችህ ሴቶቹም ወንዶቹም አስባቸው እናቴንም አስባት ከኔ ጋር ካንዲት ሆድ የወጡትንም እህቶቼ አስባቸው" በማለት ፀለየች ይህንን እንደ ጨረሸች በሠይፍ አንገቷን መቱዋት እናቷም ደስ እየተሰኘች አስከሬንዋን አቀፈችው ሳመችውም እግዚአብሔርንም አመሰገነች ቅድስት ጲስጢስም ሰማዕትነቷን ፈፀመች።

ንጉሡ አድርያኖስ ሁለተኛዋን እህቷ አላጺስን ማባባል ጀመረ እንዲህም አላት "ልጄ ሆይ እሺ በይኝ እኔን እንዳባት ተመልከችኝ አርጤምስ ለተባለው አምላክም ሥግጂ ለሕይወትሽም አስቢ" ቅድስት አላጺስ ስትመልስለት እንዲህ አለችው "ንጉሥ ሆይ እኔን ለማስከዳት ታባብለኛለህ ነገርህ ከንቱ ነው በዛሬው ለተሠየፈችው ጲስጢስ እኔ እህቷ ነኝ ራስህን አታልል እንጂ እኔን ማታለል አትችልም የፈለግኸውን በኔ ላይ አድርግ በጨካኝነትህ ታዋቂነትን እያገኘህ ነህ በዛሬው እለት አንገቷ ከተቆረጠችው እህቴ ጋር ካንድ ሆድ የወጣን ነን እናታችንም አንዲት ናት።"

ንጉሡ አድርያኖስ ዕራቆቷን አስወጥቶ በጅራፍ አስገረፋት ቅድስት አላጺስ የ፲ ዓመት ልጅ መሆንዋን ከላይ ገልፀናል። ቅድስት ሶፍያ ቁማ እግዚአብሔር ፅናቱን ይሠጣት ዘንድ ጌታዩ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ልጄን ትዕግሥትንና ፅናትን ሥጣት እንደ



www.ethiopianorthodox.org

ፊተኛዋ ልጄ በፅናት እንድትጋደልም ትሁን ትል ነበር። ቅድስት አላጺስም እናቷ የምትፀልየውን ፀሎት ሰምታ በከፍተኛ ድምፅ እየጮኸች አምላኬና ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የአሸናፊነትን ሐይል ሥጠኝ በማለት ፀለየች።

ንጉሥ አድርያኖስ ከግርፋት ብዛት ትመለሳለች ብሉ ስለገመተ ሁኔታዋን ለማየት መጣ ቅድስት አላጺስ ግን ገና ስታየው ሐይል የእግዚአብሔር ነው። አንተና መንግሥትህ ታልፋላችሁ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ግን ለዘለዓለም ይኖራል አንተ በያዝከው ሥልጣን ትመካለህ እኔ ግን በዘለዓለማዊው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ እመካለሁ አለችው አድርያኖስ ከንዴቱ የተነሳ ከእሳት ውስጥ አስገባት እሳቱ ግን በእግዚአብሔር ሐይል ጠፋ። የእግዚአብሔር አገልጋይ አላጺስ ግን እግዚአብሔርን እያመሰገነች እንዲህ አለች እግዚአብሔለር አምላኬ ሆይ ችላ አትበለኝ ትዕግሥትን ሥጠኝ በፊትህ ፀጋንና ይቅርታን አገኝ ዘንድ።

መኮንን አድርያኖስ እንደገና ከዛፍ ላይ እጆቿን አሥረው በማንጠልጠል እንዲገርፏት አዘዘ ሰቅለውም ገረፏት ንጉሡም ቆሞ ይመለከት ነበር። ቅድስት አላጺስ አንተ ከሐዲ ንጉሥ በመንፈስህ ይህ ነው የማይባል ጭንቀት ተከማችቶብሃል የሰውን ሕይወት ባጠፋህ ቁጥር የህሊና ወቀሳ ሕይወትህን ያቃጥለዋል ትዕቢትህም አንዱ ታላቅ በሽታ ነው ደስታ ያለው ሕይወት የለህም እኔስ ነፍሴን እታደጋለሁ ያንተ በሽታ የለባትም እኔ ጤነኛ ነኝ እንዳንተ አልታመምኩም በሽተኛው አንተነህ አለችው ንጉሡ ቢቸግረው በእህቷ ላይ እንዳደረገው የተለያዩ የመርዝ አይነቶች ወደተሞላ ጋን ከተታት ከዚህም እግዚአብሔር አዳናት መርዙ እሷን ሳይነካ ባካባቢው የቆሙትን የንጉሡ ወታደሮች በመጥፎ ሽታው እንዲበከሉ እንዲታመሙና በከባድ ጭንቀት

እንዲያዙ አደረገ።

አድርያኖስ በሠይፍ አንገቷ ተቆረጣ የመጨረሻውን ቅጣት ታግኝ ብሉ ስላዘዘ እየሮጠች እናቷ ወደቆመችበት ሄደችና አንቺ ቅድስት እናት ደህና ሁኚ በማለት አንገቷን አቅፋ ሳመቻት በመቀጠልም የዘጠኝ አመት ታናሽዋ እህቷን አጋጺስን አንገቷን አቅፋ እህቴ ሆይ ከኔ ዘንድ ፈጥነሽ ነይ እኔ መሄጄ ነው የምሄድበትም መንገድ ወደዘላዓለም ሕይወት የሚወስድ ነው ሕይወቱም ዘለዓለማዊ ነው ነገር ግን አትፍሪ ለዚህ ታላቅ ፀጋ የጋበዘን እግዚአብሔር አምላካችን ከኛ ጋር ነው አይለየንም አለቻት።

የእናቷንና እህቷን ስንብት ጨርሳ ወደእግዚአብሔር እንዲህ ስትል ፀለየች "አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ እኔን አነስተኛ አገልጋይህን በሰላም ተጋድሎዬን አስፈፅመኝ" እናቷ ቅድስት ሶፍያም በቅድስት አላጺስ የተጋድሎ ጽናት ደስ ስላላት "አንጀቴ ልጄ ሆይ ደስ እያለሽ መንገድሽን ቀጥይ እኔ እንደወለድኩሽም አስቢ" እያለ አፅናናቻት።

ሕፃን የአሥር ዓመት ልጅ አላጺስ ወድያው በሰይፍ አንገቷ ተቆርጣ ሰማዕትነትን ተቀበለች ተጋድሎዋንም ፈፀመች ባሸናፊነት የሰማዕታትን ክብር በመቀዳጀቷም እናቷ ቅድስት ሶፍያ ተቆርጦ ለብቻ የተጣለውንም ራስዋ አንስታ አቀፈችው ከቀረው አካላትዋ ጋር በማገናኘትም ገነዘቻት አስከሬንዋንም ሳመችው በሰላም ሁለቱን ልጆቼ ወደእግዚአብሔር ሸኘኋቸው ሁለቱ በዓለም አልተሸነፉም አለሙን አሸንፈውታል ብርቱዎች ናቸው በቀና መንገድ ሊጓዙ ችሏል አለች ፊቷንም ገና ሰማዕትነት ወደሚጠብቃት ትንሿ ልጅዋ አጋጺስ አዞረች ከፍርሐትና ከጥርጣሬ የራቀች ሁና ሰማዕትነትን ለመቀበል ስትጓጓ አይታ እጅግ ደስ አላት "ሦስተኛዋና ትንሿ


www.ethiopianorthodox.org

ልጄ ሆይ ደስ ይበልሽ ጥብአትም ይደርብሽ የምትጓዢበት መንገድ ወደዘለዓለማዊው መንግሥተሰማያት የሚወስድነው የሁለቱን ልጆቼ አክሊለመንግሥተሰማያትን ለማየት በቅቻለሁ ካሁን ጀምሮ የሥጋ መከራ በተራው ወዳንቺ ሊመጣ ነው ልጄ ሆይ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በርቺ" አላቻት።

ንጉሥ አድርያኖስ ሰአቱን ጠብቆ ቅድስት ሕፃን አጋዺስ እንድትቀርብ አደረገ ሕፃንነቷንም አይቶ ብዙ የማታለል ቃል ተናገራት እሷ ግን እስካሁን ሰማዕትነተን ከተቀበሉት ሁለት እህቶቼ ከወጡበት ሆድ መውጣቴን አታውቅምን እናታችንስ አንዲት መሆንዋን አልተረዳህንምን አባታችንምአንድ ነው የእግዚአብሔር ቃል ይህን አስተምሮናል የእግዚአብሔር ቃል ለፍጡር እንዳንሰግድ ለሱ ብቻ እንድንሰግድ አምልኮባእድ የዕብዶችና የአጋንንት ተግባር መሆኑን ከእግዚአብሔር ቃልተምረናል እናታችን ባንዲት መንገድ ነው ያሳደገችን መንገዱም አምልካተእግዚአብሔር ነው። የቀደሙት እህቶቼ የተማሩትን ሁሉ እኔም ተምሬአለሁ እኔ አሁን የምጓጓው እንደቀደሙት እህቶቼ ሰማዕትነተን ለመቀበል ብቻ ነው በማለት ዓላማዋን ገለፀችለት።

ብዙ መከራ ካደረሰባት በኋላ በጨካኝነቱ የታወቀውን ወታደሩ ልኮ በቃልሽ ብቻ አርጤምስ ታላቅ አምላክ ነው ብለሽ ተናገሪ እኔም አንቺን ማሰቃየቴን አቆማለሁ አላት ሕፃኗ ቅድስት አጋዺስ ግን አንተ ልብህ የታወረ የሠው ሠራሹ ጣኦት ታላቅነት ከምን ላይ ነው ከድንጋይ የተሠራው ደንቆሮ ጣኦት ያድነኛል ማለትህና ለሱም መቆምህ ከንቱነትህን ይገልፅብሃል በማለት ዘለፈችው። እሱም እሳት ውስጥ ግቢ አላት። ቅድስት ሕፃን አጋዺስም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ፊቷን አማትባ ወደእሳቱ ገባች። ዘልላ ስለገባች



የእሳቱ ወላፍን ተፈናጥሮ አረማውያትን ገረፋቸው በዚሁም ብዙዎቹ የአካል ጉዳት ደረሰባቸው ቅድስት አጋዺስ ግን በእቶነእሳቱ ማሕል እግዚአብሔርን እያመሰገነች ወድያና ወዲህ ትንቀሳቀስ ነበር።

ንጉሥ አድርያኖስ ከእሳት እንዲያስወጧት ወታደሮቹን ላከ። ሊያወጧት የመጡ ወታደሮች መላእክተእግዚአብሔር ከሷ ጋር ቆመው አዩ አንቺ የእግዚአብሔር ባርያ ነይ ውጪ ንጉሥ ይጠራሻል አሏት ከእሳቱ ወጥታ በወታደሮቹ ወደፍርድ አደባባይ ተወሰደች ወድያው ንጉሡ በሰይፍ ይቆርጧት ዘንድ አዘዘ። የንጉሡን ትእዛዝ ስትሰማ እግዚአብሔርን እንዲህ እያለች አመሰገነች እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ከእህቶቼ ጋር ይህን ታላቅ ሐብት ያጎናፀፍከኝ አንተነህ ይህ አሁን ልቀበለው የተዘጋጀሁት መሥዋዕትነት የገነትን በር የሚከፍት ይሆንልኝ ዘንድ ባርክልኝ ቅድስት እናቴንም ይህን በረከት እንድትሳተፍ ከኛ ከልጆቿ አትለያት እኛን ሦስት ልጆቿ ሽኝታንአለች ቅድስት እናታችን ከሁሉ አብልጣ እኛን ልጆቿ የፅድቅን መንገድ መራችን የዚህን ዓለም ኑሮዋ በሰማዕትነት ልትሰናበተው ተዘጋጅታለች ሐይልህንና ፅናትህን ሥጣት።

ቅድስት ሶፍያ እናቷ በበኩልዋ ከአጠገቧ ሁና ቅድስት አጋዺስ የ፱ ዓመቷ ሕፃን ልጅዋን በተቀደሰ ሰማዕትነት ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድዋን እንዲያቃናላት እየፀለየች እንዲህ አለች "ልጄ ሆይ ደስ ይበልሽ ጥብአት አይለይሽ መልካም መንገድን ልትሄጂ ነው የኔ ፀሎትይህ ብቻ ነው ሦስት ልጆቼን ሙሽሮች አድርጌ መሥዋዕትነትን ለኢየሱስ ክርስቶስ አቀርብ ዘንድ። ልመናዬን ሰምቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይኔ እያየ ልጆቼ የዘለዓለማዊ መንግሥተሰማያት ወራሾች ልተሆኑልኝ ነው"

ቅድስት ሶፍያ ይህን ምስጋናና ፀሎቷን እንደጨረሰች



www.ethiopianorthodox.org

በቅፅበት አከታትለው ሕፃን ቅድስት አጋጺስን በሠይፍ አንገቷን መቷት ቅድስት ሶፍያም የሕፃን ልጅዋን አስከሬን አቀፈችው አንገቷንም ከወደቀበት አንሥታ ከቀረው አካለቷ ጋር አንድ ላይ አገናኝታ ገነዘቻት ሦስቱ ልጆቿን ይህን አይነት ሽልማት ሸለመቻቸው በውድ ግምጃም ገነዘቻቸው የሦስቱን አስከሬን በሠረገላ አስጭና ከሮም ከተማ አስራ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቆ ከሚገኘው ከፍተኛ ሥፍራ ቀበረቻቸው በነሱ መቃብር ላይ ቤተክርስቲያን ተሠርቷል።

ብዙ የክርስቶስ ተከታዮች ሴቶች ሦስቱ የቅድስት ሶፍያ ልጆች ከተቀበሩበት ድረስ እየሄዱ በየጊዜው መልካም ሽቶ ያፈሱ ነበር እጅግ ዋጋው ውድ የሆነ ብዙ ሽቶ በሦስቱ ቅዱሳት ሰማዕታት ደናግል መቃብር ላይ ፈሷል።

ቅድስት ሶፍያ እስከሦስት ቀን ድረስ በመቃብራቸው ሰንብታ ለንጉሠሰማያት ወምድር ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጋና እያቀረበች ወደሮም ከተማ ተመለሰች ብዙ ቅዱሳት ሴቶችም እየመጡ መንፈሳዊ ፅናቷን አደነቁ እንደገና ወደልጆቿ መቃብር ተመላሰችና ልጆቼ ሆይ ፍፁማን ሰማዕታት ይህን ዓለም አሸንፋችሁ ወደዘለዓለም ሕይወት የሄዳችሁ ናችሁ እኔንም በናንተ መንገድ እንዝ ዘንድ ፀልዩልኝ ብላ ተማፀነቻቸው። ወድያውም ነፍስዋ ከሥጋዋ ተለየች ተከትለዋት የመጡ ቅዱሳት ሴቶችም ከልጆቿ ጋር ቀበርዋት የሦስቱ ሰማዕታት ልጆቿ በረከትንም ታደለች።

ንጉሡ አርያኖስ የሥጋ ደዌ ይዞት ተሰቃየ አማልክቶቹን ለናንተ ስል እናንተን ያዋረደሁሉ በሞት ቀጣሁ እናንተ ደግሞ ከሕመሜ አድኑኝ አላቸው የሰው እጅ ሥራዎች ናቸውና ምንም መልስ አልሠጡትም እሱም እየተሠቃየና እየተበሳጨ ሞተ። ሦስቱ ቅዱሳት ደናግል ሰማዕትነትን የተቀበሉበት ወር በግሪክኛ ሚሶሪ ይባላል። በግዕዝ ደግሞ ነሐሴ ይባላል። ነሐሴ ፩ ቀን የሦስቱ



ቅዱሳት ደናግል የዕረፍት ቀን ሲሆን ነሐሴ ሦስት ቀን የናታቸው ቅድስት ሶፍያ የዕረፍት ቀን ነው።

## ምዕራፍ ፲፩ የቅድስት መክብዩና የ፯ ልጆቿ ሰማዕትነት

የቅድስት መክብዩና ልጆቿ የትውልድ አገር አንፆኪያ ሲሆን የኖሩበት አገር ግን ሮም ነው። በዘመኑ የነበረው የሮም ንጉሥ አንጢኩዮስ ይባላል። ይህ ንጉሥ ክርስቲያን የሚል ስም ባገሩ እንዳይኖር አጥብቆ ከለከለ አዋጅንም አስተላለፈ ነገር ግን ክርስቲያኖች አዋጁን አልተቀበሉትምየሱን አዋጅ አፍርሰው የክርስቶስን አዋጅ ተከተሉ ከረከሰው የአሕዛብ መስዋዕትንም ራቁ።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ዳዊት እሥራኤልን እንዲመራና ጎልያድን ገድሎ ኢሎፍላውያንን እንዲያሳፍር እንደላከው ቅድስት መክብዮን ንጉሡ እንጢኩዮስን ታሳፍረው ዘንድ ላካት። ቅድስት መክብዩን ሰባት ልጆቿን በእግዚአብሔር ቃል አንፃ አሳደገቻቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ድሕነት ብሎ የተቀበለውንም መከራ በሕይወታቸው እንዲቀረፅና ፍቅረ እግዚአብሔር እንዲያድርባቸው አደረገች።

ሰባቱም ልጆቿ እናታቸው ያስተማረቻቸውን ትምህርት በሕይወታቸው ይመሩበት ጀመር የእግዚአብሔር ፍቅር አደረባቸው እምነታቸውንም ሁሉ በእግዚአብሔር አደረጉ። እናታቸው ቅድስት መክብዩም "ለጦርነት ተዘጋጁ አሸናፊዎች ለመሆንም ታጥቃችሁ ቁሙ አጋንንት ሰዎችን መሣርያ እያደረጉ ሊወጉዋችሁ ተነስተዋል እነሱን ማሸነፍ የሚቻለው ከፍርሐት በመራቅ፣ በእግዚአብሔር ብቻ በማመን



www.ethiopianorthodox.org

ነው። ልጆቼ ሆይ የዓለም ነገሥታት መርዛማ እባቦች ናቸው በነሱ መርዝ ከመነደፍመዳን የሚቻለው እግዚአብሔርን በማመንና እሱን ብቻ በመከተል ነው። ልባችሁን አፅንታችሁ መርዛሙን ንጉሥ ታሸንፉትአላችሁ ከሱ ከሚፈፀምባችሁ መከራ የተነሳ አትፍሩ አትደንግጡም የዚህ ዓለም የሥጋ ደስታ ኢምንት ነው መንግሥተ ሰማያትን ትወርሱ ዘንድ ታገሱ ንጉሡ በናንተ ላይ ቁጣውን ሲገልጽ አትፍሩት ተሳለቁበት እንጂ በሃይማኖታችሁም አትደንግጡ ልጆቼ ሆይ በመንግሥተሰማያት እስክትሰበሰቡ ድረስ አትለያዩ ብዙ ነጋዴዎች በባህር ነውጥ ሲጨነቁ ወደእግዚአብሔር ይጮኻሉ እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰምቶ ከመስጠም ያደናቸዋል ለመድረስ ከፈለጉት አገርም አድርሶ በሰላም ወዳገራቸው ይመልሳቸዋል። ከዚያ በኋላ የደረሰባቸውን ጭንቀት ሁሉ ረስተው ነግደው ባተረፉት ይጠቀማሉ።

እንደዚሁ ሁሉ እናንተም የሚፈፀምባችሁን የሥጋ ፈተና በትዕግሥት ተቀበሉት የመከራውን ማዕበል አልፋችሁ ወደመንግሥተ ሰማያት ወደብ እስክትደርሱ ድረስም ሕይወታችሁ ለእግዚአብሔር ሥጡ። ከዚያ በኃላ የድካማችሁ ፍሬ ተጠቃሚዎች ትሆናላችሁ ልጆቼ ሆይ የሠጠኋችሁን መብራት አታጥፉ። እናንተ ከኢየሱስ ክርስቶስ ምንጭ ቅባት የተገኛችሁ ናችሁ እኔን ሐጢአተኛዋና በደለኛዋ እናታችሁን አታሳዝኑ ንጉሡ የናንተን መከራ መቻልና መታገሥ ሲመለከት ያፍራል ውርደትም ይደርስበታል የኔ ርግቦች ንፁሐን ከዚሁ ነጣቂ ጭልፊት ተጠንቀቁ በሱ ከሚደርስባችሁ መከራ ተላቅቃችሁ የምትወርሱትን መንግሥተሰማያትን አስቡ የከሐዲዎች ነገሥታት ፈተና የዚህ ዓለም አባጣ ጎርባጣ መንገድ ነው አቀበትና ቁልቁለትም ነው። የኔ ሚዳቋዎች ከዚሁ ረዋጭ ውሻ ተጠበቁ ወደኋላችሁም አትመለሱ ቅደሙት እንጂ እሱን ስትቀድሙት ዘለዓለማዊውን ዕረፍት ታገኛላችሁ።



የከሐዲዎች ነገሥታት መከራ እንደጊዜያዊ ዝናም ነው፣ ዝናሙ ሲዘንብ ካንድ መጠለያ ሁኖ ማሳለፍ ይጠቅማል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዝናቡ ጎርፉም ፈስሶ ያልቃል። እንደልብም መንቀሳቀስ ይቻላል። የነዚህ ነገሥታት ግፍና መከራም ሲያልፍ የዘለዓለማዊ መንግሥተሰማያት ባለቤት መሆን ይከሰታል ልጆቼ ሆይ እናንተ ከዝናብ በኋላ እንዳለው ትልቅ ጎርፍ ሁኑ ጠላትን የምታሸንፉት በዚሁ ነው። እናንተ መልካም አዝመራ ሁኑ የፍርሐት በረድ አይምታችሁ ውርጬና ነፋሱም አያድርቃችሁ ጠሉና ልምላሚው አይለያችሁ እሱም የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ነው። እኔ ከሕፃንነት እስከ ወጣትነት ዘመናችሁ ድረስ አሳድጌአችሁአለሁ። ስለናንተም ብዙ ደክሜአለሁ ስለዚህ የኔንም ትእዛዝ ትጠብቁ ይገባል ክርስቶስን እንድታዩት በዚህ ዓለም የተቀበለውን መከራ አስቡ። በክርስቶስ የዓለም መድሐኒት መሆን ብዙ የቀድሞ አባቶቻችን ብዙ መከራን አሳልፈዋል በትዕግሥታቸውም መንግሥተሰማያትን ወርሰዋል ሠይፍንና ጎራዴን እየመዘዙ ቢያሳዩዋችሁ አትፍሩ፣ ለመንግሥተሰማያት ብሎ አብርሃም አንዱ ልጁን ለመሥዋእት ከማቅረብ ወደኃላ አላለም ካራውን ባንገቱ ላይ ለማሳረፍ ምንም ሳያወላውል አነሳ ይህንንም ያደረገው ስለእግዚአብሔር ፍቅር ብሎ ነው እኔም ባለኝ የናትነቴ ሥልጣን ስለክርስቶስ ፍቅርት ሞቱ ዘንድ አዝዣችሁአለሁ ከዚያ በኃላ ግን ዘለዓለማዊውን ሕይወት ታገኛላችሁ ብጠላችሁ ኑሮ ወደዚህ መከራ እንድትገቡ ባላቀረብኳችሁ ነበር። አብርሃም ይስሐቅን ለእግዚአብሔር ይሰዋው ዘንድ እንዳቀረበው እናንተም ለእግዚአብሔር ንፁሐን መሥዋእትን ሁናችሁ ቅረቡ፣ ልጆቼ ሆይከፊት ለፊቴ ሩጡ የክርስቶስንም መስቀል ተሸከሙ በማለት ብዙ ካፅናናቻቸው በኃላ ትልቁን ልጅዋን ጠራችውና እንዲህ አለችው።

www.ethiopianorthodox.org

ትልቁ ልጄና የበኸር ልጄ አንተነህ ዘጠኝ ወር በሆዴ ተሸከምኩህ ጡቶቼንም ከሌሎቹ ወንድሞችህ በፊት ጠባህ ከእግዚአብሔር የምጠባበቀውን ታላቅ ተስፋ ባንተ ይገለፅ በሰማዕትነት የወንድሞችህ አለቃ ሁን ሙሴ የነቢያት አለቃ እንደሆነም ከወንድሞችህ ቀድምህ ሰማዕት በመሆን አለቃ ሁን በሠይፍ ትሞት ዘንድ በእሳትም ትቃጠል ዘንድ በዚሁም ሁሉ ወንድሞችህን እንድትቀድማቸው ይገባል ልጄ ሀይ ራሴን አታስደፋኝ ከእግዚአብሔር ፊትም አታሳፍረኝ መከራውን ታግሣችሁ የእግዚአብሔር መንጋዎች ሁናችሁ ሳያችሁ እጅግ እደሰታለሁ የኔ ብርሃኖች ሆይ ብርሃናችሁን ሠይጣናዊ ነፋስ ሊያጠፋው ባልቻ ለጊዜ ለደስታዬ ወሰን የለውም ታግሣችሁ ነፍሳችሁን ገንዘብ ስታደርጓት ለደስታዬ ወሰን የለውም፣ የኔ ከዋክብት ሆይ ከናንተ አንዱም ሳይለይና ሳይጠፋ ሁላችሁን የመግሥተሰማያት ወራሾች ሆናችሁ ባየኋችሁ ጊዜ ለደስታዬ ወሰን የለውም ሰማዕትነትን የምትቀበሉባት ሰዓት እየቀረበች ነው አይነልቡናችሁን ወደሰማይ አንሱ የብርሃን አክሊሎችንም ተመልከቱ።

ልጆቼ ሆይ ላንዲት ሰዓት መከራና ጭንቅ ታገሱ እሷ የመንግሥተሰማያት ሠረገላ ናትና እሷ የመንግሥተሰማያት መግቢያ በር ናትና፣ እሷ የዘለዓለም ዕረፍት ማስገኛ ናትና ማለቂያ የሌለውን ክብር ማስገኛ ናትና እኔም ሆንኩ እናንተ በዚህ ወራዳ ዓለም አሸብርቀን ብንታይ ላንድ አፍታያልፋል ተዋርደን ተሰቃይተን ይህን ዓለም ብናልፈው ግን ነገ መከራውና ሥቃዩ ይረሳል በማለት አበረታታቻው። በክርስቶስ ፍቅር ፀንተው ሰማዕትነትን ለመቀበል እንደተዘጋጁ ስላረጋገጠች ፍፁምደስታ ተሰማት። ወድያውም ሰባቱ ልጆቿ ይዛ በከሐዲው ንጉሥ ፊት ለመቆምና በግልጽ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ለመመስከር ጉዞዋን ቀጠለች ከንጉሡ አደባባይም ደርሳ ከንጉሡ ፊት በኢየሱስ ክርስቶስ እንደምታምን በግልጽ ተናገረች



ልጆቿም የሷን ድምጽ በማስተጋባት እንደሷ መሠከሩ፣ በህብረትም በንጉሡ ላይ ተሣለቁበት በክህደቱም ብዙ ዘለፉት።

ንጉሡ ለሰማዕትነት ቆርጠው መነሳታቸውን ስለተረዳ እጅግ ፈራ ድንጋጤም ተሰማው። ፊታቸውንም ለማየት አስፈርቶት ፊቱን ወደኋላ አዞረ ፊታቸውም በእግዚአብሔር ፀጋ ይበራ ነበር። ፊታቸውን ወደመሬት ደፍተው እንዲይዙዋቸው አዘዘና የሁሉንም ፊት ወደመሬት ደፍተው ጣሏቸው ከመካከላቸው ማን ትልቅ ማንትንሽ እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ አልተቻለውም ፀጋ እግዚአብሔር በነሱ ላይ ነበርና ከናንተ ትልቁ ማነው ማንነታችሁንስ ሊገልፅልኝ የሚችል ማነው አላቸው።

በዚህ ጊዜ ትልቁ ልጅ ወደሱ ቀረበና አንጢኪዮስ ንጉሥ የቆምከው ከማን ፊት እንደሆነታውቃለህን ሲል ጠየቀው እኔ አሁን የቆምኩት ከእባቡና ከከሐዲው መርዝ ከተሞላ ሕዝብን ከሚያጠፋና ፈጣሪውን ከማያውቅ ፊት ነው ሲል መለሰለት አንጢኪዮስ እንደገና አነጋገርህን አታጠንክር የቆምከው ልገድልህና ላሰቃይህ ሥልጣን ካለኝ ሰው ፊት ነው ሲል መለሰለት ይህ ትልቁ የቅድስት መክብዩድ ልጅ ሥልጣንህ የሚጠፋና የሚሻር የዚህ ዓለም ከንቱ ሥልጣንነው እኔና ወንድሞቼ እናቴም ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ሥልጣን ግን የማይጠፋ፣ የማይሻርና ዘለዓለማዊ የሆነ መጨረሻ የሌለው ነው አንተ ብትገርፈኝና ብታሠቃየኝ አምላኬ በትዕግሥት እንድቀበለው ያፅናናኛል ብሉ መልስ ሠጠው።

ንጉሡ የማግባቢያ አነጋገርን በተከተለ ሁኔታ "ሁሉን ትተህ ለአማልክት ሥገድ እኔም ታላቅ ክብር እሠጣለሁ ለብዙ ዘመናት የሚበቃህንም ወርቅ እሠጥሃለሁ የፈለግኸውን ያህል ሌላ ሐብትም እሠጣሃለሁ" አለው ትልቁ የቅድስት መክብዩድ ልጅ በበኩሉ"



www.ethiopianorthodox.org

አንተም እኔ የምነግርህን አድምጠኝ እንደኔ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመንክ ሁን በዚህ የክህደት ሠንሠለት እንደታሠርክ ወደዘለዓለማዊዉ ሞት አትጓዝ ባለህበት ሁኔታ ይህን ዓለም ኑረህ ከጨረስክ ካባትህ ሠይጣን ጋር ወደ ሲኦል ትወርዳለህ" ሲል መልስ ሠጠው።

ንጉሡ እጅግ በመቆጣት ምን ከፉና አስቀያሚ ንግግር ትናገራለህ አለው ቅዱሱ የመክብዩ ልጅም የፈለግኸውን የሥጋ መከራ በፍጥነት አድርስብኝ ከዚህ ዓለምም ቶሎ አሰናብተኝ አሳርፈኝም የሚጠብቀኝን የቅዱሳን ሰማዕታት አክሊልን ለመቀበል ጓጉቼአለሁ አለው። ንጉሡ አንጢኪዮስ የማይመለስለት መሆኑን ስላረጋገጠ ከብረት በተሠራ ጋን ዘይት አፍልቶ እንደዓሣ ወደዚሁ ከተተው እሱም ሰማዕትነቱን በዚሁ ጨረሰ ከፈላው ዘይትና ይህ የመክብዩ ልጅ የገባበት በርሜል የገነት መዓዛ ሽታ እየወጣ አካባቢውን አወደው እጅግ የሚመስጥ መልካም ሽታ ሰዎችን ሁሉ ስለሸተታቸው የዚሁ ሰማዕት ቅድስናን አደነቁ። ቅድስት መክብዩ የበሕር ልጅዋን ሰማዕትነት ተመልክታ እግዚአብሔርን አመሰገነች እንዲህም አለች እቺ የስንዴ ቅንጣት ንፁህ መሥዋእት ለመሆን ታደለች ነቀዝና ብል ከማያገኘው ሰማያዊ መዝገብም ገባች። እቺ ነፍስ የተጓዘችበት መርከብ እቺ የፈላች ዘይት ናት የልጄን ነፍስ ከባህር ስጥመት ያሸጋገረች ናት። መርከቧ ደስታ ካለበት ወደብ ደረሰች ልጄ ከመጥፎ ነፋስ ያዳነ ብርሃን ነው፣ ልጄ ተኩላ ያልነጠቀው በግ ነው ልጄ ጭልፊት ያልነጠቀችው ርግብ ነው፣ ልጄ ከዝንጀሮ ያመለጠ ሚዳቋ ነው። አንተን ለሚያምኑ ፈጥነህ የምትደርስላቸው ሐይልንና ትዕግሥትን የምታጎናፅፋቸው አንተ የሕያዋን አምላክ ነህ።

መክብዩ የቀሩትን ስድስት ልጆቿ እንዲህ አለቻቸው



እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድሩን ፈጥሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ በዚች ምድር የተለያዩ ፍጥረታትን ፈጠረ እናንተንም የኔ ሰባት ልጆች ሰባታችሁን ከኔ ፈጠረ ትልቁ ወንድማችሁ ይኸውና ከክብር ወደክብር ተሸጋገረ ሁለተኛውን ልጅዋ ደግሞ እንዲህ አለችው ወንድምህ ጉዞውን ጨረሰ ተራው ያንተ ነው ተነስና ተከተለው ፈጥነህም ድረስበት የብርሃን ከጨለማ መለየት የታወቀው አሁን ነው። በመቀጠልም ስድስቱን ልጆቿ የእግዚአብሔርን ቃል በብዙ መንገድ አስተማረቻቸው።

አንጢኪዮስ ንጉሥ ሁለተኛውን ልጅዋ አስጠርቶ አቀረበውና እኔን ተመልከት አለው። እሱም ፈጣሪውን ወደማያምን እመለከት ዘንድ አይገባኝም ብሎ መለሰለት ንጉሡ "በወንድምህ ላይ የተፈፀመውን አላየህምን አንተንም እኮ የሱን ቅጣት ልፈፅምብህ እችላለሁ አለው የመክብዪ ልጅ አንተ መከራውን አየህ እኔ ደግሞ በሰማዕትነት የተቀዳጀውን አክሊል አየሁ" ስለዚህ ወንድሜ ወደ ሄደበት ትልከኝ ዘንድ ብቻ ነው በመጠባበቅ ላይ ያለሁት" ምክንያቱም ያንተ መንግሥት እጅግ እጠላዋለሁና እንቀውም አለሁና በሚያስጠላና በሚጠፋ መንግሥት ሥር መሆን አይገባኝም" የሚል መልስ መለሰለት።

ንጉሡ "ለጋ ወጣትነትህን አይቼ እራራልሃለሁ" አለው። የመክብዩ ልጅ ደግሞ አንተ ለነፍስህ ራራ ስለራስህም ራራ አይንህ እያየ ወደዘለዓለማዊ ጨለማና መከራ በመጓዝ ላይ ነህ ስለኔስ እንድትራራ አልፈልግም" አለው። ንጉሡ እኔን አትፈራኝም አለወ የመክብዩ ልጅ" እኔ እግዚአብሔርን የማይፈራና የማያምን ሰውን አልፈራም" ሲለው ንጉሡ ንጉሥህና አምላክህ የት አለ እስቲ ይምጣና ከኔ እጅ ያድንህ በማለት ጠየቀው የመክብዩ ልጅ የኔ

www.ethiopianorthodox.org

አምላክ አንተን የሚበቀልህ በዚህ ዓለም አይደለም ኑሮህ ከአጋንንት ጋር ስላደረግህና ለአጋንንትም ሕይወትህን አሳልፈህ ስለሠጠህ እግዚአብሔር አንተን ትቶሃል ግን ዘለዓለማዊ ደይን ይጠብቅሃል ስለዚህ የምትችለውን ሁሉ በኔ ላይ ፈፅምብኝ አለው።

ንጉሡ ቆዳውን ገፈው ቶሎ ሕይወቱ እንዳያልፍ በማያስችል አኳኋን እንዲያሰቃዮት አዘዘ። ይህን ያደረገበት ምክንያት መከራው ሲፀናበት ጣኦትን ወደማምለክ ይመለስ ይሆናል ብሎ በማሰብ ነው የመክብዩ ልጅ ገና ወደመከራው ከመግባቱ አስቀድሞ የፈለገው ሥቃይ ቢያደርስብኝም ወደዘለዓለም ሕይወት የምሸጋገርበት ድልድይ ስለሆነ በደስታ ነው የምቀበለው አለው። መኮንኑ ወንድምህ ላይ የፈፀምኩትን ሁሉ እፈፅምብሃለሁ ሲለው ባሮች ቀንበሩን ለሁለት ተሸክመው ሞፈርን በመጎተት መሬትን ያርሱበታል እኔና ወንድሜም መከራውን ለሁለት ተሸክመን የሰማዕትነትን እርሻ እናርስበታለን አንተ ሥጋችንን በዚህ ምድር ታጠፋለህ እግዚአብሔርደግሞ በዳግም ምፅአቱ በክብር ያነሳዋል አለው።

ንግግሩን ሲፈፅም እንደጥሬእህል ወደፈላ ውሃ ከተቱት ምንም ሳይፈራና ሳይደነግጥ በፍፁም ጥብዓት ሰማዕትትነትን ለመቀበል ወደእሳቱ ሲገባ ተመልክታ እናቱ ቅድስት መክብዩ የሁለቱ ልጆቼ ለመልካም ፍሬ መብቃት ያሳየኸኝ አምላኬ ክብር ምሥጋና ይድረስህ ካለች በኋላ ሁለቱ ርግቦቼ በጭልፊት ሳይበሉ ወደቤታቸው ገቡ አይኖቼ አስደሳች ነገሮችን አዩ፣ እጆቼም ወደሰማይ ተዘረጉ ከልቤ ስቅስቅ ብዮ ገአር የማሰማው የቀሩት ልጆቼ መርዛማው የዚህ ዓለም አውሬ እንዳይበላብኝ ወደእግዚአብሔር በመማፀን ነው የሚል ድምፅ አሰማች።

ወድያውም ሶስተኛውን ልጅዋ ልጄ ሆይ የሁለቱ ወንድሞችህን ፈለግ ተከተል እግዚአብሔር አምላክህን አትዘንጋ አትርሳውም የዚህ ዓለም ዕፀዋት በሦስተኛዋ ዕለት የመፈጠር ደረጃ እንደያዙ አንተም የወንድሞችህን የመንግሥተሰማያት ልጆች መሆን ሦስተኛውን ደረጃ ትይዛለህ ልጄ ሆይ አትስነፍ ቶሎ ሩጥና ወንድሞችህን ድረስባቸው ትጥቅህን አሳምረህ ሩጥና እነሱ ወደገቡበት ዘለዓለማዊ መንግሥት ገብተህ መልካም ሙሽራ ሁንልኝ ወንድሞችህ አሁን ካሁን ይደር ስብናል እያሉ አንተን በመጠበቅ ላይ ናቸው ይህ ከሐዲ ከእግዚአብሔር እንዲያርቅህ ከወንድሞችህ ሊለይህ ወጥመድ በማዘጋጀት ላይ ነው በማለት የማፅናናት ትምህርት ሠጠችው።

ቅድስት መክብዩ ለሰማዕትነት የሚያበቃውን ትምህርት ከሠጠችው በኋላ ንጉሡ አንጢኪዮስበሁለቱ ወንድሞቹ ላይ ያደርግ እንደነበረው ሁሉ የማግባቢያና የመደለያ ንግግሩን ቀጠለበት ሦስተኛው የቅድስት መክብዩ ልጅ ግን አንተ ኢየሱስ ክርስቶስን የማታስበው ከሐዲ በሠይጣናዊ ዕብደትህና በባትህ ሠይጣን መንገድ እኔን ለመሸንገል ትፈልጋለህን ከሁለቱ ወንድሞቼና ከሰማዕታት ሁሉ ጋር አክሊለመንግሥተሰማያትን እንዳልቀዳጅ ወደኋላ ልታስቀረኝ ትፈልጋለህን በማለት ገሠፀው።

ንጉሡ አንጢኪዮስ "የምልህን ካልሰማኸኝና ትእዛዜን ካላከበርክ አስገርፋሃለሁ ብዙ ሥቃይንም አደርስብሃለሁ በማለት ሊያስፈራራው ጀመር የመክብዩ ልጅ ግን አንተ የካድከው እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነው እሱን አምኜ ካንተ የሚፈፀምብኝን መከራ ሁሉ በእግዚአብሔር አጋዥነት እቀበለዋለሁ ወንድሞቼን የተቀበለ እግዚአሔርም እኔንም ይቀበለኛል አንተ መንግሥትህ ተሽራ ለፍርድ የምትቀርብበት ቀን ትደርሳለህ የሚጠብቅህ ጥፋትና ሐፍረት ብቻ ነው ሥልጣንህ ይወገዳል" ሲል መለሰለት።

አንጢኪዮስ ንጉሥ በዚህ ተናደደና ምላሱንና ጣቶቹን


www.ethiopianorthodox.org

እንዲቆርጡት አዘዘ። ቅዱሱ የመክብዩ ልጅ በዚህ ጊዜ አንተ ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥተህ የአጋንንት ሞግዚት የሆንከው ከሐዲ አሁን በአካላቴ ላይ የፈለግኸው እንድታደርግ ሥልጣን ተሠጥቶሃል ይኸውና ጣቶቼ ሰብአዊ ርሕራኄ ካንተ የራቀው በክፉ መንገድ ጉዞህን ስለምትቀጥል ነው ብሎ ሁለቱ እጆቹን ዘርግቶ ለቆራጮቹ ሠጣቸው ንጉሡ ግን ሐሳቡ ለውጦ ምላሱንና ጣቶቹን ሳይቆርጥ ወደፈላ ውሃ ይከቱት ዘንድ አዘዘ። መክብዩ ቅድስት ግን የልጆኖን ወደኋላ ያላማለትን ተመልክታ እጅግ ተደሰተች ልጅዋ የመንግሥተሰማያትን ወራሽ ለመሆን ተዘጋጅቶ ንጉሡን አንጢኪዮን እንዳሸነፈው አረጋግጣለችና ይህ ሦስተኛ ልጅዋ በዚሁ ሰማዕትነትን ፈፅሟልና።

ቅድስት መክብዩ አራተኛውን ልጅዋን ማፅናናቱን ተያያዘችው እንዲህም አለችው። ልጄ ሆይ ስማ ወንድሞችህንም ምሰላቸው የነሱ ሰማዕት መሆንንም አስተውል የወንድሞችህ ሰማዕትነት አናንያን አዘርያንና ሚካኤልን በመምሰል ነው። ልጄ ሆይ ይህን የአጋንንት ማህደር የሆነውን ከሐዲ ንጉሥ ፈቃድ ለመፈፀም አትቃጣ እሳት ውስጥ የምታሳልፋት ጊዜ ኢምንት ናት። እናትህን ዛሬ ደስ አሰኛት ወንድሞችህንም በመንግሥተሰማያት ደስ አሰኛቸው አንተ አራተኛ ልጄ ነህ እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን ፀሐይን፣ ጨረቃን ከዋክብትን ፈጥሯል። ልጄ ሆይ የፍጥረታት አምላክን ፈቃድ ፈፅመህ በፍጥነት ወንድሞችህ ካሉበት ድረስ፣ በትዕግሥትህም ይህን ከሐዲ ንጉሥ አሳፍረው።

ንጉሥ አንጢኩዮስ ይህን የቅድሰት መክብዩ አራተኛ ልጅ አቅርቦ ከመጠየቁ አስቀድሞ የጣኦትን ሥእል አቆመ። ከጣኦቱ ሥእል ሥር ወርቅንና ብርን አስቀመጠ ከዚያ አራተኛውን



የቅድስት መክብዩ ልጅ አቅርቦ ለዚሁ የጣኦት ምስል ከሰገድህ ከእግርየው የተከማቸውን ወርቅንና ብርን እሰጥሃለሁ አለው። ይህ ቅዱስ ሰማዕት ግን "ፈገግ" አለ ዕብደቱንም በአንክሮ ተመለከተ ንጉሱንም ዕብደት አቃለለ ወረቅህ፣ ብርህና ጣኦትህ አብረውህ ወደገሃነም ይውረዱ አንተ በዕብደት ጎዳና የምትከንፈው ከሐዲ እኔንም ይዘኸኝ እንድትጠፋ ትፈልጋለህን በማለትም ገሠፀው።

ንጉሡ ግን "ብዙ ዘለፋ ብታሰማም ስለምወድህ ለጥቂት ጊዜ እታገስሃለሁ ይህንንም በመመልከት የምልህን ሰምተህ ለጣኦት ስገድ እኔም የሚበቃህን ወርቅና ብር እሠጥሃለሁ ከፍተኛም መአረግ ሠጥቼ መኮንን አደርግሃለሁ ትልቅ ሰው ትሆናለህ" ያለ ያግባባው ጀመር። የመክብዩ ልጅ ግን ወደንጉሡ እየተመለከተ አንተ ብልሃተኛ ሠአሊ ችሎታውን ያሳየበትና ያስዋበውን የእጅ ሥራ አምላክ ነው ብዮ እንድሰግድበትና ከዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ተለይቼ እንድጠፋ ነው የምትፈታተነኝ አለና የቆመውን የጣኦት ስእል አንሥቶ ወረወረው እሱም ተሠበረ።

ንጉሡ ይህን ሁሉ ተመልክቶ እጅግ ተናደደ እንደሚዘብትበትም አወቀ ወድያው የዚሁን ቅዱስ አይኖች በእሳት እንዲያጠፋዋቸው አዘዘ። የታዘዘበትን ቅጣት ሲሰማ ለኔ የአይኖቼ መጥፋት መልካም ይሆንልኛል የሚፈፀምብኝን መከራ ከማየት እድናለሁና አንተ የካድከው የኔ አምካክ ግን ሐይልንና ትዕግሥትን ይሠጠኛል አለው ንጉሡ ግን ከብስጭትና ንዴት ብዛት የተነሳ አንደበቱ ተዘጋ የሚሠራውንም አጥቶ እጅግ ግራ ተጋባ። እንደገና ሐሳቡን ለውጦ እንደበግና እንደፍየል ቆዳውን እንዲያወጡት አዘዘ። ቅዱስ የመክብዩ አራተኛው ልጅ ቆዳዮን ብታወጣ እጄንና እግሬን ብትቆርጥ አይኔን ብታጠፋ ከንጉሠሰማያት ወምድር ኢየሱስ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ ፍቅር አልለይም ሁሉን ችየና ታግሼ አልፈዋለሁ የሚል መልስ ሠጠው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አካላቱን እየቆረጠ ወደእሳት ጣለው እጁ እግሩ የቀሩትም አካላቱ እጅግ በሚያሰቅቅ መንገድ ሲቆርጡት ሕይወቱ ቶሎ እንዲያልፍ በማያስችል ሁኔታ ነበር። በመጨረሻ ህይወቱ አለፈ ሰማዕትነቱንም ፈፀመ።

ክርስቲያኖች የቅድስት መክብዩ ፅናት እጅግ አደነቁ ልጆቿ በቅደም ተከተል ሰማዕትነትን ሲቀበሉ ሲቆረጡ እንደሽንኩርት ሥጋቸው ሲከተፍ እንደንፍሮ ሲቀቀሉና እንደእንስሳት ቆዳቸው ሲገፈፍ ቁማ ትመለከትና ታፅናናቸው ነበርና ሰማዕትነታቸውን በሚቀበሉበት ሁሉ ላንድ አፍታ እንኳ ሳትለያቸው አብራ ትገኝ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ታድያ ምን ያህል የእግዚአብሔር ፀጋ ቢዋሃዳት ነው ከደስታና የእግዚአብሔር ምስጋና በቀር ሐዘንና ጭንቀት የማይታይባት እያሉ ክርስቲያኖች ከሷ ፅናትንና ጥብአተን ይቀስሙ ነበር። የሷ ጉጉት ልጆቿ በዚህ ሐላፊ ዓለም ተድላና ደስታ አሸብርቀው እንዲታዩ አልነበረም በታላቅ ጉጉት ትከታተለው የነበረው ልጆቿ ዓለማዊ እንከን ሳይታይባቸው ንፁህ ሥንዴ እንደሆኑ ወደእግዚአብሔር እንዲቀርቡላት ብቻ ነው።

የቅድስት መክብዩ ፅናት በአንፃኪያና አካባቢዋ በሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ታላቅ መንፈሳዊደስታን አሳደረ። ቀስ በቀስ በሷ ጥብአት ብቻ እነዚህ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰገኑ ብዙዎችም ከአረመኔነት እየወጡ ኢየሱስ ክርስቶስን ተከተሉ ቅድስት መክብዩ አራተኛውን ልጅዋን በሰማዕትነት ከሸኘች በኋላ በከፍተኛ ድምፅ የሰማይና የምድር አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ከቃልህ የተነሳ ተራሮችና ኮረብታዎች ይንቀጠቀጣሉ፣ ሕያው ስምህን ፍጥረታት ሁሉ ያመሰግኑ ዘንድ የፈቀድህ አንተነህ ከመቃብር ሙታንን የማንሣት ሥልጣን ያለህ አንተ ብቻ ነህ



የተደበቁትን ሚሥጢራት ሕዝቅኤልን ያሳየኸው አንተ ነህ አንተን የሚያምኑትን የምትረዳቸው አንተ ነህ እያለች አመሰገነች።

ንጉሡ የቅድስት መክብዩን ጥብአት ተመለከተ እሷን የሚያስደነጥም ስለመሰለው አምስተኛውን ልጅዋን ያለምንም ጥያቄ እንዲገረፍና እንዲሠቃይ ከዚያም ወደእሳት እንዲጣል አዘዘ በዚሁ የዚህ ልጅ ሥቃይ እጅግ የከበደ ሆነ ግን ሥቃዩን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እየጠራ በትዕግሥት ተሸከመው ከፈላ ውሃ ከመከተ‹ አስቀድሞ አካላቱ ተቆራርጧል በመጨረሻ ከፈላ ውሃ ውስጥ ተከተተና ሰማዕትነቱን ፈፀመ። ቅዱስ መክብዩም ሳይጠፉ አምስት መብራቶችን ወደመንግሥተ ሰማያት አስገባሁ በማለት ደስታዋን ገለጠች እግዚአብሔርንም አመሰገነች።

ቅድስት መክብዩ ስድስተኛውን ልጅዋን በተራው ታበረታታው ጀመር እንዲሁም አለችው" ልጄ ሆይ የናትህን ምክር ስማ ይህ ከሐዲ ንጉሥ ከማህበረቅዱሳን ሊለይህ ይፈልጋል እግዚአብሔር አዳምን በስድስተኛው ቀን ነው የፈጠረው። የሰውን ልጅ የፈጠረው ለክብር ነበር። ለሰው ፈቃድ በመታዘዙ ግን ከገነት ወጣ የዘለዓለምን የተድላና ደስታ መኖርያህ የምታዘጋጀው አሁን የሚጠብቅህን መከራ በመታገሥ ነው።"

ልጅዋም እኔ በእግዚአብሔር እታመናለሁ ከዚህ ከሐዲ ንጉሥ የሚደርስብኝንም መከራ ሁሉ በትዕግሥት እቀበለዋለሁ ወንድሞቼ ወዳሉበትም ለመድረስ ጓጉቼአለሁ በማለት መለሰላት። ንጉሡም ከዚሁ ብዙ ሳይቆይ ይህን ስድስተኛው የመክብዩ ልጅ አስጠርቶ ከፊቱ አቆመው ነገርግን ከንጉሡ ጥያቄ ሳይቀርብለት አስቀድሞ አንተ ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥተህ ለአጋንንት



www.ethiopianorthodox.org

እጅህን የሠጠህ እኩይ ፍጥረት ነህ እነሆ ሥጋዬ በፊትህ ነው የምትፈልገውን ሁሉ በሥጋዬ ላይ ፈፅም በማለት ገሠፀው።

ንጉሡ በበኩሉ የኔ ፍላጎት አንተን መግደል አይደለም ፈቃዴንና ትእዛዜን ትፈፅም ዘንድ ነው በዚህ መሠረት ለአማልክቶቼ እንድትሠግድ ለነሱ የተሠዋውንም እንድትበላ እፈልጋለሁ አለው ስድስተኛው የመክብዩ ልጅ ግን አንተ ክርስቶስን የካድህ አንተ በእውነት ነጣቂ አውሬነህ በማታለያ ንግግርህ ልትሸነግለኝ ትፈልጋለህን ወደማይሰማው ወደማያየው ምንም ለማይጠቅም ጣኦትህ ታስገባኝ ዘንድ ትሻለህን? እኔ ለጣኦትህ አልሠግድም፣ ቃልህንም አልሰማም መሥዋእትህንም አልበላም እኔ ከአንተ የምጠብቀው በወንደሞቼ ላይ የፈፀምከውን ሁሉ እንድትፈፅብኝ ብቻ ነው ግርፋትንም ሆነ ሌላ የሥጋ መከራ በኔ ላይ ስትፈፅምብኝ 7ኛውን ወንድሜ የዚሁ ታላቅ ፀጋ ተካፋይ ይሆን ዘንድ አመጣዋለሁ ቀጥሎም እናቴን አመጣታለሁ ሲል መለሰለት።

ንጉሡ ባስቸኳይ ምላሱን አስቆረጠው /ኢየሱስ ክርስቶስን የሚጠራ አንደበቱ ለመዝጋት/ወድያው ከመጠን ያለፈ ብዙ ደም ከአፉ ፈሰሰ ፊቱ ግን እንደፀሐይ ያበራ ነበር በዚህም የከሐዲው ንጉሥ መኳንንት እጅግ ተደነቁ ፍርሐትም አደረባቸው ምላሱ ተቆርጦ እያለ ምንም እንዳልተቆረጠ ሁኖ በርቱዕ አንደበት እኔ የዓለም መድሐኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳዘጋጀልኝ ዘለዓለማዊ ዕረፍት እየተጓዝኩ ነው በማለት ነፍሱን ለእግዚአብሔር ሠጠ የመክብዩን ፅናትና የቅዱሳን ልጆቿን ፅናት የተመለከቱ የአንፆኪያ ክርስቲያን ይህ ድንቅ ሥራ ካሁን ቀደም ያልታየነው እያሉ አደናቆታቸውን ገለፁ። ይህ ቅዱስ ስድስተኛው የቅድሰት መክብዩ ልጅ በሠይፍ በመቆረጥ ሰማዕትነቱን ፈፀመ።



ንጉሡ እጅግ ተበሳጨ እንዲህም አለ "ካሁን በኃላ ምን ማድረግ አለብኝ አንዲት ሴት ከልጆቿ ጋር አሸነፈችኝ" ይህን ብሎ በዕድሜና በሰማዕትነት የመጨረሻ የሆነውን የመክብዩ ሰባተኛው ልጅ አስመጣውና ሕፃንነቱን አይቶ በተለያየ መንገድ ይሸነግለው ጀመር። እናቱንም ቅድስት መክብዩ እንቺ ሴት ይህን ሕፃን በስተእርጅናሽ ረዳት ይሆንሽ ዘንድ ልተወልሽ ነው። ሕፃንነቱን ደምግባቱና ብቸኝነቱን እንድራራለት አስገድዶኛል የዚ" ሕፃን ጠቅላላ አቋም እንደሊባኖስ ዘንባባ ይመስላል አንቺም ለሕፃኑ ሕይወት ስትይ ጥንቃቄ ማድረግ አለብሽ በሌሎቹ ስድስት ልጆችሽ ያሳየሽው ጭካኔ አሁን መኖር የለበትም በማለት ብዙ የማግባቢያ ዲስኩር አፈሰሰላት።

ቅድስት መክብዩ ግን እኔ የመጨረሻውን ልጄ ከኔ ምክር እንዳይወጣ ብቻ ነው የምመክረውካለች በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ለሰማዕትነት ይዘጋጅ ዘንድ ታስተምረው ጀመር እንዲህ እያለች ልጄ ሆይ ከወንድሞችህ ዕድል በዚሁ ከሐዲ ንጉሥ እንዳትለይ ወንድሞችህ የታገሡትን መከራ አስታውሰው፣ አንተም ተቀበለው አሁን እነሱ ከፃድቃን ዕረፍትና ከእግዚአብሔር ፀጋ ውስጥ ናቸው ይህም በዚህ ጊዜ ያልቃል የማይባለው ነው። ነፍስ ዘለዓለማዊት ናት መከራ ግን ባጭር ጊዜ የምታልፍ ናት፣ በሰላም ወደወንድሞችህ ተጓዝ፣ እርጅናዬ ሆይ ጠላት አያሸንፍህ፣ ልጄ ሆይ የሰማዕትነት አክሊል በራስህ ላይ ነው እንዳይወርድ ተጠንቀቅ ብርሃን ልጄ ሆይ ፋናህ አይጥፋ ያጥቢያ ኮከብ ልጄ ሆይ ብርሃንህ አይጥቆር ልጄ ሆይ ከወንድሞችህ አትለይ። ልጄ ሆይ እግዚአብሔር ስድስት ቀን ሥራውን ሠርቶ ባረፈባት ሰባተኛይቱ ዕለት ተመሰል ሰባተኛይቱንም ቀን ባርኳታል አክብሯታል አንተም



www.ethiopianorthodox.org

በእግዚአብሔር ዘንድ ተባረክ ክብርም አንተ የደስታዮ ፍፃሜ ነህ ካንተ በኋላ ሐዘን የለኝም ፍርሐትም የለኝም።

ቅዱስ ሕፃን ልጅዋ እንዲህ ሲል መለሰላት እናቴ ሆይ ነገር አታብዢብኝ ቶሎ መንገዴን አፋጥኚልኝ እኔ ወደወንድሞቼ ለመድረስ ጓጉቼአለሁ ንጉሡ የሱን ትእዛዝ እንዲፈፅም እየመከረችው መስሎት በፀጥታ ይመለከት ነበር። ሕፃኑ ልጅ ግን ፊቱን አዞረና አንተ ከእግዚአብሔር ቤት ወጥተህ የምትባዝነው ከሐዲ ሆይ እኔ ወደ ወንድሞቼ ለመድረስ እጓዛለሁ አንተም በፍጥነት አሰናብተኝ በረከሰው ተግባርህ እኔን ልትሸነግለኝና ከክርስቶስም ፍቅር ልትለየኝ ትፈልጋለህ እኔ ክርስቶስን ከናቴ ሆድ ጀምሬ አመሰግነዋለሁ አሁንም ወደሱ እሄዳለሁ፣ ቶሎ ድርሻዬን ስጠኝ አንተ ግን በምትከተለው ሠይጣናዊ መንገድ ወደ ጥፋት ትሄዳለህ አለው።

ንጉሡ የቅዱሱን ሰማዕት ሕፃን ቃል ሰምቶ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ፣ ደነገጠ አፈረ፣ ንጉሡም በየጥቂቱ አካላቱን እንዲቆርጡ አዘዘ አካላቱን መቆረጥ ሲጀምሩ ከሰማይ አንተ ቅዱስ ቡሩክ ሕፃን በደስታ ወደኔና ደስም ይበልህ አክሊልህ ተዘጋጅቷል ከወድሞችህ ጋርና ከቅዱሳን ሰማዕታት ጋር ቦታህ ተዘጋጅቷል የሚል ድምፅ መጣለት ወድያውም ሰማዕትነቱን ፈፀመ።

ቅድስት መከብዩ ሰባቱን ልጆቿ አሰናብታ ተደሰተች ፍፅም ደስታም ተሰማት፣ ሠገደች፣ ፀለየች ለልጆቿ ፅናትን ትዕግሥትንና የአሸናፊነትን ሐይል የሠጠ እግዚአብሔርንም አመሰገነችው። ንጉሡም ወደእሳት እንዲከቷት አዘዘ። እሷም በፈገግታ እየተደሰተች ወደእሳት ገባች ደስታዋ የልጆቹን ሠርግ የሠረገ ሰው ይመስል ነበር በዚሁም ተጋድሎዋ አለቀ። በአውግሥጦስ ወር ሰማዕትነታቸውን ፈፀሙ የአንፆኪያ ክርስቲያኖች ሰባት ቀን በተከታይ በዓላቸውን አከበሩ አርአያነታቸውንም ወሰዱ።



## ምዕራፍ ፲፭ የቅዱስ ሐሩስጡፉሩስና የሁለት ቅዱሳት አንስት ገድል

በዘመነመክስምያኖስ ንጉሥ ብዙ ሐዘንና ብዙ ስደት በክርስቲያኖች ላይ ተፈፅሟል። ንጉሥመክስምያኖስ በግዛቱ ሥር ላሉ አገሮች ሁሉ ለአማልክተሐሰት ለመስገድ ፈቃደኛ ያልሆነ ሁሉ እንዲገደል አዋጅ አስተላለፈ። በሐብቱ ብዛት የታወቀ አንድ ሰው በግዛቱ ውስጥ ነበረ ስሙ ሐሩስጥፉሩስ ይባላል ይህ ሰው በክርስቱያናዊነቱ እጅግ የታወቀ ነበር።

መክስምያኖስ ወደቤተመንግሥቱ ተይዞ እንዲመጣ አደረገና "ለአማልክት እንደማትሰግድና እንደማትሰዋ ሰምቼ ነው ተይዘህ እንድትመጣ ያደረግሁ" ሲል ንጉሡ መክስምያኖስ ሐሩስጥፉሩስን ጠየቀው እሱ ግን እኔ አንድ ብቻ አምላክ አለኝ እሱም ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አለው። ንጉሡ ሥጋው እየተበጣጠሰ ወደምድር እስኪወድቅ ድረስ እንዲቀጠቅጡ ትአዘዘ እነሱም ብዙ ደበደቡት ወድያውም ወደወህኒ ቤት ወረወሩት ይህም ያደረገው ምን አይነት ቅጣት በሱ ላይ ሊፈፀም እንደሚችል ለመምከር ነው። ከባለሥልጣኖቹ ጋር ምን መደረግ እንዳለበት ተማከረ መኳንንቱ ሁለት በቁንጅና የተዋቡ፣ በከበረ ልብስ ያጌጡ፣ እጅ እግራቸው በወርቅ የተንቆጠቆጡ ሴቶች ቢላኩለት በነሱ አማካይነት ሊማረክ ይችልና ወደአምልኮአማልክት ሊሳብ ይችላል ሲሉ አማከሩት። በተሠጠው ምክር ተመርቶ ንጉሡ ሁለት በመልካቸው፣ በአለባበሳቸውና በአሸላለማቸው የተለየ አርአያ ያላቸውን ወጣቶች ሴቶች ወደእሥር ቤቱ ላከበት።



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ሐሩስጥፉሩስ ሲመለከታቸው ደነገጠና ፈጥኖ በመነሳት እጁን በመዘርጋት ወደምሥራቅ ዙሮ ከሴቶቹ ወጥመድ አድነኝ እነሱንም ለዚህ ሠይጣናዊ ሥራ ከመገዛት ነፃ እንዲወጡ አድርግ በልባቸውም አንተን መፍራት አሳድርባቸው መንፈስቅዱስን በልቦናቸው አሳድርባቸው በሃይማኖትም አንተን ወደማፍቀር ይገቡ ዘንድ አድርግ ፈቃድህንም ለመፈፀም አብቃቸው እያለ ፀለየ። ወድያውም ሴቶቹ የዚሁ ቅዱስ ሰማዕት ጥብአትና ስለነሱ እግዚአብሔርን መለመኑ ወደእግዚአብሔር እንዲመለሱ አደረጋቸው እግዚአብሔርም ጥብአትን፣ ፅናትን፣ ትዕግሥትንና ሃይማኖትን በልባቸው አሳደረ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነናል አማልክተንንጉሥንም ክደናል እያሉ በግልፅ ስለሃይማኖታቸው መሠከሩ።

ቅዱስ ሐሩስጥፉሩስ የነሱን ባጭር ጊዜ የእግዚአብሔር ተከታዮች መሆንን ተመልክቶ እጅግ ደስ አለው እግዚአብሔርንም አመሰገነ። ትምህርተሃይማኖትንም አስተማራቸው እነሱም እግዚአብሔር ሐጢአታቸውን ይቅር ይላቸው ዘንድ በፀሎት እንዲረዳቸው ይህን ሰማዕት ተማፀኑት ቅዱስ ሐሩስጥፉሩስ ባጭር ጊዜ ልባቸው ተሠብሮ በተመስጦና በመንፈሳዊ ለዛ ወደእግዚአብሔር መመለሳቸውን ከንግግራቸው ተረድቶ ስለነሱ ለመፀለይ ጀመረ ብዙም እያለቀሰና እያዘነ እግዚአብሔርን ተማፀነ። ፀሎቱ እንደጨረሰ የንጉሡ መልእክተኞች መጥተው ሁለቱን ሴቶች ከእሥር ቤቱ አውጥተው ወሰዱዋቸው ወደንጉሡም አቀረቡዋቸው።

ንጉሡ መክስምያኖስ ሐሩስጥፉሩስን በማግባባት መለሳችሁትን ሲል ጠየቃቸው ከሁለቱ አንዷ አንተ የላክኸን ለረከሰ የሠይጣን ሥራ ነበር ነገር ግን እኛ የሱን አምላክ እንድናመልክሁናናል ርኩሳን አማልክትህንም ትተናቸዋል የዘለዓለምን ድህነት እናገኝ ዘንድ ዘለዓለማዊውን እግዚአብሔር እናመልካለን ከሱ በቀርም ሌላ አምላክ የለም ያንተ አማልክት አጋንንት ናቸው ሴቶች ልጆችንና ወንዶች ልጆችን እያረድክ መሥዋዕት የምታቀርብላቸው እነሱ ምንድር ናቸው? ስትል በድፍረት ገለፀችለት መክስምያኖስ ንግግርዋን ሰምቶ በእንጨት ላይ ይሠቅሏት ዘንድና ከበታቿም እሳት ያነዱ ዘንድ አዘዘ። የታዘዙትንም ሁሉ ፈፀሙባት።

ሁለተኛዋን ደግሞ ለአማልክቱ እንድትሠግድ አዘዛት የታዘዘችውን በመፈፀም ለአማልክት ከሠገደችና መሥዋዕትንም ካቀረበች የተለየ ክብር እንደሚሠጣት ነገራት። እሷ ግን ዝም ብላ በአርምሞ ታዳምጠው ነበር ወታደሮቹን የሱ አማልክት ወዳሉበት ይወስዷት ዘንድ አዘዛቸው እነሱም ወሰዷት ወደቤተአማልክት ደርሳ ፊቷን በትእምርተመስቀል አማተበች በእጅዋም ዳሰሰቻቸውና ድንጋይ ምንጊዜም ድንጋይ ነው። የተለየ ድንጋይ የለም ድንጋይ አይናገርም ድንጋይን የሚያመልኩም ድንጋዮች ናቸው። ካለች በኋላ እንትፍ አለችባቸው /ምራቋን ተፋችባቸው/።

ወታደሮቹ መልሰው ወደመክስምያኖስ ወሰዷትና እቺ ሴት አማልክትን አዋረደቻቸው እጅግም በማቃለል ምራቋን ተፋችባቸው በማለት ለንጉሡ ነገሩት። ንጉሡም በአማልክት ላይ የፈፀምሺውን እስቲ ግለጪልኝ አላት። ቅድስቷ ሰማዕትም አንተ የተረገምህ እግዚአብሔርን ክደህ ጣኦትን የምታመልክ ነህ እኔስ በጣኦቱ ላይ ምራቄ ተፋሁ ምንም መልስ አልሰጠኝም ሰደብኩትም ከፊቱም በክርስቶስ መስቀል ትእምርት አማተብኩ በዚሁ ሁሉ ጣኦቱ ያደረገው ነገር የለም አለችው።

መክስምያኖስ በአንገቷ ላይ ትልቅ ድንጋይ አስረው ከዛፍ ላይ እንዲያንጠለጥሏትና ሕይወቷም እስኪያልፍ በዚሁ እንድትቆይ አዘዘ እነሱም የታዘዙትን ሁሉ በሷ ላይ ፈፀሙ በዚህጊዜ ቅዱስ ሐሩስጥፉሩስን አንተ የእግዚአብሔር ሰማዕት ጌታዬ ኢየሱስ

www.ethiopianorthodox.org

አጋንንት ስታሠግደን የኖርከውን ጊዜ አይበቃህም ምንም ችሎታ እንደ ሌላቸውና ራሳቸውን እንኳ ማዳን የማይችሉ ሰው ሠራሾች እንደ ሆኑ ሳታውቅ ዕድሜህን ልትጨርስ ነው እያሉ ገሠፁት መክስምያኖስ የማግባቢያ ንግግሩን ቀጥሉ ገንዘብ አንሷችሁ ከሆነ ልጨምርላችሁ የጎደላችሁን ሁሉ ላሟላላችሁ ከሐብት ላይ ሐብት ልጨምርላችሁ ካለ በኋላ ወርቁን ዕንቁን ብሩን የተለያየ መልክ ያለውን የክብር ልብስ ሁሉ በውድ ዋጋ የሚገዛውን የቤተመንግሥቱን ዕቃ ሁሉ አስመጥቶ ከፊታቸው ዘረገፈና ይህን ሁሉ ውሰዱ አላቸው።

እነሱ ግን እንኳንስ ሊወስዱት እሱን ላለማየት ፊታቸውን ወደሌላ አዞሩ እንዲህም አሉት ወራዳ ጌታህን ኢየሱስ ክርስቶስን የካድክ አንተ፣ ወርቅህ ብርህና ሌላውም ገንዘብህ ካባታችሁ ሠይጣን ጋር ተያይዞችሁ ጥፉ እኛስ ወደመድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሄድ ተዘጋጅተናል ወደሰማያዊቱ ኢየሩሳሌምም እንሄዳለን ካንተ ጋር ለአጋንንት እጃችንን ድጋሚ አንሰጥም አንተበክፉ አእምሮህ የጨለመብህ ዕብድ ነህ ወደጥፋትና ዘለዓለማዊ ሞት ትጓዛለህና አሉት።

መክስምያኖስ እስከመጨረሻው ተስፋ ቆረጠና ከፊቱ ባስቸኳይ አስወግደው አንገታቸውን በሠይፍ እንዲቆርጡዋቸው አዘዘ እነሱም በትእምርተመስቀል ፊታቸውን እያማተቡ ሰማዕትነቱን በየተራ ተቀበሉት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ነፍሳችንን ተቀበላት እንደንፁህ ዕጣንም በፊትህ ትቅረብ እያሉም ለሚሠይፉዋቸው አንገታቸውን ይሠጡ ነበር ተጋድሎዋቸውንም በሰላም ፈፀሙ።

ለሦስተኛ ጊዜ ቅዱስ ሐሩስጥፋሩስን አቅርቦ ንጉሡ አንተ ጎልማሳ ሰው ለአማልክቶቼ አንሠግድም ያሉ መኳንንት ሁሉ በከንቱ እንደጠፉና እንደሞቱ ታውቅ የለም አንተም እንደነሱ በከንቱ እንዳትጠፋና እንዳትሞት ለአማልክቶቻችን ሥገድ አለው ቅዱስ ሰማዕት "ስለአማልክቶች ነቢዩና የተመረጠው ዳዊት የአሕዛብ አማልክት ከወርቅና ከብር ቢሠሩም አፍ እያላቸው አይናገሩም ጆሮ እያላቸው አይሰሙም..." እንዳለ አላነበብክም አሁንም ቢሆን የምታፍርና የምትጠፋ አንተነህ፣ አባትህ ሠይጣንም አብሮህ ይጠፋል እኔም አንተ ያስፈጃሀቸው ሰማዕታት ወደዘለዓለማዊ ዕረፍት ሄደዋል እኔም እነሱን ተከትዬ አጓዛለሁ ስለዚህ ካንተ የሚመጣብኝን የሥጋ መከራ አልፈራውም በትዕግሥትና በእግዚአብሔር ሐይል እችለዋለሁ ስለዚህ በሥጋዬ ላይ የምትፈልገውን ሁሉ ፈፅም እቀበለዋለሁ ወደጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስም ለመጓዝ እጅግ ጓጉቼ አለሁ የሰማዕትነት አክሊል ይጠብቀኛልና ብሉ መልስ ሠጠው።

ይህ ቅዱስ ሰማዕት የተዘጋጀበትን የሥጋ ሥቃይ እንደ ኢምንት ሲመለከተው በሱ ጥብአትና ፅናት ሌሎችም ክርስቲያን ሊሆኑ ይችላሉ ብሉ ንጉሡ መክስምያኖስ እጅግ ፈራ ባስቸኳይም ካለበት አውጥተው በሠይፍ አንገቱን እንዲቆርጡት አዘዘ። ሊቆርጡት የተዘጋጁትንም ወታደሮች ለጥቂት ጊዜ ታገሱኝ ብሉ ለመናቸው እነሱም በጥያቄው መሠረት ጊዜ ሠጡት ፊቱ ወደምስራቅአቅጣጫም በመመለስ እንዲህ እያለ ፀለየ " ጌታዩና አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በምታሥፈራው አደባባይ ትምረኝና ይቅር ትለኝ ዘንድ እለምናሃለሁ የሕይወትንም ብርሃን ታለብሰኝ ዘንድ የሰማዕታትንም አክሊል ታቀዳጀኝ ዘንድ ከቅዱሳን ሰማዕታት ማህበርም ትጨምረኝ ዘንድ እለምናሃለሁ" በማለት ፀለየ።

ፀሎቱን ሲጨርስ ፊቱት በትእምርተመስቀል አማትቦ ሠይፉን መዝዞ ሊቆርጠው ለሚጠባበቀው ወታደር አንገቱን አመቻቸለት

www.ethiopianorthodox.org

ወታደሩ ግን እጅግ ተንቀጠቀጠ ከንጉሡም ቅጣት እንዳይመጣበት በመፍራት በግዱ አንገቱን ቆረጠው ነገርግን አንገቱን ከቆረጠው በኋላ እግዚአብሔርን አመነክርስቲያንም ሁኖ ለመጋደል ተሠለፈ።

ቅዱስ ሐሩስጥፉሩስ ሰማዕትነትን የተቀበለው ነሐሴ አሥር ቀን ነው። እግዚአብሔር በሱ አማካይነት ብዙዎች ወደሱ እንዲመጡና ሰማዕትነትን ተቀብለው የቅዱሳን ሰማዕታት ማህበርተኞች እንዲሆኑ ካደረገ በኃላ በዚሁ ዕለት ጠራው።

## ምዕራፍ ፲፮ የቅዱስ ባስሊቆስ ሰማዕትነት

መክሲምስና ዲዮቅልጥያኖስ ለሁለት ተካፍለው ሮምን ይገዙዋት በነበረ ጊዜ አስቅልጥዮጶጦስ የተባለውን መኮንን ወክሎ ክርስቲያኖች እየተገደዱ ለጣኦት እንዲሠግዱና መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ለማድረግ አግዲጢስ ወደ ምሥራቁ ክፍል መጣ ባስሊቆስ ጣኦትን አላመልክም ለሱም አልሰግድም በማለቱ በእሥር ቤት ይገኝ ነበር። በእሥር እያለም ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አትርሳኝ እያለ ይፀልይ ነበር። ቤተሰቦቹን ተሰናብቶ እንዲመለስና ሰማዕትነትንም እንዲቀበል መንፈስ ቅዱስ አዘዘው። ወድያው ከታሠረበት ሁኖ ወደውጭ ሲመለከት የወህኒ ቤቱ መስኮት ተከፍቶ አየው ከዚያም አሻግሮ የወህኒ ቤቱ ጠባቂዎች ቤተሰቦቹን ተሰናብቶ ለመምጣት ይችል ዘንድ እንዲፈቅዱለት ለመናቸው።

የወህኒ ቤቱ ጠባቂዎች በበኩላቸው እኛ በፈቀድንልህ ነበር። ነገር ግን እሥረኛ ሁሉ በመዝገብ ተመዝግቧል ተቆጣጣሪዎች መጥተው የያንዳንዱን እሥረኛ ስም በሚቆጣጠሩበት ጊዜ ያንተ ስም ቢታጣ እኛን ለመከራ ይዳርጉናል። ስለዚህ እንፈራለን አንተ ግን ክርስቲያን ስለሆንክ ከሄድክበት ተመልሰህ እንደምትመጣ እናምናለን አሉት ቅዱስ ባስሊቆስ ብቻዬን እንድትልኩኝ ካልፈቀዳችሁ



ከናንተ አንዱ ተከትሉኝ ይሂድ ክርስቲያኖችን ለመፍጀት የሚመጣው እምቆማኖስ ከመድረሱ አስቀድማችሁ ይህን ዕድል ሥጡኝ በማለት አጥብቆ ለመናቸው።

ወታደሮቹ በሱ አባባል ተስማሙና በነሱ ታጅቦ ወደሥጋ ሄደ ወደቤቱም ደርሰውከናቱና ከወንድሞቹ ቤት ሲደሰቱ አደሩ ቤተሰቦቹ ደስታቸውን ለመግለፅ የቻሉት ከእሥር ነፃ ሁኖ የመጣላቸው መስሎአቸው ነው በማግሥቱ ጧት መላ ቤተሰቦቹን አብሮአደጓች ጓደኞቹን ሰብስቦ ብዙ የእግዚአብሔር መንገድን የተከተለ ምክር መከራቸው እንዲህም አላቸው "አባቶቼና ወንድሞቼ ሆይ በክርስቶስ ሃይማኖት ፅኑ አትስነፉ ለጥፋትም እጃችሁ አትሥጡ የሥጋንም መከራ አትፍሩ ሃይማኖት በምእመናን ልቦና እንድታድርም ፀልዩ እኔንም ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማዕትነት እንዲያፀናኝ ፀልዩልኝ እኔ ከናንተ ተለይቼ እሄዳለሁ ዳግም በአካለ ሥጋ አታዩኝም" አላቸው።

እነሱም በመንገድህ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ይከተልህ እኛንም ወደኢየሱስ ክርስቶስ ፀልይልን ስለጠቅላላ ክርስቲኖችም ፀልይ እግዚአብሔር ሰዎችን ከአምልኮጣኦት ይሠውራቸው ዘንድ የእግዚአብሔርም ፀጋ ይመጣላቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ፀጋ በምድር ሁሉ ትበዛ ዘንድያንተ የዘወትር ፀለትህ ትሁን በማለት ማለዱት።

ትያጥሮን፣ ጺጣሰስና ስራጺዮን ተብለው የተሰየሙ ሦስት አብያተጣኦት ነበሩ። በነዚህ ሦስት ጣኦቶች እየተገኘ መኮንን አግዲጢስ መሥዋዕት ያቀርብ ነበር ክርስቲያኖች ለነዚህ ሦስት ጣኦታት አንሰዋም በማለታቸው በየእስርቤቱ ይገኙ ነበር መኮንኑ ቅዱስ ባስሌስቆስ ቤተሰቦቹን ተሰናብቶ ወደነበረበት እሥር ቤት ከመመለሱ አስቀድሞ እሥር ቤቱን ጎበኘና ቅዱስ ባስሌስቆስን



www.ethiopianorthodox.org

አጣው፣ በዚህ ጊዜ የእሥረኞቹን ጥበቃ ክፍል ሐላፊ አሠረው "ባሰስ" ወደተባለው መኮንንም አመጣውና እሥረኛውን እንዴት ለቀቅኸው አለው። እሱም ባራት ቀን ውስጥ አመጣዋለሁ አለ የእሥረኞችን አለቃ ይዞ የመጣው መኮንን አግዲጢስ በዚሁ ተዋሰው።

መኮንን አግዲጢስ ወታደሮችንና አሳሾችን አስይዞ የወህኒ ቤቱን አለቃ ቅዱስ ባስሌቆስን ካለበት አድነው እንዲያመጡት አዘዘ። እየገረፋችሁና እየደበደባችሁ ባስሌቆስን አምጡት እንዳያመልጣችሁም ተጠንቀቁ ቢያመልጣችሁ ግን በምትኩ በናንተ ላይ የምትቅጣት ይፈፀማል አላቸው እነሱም ቅዱስ ባስሌቆስ ወደተወለደበት አገር ሄዱ ቅዱስ ባስሌቆስንም ይዘው አመጡት እያመጡት እያለም ብዙ መከራ አደረሱበት በዱላ በብረት በጅራፍ እየቀጠቀጡ ምድር ለምድርም እየጎተቱ ስላሰቃዩት ደሙ በየመንገዱ ፈሰሰ የሥጋ ዘመዶቹና ሌሎች ክርስቲያኖች ከሩቅ ይከተሉት ስለነበር እጅግ ያዝኑና ያለቅሱ ነበር በወቅቱ እናቱና ሦስት እህቶቹ በሕይወት ነበሩ። በመከራው ሰዓት እነሱ ሲያለቅሱለት አይቶ ባካችሁ አታልቅሱብኝ ይህን የጀመርኩትን ገድል እግዚአብሐር እንዲያስፈፅመኝና ባሸናፊነት እንድወጣው ፀልዩልኝ ብሎ እናቱን፣ እህቶቹንና አብሮ አደጓቹን በመሳሳም ተሰናበታቸው የዘለዓለማዊ ሕይወት ካለበት መንግሥተሰማያት ዳግም እንተያያለን ሲልም አምላካዊ ተሰፋን አሰማቸው።

ከወታደሮቹ ጋር ከመጡት አሳሾች አንዱ ቅዱስ ባስሌስቆስን ለመሰናበት የተሰበሰቡትን እናቱ፣ እህቶቹና ጓደኞቹ በሱ ላይ በመፈፀም ላይ ያለ ቅጣት በናንተ ላይም እንዳይፈፀም ወደቤታቹ ቶሎ ተመልሳችሁ ግቡ በማለት አስጠነቀቃቸው እነሱም ፈርተው ቶሎ ቤታቸው ገቡ። ቅዱስ ባስሌስቆስ ግን ከባዱን መከራ ታግሦ ከመዝሙረ ዳዊት እየጠቃቀሰ ለመከራ ጊዜ ተስማሚ የሆኑትን

መዝሙሮች ይዘምር ነበር። እሱ እየዘመረ እነሱም እያሰቃዩት "ጳቃራዚ" ከተባለው ቦታ ደረሱና ጥቂት ዕረፍት አደረጉ የዚሁ ቦታ ባለቤት የለየላት አረማዊት ሴት ስትሆን በዚሁ ቦታ ከተማ ሰመከተም ትጣጣር ነበር። ቅዱስ ባስሌቆስን በማሰቃየት ሲጓዙ ድካም ተሰምቶአቸው ለጥቂት ጊዜ ያረፉት አዳኞችና ወታደሮች ቁጥር 13 /አሥራ ሦስት/ ነበር። ነገር ግን ከዚያ ሳይነሱ ብዙ ቆዩና ቀኑ መሸ አረማዊቷ ሴት አሥራ ሦስቱ ራት እንዲበሉ ወደቤቷ ጠራቻቸው።

እነሱም ቅዱስ ባስሌቆስን ለጠኖስ ከሚባል የደረቀ ግንድ ላይ አጣብቀው በመጠፈር አሥረው ሲያበቁ የተጠሩበትን ግብዣ ለመብላት ወደአረማዊቷ ሴት ገቡ። እሱም ከታሠረበት ሁኖ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ ብዙ ሰዎችም ወደታሠረበት ተሰበሰቡ የልብሱንም ጫፍ ለመንካት ይጋፉ ጀመር በዚሁ ታላቅ ትርምስ ተፈጠረ ታላቅ ድንጋጤም ባካባቢው ሆነ በአረማዊቷ ሴትራት በመብላት የነበሩ አሥራ ሦስቱ ሰዎችም እጅግ ተደናግጠው የቀረበላቸውን ምግብ ሳይበሉ ወጡና ቅዱስ ባስሌቆስ ወደታሠረበት ቦታ መጡ።

ያ ቅዱስ ባስሌቆስ የታሠረበት ደረቅ ግንድ ለምልሞ በመጠንም አድጎ ብዙ መልካም መዓዛ ያለባቸው ቅርንጫፎች ተጨምረውለት አገኙ። ከዚሁ ዛፍ እግርም ውሃ መንጭቶ አዩ ይህን በዚሁ ቅዱስ ሰማዕት አማካይነት የተገለፀው የኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ ተአምር የተመለከቱሰዎች በቅዱስ ባስሊቆስ እግር እየወደቁ ሠገዱ ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ነው ይሉም ነበር ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ ጋኔን የያዘውንም ሰው አመጡና በቅዱስ ባስሊቆስ ዕግር ላይ ጣሉት ጋኔኑም ትቶት ወጥቶ እግዚአብሐርን ያመሰግን ጀመር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን እነዚያ ቅዱስ ባስሊቆስን እያሠቃዩ



www.ethiopianorthodox.org

በመውሰድ ላይ የነበሩ አረማውያን ምንም ወደልባቸው አልተመለሱም ባዩት የእግዚአብሔር ተአምርም አድናቆት አላደረባቸውም። ነገር ግን ሌላም ድንቅ ተአምር በዚሁ ቅዱስ ሰማዕት ዙርያ ተፈጠረ በአካባቢው የነበሩት የላሞች መንጋ ተሰበሰቡና "እምቧ" እያሉ ቅዱሱን ሰማዕት ይዞሩት ጀመር የዱር አራዊቶችም ከነሱ ጋር በመደባለቅ የየራሳቸውነ ድምፅ አሰሙ። እነዚህ ድንቅ የእግዚአብሔር ተአምራት እየታዩ ሌሊቱ ነጋና ሠራዊቶቹ ቅዱስ ባስሊቆስን ይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ፣ ብዙ ከተጓዙ በኃላ የመሰላል መሸጋገሪያ ካለበት ወንዝ ደረሱ ወንዙ ኢያሬዎስ ይባላል የመሸጋገሪያው መሰላል ከረጅም ድንጋይ የተሠራ ነበር። በዚሁ ድልድይ ላይ እየተሻገሩ ሳለ ድልድዩ ተነቃነቀ ሰዎቹም እስኪንቀጠቀጡ ድረስ በቅዱስ ባስሊቆስ አማካይነት የእግዚአብሔር ድንቅ ተአምር ታየ። ሌሎችም ድንቅ ሥራዎች በዚሁ ሰማዕት ጉዞ ጊዜ ታይተዋል።

ወንዙን ተሻግረው ብዙ ከተጓዙ በኃላ ሳዋይን ከተባለው ሥፍራ ደረሱ ከዚሁ ምሳ ለመብላት ሲቀመጡ ቅዱስ ባስሊቆስ አብሮአቸው እንዲበላ ጠየቁት ያስገድዱትም ጀመር እሱ ግን እምቢ እኔንስ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመግበኛል አላቸው። እነሱ ግን ባክህ ብላ በረሀብ ብትሞትብን ለምን አላመጣችሁትም ተብለን እንገደላለን እህል ከቀመስክ ዛሬ ሦስት ቀንህ ነው አሉት እሱ ግን የሚሞትን ምግብ አልመገብም የምመገበው የሕይወትን ምግብ ነው።እናንተ የእለት እንጀራ ያጠግባቹኋል እኔ ግን በቃለ እግዚአብሔር እጠግባለሁ እናንተ በምድራዊ መጠጥ ትረካላችሁ እኔ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እረካለሁ እናንተ በሳቅ ትደሰታላችሁ እኔ በፀሎት እደሰታለሁ፣ እናንተ መዋቹን መኮንን ትታመኑት አላችሁ እኔ ደግሞ በዘለዓለማዊው አምላክ እታመናለሁ፣ እናንተ ምድራውን ክብር ትሻላችሁ እኔ ግን ሰማያዊውን ክብር እሻለሁ፣



እናንተ ምድራዊ ውዳሴ ትሻላችሁ እኔ ግን በምታሥፈራዋ የእግዘአብሔር ዕለት ከቅዱሳን ሰማዕት ጋር በቀኝ ቆሜ የአባቴ ቡሩካን ከሚባሉ መካከል አንዱ እንድሆን እሻለሁ አላቸው።

እነሱ የሚመገቡትን መብል በሱ ቅዱስ ባስሊቆስ ደግሞ ከሥቃይ ብዛትና ረሀብ ሰውነቱእጅግ ተጎሳቆሉ ስለነበር ከመኮንኑ ፊት ሳይደርስ እንዳይሞትባቸው በመፍራት አሕያ ላይ እንጫነው አሉ። እሱ ግን አህያ ላይ መጫኑን አልተቀበላቸውም እምቢ አላቸው እንዲህም አለ"እኔን ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳርፈኛል" ከዚያ መንገዳቸውን በመቀጠል "ቆማስ" ወደሚባለው ሥፍራ ደረሱ በማግሥቱ አረሜናዊው መኮንን በሱ ከእሥር መታጣት ምክንያት ብዙዎች ክርስቲያኖችን እያሰቃየ መሆኑ ተሰማ ወታደሮቹ ቅዱስ ባስሊቆስን ሲያስረክቡት መኮንኑ የታሠሩትን ሁሉ ፈታቸው ደስታም ተሰማው ቅዱስ ባስሊቆስ ወደጣኦቱ በቀጥታ ተወስዶ እንዲሠግድና መሥዋእት እንዲያቀርብ ይጠየቅ እምቢ ካለ ግን ባስከፊ አሟሟት ይገደል ሲል መኮንኑ ወድያው አዘዘ።

የመኮንኑ ትእዛዝ የተቀበሉት ወታደሮች እየደበደቡ መኮንኑ ለጣኦቱ ሥገድ መሥዋእትንም አቅርብ ይላሃል እምቢ ካልክ ግን ከፉ ሞት ትሞታለህ እንግዲህ ውሳኔው የራስህ ነው ከሞት ብትተርፍ ይሻልሃል ለማይታይ አምላክ ብለህ አትሙት አሉት።

ቅዱሱ ሰማዕት መለሰና እንዲህ አላቸው አምላክ የማይታይ አይደለም ይታያል ሁልጊዜ ይታያል የማይታይበት ጊዜ የለም እሱ ደግሞ ሁሉን ያያል የውስጥም ሆነ የውጭ ከሱ የተሠወረ ነገር የለም እኔ እንኳ ዝም ብል ከኔ ጋር በጉዞ ላይ የሰነበቱ ሁሉ ያዩትን የእግዚአብሔር ሥራ ይነግሩአቹኋል አለ እነሱም ከቅዱሱ



www.ethiopianorthodox.org

ሰማዕት አያይዘው በየመንገዱ የተከሠቱትን የእግዚአብሔርተአምራት መሠከሩ ተአምራቶቹም በሥራይ ሊደረጉ የማይችሉ በእግዚአብሔር ሐይል ብቻ የሚፈፀሙ ናቸው ሲሉም ገለፁ። ከዚህም አያይዘው ቅዱሱን ሰማዕት አንተ ቅዱስ የእግዚአብሔርሰው ሆይ ከቤተሰቦችህ ስትለይ ጀምሮ ከዚህ እስከደረስክ ድረስ ባንተ ላይ የፈፀምነውን ግፍ አታሰብን ይቅር በለን ወደእግዚአብሔርም ፀልይልን ኢየሱስ ክርስቶስ የቅዱሳንን ፀሎት እንደሚሰማ እናውቃለንና ከቅዱሳንም አንዱ አንተ ነህ በማለት ፀፀታቸውን ገለፁለት።

የነሱ ንግግር ሳያልቅ ከመኮንኑ የተላኩ ወታደሮች መኮንኑ ለአማልክት ይሠዋ ዘንድ ባስሊቆስን ይጠረዋል አሉ ቅዱስ ባስሊቆስም ደስ እያለው ወደ መኮንኑ ሄደ ከመኮንኑ ፊትም በቀረበ ጊዜ መኮንኑ ባስሊቆስስ የምትባለው አንተነህን ሲል ጠየቀው እሱም አዎን አለ መኮንኑ ለምንድር ነው ለአማልክት የማትሠዋው ሲል ጠየቀው እኔ እንደማልሠዋ ማን ነገረህ እኔ ለዘለዓለማዊው ሕያው አምላክ የምሥጋና መሥዋእትን እሠዋለሁ የሚል መልስ ሲሠጠው መኮንኑ ተደሰተና ምሥጋናው ለአማልክት ነውን ብሉ ጠየቀው ቅዱስ ሰማዕት እኔ ለአምላኬ መሥዋዕት አቀርባለሁ አለው ወድያው የአሕዛብ አማልክት ካሉባቸው መካከል ወዳንዱ ሄደና አምላካችሁ ማን ይባላል ብሉ ጠየቃቸው እነሱም አጵሉን ይባላል በማለት መለሱለት ቅዱሱ ሰማዕት እንደበታችሁ አሣምራችሁ እንደቁም ነገር አጵሉን ይባላል ትላላችሁ እሱ የሚያምኑትን ይዞ የሚጠፋ ነው እኔ ግን የሚያምኑትን የሚያድን አምላክ ነው የማምነውና መሥዋእትንም የማቀርብለት አላቸው።

በዚህ ጊዜ መኮንኑ ለፈለግኸው አምላክ መሥዋእት አቅርብ እኛም እንይ አለው ቅዱሱ ሰማዕት እኔ የማቀርበው መሥዋዕት ምሥጋና ነው ብሉ ሲያበቃ ፀሎቱን ጀመረ እንዲህም አለ" የሰማይና የምድር አምላክ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ብቻ ነህ እውነተኛው አምላክ ልብንም የምታውቅ አንተ ነህ የማትሸነፍ ይቅር ባይ የምትታይ አምላክ መጀመርያና መጨረሻ የሌለህ ቅዱሳንህን ሁሉ የምትረዳቸው አንተ ብቻ ነህ። ቅዱስና ፃድቅም አንተ ብቻ ነህ በኔ በአነስተኛው ላይም ምህረትህን አሳይ። ሰማይን እንደብራና የዘረጋህ አንተ ነህ የፀናሃትም አንተ ነህ በከዋክብትም ሰማይን የሸለምክ አንተነህ ለፀሐይንም ብርሃን የሠኸው አንተ ነህ ምድርንም በአበባ የምትሸልም አንተ ነህ ሰውን በመልክህ የፈጠርከው አንተ ነህ አዳም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከዛሬ ንፁሕና ቅዱስ አንተ ብቻ ነህ አምላኬ ሆይ የኔን የባርያህን ቃል ስማ ወደዚህ ቦታም ና ይህንንም የአጋንንት ማደርያ ጣኦት ቀጥቅጠው ጠላቶችህ ባንተ ላይ እንደዘበቱ አይቅሩ ሐይልህን አሳይ..." ብሉ ሲፀልይ የመሬት መናወጥ ሆነ እሳትም ከሰማይ ወረደና ጣኦቱ ያለበትን ቤትና ጣኦቱ አቃጠለው።

መኮንኑ ሽሽቱን ቀጠለ ባገሩም ፍርሐትና ድንጋጤ ሆነ ሌሎቹም ሕይወታቸውን ለማትረፍ በረገጉ ቅዱስ ባስሊቆስ ብቻውን በቦታው ቀረ። እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ይዘምር ነበር። መኮንኑ በዚህ ጊዜ ጥርሱ እስከማፋጨትና ጠጉሩን እስከመንጨት እጅግ ተናደደና ቅዱስ ባስሊቆስን አስቀርቦ አንተ ወራዳ ፍጡር ያበድክና የአማልክት ጠላት ለምንድር ነው ለአማልክትመሥዋእት ከማቅረብ ፈንታ በእሳት ያቃጠልካቸው አንተ ግን የሥራይ ሰው ስለሆንክ እሳት ሳያቃጥልህ ቀረ አሁንም ቁርጡን ንገረኝ ለአማልክት የምትሠዋ ከሆነ ከሞት እንዳድንህ ፈቃደኛ ካልሆንክ ግን በፍጥነት ለሞት አሳልፌ እሰጥሃለሁ ሲል ምርጫ ሠጠው።

ቅዱስ ባስሊቆስ "እኔ ለረከሱ አማልክት አልሰዋም


www.ethiopianorthodox.org

አልሰግድምም የምሥጋና መሥዋእት በእግዚአብሔር ስም ብቻ አቀርባለሁ ካለው በኃላ ስምህ መኮንን ነው በግብርህ ግን መኮንን ሳትሆን የረከሱ ወንጀለኞችን ትከተላለህ እኔ ከመድሐኒቴና ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ሳልወጣ ሩጫዬን እንድፈፅም እፈልጋለሁ" የሚል መልስ ሠጠው መኮንኑ የመጨረሻው ተስፋ ቆርጦ እንደ ማይመለስለት በመረዳቱ አንገቱን በሠይፍ ይቆርጡት ዘንድ አዘዘ። ወታደሮች ከከተማው ውጭ ወሰዱት ብዙ ምእመናን በፀሎትህ አሥበን ኢየሱስ ክርስቶስ በረከቱንና ረድኤቱን ይልክ ዘንድ እያሉ በመከተል ሸኙት በዚሁም ወደወንዝ ተጣለ ነገርግን ቅዱሳን ምዕመናን ከተጣለበት አንሥተው ለመቅበር ይፈቅዱላቸው ዘንድ 30/ሰላሳ/ ዲናር ሠጥተው በሌሊት ወደ እርሻ ቦታ ወስደው ቀበሩትና የተቀበረበትን ቦታ ጠላቶች እንዳያውቁ በላዩ ላይ አተር ዘሩበት።

ቅዱስ ባስሊቆስን ያስገደለው አግዲቅስ መኮንን ከባድ በሽታ ታመመና መድሐኒትን ፈልጎ ሊያገኝ አልቻለም ነገር ግን ቅዱስ ባስሊቆስ የተቀበረበትን ቦታ አግኝተህ ከመቃብሩ አፈር ብትቀባ ትፈወሳለህ ተብሎ ከክርስቲያኖች ተነገረው መኮንኑም ቅዱስ ባስሊቆስ የተቀበረበትንቦታ ለማግኘት ብዙ ደከመ ነገር ግን ማንም ሊነግረው አልቻለም ቢቸግረው ወደተሰየፈበትና እስከሬኑ ወደተጣለበት ቦታ ሄደ ጥቂት ከደሙ ነጠብጣብ ደርቆ አገኘና አፈሩን አንሥቶ ተቀባው ወድያውም ከበሽታው ተፈወሰ በኢየሱስ ክርስቶስም አምኖ ተጠመቀ መክሲሞስና መክሲሚያኖስ አረማውያን ነገሥታትም በዚሁ ዓመት ሞቱ ክርስቲያኖች ከሥደት ነፃ የሆኑበትም ዘመን ተፈጠረ ትልቁ ቆስጠንጢኖስ መንግሥትነቱን ተረከቧልና።



## ምዕራብ ፲፯ የቅድስት ክርስጢና ገድል

የቅድስት ክርስጢና አባት መኮንን ሲሆን "ርባኖስ" ይባላል። ቅድስት ክርስጢና ወደር የማይገኝላት ቆንጆ ስለነበረች ያባትዋ ባለንጀሮች እሷን ለልጆቻቸው ለማጋባት ብዙ ይደክሙ ነበር። አባትዋ ግን ለማንም አላጋባትም በድንግልናዋ ተጠብቃ አማልክትን ታገለግላለች ይል ነበር። እሷ ግን በሕሊናዋ እግዚአብሔርን የምታምንና በመስኮት ወደምሥራቅ ፊቷን በማዞር ወደእግዚአብሔር የምትፀልይ ነበረች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም ሌት ተቀን በድብቅ ብዙ ትጥር ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆንም ውጭ እንድትወጣ በጭራሽ አይፈቀድላትም ነበር። ከቤት ውስጥ ተዘግታ ነበር የምትኖረው አማልክን ለማገለገል ግን ይፈቀድላት ነበር፣ ለአማልክት የሚቀርበውን ምሥጋና እሷ እንድታቀርብ አባቷ መድቧት ነበር።

ወደእግዚአብሔር በምትፀልይበት ጊዜ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ርዳኝ ጣኦትን ከማምለክም አድነኝ ትል ነበር። ለሷ የተመደቡ ሴቶች ባሮችም ነበሯት እንዚህ ባሮች ለሷ የተመደቡት ለአማልክቱ ዕጣን ሥታቀርብ እንዲረዱዋት ተብሎ ነው። እሷ ግን ለአማልክቱ ምንም የምትፈፅመው ነገር አልነበራትም ሥራውን እጅግ ተፀየፈችው። በዚህ ጊዜ ባሮቿ የኛ እመቤት ሆይ ለአማልክት የሚቀርበው አገልግሎት ታጎለ ዕጣን ማቅረቡን ትተሻል እነሱ ይቆጡሻል ባንቺ ላይም መከራ ሊያመጡብሽ ይችላሉ እኛንም ሊገድሉን ይችላሉ አሏት እሷም እናንተ ለምን እንዲህ ትላላችሁ እነሱ የረከሱ እንደሆኑና የውሸት አማልክት እንደሆኑ አታውቁምን እነሱ እኮ ነፍስ የሌላቸው የታወሩ፣ የደነቆሩ አፍ የሌላቸው ናቸው እኔ ንፁህ ምሥጋናን መሥዋእት አድርጌ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው የማቀርበው።



www.ethiopianorthodox.org

ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የኖረ፣ ያለና የሚኖር እግዚአብሔር ብቻ ነው አምላክ ብላ ነገረቻቸው ከባሮቿ ጋር ይህን ስትናገር አባቷ ለአማልክት ሊሰግድ መጣ እሷንም በማየቱ ደስ አለው ከሱ ጋርም ለአማልክት እንድትሠግድ ጠበቃት እሷ ግን ለመስገድ ሳትመጣ ቀረች ሴቶቹ ባሮች አማልክት ዕጣን ሳይቀርብላቸው ሰባት ቀን አለፈ ለአማልክትም መስገድ ካቆመች ሰባት ቀን ሁኗታል ብሎው ነገሩት እሱም ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደምትሠግድና እንደምታመልከው ስላረጋገጠ የተወደድሽው ልጄ ሆይ በኢየሩሳሌም አይሁድ ለሠቀሉት ኢየሱስ እንድትሠግጂና እንድታመልኪው ያሳመነሽ ማነው አሁንም እኔን ስሚኝ ለአማልክት ሥግጂ ካልሆነ ግን ተቆጥተው ይገድሉሻል ብሎ አስጠነቀቃት።

እሷም እኔ የምሠግደው ለሰማይና ምድር ጌታ እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው እሱ ከሰማየሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን አድኗልና ስግደት ክብርና ምስጋናም ለሱ ብቻ ይገባል ስለዚህ ከቻልክ አንተም እንደኔ ለመድሐኔዓለም ክርስቶስ ሥገድ ካልቻልክ ግን ተወኝ ብላ መልስ ከሠጠችው በኋላ ንፁህ ልብስን ለብሳ ፊቷን ታጥባ ወደ ክፍልዋ ገባችና "ወልደአምላክ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ መንበርህ በሰማያት ላይ ነው ካባትህ ዘንድ ተልከህ ወደምድር ወረድክ የሰው ሥጋንም ለበስክ ተወለድክ፣ ተጠመቅህ፣ ተሠቀልክ፣ ሞትክ በሦስተኛው ቀን ተነሣህ ይህን ሁሉ ስለሰው ፍቅር አደረግኸው ጌታዬ ሆይ ሳላውቅ ለባእድ አምላክ ስሠግድ ኖርሁ ሐጢአቴን ይቅር በለኝ በምህረትህ ብዛትም የመንግሥትህ ተካፋይ አድርገኝ" በማለት ፀለየች።

ፀሎቷን ፈፅማ ክርስጢና ዕረፍት ስታደርግ የእግዚአብሔር መልአክ ተገልፆ አፅናናት እግዚአብሔር ፀሎቷን እንደተቀበለ



ገለፀላት ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ፆምንና ፀሎትን ታዘወትር ጀመር እግዚአብሔርን እያመሠገነች ከአምልኮ ባእድ ወጥቼ ወደሕይወት ዘለዓለም እንድገባ ስላደረግኸኝ አመሠግናሃለሁ ሐጢአቴን ይቅር በለኝ ከሰማዕታት ማሕበር እንድሆንም አድርገኝ ባለፈውም ሐጢአቴ ይቅር በለኝ ካለች በኋላ ጣኦታቱን ሠባበረቻቸው ጣኦታቱ ተሸልመውባቸው የነበሩትንም የተለያዩ የወርቅ ሥራዎች በሙሉ ወስዳ ለድሆች መፀወተቻቸው አባቷ እንደልማዱ ሊሠግድ አማልክት ካሉበት ሲገባ ተሠባብረው አገኛቸው እጅግ ደነገጠና አማልክት ምን ሁነው ተሠባበሩ ብሎ የክርስጢናን ባሮች ጠየቃቸው እነሱም ልጅህ ክርስጢና ሠባብራ ጣለቻቸው ብለው ነገሩት። ይህ የቅድስት ክርስጢና አባት መኮንን ርባኖስ በዚሁ ተናድዶ ቅድስት ክርስጢናን በጥፊ መታት አማልክትን የትጣልሻቸው ሲልም ጠየቃት እሷም የሐሰት አማልክት ስለሆኑ ሠባብሬ ጣልኳቸው ከነሱ ላይ የነበረውንም ወርቅ ለድሆች መፀወትኩት አላቸው።

መኮንን ርባኖስ ለሰማይ አምላክ ከሰገድሽ ሥጋሽን ለሰማይ ወፎች እሠጣለሁ ነገር ግን የሰማይ አምላክ ለሆነው ፀሐይ ሥግጂ ወፎች... 

ወፎች እሠጣለሁ ነገር ግን የሰማይ አምላክ ለሆነው ፀሐይ ሥግጂ አላት ቅድስት ክርስጢና ደግሞ ውሸት ለመናገር ፈልገህ እውነት ተናገርህ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሰማይና ለምድር አምላክ እንድሰግድ አዘዝከኝ እሱ ሰማይንና ምድርን፣ ፀሐይንና ጨረቃን የፈጠረ ዘለዓለማዊም ነውና እሱም ወልደእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አለችው።

መኮንን ርባኖስ አማልክቱን ስትሠባብራቸው የቅድሰት ክርስጢና ባሮች ወድያው ሳይነግሩት በመቅረታቸው እንዲገደሉ አዘዘ አስገደላቸውም ቅድስት ክርስጢና ግን አንተ አመፀኛ፣ ሐጢአተኛ፣ ልብህ የታወረ የሠይጣን ልጅና የፅድቅ ጠላት



www.ethiopianorthodox.org

ባሮቼን ለምን ገደልካቸው አንተንም የጨለማ መላእክት በእሳት ሠይፍ በሰማያት ይገድሉሃል አለችው በዚህ ጊዜ እንድትገረፍ አዘዘ እሷም ተገረፈች እናቷ መገረፍዋን ለጊዜው አላወቀችም ነበር ግርፋቱንም በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ቻለችው ገራፊዎቿ ግን ደከሙ በግርፋት እሷን ማሸነፍ ተሳናቸው። ቅድስት ክርስጢና በበኩልዋ ርባኖስ መኮንን አባቷን አንተ ወራዳ ፍጡር እኔን የሚገርፉ ደከሙ ወደቁም አለችው በዚህ ጊዜ እጅግ ተናደደና አንገቷ ላይ ከባድ ብረት አስገብተው እጅና እግርዋ በእግር ብረት እንዲያስሯት ከዚያም ወደወህኒ ቤት እንዲያስገቡዋት አዘዘ።

ይህን ብሎ ወደቤቱ ሄደና ከንዴትና ከብስጭት ብዛት የተነሳ እህል ውሃ ሳይቀምስ አደረ። እናቷ በልጅዋ ቅድስት ክርስጢና ላይ የተፈፀመውን ስምታ ልብሷን በመቅደድ ኡኡ አለች በራሷ ላይም አመድ እየነሠነሰች ቅድሰት ክርስጢና ከታሠረችበት እሥር ቤት ሄደች። ሰገደችላትም እንዲህም አለቻት "ልጄ ሆይ እኔ ባንቺ ላይ በደረሰው መከራና ሥቃይ እያዘንኩ መሞቴ ነው አሁንም ለአማልክት ሥግጂና ሕይወትሽን አትርፊ አለቻት ቅድስት ክርሰጢናም"እኔንስ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደሱ ይወስደኛል። እኔም ጥሪውን ተቀብዬ ወደሱ እሄዳለሁ። እሱ ለሰው ልጆች የዘለዓለምን ሕይወት የሚሠጥ ነውና ከእግዚአብሔር ቤትወጥቼ እጄን ለአጋንንት አልሠጥም አለቻት።

የልጅዋን መልስ ሰምታ ወደቤቷ ተመለሰችና ከልጅዋ ቅድሰት ክርስጢና የሰማችውን ወደቤቷ ተመልሳ ለባልዋ ነገረችው እሱም እንደገና ከታሠረችበት አውጥተው እንደእንስሣ እየጎተቱ በከተማው እንዲያዞሯት አዘዘ እነሱም አዞርዋት። በዚህ ጊዜ ፅናቷን የተመለከቱ የከተማው ነዋሪዎች ሴቱም ወንዱም የዚች



ሕፃን አምላክ ሆይ እየደረሰባት ካለው መከራ አድናት እያሉ ጮኹ አባቷ በበኩሉ ቀርቦ ለአማልክት ሥግደትንና መሥዋእትን አቅርቢና እየተፈፀመብሽ ካለው መከራ ነፃ እንዳወጣሽ እምቢ ካልሽ ግን መከራውን አፀናብሻለሁ አላት።

ቅድስት ክርስጢና "ባንተ የሚፈፀምብኝን መከራ ታግሼ ወደሰማዕታት ማህበር እገባለሁ አንተ ግን ከፅድቅ ሐጢአትን፣ ከእውነት ውሸትን መርጠህ ለጥፋት ተዘጋጅተሃል ስለዚህ ካንተ ጋር አብሬ እንዳልጠፋ የአለም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃኑን ገልፆልኛል ካሁን በኋላ ከብርሃን ወጥቼ ወደጨለማ አልገባም" የሚል መልስ ሠጠችው በዚህ ጊዜ አባቷ መኮንን ርባኖስ ንዴቱ አገረሸበትና ከዛፍ ላይ አሥረው በማንጠልጠል እንዲገርፏዋት አዘዘ እየገረፏት እያለ ተጠግቶ ይመለከት ስለነበር በግርፋቱ ምክንያት የተቆረጠውን ሥጋዋ አንሥታ አንተ የአጋንንት መሣርያ የረከሥክ ሰው ይኸውና የልጅህን ሥጋ ብላ በማለት ፊቱ ላይ ወረወረችበት።

እሱ ግን በጭካኔው ፀንቶ ክፉ ሞት እንዳትሞቺ ለአማልክቶቼ ሥግጂ አላት። እሷ ግን አንተ የጎሰቆለ ሕይወት ያለህ ርጉም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ የዓለም ብርሃን የፅድቅም ብርሃን የዓለም መድሐኒት ከሰማያት የወረደ ዓለምን ያድን ዘንድ መሆኑን ልታምን በተገባህ ነበር ነገር ግን የሐጢአት ተገዥ እንደሆንክ ቀረህ እኔስ የፊትህን ብርሃን አጨልመዋለሁ በትዕግሥትም ሐይልህን አሸንፈዋለሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኔ ጋር ነውና የሚል መልስ ሠጠችው። አባትዋ አልጋን በእሳት አግሎ በዚያ ላይ እንድትተኛ አደረገ እግዚአብሔር ግን በኪነጥበቡ ከእሳቱ አዳናት።



www.ethiopianorthodox.org

አባቷ መኮንን ክርስጢና ሆይ ይህን ያህል ልቦናሽ ክርስቶስን በማመን ጠነከርን አሁን ቢሆን ከኔ እጅ ማምለጫ የለሽም በክፉ አሟሟት እገድልሻለሁ አላትና መልሶ እሥር ቤት አስገባት ይህም ማድረጉ እሷን ለመግደል የሚችልበትን መንገድ ለማዘጋጀት ነው። እሷ ግን "ሥራይን የምትሽር የሰማይ አምላክ ሆይ መንፈስቅዱስን ልከህ አጽናንተኸኛል እኔ ደካማ ፍጡር ነኝ በኔ በደካማዋ ሐይልህንና ሥልጣንህን ገልፀህል" እያለች ወደ እግዚአብሔር ምሥጋናዋን ታቀርብ ነበር።

መንፈቀሌሊት ሲሆን አባቷ ርባኖስ አምስት አሽከሮቹን ልኮ ወደባህር እንድትጣል አደረገ እነሱም በታዘዙት መሠረት ወስደው ከባህሩ ዳር አስቀምጠዋት ተመለሱ በዚህ ሰዓት በባህሩ አካባቢ ከባህሩም ከየብሱም ከሚርመሰመሱ አውሬዎች በቀር ማንም አልነበረም እሷም "ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ትዕግሥትን ለሰማዕታት የምታድል አንተነህ አሁንም ፈቃድህ ሁኖ ከሐጢአቴ እነፃ ዘንድ አድርግልኝ ከተማሪዎችህ ጋር ወደባሕር ወርደክ ውሃ ውንም የነፍስንና የሥጋን መድሐኒት ይሆን ዘንድ ባርከው እኔ በቅድስት ጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ እወለድ ዘንድ ፍቀድልኝ የነፍሴንም መድሐኒት እንዳገኝ አንተ ርዳኝ ከሐጢአቴ እድፍም አንፃኝ ዘለዓለማዊው ፀጋ ብርሃንም በኔ ላይ አብራ" በማለተ ፀለየች።

ርባኖስ አባቷ ጧት መጥቶ ሁኔታውን ሲመለከት ቁማ እግዚአብሔርን እያመሰገነች አገኛት የሚሆነውን አጣና መልሶ እሥር ቤት አስገባት። እሷም ከፀጋ ላይ ፀጋ እየበዛላት በትጋት ያለ ዕረፍት ትፀልይ ነበር። አባቷ ርባኖስ በዚሁ እለት ከብስጭቱ ጋር ሌላ ተደራቢ ድንገተኛ በሽታ ታመመና ሞተ በምትኩ



ድዮስ የሚባል መኮንን ተሾመ። እሱም ከክርስጢና አባት የበለጠ አረማዊ ነበር። አሽከሮቹ ክርስጢና ያለፈቻቸውን ፈተናዎችን በዝርዝር አስረዱት።

ድዮስ ቅድስት ክርስጢናን እንዳንድ ነገር ያግባባት ጀመር የነገሥታት ዘር መሆንዋንም እየገለፀ ለአማልክት መሥገድ እንዳለበት መልሶ መላልሶ ለመናት በመጨረሻም እንዲህ አላት "ብዙ መከራ መቀበለሽን፣ በብረት መቀጥቀጥሽን ከባህር መጣልሽን፣ በጋለ የብረት አልጋ መቃጠልሽን ሰማሁ ነገር ግን በዚሁ እንድትሞቺ የአማልክት ፍላጎት ስላይደለና እነሱም ውበትሽን አይተው ስለወደዱሽ ከሞት አዳኑሽ ስለዚህ አማልክት ካንቺ ሌላ ነገር አይፈልጉም እንድትሠግጂ ብቻ ይፈልጋሉ ይህም ላንቺ አይከብድም ስለዚህ ሥግጂላቸው እኔም ፅናትሽንና ጥንካሬሽን፣ ውበትሽንና መልካም ቁመናሽን በፅሑፍ ገልጬ ለነገሥታቱ እልካለሁ እነሱም ለልጆቻቸው ያጋቡሻል የቤተመንግሥት እመቤትም ትሆኚያለሽ ይህን ሁሉ ካልተቀበልሽ ግን በፀኑ አማልክቶቼ ስም በመማል ከፉ መከራ አድርሼብሽ ትሞቻለሽ ያን ጊዜ የምትሠግጂለት ክርስቶስ መጥቶ ሲያድንሽ አያለሁ።"

ቅድስት ክርስጢና "አንተም ሆንክ ንጉሥህ ክርስቶስን ማሸነፍ አትችሉም እሱ ያሸንፋቹኋል እንጂ ሐይላችሁን ያደክማል እናንተ በሱ ፊት ኢምንት ናችሁ" የሚል መልስ ሠጠችው "እሱም በድፍረቷና በመልሷ ተቆጥቶ አስገረፋት ግርፋቱን በመቀበል ላይ እያለች አንተ ወራዳና አፋራም ለረከሱ አማልክት እኔን ለማሰገድ ስትነሳ አታፍርም ከዚህ የበለጠ መከራ ብታመጣብኝ ክርስቶስ አምላኬን አልክደውም እያለች ገሠፀችው ድዮስ "አባትሽን



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሠጣቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ለመነች። ለምዕመናኑም ወደወንዝ እንዲወርዱ መንፈስ ቅዱስ ነገራቸውና ሁሉም ተሰብስበው ሲወርዱ የክርስቶስ ካህናት ከወንዙ ዳር ቆመው ቅዱሳት መፃሕፍትን እያነበቡ አገኙዋቸው ስለዚህ ሁሉም በካህናቱ እጅ ተጠመቁ።

ቅድስት ክርስጢና በአባቷ ርባኖስና ከሱ በኋላ ከተሾመው መኮንን ድዮስ የሚደርስባትን ገድል ፈፀመች ከድዮስ ሞት በኋላ የመኮንነቱን ሥልጣን ለሦስተኛ ጊዜ የተረከበው ዩልያኖስ ይባላል። ይህም ክርስቲያኖችን እጅግ የሚጠላ ነበር። በዚህም ምክንያት ቅድስት ክርስጢናን "አባትሽ ርባኖስንና ድዮስን አሸንፈሽ እንዳስገደልሻቸው እኔንም የምትገድልኝ አይምሰልሽ ስለዚህ ክፉ ሞት እንዳትሞቺ ለአማልክት ሥግጂ አላት አንተ የአጋንንት ማደርያ የሆንክ ደካማ ሰውካንተ የሚደርስብኝን መከራ ፈርቼ የምሸነፍ ይመስልሃልን ያንተንስ የማስፈራሪያ ዛቻ እኔን ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚለየኝ ይመስልሃልን" በማለት መለሰችለት።

መኮንኑ በድጋሚ እንዲህ አላት "አንቺ የተረገምሽ ልጅ ለአማልክት ስገጂ፣ ለአማልክት ከሰገድሽ የላቀ ክብር ላንቺ እሠጣለሁ ወርቅን ብርን፣ የከበረ ልብስንና የሽልማት ዕቃ ሁሉ ላንቺ እሠጣለሁ የወንድ ባርያንና የሴት ባርያን ፈቃድሽን ይፈፅሙ ዘንድ እሠጥሻለሁ ይህን ሁሉ አልቀበልም ብለሽ ለመሥገድ ካልተዘጋጀሽ ግን በእሳት ተቃጥለሽ አመድ እንድትሆኒና እንድትጠፊ አደርራጋለሁ አላት።

ቅድስት ክርስጢና ከመኮንን ዩልያኖስ ለተሠነዘረባት የማግባቢያና የዛቻ ንግግር የሠጠችው መልስ ባንተ የማስፈራርያ ንግግር ከኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ አልወጣም አንተም ራስህ የረከስክ



ነህ እኔ ግን የዘለዓለም ብርሃንን ተከትዬ ከመድሐኒቴና ከጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው ያለሁት ወደሱም እሄዳለሁ አለችው።

ዮልዮስ ነበልባል ካለበት ጉድጓድ እንድትጣል ካደረገ በኃላ የጉድጓዱን አፍ ዘግቶት እስከ ሰባት ቀን ድረስ ሰነበተ እግዚአብሔር ግን መልአኩን ልኮ እሳቱን አስጠፋው ቅድሰት ክርስጢናም ምንም ሳትሆን ከሰባት ቀን በኋላ ከእሳቱ ጉድጓድ ወጣች ወታደሮችም በሕይወት መኖርዋን አይተው ለመኮንን ዮልያኖስ ነገሩት። እሱም ወደሱ አስጠርቶ ክርስጢና ሆይ እሳት ሊበላሽ አልቻለም አሁን ለአውሬዎች እሰጥሻለሁ አላት እሷም ካንተ የሚመጣኝን ኩነኔ አልፈራውም በፀጋ እቀበለዋለሁ እንጂ ብላ መለሰችለት።

በተለየ ቦታ ተጠብቀው ከሚኖሩ መርዛሞች እባቦች ሁለቱን አስመጥቶ በነሱ እንድትነደፍ አደረገ እነሱ ግን ሩጠው ከእግርዋ ላይ ተጠቅልለው የእግርዋን ትብያ ይልሱ ጀመር እንደገና አይነታቸው የተለየ ሌሉች እባቦችን አስለቀቀባት። እነሱም ምንም አልነኩዋትም የእግርዋን ትቢያ ከመላስ በቀር ኢየሱስ ክርስቶስ በኪነጥበቡ ጠብቋታልና ዮልዮስ እባቦቹ እንዲነድፉዋት ለምን አላደረገሀም በማለት እባቦቹን ለክፋት የሚጠብቀውን ሰው ተቆጣው። ሰውየው እባቦቹን ድጋሚሊያመጣ ሲሄድ ነደፉትና ሞተ።

ቅድስት ክርስጢና ግን ወደ እግዚአብሔር ፀልያ አስነሳችው እሱም በቅድስት ክርስጢና አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ አለ የኢየሱስ ተከታይም ሆነ የሱንም ከሞት መነሳት የተመለከቱ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። ዩልዮስ መኮንን ግን እኔ ባንቺ ሥራይና በሥራይ በምትፈፅሚው ሁሉ የምሸነፍ አይምሰልሽ አሁንም በክፉ አገዳደል እንዳልገድልሽ ለአማልክት ስገጂ አላት



www.ethiopianorthodox.org

ቅድስት ክርስጢና ግን አንተ ከኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ የወጣህ ልብህ የታወረ፤በእግዚአብሔር ሐይል አሸንፍሃለሁ አለችው።

ዩልዮስ መኮንን የቅድስት ክርስጢናን ጡቶች አስቆረጠና ወደወሕኒ ቤት አስገባት በቀጣዩ ቀን ከእሥር ቤት እያለች ሊመለከታት ሲመጣ እየፀለየችና እግዚአብሔርን እያመሰገነች አገኛትና ምላሷን አስቆረጣት የምላሷን ቁራጭ አንሥታ ከፊቱ ላይ ብትወረውርበት አይኑ ታወረ እሷም አንተ ርጉም መኮንን እነሆ በጨለማ አይኖችህ ተዋጡ ከፉውን ብቻ ስለሚያዩ ታወሩ እኔ እግዚአብሔርን እንዳለመሰግን ምላሴን ቆረጥክ እነሆ ከእግዚአብሔር እጅ የት ታመልጣለህ? አለችው። ወዲያው የሱ ወታደሮች እባቦችን አመጡባትና አንዷ ደረቷ ላይ፣ ሁለተኛዋ ጎድንዋ ላይ ስለነደፉዋት በእግዚአብሔር ፈቃድ አረፈች ከሥጋ ዘመዶቿ ወገን የሆነ አንድ ሰው እሷ በምታርፍበት ጊዜ ደረሰና እሱም በእግዚአብሔር አመነ። ክርስቲያኖችም ገንዘው በክብር ቀበሩዋት።

## ምዕራፍ ፲፰ የቅዱስ እንጦዎስ ገድልና ሰማዕትነት

ቅዱስ አንጦዎስ ከፈሪሳውያን ወገን መሆኑን ራሱ ይናገራል የተወለደበት አካባቢ ቀራይስ ይባላል፣ ነገዱ ከነገደአሞሬዎን ነው። እንጦዎስ ከሌሎች ግብርአበሮቹ ጋር በመሆን አብያተ ክርስቲያናትን ለመዝረፍ ወደደማስቆ ሄደ። የሱ መምጣት ሲሰሙ የደማስቆ ክርስቲያን እጅግ ደነገጡ፣ ተጨነቁ ወደየጉራንጉሩም ሕይወታቸውን ለማትረፍ ተደበቁ። አንጦዎስ ግን በአቅራቢያው የቅዱስ ቴዎድሮስ ቤተክርስቲያን መኖሩን አወቀና ጓደኞቹን ይዞ የቤተክርስቲያኑን ንብረት ለመዝረፍ ወደቤተክርስቲያኑ ገባ።



ጊዜው ሥርዓተአምልኮት የሚፈፀምበት ስለነበር ቤተክርስቲያኑ ክፍት ሁኖ ቆያቸው እነሱም ልብሰተክህኖዋውን፣ መስቀሉን በጠቅላላ ንዋየቅድሳቱን በእሳት አቃጠሉ ቅዱስ ቁርባን በመፈፀም ላይ እያለ ይህን ድርጊት በመፈፀማቸው ክርስቲያኖቹ ወደእግዚአብሔር አለቀሱ ቅዱሱ ማእድ በአሕዛብ ተረገጠብን እያሉም ሐዘናቸውን ለእግዚአብሔር ነገሩ። በዚህ ጊዜ የእሳት ሰይፍ ከሰማይ ወደ ጠረጴዛው ሲወርድ ለእንጦዎስ ታየው በዚህም ሠይፍ ከአረማውያኑ መካከል ብዙዎቹ ተገደሉ እንጦዎስም ቀኝ ጎድኑ ተወጋ በዚህም ፃዕረሞት ያዘው። በዚህ ጊዜ እንጦዎስ በፈፀመው የውንብድና ሥራ ተፀፅቶ ኢየሱስ ክርስቶስን አመነ ድጋሜም በባእድ አምልኮ ላለመጠመድ ወሰነ ከደረሰበት አደጋም ዳነ ሰው እንዲድን እንጂ እንዲጠፋ የማይፈልግ አምላክ እኔን ወደዘለዓለም ሕይወት ጠራኝ እያለም እግዚአብሔርን አመሰገነ። አረማውያኑን በመምራት አብያተ ክርስቲያናትን ለማጎሳቆል ለመዝመት የቻለው እንጦዎስ መኮንን ስለነበረ ነው።

በእንጦዎስ መሪነት በተመዘበረው ቤተክርስቲያን /የቅዱስ ቴዎድሮስ ሰማዕት ቤተክርስቲያን/ሥርዓተአምልኮትን በመፈፀም ላይ የነበሩ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር በተላከው ሐይል በሰላም ፈፅመው ወደየቤታቸው ተመልሰዋል በሚቀጥለው ቀን ወደዚሁ የቅዱስ ቴዎድሮስ ቤተክርስቲያን ተመልሶ እንጦዎስ ሲሰግድና ሲፀልይ ስለሐጢአቱም ሲፀፀት ዋለ ከዚያ ሳይወጣም ባለበት አደረ።

ከቤተመቅደሱ ውስጥ "እንስጦስ ሆይ ንሥሐሕ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለደረሰ አንተ ከክርስቲያን ማሕበር ተቆጥረሃል..." የሚል ቃል ሰማ። እሱም እጅግ ተደሰተ በዚህ ጊዜ እንጦዎስ ሐሳቡ በሁለት ተከፈለበት፣ ካለበት ቤተክርስቲያን እንዳይጠመቅ ቤተሰቦቹ /ሚስቱናልጆቹ/ ንጉሡ ካለበት ከተማ ነው ያሉትና እንዴት



www.ethiopianorthodox.org

ሊያጠምቃቸው እንደሚችል ወይም ደግሞ ሳይጠመቅ ከቤተሰቦቹ እንዳይሄድ ቤተሰቦቹን በሚያወጣበት ጊዜ ንጉሡ ቢገድለው ሳይጠመቅ ሊሞት እንደሚችል፣ በመጨረሻ ብቻው ባለበት መጠመቅ እንዳለበት ወሰነና በፈረሱ ላይ ተቀምጦ አባ ኤልያስ የሚባል ጳጳስ ካለበት ሄደ የተከተሉት ወታደሮችም አብረውት ሄዱ።

ጳጳሱ አባ ኤልያስ በታላቅ ክርስቲያናዊ ክብር ካስተናገዳቸው በኋላ እንጦዎስን ከኔ የምትፈልገው ምንድር ነው ሲል ጠየቀው እሱም በቅዱስ ቴዎድሮስ ሰማዕት ቤተክርስቲያን ያየውን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐይል ገለፀለትና ራሱና ተከታዮቹ ሊጠመቁ መምጣታቸውን ገለፀለት። በዚህ ጊዜ ጳጳሱ አባ ኤልያስ ያካባቢውን ምእመናን ሰብስቦ መንፈሳዊ ደስታን አደረገ ማሕበረምእመናን ባሉበትም ሥርዓተ ጥምቀቱን ለእንጦዎስና ለተከታዮቹ ፈፀመላቸው በዚሁም ጊዜ ዓምደብርሃን ከሰማይ ወደምድር ተተክሎ በዚሁ ቦታ ለተሰበሰቡ ሁሉ ታያቸው።

በዚሁ እለት የተጠመቁ ሰዎች አሥር ሺ ሰባት መቶ ሰድሳ ስምንት ያህሉ ናቸው። ከአይሁድ፣ ከአረማውያንና ከአረቦች እግዚአብሔርን የማያውቁ እግዚአብሔርን አወቁ። በማንም ጊዜ ያልታየ ድንቅ ተአምር በዚሁ እለት ታየ ጳጳሱ አባ ኤልያስ የሚመራው ቅዳሴ ተካሄዶ ሁሉም ከጥምቀት በኋላ ሥጋ ወደሙ ተቀብለዋል።

እንጦዎስና ወታደሮቹ ጥምቀቱን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ደማስቆ ከተማ ተመልሰው ሦስት ቀን ሰነበቱ ከቅዱስ ቴዎድሮስ ቤተክርስቲያንና ከቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያንም በመሄድ በረከትን ተቀበሉ። ቅዱስ እንጦዎስ በንቅልፍ ላይ እያለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታየችውና በእጁ ይዛ ወደብርሃን



አስገባችው በማግሥቱ ከወታደሮቹ ጋር በመሆን ወደግብፅ ጉዞውን ቀጠለ፣ በሕብረትም ግብፅ ደረሱ። የግብፅ ንጉሥ የእንጦዎስ ክርስቲያን መሆንን አስቀድሞ ሰምቶ ስለነበር እሥር ቤት አስገባው ኢየሱስ ክርስቶስ በዚሁ እንዲታሠር ስላልፈቀደ ከታሠረበት አወጣውና ወደኢየሩሳሌም ሄደ ኢየሩሳሌም የደረሰው በእለተሰንበት ስለነበር ወድያው ሥጋወደሙ ተቀበለ። በዚሁ እለት እየተቀደሰ እያለ የነጭ በግ አምሳል ያለውን እንስሳ ቀዳሹካህን በዕርፈ መስቀል ሲያርድ ታይቶታል ርግብ በመሠዊያው ላይ አንገዥ ብባ ትታየው ነበር።

ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ እንጦዎስ ወደ ደማሰቆ ሄደ ደማስቆ እንደደረሰ የዓረብ ተወላጆችናየአሞሬዎን ነገዶች ከንጉሣቸው ጋር ተባብረው ያዙትና እሥር ቤት አስገቡት በዚሁ እሥር ቤት ያላንዳች ጥያቄ ሰባት ወር ታሠረ። ከዚያ በኋላ ወደንጉሡ ወሰደው አቀረቡት ንጉሡም ለምን ካድከኝ ለምንስ አማልክቶቼን ካድካቸው አማልክት አንተን ፈጥረዋል ባህርንም አፅንተዋል። አንተ ከትንሽነትህ የኔ ተከታይ ሁነህ የኖርክ ፈሪሳዊ አይደለህም ወይ ብሎ ጠየቀው።

እንጦዎስ ግን አዎን አንተን ሆንክ አማልክቶችህ ከጃችሁ አለሁ ለምን ቢባል የነፍሥንና የሥጋን ድሕነት እንዳገኝና ሥጋ የሥጋን መንገድ ታሥባለች የሥጋ መንገድም መብልና መጠጥ ነው። ነፍስ ደግሞ የነፍስን መንገድ ታሥባለች አለ። ንጉሡ አንተ ጎስቋላ "ነፍስ" የምትኖረው የት ነው ሰው ሁሉ ከሞተ በኋላ አፈር ይሆናል ካሁን በፊት የሞተ ሁሉ ሐመድ ሆነ እንጂ በማለት ንጉሡ መለሰለት እንጦዎስ ለዚሁ የሚከተለውን መልስ ሠጠ አንተ የሥጋን ብቻ ታስባለህ ሥጋም አንተ እንዳልከው አመድ ይሆናል ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ይነሳል



www.ethiopianorthodox.org

ነፍስ ግን ከፈጣሪዋ ጋር ትኖራለች ልትሞትም አትችልም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድሐኒት ስለሆነ አንተም የምትከተለውን የዕብደት መንገድ ተውና ወደጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግባ እሱ የሞቱትን የሚያነሳ የነገሠታት ንጉሥ ሕያዋንን የሚገድል ፃድቃንን የሚያስደስት ነው አለው።

ንጉሡ እንደሚከተለው መለሰለት "አንተ ራስህ በድን እንደሆኑ ሰዎች ትቆጠራለህ አንተ የምታመልከውም የአይሁድ ሌሎዎች ገድለውት በኢየሩሳሌም አፈር ሁኖ ቀርቷል አንተ ዕብድ ሰነፍ ለምን እሱን ታመልካለህ ተው አትሟሟት ከመልካም ኑሮህ አትፈናቀል መልካም እየበላህ መልካም እየጠጣህ እንዳማረብህ ከብረህ ብትኖር ይሻልሃል ዘመድ ወዳጅና ቤተሰቦችህም አታዋርዳቸው የማይጠቅምን ነገር ነው በመከተል ላይ ያለኸው"

ቅዱስ እንጦሉስ ለዚሁ የሠጠው መልስ ደግሞ የሚከተለው ነው "ልብህ የእከይ መዝገብ ነው፣ የዲያብሉስም ማደርያ ነው ንግግርህም አስፀያፊ ነው ለሚሰሙት አማንያን እጅግ ያስጠላል አንተ አፈር ከሆንክ በኋላ የትንሣኤን ምሥጢር ታየዋለህ ይህም የሚሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድነው ሥራዬ ከፉ ነውና ለፍርድ ለመቅረብ አልነሣም ብትል እንኳ የሚተውህ የለም ተነሥተህ ፍርድህን ተቀብለህ ከአባትህ ዲያብሉስ ጋር ለዘለዓለም ነፍስህና ሥጋህ ስትሠቃዩ ትኖራላችሁ እንጂ"

ንጉሡ በዚህ ጊዜ በዱላ መንጋጋው ላይ አምስት ጊዜ እንዲመቱት ወታደሮቹን አዘዛቸው እነሱም እንደታዘዙት አምስት ጊዜ አፉንና አገጩን ቀጠቀጡት። ጥርሶቹ ረገፉ፣ ከአፉ ደም ጎረፈ። ንጉሡም በመጥፎ አነጋገርህ ይህ ቅጣት ተፈፀመብህ



ይህን ሁሉ ድፍረትና ክፋት ከየት አመጣኸው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኔ ታማኝ ባለሥልጣን ነበርክ ዛሬ ግን በክፋት ተሞላህ በክርስቲያን ሥራይ ጥበብ ተማረክህ፣ እስቲ ከኔ እጅ የሚያድንህ ልይ፣ የምትታመነው በአጥንትና በአፈር ነው። እኛ ግን ለዘለዓለም በማይሞቱ አማልክት ነው የምናመልከው እነሱም አይበሉ፣ አይጠጡ፣ በጠላት ላይ ድልን ያቀዳጃሉ እንጂ አሁንም ከእጄ የሚያድንህ ካለ እስካይ ድረስ አንተን ከማሰቃየት አላርፍም ከዚያ በኃላ መከራው ሲጠናብህ ወደቀድሞው ደግነትህ ትመለሳለህ አለውና ወደእሥር ቤት ወሰደው ከደረቅ ግንድ ጋር አጣብቀው በማሠር እህል ውሃን ሳይሠጡ እስከሰባት ቀን ድረስ እንዲያሰነብቱት ወታደሮቹን አዘዘ።

ወታደሮቹ ሊያስሩት ሲወስዱት ለዚህ ታላቅ ክብር ያበቃኸኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምሥጋና ይገባሃል እያለ ያመሠግን ነበር እነሱም እንደታዘዙት አስረው በተለየ የጨለማ ክፍል ዘግተውበት ሄዱና በሰባተኛው ቀን ብቻ ሁኔታውን ለማየት ሲሄዱ ከታሠረበት ሁኖ እግዚአብሔርን እያመሠገነ አገኙት ተመልሰውም በረሐብ በእሥራትና በመከራው ብዛት ምንም አልሆነም ኢየሱስ ክርስቶስን እያመሠገነ አገኘነው ሲሉም ለንጉሡ ገለፁለት ሁኔታውን ለማረጋገጥ ንጉሡ አስቀርቦ ቢመለከተው ፊቱ እየበራ ምንም የጉስቁልና መልክ የማይታይበት ሁኖ አየውና ለምን ከታሠረበት ቦታ እየወሰዳችሁ ምግብ ሠጣችሁት በማለት ወታደሮቹን ተቆጣቸው እነሱ ግን ለሰባት ቀን ከዘጋንበት ክፍል እንድንመለከተው ባዘዝከን መሠረት ከፍተን አየነው እንጂ የሚበላም ሆነ የሚጠጣ ምንም አልሠጠነውም አሉት ንጉሡ ወደቅዱስ እንጦዎስ ፊቱን አዙሮ ማነው ሲመግብህ የሠነበተው ብሎ ጠየቀው እሱም "አንተ ትዕቢተኛና ማስተዋል የጎደለህ ሰው፣ ሰው በእንጀራ ብቻ



www.ethiopianorthodox.org

ንጉሡ አንተ ከሞትክ በኋላ አክሊልን ትመኛለህ እኔ አንገትህን አስቆርጥሃለሁ አክሊሉንከየትኛው ራስህ ልትደፋው ነው ብሎ የተሰፋ መቁረጥ ንግግሩን አሰምቶ በሠይፍ አንገቱን እንዲቆርጡት አዘዘ። ወታደሮቹ ጥብርያጾስ ከተባለው ባህርዳርቻ አንገቱን ለመቁረጥ ሲወስዱት ይፀልይና እግዚአብሔርንም ያመሰግን ነበር በዚህ ጊዜ ከወታደሮቹ አንዱ ሳይፈራ አይቀርም የማለት ግምት ስላደረበት ለአማልክት ከሠገድክ እኮ አንገድልህም ባክህ ሥገድና እኛም ለንጉሡ የምሥራች እንንገረው አንተም በሕይወት እንተውህ አለው እሱ ግን ቶሎ ቶሎ እፀልያለሁ አንተምቶሎ ግደለኝ ብሎት ፊቱን ወደምሥራቅ አዞሮ ሁለቱ እጆቹን ወደሰማይ በመዘርጋት ነፍሱን ለእግዚአብሔር አደራ ሠጠ" በፈቃዴ እኔ ወዳንተ አልመጣሁም አንተ በፈቃድህ አመጣኸን እንጂ የሠራሁትን ሐጢአቴ ይቅር በለኝ በማለትም የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ይለምን ነበር ከሰማይም "የመረጥኩህ ባርያዩ በሰላም ገድልህን ፈፅመሃል ከቅዱሳን ሰማዕቶቼ ጋር ታርፋለህ የሚያልፈውን የምድር ሐብትና ሹመት ትተህ ሰማያዊውን ክብር መርጠሃል ወደኋላህ አልተመለከትክም ቤትህን ልጆችህን ሚስትህንና ንብረትህን እየወደድካቸው ጥለሀቸው እኔን ወደድክ እኔም ዘለዓለማዊውን መንግሥተሰማያት አወርስሃለሁ" የሚል ቃል ሰማ ደስ እያለውም ሠይፍ ይዘው አንገቱን ለመቁረጥ የተዘጋጁትን ተልእኮዋችሁን ፈፅሙ አላቸው እነሱም ትህትና የተሞላበትን ንግግሩ ሲሰሙ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ወደሠርግ ቤት የሚሄድ ይመስል እንዴት ይደሰታል እያሉም ሠይፉን ከአንገቱ ላይ ለማሣረፍ አልጨከን አሉ እሱን ለመግደል የተመደቡትና በቦታው የነበሩ ሃያ ያህሉ ነበር። በመጨረሻ አንተ፣ ምታው፣ አንተምታው



በመባባል ተፎካከሩ እሱ ግን አንገቱን ዘንበል አድርጎ የሠይፉን ሥለት ለመቀበል ይጠባበቅ ነበር።

እነሱን ለማዘዝ የመጣ አንድ የመቶ አለቃ ከነሱ ጋር ነበር ይህ ሰው የሆነ ይሁን የንጉሡን ትእዛዝ ብቻ የሚፈፅም እንደንጉሡ ጨካኝ ነበር ሰውን ለመግደል ንጉሡ ሲፈልግ እሱን አብሮ ይልካል ሁለተኛ ደግሞ እየታዘዙ የሰውን አንገት ከሚቆርጡ አንዱ የሆነ በመቶ አለቃው የሚታዘዝ ወታደር ከዚሁ ተገኝቶ ነበር ስሙም አቅራጥስ ይባላል። መቶ አለቃው አቅራጥስን ቅዱስ እንጦንስን በሠይፍ እንዲመታው አዘዘው አቅራጥስ ግን ጠጋ ብሎ እኔ አንተን አልገድልህም ብትሞትም ካንተ ጋር ለመሞት ወስኛለሁ ካሉት ወታደሮች መካከል የሰውን አንገት በመምታት የታወቅሁ ነኝ እኔ በሕይወት ወደምትኖርበት አገር ይዤህ ልጥፋ አለው ቅዱስ እንጦንስ ግን በዚሁ ሰማዕትነቴን እጨርሳለሁ አለውና የቀሩትን ወታደሮች ልትገድሉት ትችላላችሁ አላቸው በመጨረሻም አንገቱን ቆረጡት ነሐሴ አሥራ ሰባት ቀን ሰማዕትነቱን ፈፀመ።

የቅርጣስያ ኤጴስቆጳስ ይህ ሰማዕት የተቀበረበትን ቦታ አከበረው በስሙም ቤተክስርቲያንን አሠርቶ ራሱ ቀደሰባት በዚሁ ቅዱስ ሰማዕትም እግዚአብሔርን እየተማፀኑ ከደዌአቸው ይፈወሱ ነበር የዚህ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት በእግዚአብሔር ዘንድ የተሠጠው ክብርና ልዕልና በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ይታወቅ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲፱ የቅዱስ እንድርያኖስና የሃያአራቱ ሰማዕታ እንዲሁም የቅድስት እንጦልያ ገድልና ሰማዕትነት

ከሐዲው መክስምያኖስ ንጉሥ ለሁለተኛ ጊዜ አሠሣ አካሄደ በመቄዶንያ ብዙ ክርስቲያኖችን ፈጆ ለአማልክትም መሥዋዕት ያገቡ ዘንድ የመቄዶንያን ሰዎች አዘዛቸው ሕዝቦቹ አረማውያን ስለነበሩ የበሬ የላም የበግና የወፎች መሥዋእት አገቡ የተሠበሰቡትም እንስሳት በሙሉ በያሉበት ታርደው በእሳት ስለተቃጠሉ ያካባቢው አየር በጢስ ተሸፈነ ያካባቢው የአየር ሽታም እጅግ ተበከለ በዚሁ እለት ለጣኦት ብሉ እንስሳትን ያላረደና በእሳት ያላቃለጠ ከተገኘ እያደኑ የሚገድሉ የንጉሡ ታማኝ ወታደሮች በየቦታው ተበተኑ። ምናልባት ሳይሰዋ ተደብቆ የሚቀር ካለ ንብረቱን ለጠቆመ ሰው እንደሚሠጥ አሳሾቹ መልእክት አስተላለፉ።

በዚህ ጊዜ ብዙዎች ከአረመኔነታቸውም በተጨማሪ በፍቅረ ንዋይ ስለተሳቡ አባት ልጁን ልጅ አባቱን፣ ወዳጅ ወዳጁን እየጠቆሙ አሳልፈው ወገኖቻቸውን ለሞት ሠጡ። ብዙዎች ደግሞ ክርስቲያን ሁነው እያለ በእምነት ስላልፀኑ የንጉሡን ኩነኔ በመፍራት አባታቸውን፣ እናታቸውን፣ ወንድማቸውን ለሞት አሳልፈው ሠጡ። እንዲገደሉ ከተጠቆመባቸው መካከል ብዙዎች በሌሊት እየሸሹ ወደዋሻ ተደበቁ ከነዚህ መካከል እረኞችም ነበሩ። ነገር ግን ወታደሮች ተከታትለው የተደበቁበትን ዋሻ ከበቡና በአፈና ሁሉንም ይዘው ወዳገሩ ንጉሥ ወሰዱዋቸው። የነዚህ ቁጥራቸው 24 ነበር።

ንጉሡ ከየት የመጣችሁ ናችሁ ብሉ ቢጠይቃቸው እኛ ገሊላውያን ነን የምናመነውም ኢየሱስ ክርስቶስን ነው አሉት ለአማልክት ያልሠገደ ሊገደል እንደታወጀ አልሰማችሁምን ክርስቶስን ያመኑ እንደተፈጁስ አላወቃችሁምን አላቸው እነሱም "አንተ



ክርስቲያን እንዳስፈጀህ ሰምተናል ባንተ ዕብደትም ስቀናል የምትሠግድለትንም ሠይጣን ዘብተንበታል" ብለው መልስ ሠጡት። ወድያው በእንጨት አስቀጠቀጣቸው እየተቀጠቀጡ ግን መከራችን በበዛ ቁጥር እምነታችን ይፀናል እያሉ እግዚአብሔርን ያመሠግኑ ነበር የነሱንም ፅናት ሲያዩ ሌሎችም ወደነሱ ኢየሱስ ክርስቶስን እናምናለን እያሉ ይጨመሩ ነበር። እርስ በርሳቸውም በርቱ፣ ፅኑ ይህን የምንቀበለው ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ አክሊለ ሰማዕትን ያቀዳጀናል ይባባሉ ነበር ንጉሡ የሚሉትን አድምጦ ራሳቹሁን ቆርጬ እጥለዋለሁ አክሊሉን ከምን ላይ ነው የምትቀዳጁት ይላቸው ነበር።

አንተ ለአጋንንት እየሰገድክ ነፍስህን ለዘለዓለማዊ ኩነኔ አሳልፈህ ትሠጣለህ እኛ ደግሞመድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለተከተልንና በሱም ስለምናምን ካንተ የሚደርስብንን ሥጋዊ መከራ ታግሠን ወደዘለዓለማዊ ሕይወት እንሄዳለን በማለት ሲመልሱለት ምላሳችሁን ቆርጬ እንዳትናገሩ አደርጋችሁአለሁ አላቸው ምላሳችንን ብትቆርጥ ልቡናችንና አእምሮአችን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ከፊቱም ይጮኻሉ አሉት።

ጥብአታቸውን በመረዳት እነዚህ ከሁሉ በከፋ ቅጣት ከሞቱ በሌላ ሕዝብ መቀጣጫ ይሆናሉ የሚቀጡበትን የቅጣት አይነት እስክናዘጋጅ ድረስ ወደእሥር ቤት ውሰዱዋቸው አለ።

ከንጉሡ መኳንንት መካከል አድርያኖስ የሚባል መኮንን ቅዱሳት ሰማዕታት ከንጉሡ ጋር የሚያደርጉትን ክርክር በፅሞና ይሠማ ነበር። በጥብአታቸውና ከእግዚአብሔር የተሠጣቸውንም መከራን የመታገሥ ፀጋ እጅግ ያደንቅ ነበር የአድርያኖስ ሹመት በንጉሡ ዘንድ የጎልማሶች አለቅነት ነበር ንጉሡ እየሰማውም እኔም እንደናንተ ኢየሱስ ክርስቶስን አምኜአለሁ በሰማዕትነት



www.ethiopianorthodox.org

ከማሕበራችሁ አስገቡኝ እንዴትም እንደማምን አስተምሩኝ በማለት ተማፀናቸው እነሱም ባጭሩ ድሕነተመስቀልን አስተማሩት የኢየሱስ ክርስቶስ የአለም ቤዛነትንም አስረዱት ንጉሡ ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ሊመረምራቸው የሚያስለፈልፋቸው መስሎት ነበር ወድያውም ግራ ተጋባ።

አድርያኖስ መኮንን ከነበረበት የክብርወንበር ዘሎ ተነሳና ወደነሱ ሄዶ ተጨመረ ክርስቲያኖችን እየመዘገቡ ለቅጣትና ለሞት የሚያቀርቡትንም የስም ዝርዝር መዝጋቢዎች የኔንምስም ከነዚህ ሰማዕታት ጋር መዝግቡ ከዛሬ ጀምሮ እኔ ከነሱ እንዳንዱ ነኝ ኢየሱስ ክርስቶስን የማምን ክርስቲያን ሁኛለሁና አላቸው። ንጉሡ አድርያኖስ ሆይ አበድክን ከንቱ ልትሆን ትፈልጋለህን እንዴት እያወቅህ ትጠፋለህ አለው አድርያኖስ ለንጉሡ "አላበድኩም ከዕብደት ተመለስኩ እንጂ" አለው ንጉሡ ስለተናገርከው ከባድ ስህተት ንሥሐ ግባ አለው፣ አድርያኖስ እኔ ንሥሐ የምገባው እስካሁን በሠራሁት ሐጢአት ለአለም ቤዛ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ላንተ አይደለም አለው።

ንጉሡ በአድርያኖስ የኢየሱስ ክርስቶስ ምርኮኛ መሆንን እጅግ አበሳጨውና ከቅዱሳን ሰማዕታት ጋር እንዲታሠር አደረገ እሱንና /አድርያኖስን/ ሌሎቹ ቅዱሳን ሰማዕታት ወደሱ የሚቀርቡበትን ቀነቀጠሮ ሠጥቶም ከፍርዱ አደባባይ ተነሳ። ከአድርያኖስ ተከታዮች አሽከሮች አንዱ ወደቤተአድርያኖስ እየሮጠ ሄዶ የአድርያኖስን መታሠር ለሚስቱ ነገራት የአድርያኖስ ሚስት እንጦልያ ትባላለች እሷም ደንግጣ ኡኡ አለች አለቀሰች የታሠረበትንም ምክንያት ጠየቀችው። እሱም እንዲህ አላት ቅዱሳን ሰማዕታት በስመኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ሲቀበሉ የነሱን ፅናት አይቶ እኔም ኢየሱስ



ክርስቶስን አምኜ ከነሱ ጋር መከራ መቀበል ይሻለኛል በማለት ክብሩን ጥሎ ወደነሱ ስለገባ ታሠረ አላት ቅድስት እንጦልያ እነዚያን ሰማዕታትንስ በምን ምክንያት እንዳሠቃዩዋቸው አውቀሃልን ስትል ጠየቀችው ለአማልክተንጉሥ አንሠግድም ስላሉ ነው የተሠቃዩት አላት በዚህ ጊዜ ሐዘንዋን ረሳች እጅግም ተደሰተች የተቀደደውንም ልብሷ ጥላ ደህና ልብስ ለበሰች እየሮጠችም ባልዋ አድርያኖስ ከቅዱሳን ሰማዕታት ጋር ወደታሠረበት ወህኒ ቤት ሄደች እሷ ከክርስቲያኖች ወገን ናትና ዘመዶቿም በሰማዕትነት አልቀዋልና ክርስቲያንነቷን ደብቃ እያለ ለጣኦት እንድትሠግድ እንዳያስገድዱዋትም ትፈራ ነበር። ከአድርያኖስ ጋር የታሠሩት [24] ሰማዕታት ገና በወጣትነትና በሕፃነት ዕድሜ መካከል የነበሩ ናቸው።

ወደ ወህኒ ቤቱም ገባችና በግንባርዋ ተደፍታ የታሠሩበትን ዕግረብረት አቀፈችው ሳመችውም ባለቤትዋንም አድርያኖስ ጌታዬ ሆይ ብፁዕ ነህ ዘመዶችህ ያላወረሱህን ክብር አገኘህእግዚአብሔር ያበፈፅምህ በስተእርጅናህ የማታገኘውን የእግዚአብሔር ፀጋ በወጣትነት ዘመንህ አገኘኸው ይህን ዓለም ሳትተክዝና ሳትዘናጋ ልታልፈው ነው ባለፀጎች በሚደኸዩበት ጊዜ አንተ ባለፀጋ ልትሆን ነው ነዳያን ትርፋቸውን በሚሰበስቡበት ወቅት አንተም ዘለዓለማዊ ሐብት ልትሰበስብ ነው በምታስፈራና በምታስጨንቅ አደባባይ ሁሉም ዋጋውን በሚቀበልበት ጊዜ የከበረ ቦታ ተሠጥቶህ ልትዘምር ነው ማንም ማን በማይረዳበት ጊዜ አንተ ባለብዙ ረዳትና አይዞህ ባይ ልትሆን ነው የምትፈራውን መዓኢ መከራ አይኖርም ጌታዬ ሆይ መድሐኒዓለም ክርስቶስ ጠርቶሃል በተጠራህበት አደባባይ ፀንተህ ቁም ወደኋላ አትበል ስለዘመድ ስለሐብት ስለልጅ በማንኛውም ምድራዊ ነገር አትጨነቅ ሁሉ አላፊ ነው ሁሉም ጠፊ ነው ጓደኞችህ ትዝ አይበሉህ የአረማውያንን ምክር ጨርሰህ



www.ethiopianorthodox.org

በማምጣት የሰማዕታቱን እግር እያጠበችና እያከመች ሰባት ቀን አሳለፈች።

ሰባት ቀን ቅድሰት እንጦልያ ስታከማቸው ቆይታ በመጨረሻ ንጉሡ እንዲቀርቡ አዘዘ ከእግርብረት ሥቃይ የተነሳ ሊንቀሳቀሱ ስላልቻሉ በአህዮች ተጭነው እንዲመጡ ተደረገ አድርያኖስ ግን ምንም እንኳ ሕመሙ ባይቀርለትም በእግሩ ይጓዝ ነበር። ከንጉሡ አደባባይ እንደደረሱ ንጉሡ እጅግ ተዳከመው አያቸውና ከዚህ ላይ ሌላ ቅጣት በነሱ መፈፀም አስፈላጊ አይደለም ይህን ዓለም ስለጠሉት ቶሎ ሊሰናበቱት ይፈልጋሉ ስለዚህ ቶሎ እንዳይሞቱ ሌላ ቅጣት አትጨምሩባቸው አድርያኖስን ግን አቅርቡትና እጠይቀዋለሁ ብሎ ንጉሡ አዘዘ።

ቅዱሳን ሰማዕታት አድርያኖስ ከነሱ ተለየቶ ለጥያቄ እንደሚቀርብ ባወቁ ጊዜ ወደ ኋላህ እንዳትመለስ መስቀልህን ተሸከም ወደኋላ አትበል የሚደርስብህን ሁሉ በአኮቴት ተቀበለው የዚህ ዓለም ሕማም ለጊዜው ቢያስጨንቅም ያልፋል አንተና እኛ የሚጠብቀን ፀጋ ታላቅ ነው ይህም ፀጋ ዘለዓለማዊ ነው እያሉ አፅናኑት። ቅድስት እንጦልያም ወደሱ ቀረበችና ጌታዬ ሆይ አሳብህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሁን ልብህ አይደንግጥ የመከራ ብዛት አያሸንፍህ የሥጋ ሕማም ጥቂት ነው ይህም ዘለዓለማዊ ክብርንና ዘለዓለማዊ ዕረፍትን ያሠጣል ከመላእክት ጋር ልትኖር ነው፣ የሚፈፅሙብህን መከራ ሁሉ ለመንግሥተሰማያት ስትል በትዕግሥት ተቀበለው ስትል መከረችው።

ከቅድስት እንጦልያ የሚሠጠውን ምክርና ትምህርት በመስማት ላይ እያለ ወታደሮቹ እየገፉ ወሰዱት ያለኸው በእጄ ሥር ነው በመጥፎ አሟሟት እንዳትሞት ተጠንቀቅ ለምንድር ነው እንደኔና እንደሕዝብ ሁሉ ለአማልክት የማትሠግደው



መሥዋእትንም የማታቀርብላቸው አለው አድርያኖስ አንተ ራስህ ጠፍተህ እኔንም እንድታጠፋኝ ትፈልጋለህን አንተን ተከትለው ነፍሥና ሥጋ ለሌለው የሰው ሥራ ዕቃ ሲሰግዱ ብዙዎች ጠፍተዋል። እግዚአብሔርንም ትተዋል ሰማይን ምድርን ባሕርንና በውስጣቸው ያሉትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን አንተና መሰሎችህ ከእግዚአብሔር ወጥታችሁ ለጣኦታት ስትሠግዱ ትኖራላችሁ የሚል መልስ ሠጠው። ንጉሡ ከአማልክት ሁሉ የበላይነት ያላቸውን አማልክት ታቃልላለህን አለው አድርያኖስ ሲመልስ እኔ አላቃላልኳቸውም ክብርም አልሠጠሁዋቸውም እነሱ ኢምንት ናቸውና አለ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ እጅግ ተናደደና በዱላ ይቀጠቅጡት ዘንድ አዘዘ እነሱም ቀጠቀጡት።

ባለቤቱ ቅድስት አንጦልያ መቀጥቀጡን ሰምታ ጌታዬ ሰማትነትን መቀበል ጀመረ ስትል በሩጫ ወደእሥር ቤቱ ሄዳ ቅዱሳን ሰማዕታትን ነገረቻቸው እነሱም እግዚአብሔር ትዕግሥቱን ይሠጠው ዘንድ ፀለዩለት። ንጉሡ ደብዳቢዎቹን አማልክትን እንዳይሠድብ ንገሩት አለ አድርያኖስ ግን እኔ የምደበደበው እነሱ አማልክት ስላይደሉ አይደለም ወይ አንተስ ዘለዓለማዊውን አምላክ እንዴት ልትክደው ቻልክ አለው። እነዚያ አሳሳቾች እነዚህን ቃላት አስተማሩህን በማለት ንጉሡ መለሰለት አድርያኖስ "ቅዱሳን ሰማዕታት መስሕታን አይደሉም እነሱ ወደዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመሩ ናቸው አንተና ተከታዮችህ ግን ሰዎችን በክህደት ወጥመድ ታጠመዱዋቸው አላችሁ" አለው።

ንጉሡ በቅዱስ አድርያኖስ ንግግር ተናዶ ለ4ኛ ጊዜ በወፍራም ዱላ እንዲደበደብ አዘዘ፣ ቅዱስ አድርያኖስ አንተ ባስደበደብከኝ ቁጥር ሰማዕትነቴ እየበዛ ይሄዳል አለ ቅድሰት እንጦልያ የሚናገረውን የሰማዕትነት ቃል ከሩቅ በማዳመጥ

www.ethiopianorthodox.org

እየሄደች ለቅዱሳን ሰማዕታት ትነግራቸው ነበር።

ንጉሡ አንተን ያህል መልከ መልካም ከደጋግ ሰዎች የተወለድክ በሥልጣንህ የከበርክ እኔም በመንግሥታዊ ሥልጣን ያስቀመጠኩህ የክብር ሰው ነህ። ካንተጋር የተሰለፉት ግን ከሥር መሠረታቸው የድሆች ዘሮች ናቸው በማለት ብዙ አግባባው አድርያኖስ በበኩሉ የነዚህ ቅዱሳንን ማንነት ብታውቅ ከእግራቸው ወድቀህ ወደእግዚአብሔር እንዲፀልዩልህ በለመንካቸው ነበር ባልደበደብካቸውም ነበር ብሉ ሲመልስለት ንጼቱ አገርሽቶበት ሆዱ ላይ እንዲደበድቡት አዘዘ አስደበደበውም ከሆዱ ላይ ደም ሲፈስ አይቶ ድብደባውን በማስቆም አንተ የ28 ዓመት ወጣትነህ እኔም አሳዘንከኝና ድብደባውን አስቆምኩልህ በዚሁ የኔን ደግነት ተመልከት አሁኑኑ ለአማልክት ለመስገድ ፈቃደኛ ከሆንክ ስለደረሰብህ የአካል ጉዳት ባለመድሐኒቶች አስመጥቼ አስፈውስህ አለው ተመልሠህ ወደታች አትውረድ እያለ ያግባባው ጀመር። ቅዱሱና የ28 ዓመት ወጣቱ አርያኖስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የቆሰልኩትና የጎደለው አካሌ እንደገና እንዲድን አልፈልገውም ከቅዱሳን ሰማዕታት ማሕበርንም ወጥቼ ለአምልኮባእድ እጄ አልሠጥም ቢለው ምንም ሳይል የሚቀርብበትን ቀነቀጠሮ ሠጥቶ ከሰማዕታቱ ጋር ከነበረበት እሠርቤት መለሰው አብዛኞቹ ቅዱሳን ሰማዕታት ከድብደባ፣ ከዕሥራትና ከምግብ እጦት የተነሣ አካላቸው መንቀሳቀስ ስለተሳነው እየሳቡ ወሰደቻው ቅድሰት እንጦልያ እጆችዋን በአድርያኖስ ትከሻ ላይ በማሳረፍ ጌታዮ ሆይ እነሆ ከቅዱሳን ጋር እንድትቆጠር እግዚአብሔር ፈቀደልህ ጌታዮ ሆይ ስለታመመው ኢየሱስ ክርስቶስ ታመምክ እሱም ስላንተ ነው የታመመው እነሆ ብርሃኑን ታይ ዘንድ ትሄዳለህ እያለች እስከ እሥርቤቱ ድረስ ሸኘችው።



ከእሥርቤቱ ሲደርሱ ቅዱሳን ሰማዕታት ጋር ተገናኘ እነሱም በአምሃ መንፈሳዊ ሰላም አሉት ደስም እያላቸው ወንድማችን የመጀመርያውን ፈተና አለፈልን አሉ። ከያሉበት እግር ብረታቸውን እየጎተቱ በእጃቸው እየተሳቡ ነው ወደሱ ሊሰባሰቡ የቻሉት ሰውነታቸውም ከከባድ ጉስቁልና ጋር በከባድ የድብደባና ግርፋት በቁስል እንዳልሆኑ ሁኖ ነበር ቅድስት እንጦልያ በዚህ ጊዜ ቁስሉን በተለያየ መድሐኒት ታሸለት ነበር ቅዱሳን ሰማዕታትም እየመላለሱ በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ ስምህ ከቅዱሳን ሰማዕታት ጋር ተፅፏልና ይሉት ነበር ቅዱስ አድርያኖስ በበኩሉ ልትደሰቱ የሚገባችሁ እናንተ ናችሁ አክሊል ገንዘባችሁ ነውና ሕማምንና ምንዳቤን ታግሣችሁታልና አሁንም ልሰብስበው የጀመርኩትን አዝመራ ዲያብሎስ እንዳይበትንብኝ ፀልዩልኝ እኔ ደካማ ነኝና በማለት ተማፀናቸው እነሱም ካሁን በኋላ ዲያብሎስ በትዕግሥትህ ተሸንፏል ካንተም ርቋል አሉት።

ቅዱሳን ሰማዕታት በመከራው ላይ እያሉ የሚያገለግሉዋቸው ክርስቱያኖች ሴቶች ነበሩዋቸው እነዚህ ሴቶች እግዚአብሔርን የሚፈሩ ከመሆናቸውም በላይ ብዛት ነበራቸው እነዚህ ሴቶች ወደእሥር ቤቱ እየተመላለሱ የቅዱሳን ሰማዕታት የቆሰለውን ሰውነት ያክሙ ነበር ግማሻቸው ቁስላቸውን ያጥባሉ፣ ያሻሉ ግማሻቸው እህል ውሃ ያቀርቡላቸዋል ግማሻቸው እየደገፉ ያንቀሳቅሱዋቸዋል።

ንጉሡ የሴቶቹን መልካም ክርስቲያናዊ ሥነምግባር ሲሰማ ማንም ሴት ወደታሠሩት ቅዱሳን ሰማዕታት እንዳይገባ ከለከለ ቅድስት እንጦልያ ሴቶች ቅዱሳን ሰማዕታት ወዳሉበት እንዳይገቡ መከልከላቸውን አወቀችና ጠጉርዋን ቆርጣ የወንድንም ልብስ ለብሳ



www.ethiopianorthodox.org

ወንድ በመምሰል እየገባት የሴቶቹን ሕክምና ብቻዋ ሴት ተቀን ታሟላላቸው ነበር። የማከም ሥራዋን ካጠቃለለች በኋላ ወደባልዋ ቅዱስ አድርያኖስ ዘንድ ቀርባ ጌታዬ ሆይ እኔ ወደዚህ የተቀደሰ ገድል እንድትገባ አደፋፈርኩህ አሁን ከቅዱሳን ሰማዕታት አንዳንዱ ሁነህል። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ጣዕምም ከሕይወትህ ተዋህዷል። ጌታዬ ሆይ እኔንም መድሐኒዓለም ክርስቶስ የመንግሥተሰማያት ተካፋይ ያደርገኝ ዘንድ በፀሎትህ አስበኝ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔንም እንዲቀበለኝ ካንተ ጋርም የመንግሥቱ ተካፋይ እንዲያደርገኝ ለምንልኝ እኔ ገና በአካል ንእስት ነኝ ያንተ መንታ ነኝ ይህ ከሐዲ ንጉሥ እንዳያረክሰኝ ፀልይልኝ በጉልበትም ለከሐዲዎች አሽከሮቹ አሳልፎ እንዳይሠጠን ኢየሱስክርስቶስ ያድነኝ ዘንድ የሕመሙና የመከራውም እንደናተ ተካፋይ እሆን ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስንለምነው ካንተ ጋር ያለኝን የባለቤትነት ክብር እንደጠበቅሁ ከናንተ ጋር በሞት ይህን ዓለም እለየው ዘንድ ሁላችሁም በፀሎት ርዱኝ ብላ አድርያኖስንና አብረውት ያሉትን ቅዱሳን ሰማዕታት ከተማፀነች በኋላ እንደተለመደው የያንዳንዳቸውን ቁስል አከመች እንደየፍላጎታቸውም ቀላልና ከባድ ምግብን አቀረበችላቸው።

የቅድስት እንጣልያ ወንድ እየመሰለች በመግባት ለቅዱሳን ሰማዕታት ርዳታ ማድረግን ሲሰሙ እነዚያ ወደነሱ እንዳይገቡ የተከለከሉ ቅዱሳት እንሰት እንደሷ ወንድ እየመሰሉ ወደ ቅዱሳን ሰማዕታት ይመጡ ጀመር ቅዱሳት ሴቶች በዚሁ ዘዴ እየተጠቀሙ ቅዱሳን ሰማዕታትን ሲያገለግሉ ከነሱ ጋር እየተደባለቁ ክፉዎች ሴቶች በበኩላቸው ሰማታቱን እንዲሰቃዩ ያደርጉ ነበር።

ንጉሡ ከቅዱስ አድርያኖስ የታሠሩት ሰማዕታትና አድርያኖስ እንዳልተመለሱለት ስላወቀ እንደሰው ሁሉ ደህና ሞትን መሞት



የለባቸውም በማለት እጅና እግራቸው ቀስ በቀስ እየቆረጡ በከባድ አገዳደል እንዲገድሉዋቸው አዘዘ በዚህ ጊዜ ቅድስት እንጦልያ ሌሎቹ ሰማዕታት እየተሠቃዩ ሲገደሉ አይቶ ወደኋላ እንዳይልብኝ አድርያኖስን ለሞት አስቀደምልኝ እያለች ወደእግዚአብሔር ፀለየች እግዚአብሔርም ፀሎቷ ሰምቶ ወታደሮቹ የመግደሉን ተግባራቸው በአድርያኖስ ጀመሩት፣ በቅድሚያ ሁለቱን ጭኑ ቆረጡ ይህን ስትመለከት ቅድስት እንጦልያ አድርያኖስ እጁን ሠጣት እሷም እየሳመች ስትሰናበተው ወታደሮቹ ይህንን እጁ ቆረጡ በዚህ ጊዜ ሕይወቱ አለፈች ወታደሮቹ አድያኖስን በዚህ መንገድ ከገደሉ በኋላ ወደሌሎቹ ዞሩ በየተራም በየጥቂቱ አካላቸውን እየቆረጡ እጅግ በሚከብድ አገዳደል ይገድሉዋቸው ነበር። እነሱ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ነፍሳችንን ተቀበላት እያሉ ይማፀኑት ነበር።

ሰማዕታት ሁሉ ከአድርያኖስ ጋር እንደሞቱ ካወቀ በኋላ ገሊላውያን /ክርስቲያን/ መጥተውእንዳይወስዱዋቸው አስከሬናቸውን በእሳት አቃጥሉ አለ ይህን ስትሰማ አንጦልያ እየሮጠች ሄዳ የአድያኖስን እጅ ይዛ ሄደችና ከወገቧ ላይ ታጠቀችው ወታደሮቹ የቅዱሳን አስከሬን በእሳት ለማቃጠል በሚወስዱበት ጊዜ የሚንጠባ ጠበውን ደማቸው በእጅዋ እየተቀበለች ፊቷ ላይ ትቀባው ነበር። የሥጋ ዘመዶቿ የሆኑ ሴቶችም እየተከተሉ ከሚወድቀው ሥጋቸው እያነሱ ወደቅዱሳን አፅም ለመጨመር ይሰበስቡት ነበር።

ወታደሮቹ እያንዳንዳቸው ሰማዕታቱን ወደእሳቱ ቦታ ተሸከመው ሲወስዷቸው በሰማዕታቱ ደም ልብሳቸው ሙሉ ተነከረ ወሰደው ወደእሳቱ አስከሬናቸውን ሲወረውሩ ደጋጎቹ ክርስቲያን ሴቶች ቅዱሳን ሰማዕታት ሆይ በእግዚአብሔር ዘንድ አስቡን ይሉ ነበር ቅድስት እንጦልያ እኔም ከነሱ ጋር ወደእሳቱ ልግባና ሰማዕትነቴን



www.ethiopianorthodox.org

ከነሱ ጋር ልጨርስ በማለት ከፍተኛ ድምፅ አሰማች ወድያው ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እጅግ የከበደ ዝናም አካባቢውን አጥለቀለቀው እሳቱም የሰማዕታቱን አስከሬን ሳይበላ ጠፋ ወታደሮቹም በድንጋጤ ሮጡ።

አንድ በሰደት የሚኖር ደግ ሰው መጥቶ በዚሁ ሌሊት ሌሎች ክርስቲያኖችን በማሥተባበር የቅዱሳኑን ሰማዕታ ዳግም እንዳይቃጠል ደበቀው። ቅድስት እንጦልያ ደግሞ ቀደም ሲል በእጅዋ ያስገባችውን የባለቤቷ ቅዱስ አድርያኖስ የእጅ ቁራጭ በመልካም ሽቶ ቀብታ ከትራስዋ ላይ አስቀመጠችው ይህንን ሰው እንዳያውቅባት በምሥጢር ትጠብቀው ነበር ባገሩ አንድ የሻለቃ /መኮንነ፲፱/ ይኖር ነበር። ይህ መኮንን ወደንጉሡ ሄዶ እንጦልያን እንዲያገባት ይፈቅደለት ዘንድ ለመነው እሱን ለማግባት ፈቃደኛ ትሆን ዘንድም የሚያግባቧት ሴቶችን ላከባት።

ቅድስት እንጦልያ ለሴቶቹ ለጋብቻ ዝግጁ እሆን ዘንድ እስከ ሦስት ወር ታገሱኝ አለቻቸውና ቤቷን ዘግታ ወደእግዚአብሔር እየፀለየች እንዲህ አለች "የችግረኞች አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ለነዚህ አረማውያን አሳልፈህ አትሥጠኝ የሰማዕትነትን ዕድል ሥጠኝ ቅዱሳንን የምከተልበትን መንገድ አዘጋጅልኝ ተለይቼ የአጋንንት መዛባበቻ እንዳልሆን የሥጋን መከራ ተቀብዮ ወዳንተ የምመጣበትን መንገድ አዘጋጅልኝ እኔ ከቅዱሱ ሰማዕትህ አድርያኖስ ሥጋ አንድሁኜ አለሁ የቅዱሱ ሰማዕትህ አድርያኖስ መኝታ አይርከስ በአረማውያን ሠይፍ አንገቴ እንዲቆረጥ እንጂ በጋብቻ ከነሱ ጋር እንድደመር አታድርገኝ" ብዙ ከፀለየች በኋላ ተኛች በሕልሟም ከባልዋ አድርያኖስ ጋር ሰማዕትነትን ከተቀበሉ አንዱ ታያትና "አይዞሽ ኢየሱስ ክርስቶስ ቸል አላለሽም ወደኛ



ትመጫለሽ..." አላት። ሲነጋ ቤቷን ትታ ከባሮቹም ሆነ ከሌሎች ቀራቢዎቿ ማንም ሳያውቅ የቅዱሳኑ አስከሬን ወደተደበቀበት ቦታ ሄደች ወድያውም ከከሐዲው ንጉሥ የሚሸሹ ክርስቲያኖችን አገኘችና አብራቸው እንድትሰደድ ለመነቻቸው እነሱም በደስታ ተቀብሏትና ከሐዲው ንጉሥ ከማይደርስበት አገር ለመሄድ መርከብ ተሳፈሩ ነገር ግን የመርከቡ ጌታ ከአረማውያኑ ወገን ስለነበር እያታለለ አቅጣጫን በማሳሳት ወደአረማውያኑ እጅ እንዲያስገባቸው ሞከረ በዚህ ጊዜ ማዕበል ሊያስኬደው ስላልቻለ ተመልሶ ከወደቡ ላይ ቆመ ቅድስት እንጦልያም የባልዋ አድርያኖስን ጨምሮ የቅዱሳኑ ሰማዕታት አስክሬን ካረፉበት ቦታ ሄዳ እግዚአብሔርን ከነዚህ ቅዱሳን አትለየኝ፣ ቤቴን ትቼ መጥቼ አለሁ መንግሥተሰማያትን አትዝጋብኝ እያለች ስትፀልይ ከቆየች በኋላ እጅግ ደከማትና ዕረፍት ወሰደች ባለችበትም ነፍሷ ከሥጋዋ ተለየ።

ብዙ ክርስቲያን ሴቶችም ወንዶችም እህል ውሃ እንድትቀምስ ለመጠየቅ ቢጠጉዋት መሞቷን አወቁ። በሕብረት ሁነው ከፀለዩ በኋላ ከቅዱሳት አስከሬን ጋር የሷንም አስከሬን አስቀመጡ የሰማዕትነትንም አክሊል ተቀዳጀች እግዚአብሔር ምኞቷን ፈፀመላት ክብርና ምስጋና ለሱ ይሁን አሜን።

## ምዕራፍ ፳ የኔፊኔዎስ ጳጳስ ሰማዕትነት

መክስምያኖስና ዲዮቅልጥያኖስ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ጳጳሱ ሄሬኔዎስን ለሮቦስ የተባለው መኮንን ለጣኦት እንዲሠግድ አዘዘው በዚህ ጊዜ ከጳጳሱ ሄሬኔዎስ ሥር የነበሩ ብዙ ዲያቆናት ተሰደዱ ጳጳሱ ሄሬኔዎስ ግን አልሰደድም ሰማዕትነትን እቀበላለሁ ብሎ ካለበት ቀረ መኮንኑ በዕለተቀዳሚት ሰንበት አማልክተሐሰት ካሉበት ጳጳሱን ሄሬኔዎስ አስወሰደውና ለምን ለአማልክት



www.ethiopianorthodox.org

አትሠዋም አለው ልጆች አሉህን ብሉ መኮንኑ ሄሬኔዎስን ጠየቀው አዎን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ልጆች አሉኝ ክርስቲያኖች ሁሉ ልጆቼ ናቸው አለው አንተ ገና ወጣት ነህ እንዴት ይህን ያህል ልጅ ሊኖርህ ቻለ ሲለው በቤተክርቲያን አባትነቴ የተረከብኳቸው ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሠጠኝ መንፈሳዊ አባትነት የወለድኩዋቸው እንጂ በሥጋ የወለድኩዋቸው አይደሉም አለው።

መኮንኑ በድጋሚ ለአማልክት ከሠዋህ ከክብር ላይ ክብር ይጨመርልሃል አለው ሄሬኔዎስጳጳስ ግን የምታደርገውን አድርግ እንጂ ከእግዚአብሔር የተሠጠኝን የኖላዊነት ሥልጣን ሽሬ ለባእድ አምልኮ አልሠዋም የኔ መኮንን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ለሱ እሠግዳለሁ ንፁሕ መሥዋዕትንም ለሱ አቀርባለሁ የሚል መልስ ሠጠው። ወድያውም ወደሚሰቃይበት ቦታ ወስደው ወደረግረግ ከነሕይወቱም ሊያሠጥሙት ሲዘጋጁ ጌታዮ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ቤተክርስቲያንህንም ጠብቃት ለምዕመናኑ እረኛ አባትን ላክላቸው እያለ ከፀለየ በኃላ ልብሱን አስወልቀው እጅግ የራቀ ጥልቀት ካለበት የረግረግ አዘቅት ወረወሩት በዚሁም ሰማዕትነቱን ፈፀመ። እለቱ ነሐሴ 29 ቀን አረፈ።



www.ethiopianorthodox.org